


@BOOKALEM

# ቡክ - አለም

@BOOKALEM

የመፅሐፍት መንደር

የቴሌግራም ቻናሉን

SUBSCRIBE

ያድርጉ

@BOOKALEM

## ክፍል አንድ
# ከውብ ሰማይ በታች

## አንድ

## ባህራም
## ከሩቅ

ይሄ ሁሉ የሆነውና የተደረገው ኢክስ ውስጥ ነበር . . .

ኢክስ (ኢክስ-አን-ፕሮቫንስ) በፈረንሳይ ደቡብ ከማርሰይ አጠገብ የምትገኝ ትንሽ የዩኒቨርሲቲ ከተማ ናት፡ ህዝቧ ግማሽ በግማሽ ተማሪ ነው

የኢክስ ሰማይ አብዛኛውን ጊዜ ብሩህ ሰማያዊ ነው፡ አንዳንድ ጊዜ ውሀ አረንጓዴ ይሆናል፣ ወደ ማታ ላይ እንደ ልጃገረዶቹ ጉንጭ ይቀላል

የኢክስ አየር ጠባይ የተመሰገነ በመሆኑ፣ ሀብታም በሽተኞችና ሽማግሌዎች በሀኪም ምክር ወደ ኢክስ መጥተው ይኖራሉ። ስለዚህ «ኩር ሚራቦ» የተባለው የኢክስ ዋና ጎዳና ላይ ሽማግሌዎች፣



@BOOKALEM

አሮጊቶችና፣ ባለፃኞዎች – እግራቸው ረግኘርም ቀጫጭን የሆነ፣ የተነፋ ደረታቸው ውስጥ እንገታቸው የተቀበረ ባለሻኛ ሰዎች – በቀስተኛ እርምጃቸው ሲዘዋወሩ ይታዩበታል:: ባቡር መንገድ ዳር የተደረደሩት እግድም ወምበሮች ላይ የአሮጊትና የሽማግሌ መአት ቁጭ ብሉ ሹራብ እየሰራ ወይም ጋዜጣ እያነበበ ፀሀይ ይሞቃል፣ ወይም ዝም ብሉ ባዶ ብርጭቆ መሳይ ፈዛዛ አይኑን አተኩሮ (ምን ያይ ይሆን?) ከንፈሩን ያለማቋረጥ ያንቀሳቅሳል (ምን ይል ይሆን?)

በጣም ይቀፋሉ የፈረንጅ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች:: ጨምዳዳ ቆዳቸው የተሰነጣጠቀ ደረቅ ሰም ይመስላል:: ቀጥቃጣዎች:: ዝምተኞች:: እገጫቸው ተገንጥሎ ወደታች የወደቀ፣ ከንፈራቸው የተንጠለጠለ፣ ጥርሳቸው የፈራረሰ ሽማግሌዎች:: ጥርሳቸው አልቆ አፋቸው ወደ ውስጥ የጎደጎደ ፂማም አሮጊቶች:: የመኖር ጊዜያቸው አልፎ፣ የሞት ጊዜያቸውን ዘመናዊ ህክምና ከልክሏቸው፣ ታችኛ ከንፈራቸውን እንደ ጡጦ እየጠቡ ሞትን ሲጠብቁ 'ሚውሉ የህይወት አናዎች:: ዝምተኞች:: ለአይን ብቻ ሳይሆን ላፍንጫም ይቀፋሉ:: የልዩ ልዩ መድሀኒት፣ የእርጅና፣ የሞት ሽታ. . . ሳይቀበር መግማት የጀመረ ስጋ

ደሞ መብዛታቸው! ከተማሪው እኩል ሳይሆኑ ይቀራሉ? ማታ መቸስ ፀሀይዋ ሙቀቷን ይዛ ስትሄድ ወደየአልጋቸው ይከተታሉ:: ቀን ግን የትም ይገኛሉ፣ ኢክስን ይወረታል:: ኩር ሚራቡ ግዛታቸው ነው፤ ዩኒቨርሲቲው አጠገብ ያለው መናፈሻ ቤተ መንግስታቸው ነው፤ ካፌዎቹ ቅኝ ሀገራቸው ናቸው:: ቀን ሲኒማ የገባህ 'ንደሆነ፣ በጭለማው ሳይታወቅህ፣ ሳይተኛ ከሚያንኩራፋ ሽማግሌ፣ ወይም በየሰበት ሰከንዱ «እክ!» ከምትል አሮጊት አጠገብ ትቀመጣለህ. . .

ደግነቱ ይሄ ታሪክ ስለአሮጊቶችና ስለሽማግሌዎች አይደለም:: ስለኛ ስለወጣቶቹ ነው፤ ስለባህሩም፣ ስለኒኮል፣ ስለሲልቪ፣ ስለሉልሰገድ፣ ስለሌሎችም ወጣቶች. . . ጥሩ ነው ወጣት መሆን:: ገንዘብ ባይኖርህም ጤና ይኖርሀል፤ መልክ ባይኖርህም እንጎል ይኖርሀል፤ እውቀት ባይኖርህም ጉራ ይኖርሀል፤ ፍቅር ባይኖርህም ተስፋ ይኖርሀል፤ ደስታ ባይኖርህም ንዴት ይኖርሀል. . . መ... ቢበዛብህ ሪቮሉሽን ታነሳለህ. . . መኖር ቢያስጠላህ ወይም ቢያት...



@BOOKALEM

ራስህን ትገድላለህ. . . . ሰው ቢያውቀውም ቅሉ ታሪክ ይናርሀል፣
መሆት ነሆና. . .

የኢክስ የበጋ ሙቀት እየከበደኝ አላስራ ስለሚለኝ ከሰአት በኋላውን ተኝቼ 'ውልና ሌሊት ስስራ ለማደር 'ሞክራለሁ፡፡ እየመረርኩ፡፡ ደስ ይለኛል በሌሊቱ ኢክስን መዞር፡፡ ትንሽ ከተማ በበሆኑት ስባት ሰአት ሲደርስ ሁሉ ነገር ተዘግቷል (ከካፌ «ሰንትራ» እና ከ«ላ ፓሌት» ናይት ክለብ በቀር) በቀን ጠባቦቹን መንገዶች የሚያስጨንቃቸው ህዝብ በሙሉ ተኝቷል፣ እነዚያ ቀን የሚያስፈሩኝ፣ መምጫቸው የማይታወቅ አብድ ፈረንሳይ ነጂዎች በየአሊጋቸው ተከተዋል፣ ኢክስ-አን-ፕሮቫንስ ሰላም ነው፡፡ ቤቶቹ ሁሉ ጨልመው፣ የመንገድ መብራት በርቶ፣ በፀጥታው የፏፏቴውን ድምፅ ብቻ እየሰማሁ ስራመድ፣ ባዶ ከተማ ውስጥ እንዳለሁ ሆኖ ይሰማኛል፡፡ አልፎ አልፎ በየአደባባዩ የሚገኙት ሰው ሰራሽ ምንጮች ወደ ክበቦቹ በኩል እየዘለሉ ከሌሊቱ ጋር ይንሾካሾካሉ.

አንድ ሌሊት ወደ ስምንት ሰአት ላይ አንዱን መንገድ ይዤ ስራመድ ቆይቼ ወደ ግራ በኩል ስታጠፍ፣ ከፊቴ አራት የሚታገሉ ፈረንጆች ድንገት ብቅ አሉ፡፡ ብቅ ያልኩትስ እኔ ነበርኩ፣ ግን እነሱ ብቅ ያሉብኝ መሰለኝ፡፡ በበጋው ሙቀት ምክንያት አራቱም በሸሚዝ ናቸው፣ ይታገላሉ፡፡ በሌሊቱ ፀጥታ ጫማዎቻቸው ከአስፋልቱ ጋር ሲፋተጉና ትንፋሻቸው ሲቆራረጥ ይሰማል፡፡ ለጊዜው ማን ከማን ጋር 'ንደሚታገል ለማወቅ አልቻልኩም፡፡ ዝም ብዬ ስመለከት፣ ሶስት ግዙፍ ሰዎች አንዱን ደቃቃ ብጤ ገጥመውት ኖሮ፣ ከጥቂት ትግል በኋላ ሁለቱ በቀኝና በግራ በኩል ያዙት፡፡ ሶስተኛው ከፊቱ ቆመ፡፡ ዛሁም ቁና ቁና ይተነፍሳሉ፡፡ ደቃቃው ሰውዬ ይፍጨረጨራል፣ ግን ድምፅ አያሰማም፡፡ ለምን ኡ ኡ 'ንደማይል 'ንጃለት

ከፊት የቆመው ግዙፍ አንዴ በጥፊ መታውና፣ ዘወር ብሎ አጠ ገባቸው ካለው ግድግዳ ስር አንድ ትንሽ ነገር አንስቶ መጣ፣ በዚህ ጨለጠው ነገር የትንሹን ሰውዬ ግምባር ፈተገው፡፡ ትንሹ ሰውዬ ጣብት፡፡ ግዙፉ በሹክሹክታ እየተሳደበ ወይም እየተራገመ ከሱሪ ኪሱ መሀረብ አውጥቶ ፊቱን ጠረገና ሲያበቃ፣ ደቃቃውን አንድ



@BOOKALEM

ቃሪያ ጥፊ አላሰው። ጥፊው ጧ ሲል ቀሰቀሰኝ፣ ግና እሁን ከመኝታዬ ነቃሁ። ዘወር ስል፣ አጠገቤ ለመንገድ መጠገኛ ይሁን ለቤት ማደሪያ የተከመረ ኮረት አየሁ። በፍጥነት አንድ ሰባት ከባድ ጠጠር አነሳሁና እያንጓጠርኩ ሰዎቹ ላይ መወርወር ጀመርኩ (ስወረውር «የሀበሻ ነገር!» የሚል ሀሳብ በሀይል አሳቀኝ) ከት ከት ብዬ እየሳቅኩ የወረወርኳት ድንጋይ (ሶስተኛዋ) በጥፊ ተማቺውን ሰውዬ ያረገን ይለቀቸው፣ አራተኛዋ የአንዱን ትክሻ መታች። ድንጋዩና ሳቁ አስደንግጧቸው፣ ትንሹን ሰውዬ ለቀቁትና ተፈተለኩ። ለምሬት ያህል እጄ ውስጥ የቀሩትን ድንጋዮች ወረወርኩባቸው። በድንጋዮቹ ሸኝነት ጥቂት እንደሮጡ ወደ ቀኝ በኩል ታጠፉ፣ ጠፉ

ሳቄም ድንገት ጠፋ። የፍርሀት ሳቅ ኖሯል። አጠገባችን ምንጭ ሰማሁ። ግና አሁን ሰማሁት! ለካስ «ፕላስ ዶ ካትር ዶፊን» እተባለው አደባባይ ውስጥ ነን

ትንሹ ሰውዬ ግራ ገብቶት መንገዱ መሀል ቆሞ እኔን ያየኛል። እጄን እያራገፍኩ ወደሱ ሄድኩ። ይህን ያህልም ደቃቃ አይደለም፣ ከኔ ትንሽ ተለቅ ይላል። ደቃቃ የመሰለኝ ጠላቶቹ በጣም ግዙፍ ስለነበሩ መሆን አለበት

«Bon soir,» አልኩት (ቦን ሷር)

«Bon soir! አንተ ነህ ’ንዴ? ሀለላሲ ሙት!» አለኝ እየሳቀ

ባህሪም ነው። ከዚህ በፊት ከሀበሾቹ ጋር ብዙ ጊዜ አይቼዋለሁ። ግን ያን ጊዜ ያገሬን ልጆች በብዙ ስለማልጠጋቸው፣ ይህን ባህሪም ተዋውቄው ወይም አናግሬው አላውቅም ነበር

ድምፁ ወፍራም ሆኖ ለጆሮ ደስ ይላል። ፈረንሳይኛው የፈረንሳዮቹ አይደለም፣ መልኩ ግን ትንሽ የደቡብ ፈረንሳዮችን ይመስላል። ፊቱ እንደ ፈረንጅ ነጭ ሳይሆን፣ ፀጉሩ በጣም ጥቁር ነው። «ሀለላሲ ሙት!» ያለኝ ሀበሻ መሆኔን ስላወቀ ነው። አብሯቸው የሚሄድ ሀበሾች ብዙ ጊዜ «ሀይለሰላሴ ይሙት!» ሲሉ ሰምቷል

«ሀበሻ መሆኔን ’ንዴት አወቅክ?» አልኩት

«እረ ስምህንም አውቀዋለሁ። ከነተመስገን ከነሉልሰገድ ጋር ነው ’ምውለው። ከፈረንሳይ ህግ ጋር ስንጻረት እንውላለን። ከናት



@BOOKALEM

ብዙ ጊዜ አይቼሀለሁ»

«ይሄ ምንድነው?» አልኩት:: ግምባሩ ላይ በከሰል «C» የሚመስል ፊደል በጥቁር ተጭሮበታል:: የተጫረበት ቦታ ግምባሩ በጣም ቀልቷል

«አሁን ነው የጻፉብኝ:: ቆይ 'ስተ፥» አለና ከኋላ ኪሱ ቦርሳ 'ውጥቶ፣ እዚያ ውስጥ ባለችው ትንሽ መስተዋት ፊቱን አየ:: ሳቀ:: ከኪሱ መሀረብ አውጥቶ ከሰሉን ከግምባሩ እየጠረገ «ይሄ ፊደል «C» (ሲ) ነው:: ኮሙኒስት ማለት ነው» አለኝ ፈረንሳይኛው ብዙ የሰዋሰው ስህተት አለበት

«ኮሙኒስት ነህ ማለት ነው?» ስለው፣ መሀረቡንና ቦርሳውን መልሶ ኪሱ እየከተተ፣

«ሀለላሴ ሙት! ለራስህ ተመልከት» አለና ወደ ግድግዳው ጠነቆለ:: ግራጫው ግድግዳ ላይ በትልቁ (ከሩቅ እንዲታይ) በከሰል የተፃፈ ይነበባል

Vive Ho Chi Minh!
Vive le Peuple Viet-Namien!
A bas l' imperialisme Americain!
Yankee go home!
(ሆ ቺ ሚን ለዘላለም ይኑር!
የቬየትናም ህዝብ ለዘላለም ይኑር!
የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ይውደም!
ያንኪ አገርህ ግባ!)

«ይህን ስትፅፍ አግኝተውህ ነው እነዛ ሰዎች ሊደበድቡህ የፈለጉት?»

«ሰዎች አይደሉም:: አሜሪካኖች ናቸው» አለኝ

እየሳቅኩ «በል 'ንሂድ ከዚህ ሳይመለሱ» አልኩት

«አትስጋ:: አይመለሱም:: ፈሪዎች ናቸው»

ይህን ጊዜ ከዘላያችን ከሶስተኛው ፎቅ አንድ መስኮት ተከፈተና፣ ጆሮ 'ሚበሳ የሴት ድምፅ

«Laissez-nous dormir, non?» (እንተኛበት!)



@BOOKALEM

«Pardon, madame, on s'en va» አላት (ይቅርታ እመቤት መሄዳችን ነው)

«Si l' on ne peut pas dormir chez soi, alors. . .» እያለች እያጉረመረመች መስኮቷን ዘጋች («በገዛ ቤታችን ውስጥ መተኛት ካልቻልንማ. . .»)

«አ! እንሂድ ከዚህ» አለኝና ወደ ኮር ማሪብ በኩል መራመድ ጀመርን:: በጥፊ የተመታ ፊቱን እያሸ

«ፈረንሳዮችም ጨቅጫቃ ናቸው፣ አሜሪካኖችም ቂል ናቸው:: ሰው ማለት የኢትዮጵያ ሰውና የኢራን ሰው ነው!» አለኝ:: ቀልደኛ ነው

«የኢራን ሰው ነህ ማለት ነው?» አልኩት

«ነኝ»

«የኡመር ካያም ሃገር ልጅ ነህ!»

«ነኝ»

«የሱን ግጥሞች በቃል ታውቃቸዋለህ?»

«ሁሉንም አላውቃቸውም»

«የምታውቀውን በልልኝ 'ስቲ:: እኔ ያነበብኩት በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ ነው:: እሱ ራሱ የፃፈውን በጆሮዬ መስማት 'ፈልጋለሁ»

አለልኝ:: በጣም ደስ ይላል:: ቋንቋው «ሸ» እና «ቸ» ይበዛበታል:: ደሞ የሰውየው ድምፅ ወፍራምና ልዝብ ሆኖ፣ ኡመር ካያምን ራሱን የሰማሁት መሰለኝ:: ድገምልኝ አልኩት:: ደገመልኝ:: ሌሎችንም በቃሉ ወጣልኝ

«ከሳዲ፣ ከሩሚ፣ ከፊርዶሲ በልልኝ 'ስቲ» አልኩት

«እነሱንም ታውቃቸዋለህ?» አለኝ

«የለም፣ ስማቸውን ብቻ ነው:: ባገራችሁ ከኡመር ካያም እንደሚልቁ አውቃለሁ፣ ግን ተተርጉመው ደስ አይሉም:: ስለዚህ አላነባቸውም:: በልልኝ» አልኩት

አለልኝ እየተረጎመ

ኩር ሚፊብ ስንደርስ «ስለደረስክልኝ ያላመሰገንኩህ...»

አቋረጥኩት «ለመሆኑ፣ ሰው 'ንጂደርስልህ ለምን አልሞህ ከም?» አልኩት

«አስበው 'ንጂ» አለኝ «እንዴት እንደ ኢራናዊ ሰላት አሜሪካኖች ያዙኝ ብለሽ ይሮጣሀል?» ሁለታችንም ሳቅን «ደሞ ፈረንሳዮችን ታውቃቸዋለህ:: ስለምንም ነገር «je m'en fous!» ነው:: ሰማዩ እስኪሰንጠቅ ብጮህም ማንም አይደርስልኝም:: ለመሆኑ፣ አንተ ወዲህ ስፈር ምን ልታደርግ በዚህ ሰአት መጣህ?»

«የካርል ማርክስ ወይም የሌኒን መንፈስ ወዲህ መርቶኝ ይሆናል!» ሳቀ:: ሳቁ ደስ ይላል፣ ተላላፊ ነው

«አሁን ሳስበው ጊዜ ደንግጥኩ» አለኝ

«ምኑን?»

«እነሱን ስተህ በድንጋይ እኔን አንክተኸኝ ቢሆንስ?»

«አታስብ:: ሀበሻ ድንጋይ ወርውሮ አይስትም:: አፍሪካውያን እንደ መሆናችን መጠን፣ ገና ድንጋይ ዘመን ውስጥ ነው ያለነው:: ጦርነት ስንዘምትም በድንጋይ ነው»

እየሳቀ «እንደኛ ናችኋ! እኛ ግን ገና ድንጋይ ዘመንም አልደረስንም»

«የት ዘመን ናችሁ?»

«ጥርስና ጥፍር ዘመን! እንደ ነብር ሆኝ!»

ስንስቅ «ለመሆኑ ጣልያንን በምኒልክ ጊዜ ድል ያደረጋችሁት በጱላና በድንጋይ ብቻ ነበራ?» አለኝ

«እና በመልካችን አስፈሪነት፣ እና በሽለላችን!»

«ታዲያ ትንሽ ሽለላ 'ታስተምሩንም? አሜሪካኖቹን እንድናስወጣበት»

«የሚገባችሁ የናንተው ሻህ መሰሉኝ»

«ነው፤ ግን ሻህ የአሜሪካኖቹ አሽከር ነው»

«እንዴት አባክህን!? የነፈርዶዚ፣ የነኡመር ካያም አጥንት



@BOOKALEM

አይቆረቁራችሁም? የካራቴስትራ መንፈስ አይቀየማችሁም?»

«እሱ ነውኮ 'ሚገርምህ» አለኝ፡፡ በሃምር ድምፅ «ግን ታያለህ ኢራን 'ንደገና የነፃነት አገር 'ምትሆንበት ጊዜ ይመጣል» አለኝ «ብቻ እሱን ለጊዜው 'ንተወውና 'ስንትራ' እንሂድ፣ ቢራ ልጋብዝህ»

«ጥሩ»

«ረስቼ፡፡ ስሜ ባህራም ይባላል፡፡ ባህራም አፍሻር»

«Enchanté» አልኩትና ተጨባበጥን፡፡ ሳቅን፡፡ እኔም ስሜን ነገርኩት፡፡ ካፌ ስንትራ ገብተን ቢራ 'የጠጣን ትንንሽ ፖለቲካ እያወራን ከሳቅን በኋላ ስንለያይ

«Vive l'age de pierre!» አለኝ («የድንጋይ ዘመን ለዘላለም ይኑር!»)

«Pour chasser les Yankees» («ያንኪዎቹን ለማባረር»)

«ሀለላሴ ሙት!» አለ

ተለይቼው ስሄድ ሳቁ ተከተለኝ

በነጋታው ማታ ተመስገንን ሲኒማ 'ገኘሁትና ቢራ ልጋብዝህ ብዬ ካፌ ወሰድኩት፡፡ ግዙፍ ብጤ ጠይም ልጅ ነው፣ አይኖቹ ትንንሽ ናቸው፡፡ ስላየነው ፊልምና ስለሌሎች ፊልሞች፣ ስለፈረንሳዮች፣ ስለአገራችን፣ ስለሴቶች ስናወራ ከቆየን በኋላ፣ ጨዋታውን ቀስ አድርጌ ወደ ባህራም መራሁት፡፡ እንዴት ያለ ሰው ነው? አልኩት

«ለማወቅ የማይቻል ሰው ነው» አለኝ «ያወራል፣ ይለፈልፋል፡፡ ግን በልቡ ውስጥ ምን 'ንደሚያስብ በእውነት ለመገመት አይቻልም፡፡ የሚያወራውን ወሬ ብትሰማ በጭራሽ ብልጥ አይመስልህም፣ እንዲያውም ወደ የዋህነት ይወስደዋል፡፡ ግን ደሞ ባንድ በኩል ስትመለከተው ብልጥ መሆን አለበት»

«እንዴት?»

የተመስገን ትንንሽ አይኖች የባሰውን አነሱና እንደማብራት



@BOOKALEM

አሉ። ሳቅ ማለቱ ነው። ሲጋራውን እየኮሰተረ

«እኛ በወር ስድስት መቶ ፍራንክ እናገኛለን» አለኝ «ግብራም አስኮላርሺፕ የለውም፤ በቤቶቹ ገንዘብ ነው የመጣው። ግን ቤቶቹ ሳንቲም ከላኩለት ደኸው ስድስት ወር አለፈ። ምን 'ንደ ሆነቸው አይታወቅም። ታዲያ እሱ ሳንቲም ሳያገኝ፤ እኛ በወር 600 ፍራንክ እየበላን፤ ከኛ እኩል ካፌ 'የገባ ይወጣል፤ ከኛ እኩል ሲኒማ ይገባል፤ ከኛ እኩል ፓርቲ 'የመጣ ይደንሳል፤ ሴት ያሳድዳል»

«ቤት ያስቀመጠው ገንዘብ እንዳለው?»

«በጭራሽ ገንዘብ ማስቀመጥ 'ሚችል ሰው አይደለም»

«ታዲያ ገንዘብ ከየት ያመጣል?»

ተመስገን ጠይም ፊት ላይ የማፈርና የመሳቅ ፈገግታ መጥቶ አይኖቹን ሸፈናቸው

«እኔ ያበደርኩት እስካሁን ከ200 ፍራንክ በላይ ይሆናል። ሱልበገድ አንድ መቶ ሃምሳ ያህል አበድሮታል። ሌሎችም ሀበሾች እንደያቅማቸው አዋጥተዋል። ተካ ግን ከሰላሳ ፍራንክ በላይ አልገባበርም አለ»

«ምነው አለ?»

«ምን መጣብኝና ለማንም አቃጣሪ አረብ እገብራለሁ? አለ»

«ለምን አቃጣሪ ይለዋል?»

«ከሴቶች ጋር ያየዋል። ደሞ ቤቶቹ ገንዘብ ሳይልኩለት ከኛ እኩል ይኖራል። ስለዚህ አቃጣሪ መሆን አለበት»

«ሌላ ማስረጃ ሊኖር አይችልም?»

«ቢኖርስ? ተካን 'ንዴት ልታስረዳው ትችላለህ? አቃጣሪ አረብ ነው ካለ አቃጣሪ አረብ ነው ማለት ነው። በቃ። ተው አረብ አይደለም የኢሬን ሰው ነው ብንለው 'ንኳ፤ አረብ ነው ብሉ ድርቅ አለ»

«አንተስ አቃጣሪ ይመስልሀል?»

«አይመስለኝም። ግን እኛ ያበደርነው አንድ አራት መቶ ፍራንክ፤ እንኳን ለስድስት ወር ላንድ ወር አይበቃውም።



@BOOKALEM

ይመስለኛል፣ ቤቶቹ በብዙ ያግዙታል:: ለምሳሌ የምግብ ቲኬቱን 'ምትችልለት ኒኮል ነች»

«ኒኮል?»

«እንዲት እጠር ያለች፣ ጥርሷ 'ንደ አይጥ የተዘረዘረ፣ ፀጉሯ አያሯ የተነሰነሰበት 'ሚመስል እለች፣ እሷ ናት:: ደሞ በወር ዘጠና ፍራንክ የተከራየው ቤት አለው:: ባለቤትየው ስድስት ወር ሙሉ ዝም 'ሚለው አይመስለኝም:: ታድያ ኪራዩን ከየት አምጥቶ ይከፍላል? ቤቶቹ ይከፍሉለት ይሆናል ብዬ እሰባለሁ»

«ማን? ኒኮል?»

«ወይ ኒኮል፣ ወይ ሌላ:: መአት ቤቶች አሉት:: ምኑ 'ንደሆኑ እንጃ:: ብቻ ምን ልበልህ፣ ስለባህራም ለማወቅ አይቻልም::»

ሊሎቹንም ሀበሾች ስለባህራም ብጠይቃቸው በሌላ አነጋገር ይህንኑ ደገሙልኝ

ተካ ስለባህራም ነግሮኝ ሲጨርስ፣ ጥፍሮቹን 'የነከሰ «ገንዘብ እንዳታበድረው ተጠንቀቅ» አለኝ «እነሉልሰገድ የፈቀዱትን ያህል ይገብሩለት:: ሉልሰገድም አባቱ ሀብታም ነጋዴ ናቸው፣ ከኢትዮጵያ ህዝብ ያጭበረበሩትን ገንዘብ ጥቂቱን እንድ ምስኪን አረብ ቢጠቀምበት ምንም አይደለም:: ተመስገንም አባቱ ሚኒስትር ናቸው፣ ከህዝቡ የቀሙትን ገንዘብ እንደልብ ሊልኩለት ይችላሉ:: ስለዚህ ለባህራም ይስጠው:: አንተ ግን የኔ ብጤ ድሀ ነህ፡ እንዳትታለል ተጠንቀቅ:: ይሄ ባህራም ዋና አጭበርባሪ ነው»

ይህን ባህራምን ማወቅ ፈለግኩ:: ራሴን «ለወደፊት ደራሲ ለመሆን ካቀድክ፣ እንደ ባህራም ያለ ሰው ሲያጋጥምህ በተቻለህ መጠን ልታውቀው መጣር አለብህ» አልኩት:: ሰውን 'ምናውቀው ስለራሱ የነገረን 'ንደሆን ነው:: ግን ከጠየቅነው አይናገርም፣ ቢናገርም እውነቷን ፍርጥ አድርጎ አይደለም:: ስለዚህ መታገስ ያሻል፣ ጊዜን መጠበቅ:: እንዲት ሰአት ትመጣለች፣ ሰውየው መናገር የሚፈልግባት ሰአት:: መቼ 'ንደምትመጣ ለማወት አይቻልም፣ ግን መምጣቷ አይቀርም:: ስለዚህ ዘወትር ዝግጁ መሆን ያሻል

ዞር ዞር እኔና ባህራም መተዋወቃችን 'ንደማይቀር እርግጠኛ



@BOOKALEM

ስለነበርኩ ነው መሰለኝ፣ ላውቀው በጭራሽ አልቻልኩትም። ብቻ ስለ ስለራሱ በሚነግረኝ ጊዜ ንግግሩ በደምብ እንዲገባኝ በማለት፣ ሌሎቹ ስለሱ ምን እንደሚያስቡ አጠይቅ ነበር። በዚያውም እነሱ ራሳቸውን ትንሽ ትንሽ አውቃቸው ጀመር



@BOOKALEM

# ሁለት

# አማንዳ
# ለጥቂት ጊዜ

ያን ሰሞን አንዲት ቆንጆ አሜሪካዊት ነበረችኝ፣ አያና ስማያዊ፣ ፀጉሯ በጣም ንፁህ ቡና አይነት:: እጅግ ደስ ትላለች፣ አልጋ ውስጥ ልብ ታጠፋለች:: ግን በማልፈልጋት ሰአት ሆቴሌ እየመጣች አላሰራ ስላለችኝ፣ ቤተ መፃህፍት እየሄድኩ መስራት ግድ ሆነብኝ:: ሆቴሌ ስታጣኝ ወደ ቤተ መፃህፍቱ መምጣት ጀመረች::

እሷን ለመሸሸና በዚያውም ባህሪምን ለማወቅ ስል ሀበሾቹን እጠጋቸው ጀመር:: ምግብ ቤት አብሬያቸው እገባለሁ፣ ካፌ ዶርቢቴል አብሬያቸው ካርታ 'ጫወታለሁ:: ከባህሪም ጋር ግን ሳይ ላዩን እየቀለዱ ለመሳቅ 'ንጂ፣ የልብ ለመጫወት አጋጣሚ ለጊዜው አላገኘሁም:: ይልቅስ ከሀበሾቹ ጋር ግንኙነት በማድረጌ «ሚስቶቻቸውን» በመጠኑ እያወቅኳቸው ሄድኩ::

የነበርንበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሴቶቹ ከወንዶቹ በጣም ይበዛሉ:: ስለዚህ ለሁሉ ሴት 'ሚዳረስ ወንድ የለም. . . አሉ ሶስት፣ አራት፣ አምስት 'የሆኑ ወንድ 'ሚያድኑ ልጃገረዶች:: ታድያ ወንዱን ቆንጆ ቆንጆዎቹ ይዘውታል፣ ተጠምጥመውበታል:: ነፃ የሆነ ወንድ አይገኝም፣ ቢገኝም ወይ የደስ ደስ የለውም፣ ወይ ጥቁር ነው:: ጥቁር ደሞ ምን ቢወዱት አገሩ መመለሱ አይቀርም:: ብልጥ ወይም ውብ ወይም እድለኛ ካልሆኑ፣ ፈረንሳይ ወንድ ማግኘት አይቻልም:: ሳያገቡ የማርጀት ፍርሀት በወራቱ ዋሻ፣ በአመታቱ ጫካ አድፍጦ ይጠብቃል. . .

ጥቁሮቹ ወንዶች ገና 'ንደመጡ፣ በንግድነት ምክንያት ቆንጆ ሴት ማጥመዱን ለጊዜው ስለማያውቁበት፣ የተገኘችውን እሺ ብለው



@BOOKALEM

ይቀበላሉ:: የምትገኘው ደሞ ቆንጆ ያልሆነች ናት፣ ስለዚህ ማቆያ ናት . .

የሀበሾቹ «ሚስቶች» ጎደሉ ብጤዎች ነበሩ… እዚህ ቅርፅ ይጎድላል፣ እዚያ ድምፅ ይጎድላል፣ እዚያ ጠባይ ይጎድላል:: ብቻ፣ ሉልሰገድ እንዳለኝ «ሁሉም ያ ነገር አላቸው» ለጊዜው ሀበሾቹ የፈለጉት እሱን ነው:: መልኩ፣ የደስደሱ፣ ደማምነቱ፣ ጠባዩ፣ በኋላ ዝግ ተብሎ ይፈለጋል

ከሁሉም አስቀያሚ አማንዳ ሳትሆን አትቀርም:: ድብልብል አሜሪካዊት ናት:: ወፍራም አንገቷ ዙርያ ስጋው ተጣጥፏል፣ ሽንጥ 'ሚሉት የላትም፣ ስትራመድ የሚንቀጠቀጠው ባቷ ረዥም ቂጥ ይመስላል:: በጭራሽ ስሜት አትቀሰቅስም:: ሉልሰገድ ለምን 'ንደያዛት ለጊዜው ሊገባኝ አልቻለም:: የቸገረው እርጉዝ ያገባል ይባላል፣ እሱ ግን አቅፏት ይዞራል:: ወገቧ ዙርያ እጁ ስለማይደርስ ትከሻዋን አቅፎ እሷ ወገቡን አቅፋ ሲሄዱ አያቸዋለሁ:: የአማንዳ ፈገግታ ደግና ንፁህ ነው፣ ትንንሽ አይኖቿ ንፁህ ሰማያዊ ናቸው፣ ረዥም ፀጉሯ በጣም ንፁህ ነጭ ሆኖ፣ ጨረቃ ውስጥ ተነክሮ የወጣ ይመስላል:: ግን ይህን ሁሉ ውበት ሙማዋ አፍኖ ይዞ እንደሌለ አድርጎታል:: ስታያት ውፍረዋ ነው 'ሚታይህ፣ ስታስታውሳት ሙማዋ ነው ትዝ 'ሚልህ

ሲልቪ ግን በጣም ቆንጆ ናት:: «እጥር ምጥን» ያለች ፈረንሳዊት ሆና፣ ቡናማ ጉልህ አይኖቿ ውስጥና ውብ ስሬ አፏ ዙርያ እንደ ነበልባል የሚውለበለበው ፈገግታዋ ልብ ያሞቃል:: ወደ ኋላ የተለቀቀው ንፁህ ጥቁር ፀጉሯ ያብለጨልጫል፣ ስትራመድ ረዥም አንገቷን እያወዛወዘች ስለሆነ፣ ይሄ ጥቁር ሀር ፀጉሯ ዥው ዥው ይጫወታል:: ከታች ደሞ አበጥ ያለው ዳሌዋ ያንኑ ያህል ይወዛወዛል:: እግሯ በብዙ ጥንቃቄ የተቀረፀ ውብ ፍጥረት ነው:: ፍቅርም ምኞትም የምትቀሰቅስ ወጣት ትመስላለች:: ተመስገንን በጣም ትወደዋለች ሲሉ ሰምቻለሁ:: ይሄ ተመስገን ፈረንሳይ አገር የተሰማማው ይመስላል

* * *

ዩኒቨርሲቲውን «ሲቴ» ይሉታል:: ሲቴ ውስጥ መኝታ ቤት ያላቸው ሀበሾች ተመስገን፣ ሉልሰገድ፣ ተካ፣ ሀይለየሱስ ናቸው::

ሌሉቹ እንደኔው የሆቴል ክፍል ወይም የከተማ ቤት ተከራይተው ይኖራሉ

ቆንጆዋን አሜሪካዊት እንዳላገኝ ስፈልግ ከሉልሰገድ ወይም ከተመስገን ቁልፍ ለምኜ መኝታ ቤታቸው ቁጭ ብዬ 'ሰራለሁ:: ሀይለየሱስ ቤት 'ንዳልሰራ ሰውየውን አልወደውም:: ተካ ቤት 'ንዳልሰራ ደሞ የተካ ቤት ይገማል:: አይ ተካ! እግዜር ይይለት! አንዳንዴ 'ንኳ እግሩን ቢታጠብና እግር ሹራቡን ቢያጥብ ምን ችግረው ነበር? ዝም ብሎ ብቻ ጥፍሩን እየነከሰ መነጫነጭ ምን ያረግለታል?

ሉልሰገድ ወይም ተመስገን ቤት ቁጭ ብዬ ስሰራ አንዳንዴ ባህራም ይመጣል:: ትንሽ እናወራና ፒሙን ተላጭቶ «መልካም ስራ» ብሎኝ ይወጣል:: ፀጉራም ነው:: እጆቹን፣ ደረቱን፣ አንገቱን፣ ፊቱን ፀጉር ወርቷል:: ፂሙን ሲላጭ አይኑ፣ አፍንጫውና ጆሮው ብቻ ናቸው መላጨት የሌለባቸው:: ቢሆንም ፀጉሩ አያስቀይምም:: በጣም ንፁህ ሰው ነው::

አንዳንዴ ደሞ ቁጭ ብዬ ስሰራ ድቡልቡሏ አማንዳ ወይም ውቢቷ ሲልቢ ይመጣሉ – ወዳጆቻቸውን ፍለጋ:: ቀስ በቀስ እነዚህን ሁለት «ልጃገረዶች» እያወቅኳቸው፣ እየወደድኳቸው ሄድኩ:: እነሱም ሊወዱኝ እንደጀመሩ ታወቀኝ:: ስለራሳቸው ኑሮ በመጠኑ ይነግሩኝ ጀመር. . .

እንዳንድ ቅዳሜ ማታ ሀበሾቹና ጓደኞቻቸው «ሱርፕራዝ ፓርቲ» ያደርጋሉ:: «ሱርፕራዝ ፓርቲ» ድንገተኛ ብጤ ነው:: ታስቦ የታቀደ ፓርቲ ሳይሆን፣ ጓደኞሞች ሲገናኙ «ዛሬ ምን እናርግ? ሲኒማ 'ንግባ ወይስ ምን ይሻላል?» ይባባሉና «ለምን ሱርፕራዝ ፓርቲ አናረግም?» ይላሉ:: ያን እለት ማታ ፓርቲው ይደረጋል:: የተገኙ ሰዎች ይጠራሉ፣ የራሳቸውን መጠጥ ይዘው እንደሚመጡ የታወቀ ነው:: አንዱ ቤት ፓርቲው ይደረጋል:: ለዚህ ጉዳይ ሀበሾቹን ባህራም ያገለግላቸዋል – እንደ እውሉ ነፋስ በፍጥነት መዘዋወር ይጀምራል፣ ወንዶቹን ይጠራል፣ ሴቶቹን ይጋብዛል፣ እዚህ ትእዛዝ



@BOOKALEM

እዚያ ምክር ይሰጣል፣ ከዚህ ዲስኮ ከዚያ ሴት ይጥላል፣ ፓርቲው ይጀመራል:: ተሳታፊዎቹ ወንዶች አብዛኞዎቹ ኢትዮጵያውያንና ኤሬናውያን ናቸው፣ የሁለቱ አገሮች ማህበር ይመስላል

እንዲህ አይነት ፓርቲ ውስጥ ነበር ሉልሰገድ አማንዳን ያገኛት:: ፓርቲው ውስጥ ጥቂት ሴቶች ብቻ ነበሩ፣ እነሱም ተይዘዋል:: ያልተያዙ አንዲት በጣም ደቃቃ የሆነች የሩቅ ምስራቅ ልጅና አንዲት አስቀያሚ ድቡልቡል አሜሪካዊት ብቻ ናቸው:: ምስራቃዊቱ በጣም ደስ ትላለች፣ ግን ሉልሰገድ እሷን ይዞ አልጋ ውስጥ ሲገባ ሊታየው አልቻለም:: «ዎ! ብትሞትብኝስ?» ብሎ አሰበ:: ተዋት:: ድቡልቡሏ አሜሪካዊት ፊዕማ ደስ አትልም፣ ግን ሙዚቃውና መጠጡ እየገፋፉ ወደሷ ወሰዱት:: ተዋወቃት:: ስሟ አማንዳ ነው አለችው፣ አብረው ይደንሱ ጀመር:: በእንግሊዝኛ እያወሩ ሁለቱም በብዙ ጠጡ፣ ሞቅ አላቸው:: ስታቅፈው ስታናግረው በጣም ደስ እያለችው ሄደች— ይስማት ጀመር

«ተው እዚህ አትሳመኝ» አለችው

«ምናለበት?» አላት ጆሮዋን እየሳመ

«አልችልም:: ስሜቴ በጣም ይቀሰቀሳል» አለችው:: ድምፅዋ በጣም አቆመበት::

«ታድያ ምናለበት?» አለ እየተሻሻት

«ያኔ መሳም ብቻ አይበቃኝም» ብላ በሀይል ተጠጋችው::

ሉልሰገድ ቀስ ብሎ ወደ አንዱ መኝታ ክፍል ገብቶ እዚያ ይሳሳሙ የነበሩትን ሁለት ፈረንሳዮች አስወጣቸው:: (መኝታው የማን እንደሆነ እንጃ) መብራቱን አጠፋ:: ተመልሶ መጥቶ አማንዳን ወደዚህ ጭለማ መኝታ ቤት ወሰዳት:: በሩን ቆለፈ:: አልጋው ላይ ኢጋድሞ ይስማት ጀመር:: እየሳመ፣ እያሻሸ ሙታንታዋን አስወለቃት:: ጭለማ በመሆኑ አስቀያሚ መልኳ ስለማይታየውና፣ አሳሳም ከማወቋም በላይ ወፍራም ገላዋ ምቹ ስለሆነ፣ እጅግ በጣም ተደሰተባት

ጠግቦ ከለከለችው ከላይዋ ሊነሳ ሲል፣ እቅፍ አደረገችውና እንዳይነሳ

«እባክህን ትንሽ ቆይልኝ» አለችው:: እንድ የማይታወቅ ሀዘን



@BOOKALEM

ከድምፅዋ በኩል መጥቶ ልቡ ውስጥ ገባ። ዝም ብለው ቆዩ።

«ይሰማሀል ዘፈኑ?» አለችው

እዚያኛው ክፍል ውስጥ፣ ዝግ ያለ ያዘነ የአለን ባርዬር ዘፈን ይሰማል።

"Elle était si jolie
Je n'oublierai jamais…"

(እጅግ የተዋበች ነበረች፡— እስከመቸም አልረሳትም. . .)

በፈረንሳይኛ «አንተ ግን አሁን ትረሳኛለህ» አለችውና እቅፍ አደረገችው። እንባዋ ጉንጬን ነካው። የሚያደርገውን አጣ፤ የሚናገረውን አጣ። ዝም ብሎ አቀፋትና በእንግሊዝኛ

«አልረሳሽም፤ ለምን እረሳሻለሁ?» አላት

«ርካሽ ሴት መስዬ እታይሀለኋ»

«በጭራሽ ርካሽ አትመስይኝም»

«ርካሽ እመስላችኋለሁ፤ ግን ርካሽ አይደለሁም። ነገሩ ሌላ ነው»

«እኔ ርካሽ ሆነሽ አትታይኝም»

«እውነትክን ነው ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ»

«እውነቴን ነው። ለምንድነው 'ምታለቅሺው?»

«እንዲሁ»

«ንገሪኝ» አላት፣ በእጁ እንባዋን እየጠረገ

«ሌላ ቀን እነግርሀለሁ. . . የተገናኘን 'ንደሆን»

«ለምን አንገናኝም?»

«ትሸሸኛለህ። ይታወቀኛል»

«ለምን?»

«እጣዬ 'ንደሱ ነው»

«ተሳስተሻል»

«እስቲ 'ናያለን። ስማ. . .»



@BOOKALEM

የአለን ባርዬር ዘፈን ተደግሟል፡–

"Aujourd'hui c'est l'automne
Et je pleure souvent
Aujourd'hui c'est l'automne
Qu'il est loin le printemps…"

(ዛሬ በልግ ነው
ዘወትር አለቅሳለሁ
ዛሬ በልግ ነው
ፀደዩ ምንኛ ይርቃል!. . .)

ሲያባብላት ትንሽ ከቆየ በኋላ ተነስተው ወደ መደነሻው ክፍል ገቡ። በብርሀን አያት። ከነጭ ፀጉሯ ሌላ መልክ የላትም። ዙሪያ ፊት፣ ጮማ ውስጥ የተቀበሩ አይኖች፣ ካገጯ በታች ትርፍ አገጭ፡– እስቀያሚ ነች። ግን ስታሳዝን! ሉልሰገድ ሊለያት አልፈለገም። ሲያስደንሳት ሲያጫውታት አመሸ

ሌሊት ቤቷ ሲያደርሳት «መቼ አገኝሀለሁ?» አለችው። በምሳ ሰአት ምግብ ቤቱ በር እንዲገናኙ ተቃጠሩ።

* * *

ተካ ብሽቅ ነው 'ንጂ መጥፎ ልጅ አይደለም። እንዲያውም ልቡ በጣም ሰፊ ነው። ለምሳሌ አንድ ቀን ስናወራ

«እኔ ሰው አውቆ ክፉ ይሰራል የሚባለውን አልቀበልም» አለኝ «ማንም ሰው በጣም ክፉ የተባለው 'ንኳ ቢሆን፣ ክፉ 'ሚሰራው ደግ የሰራ እየመሰለው ነው። ባለማወቅ ነው»

«ሚስትህን ወይም እጮኛህን ቢያማግጥብህስ?» አልኩት

«አንተን ለመጉዳት አይደለም፣ ሴትዮዋን ሊደስትባት ፈልጎ ነው 'ንጂ»

«አሳብቆ ሲያጣላህስ?»

«ለክፋት ያለው አይደለም። ወይም ስብቀቱ ትልቅ ደስታ ስለ ሚሰጠው ነው፣ ወይም ስትጣሉ እሱ የተጠቀመ እየመሰለው ነው። ለክፋት ብሎ ክፋት አይሰራም። ባለማወቅ፣ ባለማመዛዘን ነው»

«እሁን አንዱ ቢጎዳህ አትቀየመውም?»



@BOOKALEM

«ለጊዜው እቀየመዋለሁ:: ግን ንዴቱ ሲበርድልኝ፣ ለክፋት ብሎ እንዳልጎዳኝ ይገባኛል:: ስለዚህ እሸሸዋለሁ 'ንጂ አልጠላውም»

«ባንተ ቤት የሰው ልጅ ጥሩ ነው?»

«አዎን:: ጥሩ ባይሆንም ክፉ አይደለም:: የሚያበሳሸው አለማወቅ ብቻ ነው:: ብታስብበት፣ አንድ ነገር በእውነት መጥፎ መሆኑን ካየ፣ ሊያደርገው አይችልም»

ተካ በልቡ ጥሩ ልጅ ነው:: ግን አቤት ሲያበሽቀኝ! ጥፍሩን መንከሱ፣ ሰውነቱን አለመታጠቡና ጥርሱን አለመቦረሹ የራሱ ጉዳይ ነው:: ግን ባገኘኝ ቁጥር «ከየት ነው 'ምትመጣው?» ብሎ ይጠ ይቀኛል:: መመለስ አለብኝ:: «ምን ትሰራ ነበር?» ይለኛል:: እመልሳ ለሁ:: ቀጥሎ «ወዴት ነው 'ምትሄደው?» ይለኛል:: እነግረዋለሁ:: «ምን ልታረግ ነው እዛ 'ምትሄደው?» ይለኛል:: እነግረዋለሁ

ባገኘሁት ቁጥር እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ይሰለቸኛል:: ግ እርር ቅጥል የሚያረገኝ ምንድነው? ከየትም ብመጣ፣ ወዴትም ብሄድ፣ ምንም ብሰራ፣ በጭራሽ ደንታ የለውም! እንዲሁ ነው 'ሚጠ ይቀኝ:: ያለ እንዳች ምክንያት! ልማድ ስለሆነበት ብቻ

ሌሎቹን ሀበሾች ግን ይሄ የተካ ጥያቄ ማብዛት አያናድዳቸውም፣ በመጠኑ ያስቃቸዋል 'ንጂ:: እነሱን የሚያናድዳ ቸው (እና እኔን የሚያስቀኝ) ሌላ አመል አለው:: እርር ቅጥል የሚያረጋቸው! አንዲት ልጅ ደስ ብላቸው ሊያበስሏት የፈለ 'ንደሆነ «እባክህን ለኔ ተውልኝ፣ ልቤን ወስዳዋለች:: ልሞክራትና እምቢ ያለችኝ 'ንደሆነ አንተ ትሞክራለህ» ይላቸዋል

እንግዲህ እነሱ ለጊዜው ሌላ ሴት ስላላቸውና እሱ ሴት ስለሌለው አስበውለት ይተዉለታል:: ታድያ ምንም አይሰራም ሞክሮ ቢያቅተው 'ንኳ ያዝኑለት ነበር:: በጭራሽ ሊያነጋግራት አይሞክርም 'ንጂ:: እንዲያው ብቻ «ዛሬ እንዲህ ብላ አየችኝ- ዛሬ እንዲህ 'ንዲህ እያለች ባጠገቤ አለፈች» ይላቸዋል:: በመሀሉ አን ፈረንሳይ ይቀልባታል:: ጓጉተው ይቀራሉ

ሀበሾቹ በተካ ምክንያት ከዚህ የባሰ የሚበሳጩበት ጊዜም አለ ፓርቲ ላይ አንዲቱን አብስለው ሰብከው አስደስተው ሊያሰኙዋት ትንሽ ይቀራቸዋል:: በዝግተኛ ሙዚቃ አትፈዋ



@BOOKALEM

እየተወጣወጡ በጆሮዋ አስደሳች ምናምን እያንሾካሾኩላት «ዛሬ አብረን ብናድር እንዴት ጥሩ ነበር! የሚቻልሽ ይመስልሻል?» ይሉዋታል:: «አይመስለኝም» ትላቸዋለች:: የምሯን ይሁን ወይስ መግደርደሯ ይሁን አያስታውቅም:: ስለዚህ የበለጠ እያስጠጉዋትና እየተሻሹዋት «እሬ ባክሽን አስቢልኝ:: ተሰቃየሁ'ኮ» ይሏታል:: ዝም ትላቸዋለች:: «ታድያስ የኔ ቆንጆ፣ እሺ ትይኛለሽ?» ይሏታል

ይሆን ጊዜ ተካ ኩትፍ ይልና «አንድ ጊዜ እንደገና?» ብሎ ልጅቷን ይወስዳታል:: እዚህ ላይ ያለ ንዴት! ታድያ ምንም አያረጋትም'ኮ:: እንዲሁ ነው

ይኸው ካዲስ አበባ ከመጣን ስባት ወር ያልፋል:: ተካ እስካሁን እንዲት ሴት እሺ አስኝቶ አያውቅም:: ሴት ሲያምረው ማርስይ ይወርድና ሸርሙጣ ተኝቶ ይመለሳል:: ለዚህ ነው አንድ ቀን ስለአማንዳ የነገረኝን በሙሉ ላምነው ያልፈለግኩት

ከምሳ በኋላ ነበር:: ሲቴ (ዩኒቨርሲቲው) አጠገብ ያለው መናፈሻ ውስጥ እኔና ተካ ቁጭ ብለን ፀሀይ ስንሞቅ፣ አማንዳ መጣችና «ሉን አላያችሁትም ወይ?» አለችን:: (ሉልስገድን ሉ ነው 'ምትለው) «አላየነውም» አልናት:: እየተድበለበለች ሄደች:: ውብ ነው ፀጉሯ ወደ ኋላዋ ተለቆ ፀሀይ ውስጥ ይብለጨለጫል፣ የረጋ የጨረቃ ብርሀን ይመስላል:: ተካ ጥፍሩን እየነከሰና የጥፍሩን ብጥስጣሽ «ቱ» እያለ እየተፋ

«እቺ ቂንጥራም! አሁን'ኮ ቁላ አምሯት ነው» አለ:: አበሸቀኝ::

«ለሌላ ጉዳይ ሊሆን አይችልም?» አልኩት

«ኡም! ቁላ ፍለጋ ነው እያልኩህ!»

«ለምን 'ንዲህ ትሆናለህ? የት ታውቃታለህና ነው 'ንደዚህ ስሟን 'ምታጠፋው?»

«ይልቅ አንተ የት ታውቃታለህና ነው 'ንዲህ 'ምትከራከርላት?»

«እኔማ አላውቃትም»

«እንግዲያው ለምን ትከራከርላታለህ? እንዲት ቂንጥራም



@BOOKALEM

አሜሪካን ኖት፣ ቢቃ»

አብዛኛውን ጊዜ ተካ ምንም አይነት መራራ ነገር ቢናገር ያነዘኛል እንጂ አልናደድም፡፡ ዛሬ ግን ምን እንደነካኝ እንጃ፣ ስለማንዳ ተቆርቋርኩላት፡፡ ተናድጄ

«የት ታውቃታለህ? እንዳንተ ያለ የት ያውቃታል?» አልኩት

«እእ አውቃታለሁ አላልኩም'ኮ»

«እንግዲያው አታውቃትማ»

«አላውቃትም»

«ጥሩ፣ እንግዲያው ስሟን አታጥፋ»

አጭር ዝምታ፡፡ ከኛ ፊት ብለው የፈረንሳይ ሀገናት አሸዋ እየስፈሩ ይጫወታሉ፣ ይንጫጫሉ፡፡ አግድም ወንበሮቹን አርጊቶችና ሽማግሌዎች ስፍረውባቸዋል

«አላውቃትም፡፡ ግን አሁን ቁላ ፊልጋ 'ንደሆን እርግጠኛ ነኝ» አለ ተካ

ከመናደዴ የተነሳ ወደሱ በኩል ተንጠራርቼ ፊቴን ወደ ፊቱ አስጠጋቼ

«እንዴት እንደዚህ እርግጠኛ ሊሆኑ ቻሉ፣ እባክዎትን» አልኩት

በጭራሽ ሳይናደድ፣ እንዲያውም ያልተጠረገ ጥርሱን በብዛ ብጤ ፈገግታ እያሳየኝ፣ ዝቅ ባለ ስላማዊ ድምፅ

«ብድቻታለኋ!» አለኝ፡፡ (ትንፋሹ!)

እየሳቅኩ ወደ ቀድሞ ቦታዬ ተመለስኩ

«እውነቴን ነው» አለ «ያለፈው ቅዳሜ ሳምንት ኢራንያኖቹ ቤት ሱርፕራዝ ፓርቲ ነበር፡፡ ሉልሰገድ አልነበረም፡፡ እሷ ስክራ ነበር፡፡ ትንሽ ተጠጋኋትና ስተሻሻት ጊዜ ቆመባት፣ እቺ ቂንጥሬም!»

«ቂንጥሬም አትበላት! ካልስደብኩት ማውራት አትችልም 'ንዴ?»

«ፓርኪስ መኝታ ቤት አስገባኋትና በጭለማው እየደነስን እጄን ልብሷ ውስጥ ከትቼ ወፍራም ቂጧንና እምሷን አሻሸሁላት፡፡ እምሷ



@BOOKALEM

ረጠበ፣ ጨቀየ፣ ጣቴን ከተትኩባት። ማቃሰት ጀመረች። ሙታንቲዋን ሳወልቅ ስል

«ሉን እንዳትነግረው ቃልህን ስጠኝ» አለችኝ

«ቃሌን ሰጠኋት። ሞላኋት። ከጨረስኩ በኋላ «እንዴ. እንድገም?» አለችኝ

«ምን አልካት?» ብዬ ጠየቅኩት

«Go to hell!» አልኳት («ገደል ግቢ.»)

«ለምን?»

«አስጠላችኝ! ብተፋባት አልጠላም ነበር» ዝም አልኩት

«ሉሪዬን ስታጠቅ 'ሉ እንዳያውቅ ቃልህን ሰጥተኸኛል' አለችኝ»

«Shut up!» አልኳት («ዝም በይ!»)

«ከዚያ በኋላ ሌላ ጊዜ ተኝተሀት ታውቃለህ?» አልኩት

«የለም»

«እምቢ አለችህ?»

«የለም። በነጋታው ለሉልሰገድ ነገርኩት»

«ለምን? ለምን ነገርከው? ምን ይጠቅመኛል ብለህ ነገርከው? ምን ጥቅም አገኘህበት?»

«እውነቱን ይወቅ ብዬ ነዋ!»

«ልጅትዋስ? አትቆጠርም? የሰጠሀት ቃልስ? ዋጋ የለውም?»

«ላንዲት ቲንተሪም አሜሪካን ብዬ ከእውነቱ ልራቅ 'ንዴ?»

«ቲንተሪም አትበላት አልኩህ!»

«እሺ»

«ለምን መጀመሪያውኑ ቃልህን ሰጠሀት?»

«እንድትሰጠኝ ብዬ ነዋ!»

«ሉልሰገድ ምን አለ የነገርከው ጊዜ?»

«ምንም አላለም:: ‹ይቅርታ አርግልኝ ቆሞብኝ ስለነበረ ነው› አልኩት»

«ምን አለህ?»

«ምንም ይቅርታ አያስፈልግ፣ እርሳው» አለኝ

«ሌላ ምንም አላለህ?»

«እንደነገርከኝ አማንዳ እንዷታውቅ:: ያወቀች ‹ንደሆነ ትጣላኛለህ፣ አለኝ»

«ስለዚህ ጉዳይ ሌላ ‹ምትነግረኝ አለ?» አልኩት ተካን

«የለም» አለኝ

ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ

«የት ልትሄድ ነው?» አለኝ::

«የትም:: ካንተ መሸሼ ነው»

«ምነው? ምን አረግኩህ?»

«አናደድከኝ»

«ለምን?»

«በልጅቷ ምክንያት»

«ምን የሚያናድድ አለው? አንተ ጉዳዩ ውስጥ የለህበት»

«አሁን ዝም በለኝ!» ብዬው ሄድኩ

ታድያ ለእራት አገኘኝና፣ ልክ ምንም እንዳልተባባልን ያሀል አነጋገረኝ:: ተካ ቂም አይይዝም:: በዚህ በኩል ልቡ ንፁህ ነው

ይህን የተካንና የአማንዳን ታሪክ ላምነው አልፈለግኩም:: ግን ተካ ከመሬት ተነስቶ የሚዋሽ ዓይነት አይደለም:: ቢሆንም. . .

ምናልባት ግማሹ እውነት ሊሆን ይችላል:: ግን ከጨረሱ በኋላ «እንዴ እንድገም?» ያለችው ውሸት መሆን አለበት

ለመሆኑ ለምን ይህን ታሪክ ነገረኝ? ሴት ማግኘት መቻሉን ለማሳወቅ ያለው ይሆን? ምስኪን ተካ!

* * *

ጠካፌ ዶርቢቴል በኩል ሳልፍ ሉልሰገድ ከዚያ ወጣ:: ቀይ ፊቱ



@BOOKALEM

ደም ለብሷል:: ጉልህ ዓይኖቹ ጉድጓዳቸው ውስጥ ይገላበጣሉ:: በጣም ተናዷል::

«ምን ሆንክ?» አልኩት

«ይህን ተካ አስታግስልኝ፣ አለዛ አንድ ቀን እገድለዋለሁ» አለኝ

«ምነው?»

«ባገኘኝ ቁጥር ያበሽቀኛል:: ላብድ ነው»

«ለምን ሁለተኛ እንዳታናግረኝ አትለውም?»

የተዘረዘሩ ጥቃቅን ጥርሶቹን በተሸነፈ የንዴት ሳቅ እያሳየኝ

«ቢያንስ አስር ጊዜ ብየዋለሁ» አለ «ሁለተኛ ያናገርከኝ 'ንደሆን፣ ወይ ለፖሊስ እነግራለሁ ወይ እገድልሀለሁ ብዬዋለሁ:: ደጋግሜ ደጋግሜ ነግሬዋለሁ:: ሰድቤዋለሁ»

«ታድያስ?»

«በሚቀጥለው ጊዜ ሲያገኘኝ ያነጋግረኛል:: ትንሽ ካናገረኝ በኋላ ያበሽቀኛል»

«አታኮርፈውም?»

«አይገባውማ!»

«አሁን ምን ይሻላል?»

«እኔ 'ንጃ:: ይህን ከተማ ለቅቄ ልሂድ መሰለኝ»

እየሳቅኩ «እስከዚያው ና ምን የመሰለ ቢራ ላጠጣህ» አልኩና ባቡር ጣብያው አጠገብ አንዲት ስም የሌላት ካፌ አለች፣ እዚያ ወሰድኩት:: አንድ ቡና አይነት ቢራ አለ፣ ከስኮትላንድ የሚያስመጡት:: ፀሀይ ላይ ቁጭ እንዳልን እሱን ቀመሰና

«ይህን እንዴት አገኘኸው 'ባክህን? እኔ ሁለተኛ ሌላ ቢራ አልቀምስም» አለ:: ንዴቱን መርሳት ጀምሯል:: ራሱን እየነቀነቀ

«የተካ ዋና ፕሮብሌሙ ምን መሰለህ?» አለኝ «ጥሩ ልጅ ነው:: ከሰው ጋር ተስማምቶ መኖር ይፈልጋል:: ግን በሄደበት ሰውን እንዳበሸቀ ነው:: ወዶ አይደለም:: ፍጥረቱ ነው»

«አውቃለሁ:: ረስቼ— አማንዳ ስትፈልግህ ነበር»



@BOOKALEM

ዝም አለ። ገባኝ

«የፈረንጅ ሴቶች ሲስለቹ!» አልኩት

«ያንተም ስልችታሀለች?» አለኝ

«ፈረንጅ አይደለች?»

«አንተስ አትረባም» አለኝ

«ለምን?»

«ያችን የመሰለች ቆንጆ ምኗ ይሰለቻል? ድምፅዋ ብቻ ይበቃል። በዛ ሰማያዊ አይኗ እያየችህ ያን ፈገግታ ስትሰጥህ— አንድ ፈገግታ እንደሱ ብታጠግኝ ችዬ ከሷ አልለይም ነበር። በዚያ ወፍራም ድምፅዋ 'ሉ ሃኒ ሉ' ብትለኝ ለዘለዓለም እታሰራለሁ»

«ፈገግታውንም ቁልምጫውንም ትሰጥሀለች ከፈለግክ»

«እንዲህም ብልህ'ኮ፣ ፈገግታውና ቁልምጫው ብቻ አይበቃም»

«አንተ ከፈለግክ ሌላውንም ትሰጥሃለች»

«እሱን ተወው! ካንተ ጋር ፍቅር እንደያዛት ያስታውቃል»

«ይመስልሀል» አልኩት

«ትወድሀለች ስልህ!»

«እሺ ይሁን። ግን አንዳንዴ ስላንተ ጣል የምታረገው ንግግር አንተም ጠጋ ብትላት እንደማትሸሽህ ያሳያል»

«እዬ? ምን አለች?»

«አይ፣ እሱን አልነግርህም። ጠጋ ብትላት ራሷ ትነግርሀለች»

«እውነት እንድወስድልህ ትፈልጋለህ?» አለኝ

«አዎን። ግን ለሀበሾቹ እንዳትነግር»

«ግድ የለህም። እኔ ምልህ— የኔን ሸክም ደሞ አንተ ትንሽ ብትሸከምልኝ። አውቃለሁ አስቀያሚ ነች። ግን ጠጋ ስትላት የደስ ደስ አላት። ደሞ ከዛች ከቆንጆ ጋር ስንብተህ ወደዚችኛዋ ስትመ



@BOOKALEM

ጥሩ ለውጥ ሳይሆን አይቀርም:: ሞክር እስቲ»

«አንተም ሞክር»

«Shake on it! (ጨብጠኝ)» አለኝ:: ተጨባበጥን

ትንሽ ቆይቶ፣ ራሱን እየነቀነቀ

«አባቶቻችን አሁን የተባባልነውን ቢሰሙ ምንኛ በናቁን!» አለ

እኔና ሉልሰገድ ሚስቶቻችንን እየያዝን አብረን ሲኒማ ገባን፣ አብረን ናይት ክለብ ሄድን:: ለመለዋወጥ ሞከርን:: አልቻልንም:: እነሱም ጓደኝነት ተያያዙ:: እንደተሸነፍን ገባን

«ገና የፈረንጆቹን ያህል አልሰለጠንንም 'ባክህ» አለኝ

«እስከመቸም አንሰለጥንም» አልኩት

ሚስት መለዋወጥ ሲያቅተን ጊዜ ታሪክ ተለዋወጥን:: የኔን እንዴት እንዳገኘኋት ነገርኩት:: እሱም ተራውን ነገረኝ:: ታሪኩን ሲጨርስ፣

«አንድ ቀን ምን ሆንኩ መሰለህ?» አለ «ከእራት በኋላ እቤቴ እንድንገናኝ ተቃጠርን:: የቀጠሮው ሰአት ሲደርስ ቤቴ መሄድ በጣም አስጠላኝ:: ሴት አጥተው ብቻቸውን የሚያድሩትን ጎረምሶች በጣም ቀናሁባቸው:: ቡና ጠጥተህ፣ ሲኒማ አምሽተህ ቤትህ መመለስ፣ ፒጃማህን ለብሰህ ጥቅልል ብለህ ብቻህን መተኛት፣ ይሄ በጣም ትልቅ እድል መስሎ ታየኝ! ገደል ትግባ! አልኩና ሲኒማ ገባሁ:: የጀምስ ቦንድ ፊልም ነበር ያየሁት:: ስለላውን፣ ተኩሱን፣ ቦክሱን፣ ድፍረቱን ከምንም አልቆጠርኩለት:: ትልቅ ጉብዝና ሆኖ የታየኝ ምን መሰለህ? ይሄ ጀምስ ቦንድ ያሰኘችውን ሴት ተኝቶ፣ ሲበቃው ዘወር ማለት ነው፣ አለቀ በቃ:: እኔ ግን ከአንዲት ሴት ዘወር ማለት አቅቶኝ እየቀጠርኳት ሲኒማ 'ገባለሁ:: ራሴን እንዴት ናቅኩት!

«ስለጀምስ ቦንድ እያሰብኩ ወደ ሲቴ ሄድኩ:: አኩርፋ እንደምትቆየኝ ስላወቅኩ፣ የምነግራትን ውሸት እያሰላሰልኩ መኝታዬ ገባሁ:: መብራቱን አበራሁ:: እንቅልፍ ተኝታለች:: መስኮቱ ላይና ወንበሩ ላይ ሸሚዞቼ፣ ካናቴራዎቼ፣ ሙታንታዎቼ፣ እግር ሹራቦቼ ታጥበው ተሰጥተዋል:: የተሰማኝን ልገልፅልህ አልችልም:: እፍረት

ነው ይመስለኛል:: ድቅቅ አልኩ:: ተሸነፍኩ

«ልብሴን አውልቄ አልጋ ውስጥ ስገባ ነቃች:: የት ቆየህ አላለችኝም:: ዝም ብላ አቀፈችኝ:: እቤት እንዴት ነው ያሳዘነችኝ! ሳለቅስ ምንም ያህል አልቀረኝም. . .

«በነጋታው ከሷ ጋር ዋልኩ:: ስለሷ ማወቅ ፈለግኩ:: ጠያየቅኳት:: ነገረችኝ:: ያልደረሰባት ግፍ ያለ አይመስለኝም— ማለቴ በወንድና በሴት መካከል የሚደረግ ግፍ:: ባሜሪካን አገር የሚደረገው ነገር አንዳንዴ ከኛ አገር ይብሳል:: ባስራ ሁለት አመቷ ሶስት ጎረምሶች በግድ ያዟትና ጭኗን ከፍተው ሻማ ጨመሩባት:: ይህን ምን ትለዋለህ? እስቲ እንደ ሴት ቢበዷት ምን ቸገራቸው ነበር? ባስራ ሰባት አመቷ ደሞ የታላቅ እህቷ ባል በጉልበት ተኛት:: ይህንንስ ስትነግረኝ አለቀሰች:: 'ቆንጆ 'ንኳ ብሆን ደስ ብየው ነው፣ አላስችል ብሎት ነው ይባላል:: ግን ቆንጆ አይደለሁም:: ምኔም ደስ አይልም:: እንግዲያው ለምን አዋረደኝ? ክፋትንና ጭቆናን የሚስብ አብሮኝ የተፈጠረ አንድ ነገር አለ መሰለኝ' አለች

«እውነት ይህን ምን ትለዋለህ» አለ ሉልሰገድ «አንድ ሰካራም አጎት አላት:: እሱ ደሞ አንድ ቀን በግድ ሊተኛት ሞከረ:: ታግላ አመለጠችው:: ግን መሞከሩ እጅግ ጎዳት:: ምን ትለዋለህ ይህን አይነት እድል? ከዚህ ሁሉ በኋላ ወንዶችን ጨርሳ መሸሽ ነበረባት:: እሷ ግን ተቃራኒ አደረገች:: ለለመናት ሁሉ መስጠት ጀመረች:: እኔ ለዚህ ማስረጃ ላገኝለት አልችልም:: ግን ምናልባት ለሁሉም መስጠት ያው ለማንም እንዳለመስጠት ይቆጠር እንደሆን?

«ብቻ ምን ልበልህ? በጭራሽ አምላክ ያጠቃት ልጅ ናት:: 'ካወቁኝ ወንዶች ሁሉ አንተ ብቻ ነህ እስካሁን እንደ ሰው የቆጠርከኝ' አለችኝና እንደገና አለቀሰች:: አልጋው ግርጌ ተንበረከከችና ጉልበቴን አቅፋ "If you only knew what it means to me! I'll never be able to repay you, never, never!" እያለች እንባዋን አወረደችው:: («ለኔ ምን ማለት እንደሆነ ባወቅከ! እስከመቸም ውለታህን ልከፍል አልችልም፣ እስከመቸም!»)

«ራቁቷን ተንበርክካ ሳለ፣ ኑሮ ገላዋ እንዴት ድቡልቡልና አስቀያሚ 'ንደሆነ ታየኝ:: በጣም አሳዘነችኝ:: እንደዛ እንዳ አላውቅም:: አብሬያት አለቀስኩ»

«'ምነው አለቀስክ? ትወደኛለህ 'ንዴ?' አለችኝ»

«ምንም ምርጫ አልነበረኝም»

«'አዎን እወድሻለሁ' አልኳት»

«'ምንም ወፍራም ብሆን?'»

«'ምንም ወፍራም ብትሆኚ'»

«ምንም ርካሽ ብሆን?»

«ምንም ርካሽ ብትሆኚ:: ደሞ ርካሽ አይደለሽም:: ተጠቃሽ ተበደልሽ እንጂ አንቺ ያጠፋሽው ጥፋት የለም:: You are a victim («ጥቃት የደረሰብሽ ነሽ»)

"'Yes I am a victim. God, I am a vicitim with no one to defend me,' አለችና የባሰውን ስቅስቅ ብላ አለቀሰች

(«አዎን ተጠቂ:: ማንም ተከላካይ የሌለኝ ተጠቂ ነኝ»)

«ሳባብላት ብዙ ጊዜ ወሰደብኝ

«እና ይኸውልህ፣ አገሯ እስክትገባ ድረስ እንድወዳት ከራሴ ጋር ግዴታ ገብቻለሁ»

«መቼ ነው 'ምትሄደው?» አልኩት፣ ውስጥ ውስጡን እያደነቅኩት

«ካንድ ወር ተኩል በኋላ»

«አይ! አጭር ጊዜ ነዋ»

«በኔ ቦታ ብትሆን አጭር ጊዜ አይመስልህም ነበር:: ያንተስ መቼ ነው 'ምትሄድልህ?»

«የኔ እንጃ መሄዷን:: ግን እጮኛዋ ካንድ ሁለት ወር በኋላ ይመጣል»

«እጮኛ አላት?! ትወደዋለች ይመስልሀል? ፍቅር ማለቴ ነው»

«አዎን»

«ታድያ ካንተ ጋር. . .»

«ከኔ ጋር ያ ነገር ብቻ ነው:: አየህ፣ አገሯ ሳለች ከጥቁር ጋር

መተኛት በጣም ያምራታል:: ግን አትደፍርም:: ስለዚህ፣ ፍራንስ የነፃነት አገር እንደመሆኑ መጠን. . .» ትከሻዬን እንቀሳቀስኩ

«እርሙኛዋስ ምን ይላል?» አለኝ ሉልሰገድ

«እንዴት ያውቃል?»

«አይ ሴቶች! እኛም'ኮ ስናምናቸው እንደዚህ ይጫወቱብናል»

«ምን አለበት? እኛስ እንጫወትባቸው የለ?»

«ቢሆንም አንድ አይደለም»

«ለምን አንድ አይደለም?»

«እነሱ ሴቶች ናቸዋ!»

በዚህ ሰንበት «እኔ ምልህ» አለኝ «ብዚያ በሰማያዊ አይኗ ስታይህ ፍቅር የያዛት ይመስለኝ ነበር:: ለካስ ጥቁር ወንድ ስለሚያምራት ኖሯል?»

«አዎን»

«እንዲህ ከሆነማ ብሞክር ሳይቀናኝ አይቀርማ»

«እርግጠኛ ነኝ ይቀናሃል:: በጣም ደስ ትላታለህ ስልህ!»

እንደማፈር ብሎ፣ ግን ጉልህ አይኖቹ እየሳቁ

«ምኔ ነው ደስ የሚላት?» አለኝ

«ምን ልበልህ፡ ብዙ ነገር ነው:: አይኖችህ፣ ቅላትህ፣ አረማመድህ:: ከሁሉ ይበልጥ ደስ የሚላት ግን ምን መሰለህ?»

«ምንድነው?» አለኝ

«ሌላ ቢራ እዘዝልኝና 'ነግርሀለሁ» አልኩት:: አዘዘልኝ

«ምኔ ነው ከሁሉ ደስ የሚላት?» አለኝ

«ቆይ ቢራው ይምጣ» አልኩት:: በሽቀ:: ጠረጴዛው ላይ በጣቶቹ ታምቡር እየመታ እኔ እያየሁት እየሳቅኩ ቆየን:: ቢራዬ መጥቶ አንዴ እንደተጎነጨሁለት፣

«ተናገር 'ንጂ!» አለኝ

«ከሁሉ ደስ የሚላት ፈገግታህ ነው»



@BOOKALEM

«ሙት? ቆይ 'ስቲ» አለና ከኪሱ አንድ ትንሽ መስተዋት አውጥቶ መስተዋቱን እያየ ፈገግ አለ:: ራሱን እየነቀነቀ «እቺ ልጅ አልተሳሳተችም:: እነዚህ ጥርሶቼ እንደ አይጥ ጥርስ ቢዘረዘሩም፣ ፈገግታዬ ልብ ያጠፋል:: ፈገግታዬ ልብህን አያጠፋውም?»

«እናትክን! ይልቅ ምን እንዳለች ልንገርህ» አልኩት

«ንገረኝ»

«ፈገግታው በሀይል ደስ ይለኛል:: ጥርሶቹን ሳያቸው ጭኖቼ መሀል ትኩሳት ሲቆሰቆስ ይሰማኛል» አለች

«እውነትክን ነው? ጥርሶቼ ይህን ያህል sex-appeal (ማራኪነት) አላቸው? እቺ ልጅ በጣም አስተዋይ መሆን አለባት»

«እንዲህ አይምሰልህ:: ሌላ ምን አለች መሰለህ?»

«ምን አለች?»

«እዚህ አለም ላይ ምን ያምርሻል ብትለኝ» አለች «ሉልሰገድ ጭንና ጭኔን ክፍት ቢያደርገኝና—» አቋረጥኩ

«እና?» አለ:: ተንገብግቧል

«እና ብልቅጥ ሲልለት፣ ሉልሰገድ ይህን እምሴን በጥቃቅን ቆንጆ ጥርሶቹ ጋጥ ጋጥ! ጉርስ! እኝክ! ቢያደርግልኝ ያምረኛል» አለች

«በሽቃጣ! አንት እርኩስ!»

«እኔ ምን አጠፋሁ? የፈለገችህ እሷ» አልኩት

ሁለታችንም መሳቅ ጀመርን:: ሌላ ቢራ አዘዝን:: ብዙ ሌላ ወሬ አወራን:: ስለባህራም ጠየቅኩት:: እንዲህ አለኝ

«በእውነቱ አውቀዋለሁ ልልህ አልችልም:: የሚታወቅ አይነት ሰው አይደለም:: ስምንት ወር ሙሉ ገንዘብ ሳታገኝ መኖር፣ ግን ገንዘብ ከሚያገኙ ሰዎች እኩል መኖር፣ ቀልድ አይደለም:: ኮሙኒስት መሆኑን ታውቅ የለ? አንዳንዴ ከሀበሾቹ ወይም ከኢራኖቹ ጋር ሳይሆን ከፈረንሳይ ጓደኞቹ ጋር ማታ ማርሰይ ሄዶ አምሽቶ ወይም አድሮ ይመለሳል:: የኮሙኒስቶች ስብሰባ ነበረን ይላል:: ግን አንዳንዴ ምን ብዬ አስባለሁ ይመስልሀል? በእውነት ኮሙኒስቶች ስብሰባ ይሄዳል? ወይስ ማርሰይ ጋንግስተሮች ጋ



@BOOKALEM

እንቆቅልሽ ፍች ይገኝለታል፣ እየሀ ይሄዳል? እንደሱ ከሆን ለገንዘቡ እንቆቅልሽ ፍች ይገኝለታል፣ እየሀ

ይሄዳል? እንደሱ ከሆነ ለገንዘቡ እንቆቅልሽ ፍች ይገኝለታል፣ እየሀ ይሄዳል? እንደሱ ከሆን ለገንዘቡ እንቆቅልሽ ፍች ይገኝለታል። እዚህ ከመምጣቴ

«ይህን የሚያስፕኝ አንድ ምክንያት አለ። እዚህ ከመምጣቴ በፊት በይሩት ነበርኩ ይላል። ሁለተኛ አመት ኮሌጅ ጨርሼ ሶስተኛ አመት ስገባ በያስሚን ፍቅር ምክንያት ወዲህ መጣሁ ይላል። ያስሚን ይወዳት የነበረ የሊባኖስ ልጅ ናት። ግን ባንዲት ልጅ ፍቅር ምክንያት ትምህርትህን እጋምሰህ አይንህን ጨፍነህ ትሸሻለህ? ደሞ፣ በይሩት ሳለሁ ቤቶቼ ብዙ ገንዘብ ይልኩልኝ ነበር፣ እዚህ ስመጣ ጊዜ ግን ድንገት ድምፃቸው 'ንኳ ጠፋ ይላል። ለምን? ሌላ ነገር ደሞ። በይሩት የመካከለኛው ምስራቅ ሰላዮችና ጋንግስተሮች ዋና ከተማቸው ነው ሲባል ሰምቻለሁ። ባህሪም የሚለው ሁሉ እውነት ሊሆን ይችላል። ግን አይመስልም

«ይህንም ስልህ፣ እንዲሁ የሚመስለኝ ነው፣ እንጂ፣ ለምን እንዲህ ይመስልሀል ብትለኝ በቂ ምክንያት ልሰጥህ አልችልም

«እኔ በበኩሌ ጋንግስተር ሆን ኮሙኒስት ሆን ግድ የለኝም። ልጁ እንደተካ ብሽቅና ነጃሳ ሳይሆን፣ ተወዳጅና አብረኸው ስትሆን የሚያስቅህ የሚያስደስትህ ነው። ስለዚህ ባላውቀውም እወደዋለሁ። ሲቸግረው አንዳንዴ ጥቂት ፍራንክ እፀድቅበታለሁ»

«አቃጣሪ ሊሆን ይችላል?»

ጥያቄዬ አሳቀው፣ በጉልህ ውብ አይኖቹ ብቻ ሳይሆን በጥቃቅን ዝርዝር ጥርሶቹ ጭምር ሳቀብኝ

«ይህን ሀሳብ ያሳደረብህ ተካ መሆን አለበት» አለኝ

«አዎን»

«አይ ተካ ብሽቁ! ለምን ደግ ሲውሉለት አይገባውም? ስለሱ ልንገርህ። አንድ ቀን ማታ ሱርፕሪዝ ፓርቲ አድርገን ሁላችንም ስንደንስ ሴት ስናበስል፣ ተካ አንድ ማእዘን ጋ አንድ ወምበር ላይ ቁጭ ብሎ ነጭ ወይን እየጠጣ ሲጋራ ያጨሳል፣ ጥፍሩን ይነክሳል። ባህሪም እንዲህ አለኝ 'ይሄ ተካ ብቻውን ቁጭ ብሎ አሳዘነኝ። ያቺ ልጅ አልተያዘችም ቀስ አርገን እናያይዛቸው።' እኔ መቸም ተካን አቀዋለሁ፣ እምቢ አልኩ። ባህሪም ተቆጣኝ 'አትረባም' አለኝ። ሄዶ ተመስገንን አግዘኝ አለው። ተመስገንም እምቢ አለ። ባህሪም 'እናንተ ሀበሾች በጣም ጥሩ ሰዎች ትመስሉኝ ነበር፣ ለካስ አትረቡም።



@BOOKALEM

ለራሳችሁ ደስታን ካገኛችሁ፣ ሌላው ቢቀና ቢበሳጭ ግድ የላችሁም፡፡ በሉ ተውት! ብቻዬን እሞክራለሁ' አለ፡፡ ተው ይቅርብህ አልነው፡፡ እምቢ አለ፡፡ ተካንና ያችን ልጅ ሊያያይዛቸው ሞከረ

«ለመልካም ሙከራው ተካ ሲያመሰግነው ሰምቶሀል

«እንተካ ነጃሳ ያሉትን ቢሉ፣ ባህሪም የሚወደድና የሚከበር እንጂ የሚናቅ አይደለም» አለኝ

ይሄ ሉልሰገድ ራሱ የሚወደድና የሚከበር ልጅ ነው፣ ያስታውቃል

* * *

አንድ ቅዳሜ ከሰአት በኋላ ሉልሰገድ ቤት ውስጥ ቁጭ ብዬ ስሰራ አማንዳ ቁና ቁና እየተነፈሰች ገባች (ሶስተኛ ፎቅ ነው ቤቱ)

«ፈረንሳዮቹ ለምን ኤለቬተር አይሰሩም?» አለችና አልጋው ላይ በጀርባዋ ተከመረች፡፡ ስራዬን ትቼ ወንበሬን ከመጻፊያው ጠረጴዛ ወደ አልጋው በኩል አዞርኩት

«ስራህን አሳቋረጥህ» አለችኝ

«ምንም አይደለም» አልኳት

ወሬ ጀመርን፡፡ ሞርሞን ነኝ አለችኝ፡፡ ስለሞርሞን ሀይማኖት ብዙ ስለማላውቅ ጠያየቅኳት፡፡ ስለጆዜፍ ስሚዝና ስለወንጌሉ፣ እንዴት ሁለቱ «የጠፉ የእስራኤል ነገዶች» ውቅያኖስ አቋርጠው አሜሪካ እንደደረሱ፣ እንዴት በሀጢአታቸው ምክንያት ነጮቹና ቀዮቹ እንደዋጡዋቸው፣ ምናምን ዝብርቅርቅ ታሪክ ዘበዘበችልኝ፡፡ አሁን አብዛኛውን ረስቼዋለሁ፡፡ ግን ስለራሷ የነገረችኝን አስታውሳለሁ

«እኔ የሞርሞንን ሀይማኖት በሙሉ ልቤ እቀበለዋለሁ» አለች «የሞርሞን ሀይማኖት ደሞ የጥቁሮች ፍጥረት ከነጮች ፍጥረት በታች ስለሆነ፣ ነጮች ከጥቁሮች ጋር አይጋቡ ይላል፡፡ እኔ ግን ቢቻለኝ ከሉ ጋር ልጋባ እፈልግ ነበር፡፡ ሉን ምን ያህል እንደምወደው ይታይህ»

«ለመሆኑ ሉልሰገድ የት ሄደ?» አልኳት

«በመኪናዬ ኒስ ሄደ፡፡ ማታ ይመለሳል»

«መኪና አለሽ 'ንዴ?»



@BOOKALEM

«አዎን፣ ስፖርት ጃጉዋር:: ካራት ቀን በፊት ከኢንግላንድ መጣልኝ»

«ጃጉዋር?»

«አዎን:: አባቴ ሀብታም ነው:: ከሁለት ወር በፊት ነበር መኪናው ይደርስሻል ያለኝ፣ ገና ዛሬ ደረሰኝ:: ስለዘገየብኝ ተበሳጭቼ ነበር፣ አሁን ግን እንኳን ዘገየ እላለሁ»

«ለምን?»

«ያን ጊዜ መጥቶልኝ ቢሆን ኖሮ ከሉ ጋር ከመተዋወቄ በፊት ይሆን ነበር:: እና ሉ የተጠጋኝ ለራሴ ሲል ይሁን ወይስ ለጃጉዋር መኪናዬ ሲል ይሁን ለማወቅ አልችልም ነበር:: እንዲያውም ለመኪናዬ ሲል ነው ማለቴ አይቀርም ነበር እርግጠኛ ነኝ:: አሁን እንደዛ አይነት ሰው እንዳልሆነ አውቃለሁ:: ግን ከመተዋወቃችን በፊት ጃጉዋር ቢኖረኝ ኖሮ እንዴት ላውቅ እችል ነበር? የፈረንሳይ ቆንጆዎች እንደ ልቡ ሊያማርጥ ሲችል ለምን እኔን ይጠጋኛል? 'ለጃጉዋሬ ሲል' ብዬ ማሰቤ አይቀርም ነበር:: እና ይህ ሁሉ ደስታ ይቀርብኝ ነበር»

«ደስታ ይሰጥሻል?»

«እንዲህ አይምሰልህ:: እሱን ከማግኘቴ በፊት ደስታ ምን እንደሆነ አላውቅም ነበር:: አሁን ግን. . .»

«ፍቅር ይዞሻል»

«ያውም ውብ የሆነ፣ የቀስተ ደመና ቀለማት የለበሰ ፍቅር ነዋ!» ወፍራም ክብ ፊቷ ላይ የልጅ መሳይ ፈገግታ ይጫወታል፡ ቆንጆ ነጭ ፀጉሯ ትራሱ ላይ ተበትኗል

«ቅድም ጓደኞቼ ማርሰይ እንሂድ ብለውኝ ነበር» አለች «የራሱ አልጋ ደሞ ከዚህ ይበልጥ ይመቻል. . . ግን እዚህ መምጣት ፈለግኩ:: ሉ ባይኖርም የሉ ቤት ውስጥ ቁጭ ብዬ ወይም የሱ አልጋ ላይ ተጋድሜ፣ በሱ እቃዎች ተከብቤ መቆየት አንድ አይነት ጥሩ ስሜት ይሰጠኛል. . . ፍቅር ይዞህ ያውቃል?»

«አዎን»

«እንግድያው ምን ማለቴ 'ንደሆነ ይገባሀል»

«በደምብ ይገባኛል:: ታድለሻል»



@BOOKALEM

«እኔም ታድያለሁ እላለሁ— ምንም እንኳ ላጭር ጊዜ ብቻ ቢሆን»

ዝም አልኩ:: ፊቷ ላይ ሀዘን እንዳላይባት መሬት መሬቱን አየሁ::

«ቴኒሰንን እንብበህ ታውቃለህ?» አለችኝ

«አዎን»

«ይህንን ጥቅስ ታስታውሳለህ?—

«I hold it true, what'er befall,
I feel it when I sorrow most___»

ተቀበልኳት

"'Tis better to have loved and lost
Than never to have loved at all"

ሳቅ እያለች

«Wow, man!» አለችኝ

ቴኒሰን አቀራረበን

«ቡና ላፍላልህ?» አለችኝ

«አብረሽኝ ትጠጪ 'ንደሆን» አልኳት

ቡናውን ከቀዳችልን በኋላ ተመልሳ አልጋው ላይ ተከመረችና ወሬያችንን ቀጠልን:: ስለሞርሞን ሀይማኖት፣ ስለአሜሪካ፣ ስለኮሙኒዝም ስናወራ ቆይተን፣ ወሬው ወደ ሉልሰገድ ወሰደን:: እንዲህ አለችኝ

«ሉን ከማግኘቴ በፊት ርካሽ የርካሽ መጨረሻ ነበርኩ:: እሱ 'ንኳ ሱርፕሪዝ ፓርቲ አግኝቶኝ፣ ያኔውኑ ወደ አንድ ክፍል አስገብቶ ተኛኝ:: ያን ጊዜ በሉ ቦታ ማንም ወንድ ቢለምነኝ ኖሮ እሺ እል ነበር:: ይተኛኛል፣ ሌላ ጊዜ አንገናኝም፣ በቃ:: ሉ ሲተኛኝ ግን ሌላ አይነት ስሜት ተሰማኝ:: እንዳይተወኝ ፈራሁ:: አለቀስኩ:: ቢሆንም ገና የእውነት ፍቅር አልያዘኝም ነበር:: ይህን 'ምልበት ምክንያት አለኝ:: በሳምንቱ እዚያው ቤት ሌላ ፓርቲ ነበር:: ሉ አልነበረም:: ተካ እዚያ ነበር:: ተዋወቀኝ፣ አስደነሰኝ፣ ሊተኛኝ ፈለገ:: እኔ 'ንኳ አልፈለግኩትም ነበር:: ግን ከሉ ጋር ፍቅር እንዳይዘኝ



@BOOKALEM

ፈርቼ ስለነበረ፣ ዝም ብዬ እንደ ድሮዬ መሆን ይሻለኛል በማለት ተነስን እሺ አልኩት:: በኋላ በጣም ቆጨኝ»

«ለምን ቆጨሽ?»

«ምክንያቱም፣ ከሉ ጋር ስተኛ ንፁህ እንደሆንኩ መሰሉ ተሰምቶኝ ነበር:: ተካ ተኝቶኝ ሲነሳ ግን ቁሸሽ ያልኩ ቆሻሻ እርኩስ እንደሆንኩ ተሰማኝ:: ትቶኝ ሲሄድ እዚያ ጭለማ ውስጥ ብቻዬን ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ»

ሁለታችንም ዝም አልን:: ትንሽ ቆይታ ቀጠለች

«አሁን በቅርቡ ሉን ስለተካ ነገርኩት:: ማንም ወንድ ቢሆን፣ ሸርሙጣ ነሽ ብሎ ይሰድበኝ ወይም ይመታኝ ነበር፣ ወይም እስከነጭራሹኑ ይተወኝ ነበር:: ሉ ግን ምን እንዳለ ልንገርህ? 'ምንም አይደለም:: የበፊት መጥፎ ልማድሽ ባንዳፍታ ሊለቅሽ አይችልም መቸስ:: ደሞ አትደግሚውም:: የምትደግሚው ቢሆን ኖሮ አትነግሪኝም ነበር:: ስለዚህ አልፏል ማለት ነው፣ እንርሳው' አለኝ

«ጥልቅ ፍስህ ስለተሰማኝ አለቀስኩ:: ከዚህ በፊት ማንም አስቦልኝ አያውቅም፣ እየህ:: ሉ ሊያሻሽለኝ ይሞክራል፣ ርካሽነቴን ሊያስተወኝ ከልቡ ይጥራል

«ርካሽነትን ካልተውሽ ራስሽን ለማክበር አትችይም:: ራስሽን ካላከበርሽ ደሞ ሰው ሊያከብርሽ አይችልም:: ሰው ካላከበረሽ ደስታን ልታገኚ አትችይም' ይለኛል:: እንዲያ እያሰበልኝ እንዴት ላልወደው እችላለሁ?» የፊቷ ጡማ ያፈናቸው ንፁህ ሰማያዊ አይኖቿ እምባ አቀረሩ

«እኔ ላለቅስ ነው፣ ወሬ እንለውጥ» አለችኝ

«እሺ:: ስለምን እናውራ?» አልኳት

«ስላንተ:: ፍቅር ከማን ጋር ነው የያዘህ?»

«አንዲት ያገሬ ልጅ አለች»

«ቆንጆ ናት እርግጠኛ ነኝ»

«እንዴት እርግጠኛ ሆንሽ?»



@BOOKALEM

«ሉ ነገረኝ»

«ምን አለሽ?»

«እንደሷ ቆንጆ አይቼ አላውቅም» አለኝ። ደሞ—»

በር ተንኳኳ። ወንድ መኝታ ቤት ሴት ማስገባት ክልክል ስለሆነ ፈራን። እንደገና ተንኳኳ

«ማነው?» አልኩ በፈረንሳይኛ

«እኔ ነኝ። ክፈት» አለኝ

«ሉ ነው!» አለችና ካልጋው ዘላ ተነስታ በሩን ከፈተች

«ከግማሽ መንገድ ተመለስኩ» አለ ሉልሰገድ

«ምነው? መኪናዋ ተበላሸች?» አለችው

«የለም፣ ሳስብበት ጊዜ፣ ለምን ከኔ ጋር አትመጪም?» አላት

«እንድመጣ ትፈልገኛለህ?» አለችው

«አለዚያ ለምን እመለስ ነበር?» አላት

ሲወጡ ከበሩ ጋ መለስ አለችና፣ እሱ እንዳይሰማ

«እኔስ ምን አልኩህ?» አለችኝ። በጣም ደስ ብሏታል

ይሄ ሉልሰገድ ተራ ሰው አይደለም። ከአማንዳ ጋር ባደረገው ግንኙነት የታየኝ ጠባዩ የሀበሻ ጠባይ አይመስልም። . . . እስተያሚ ሴት መተኛቱስ የሀበሻ ደምብ ነው— ሰው ሁሉ እያየው እትፍት መዞር ግን! እምሪው ቢተኛት ያባት ነው— እየስለቸችው እየታከተው እወድሻለሁ ማለቱ ግን! ልጅቱ እስተያሚ በመሆኗ አይወዳትምና፣ ተካ ተኛኋት ብሎ ሲነግረው ከተካ ጋር አለመጣላቱስ እሺ— እሷ ራሷ ተካ ተኝቶኛል ብላ ስትናዘዝ ሰበብ አገኘሁ ብሎ እሷን አለማባረሩ ግን!. . . ይህ ጠባዩ በጭራሽ የሀበሻ አይመስልም። በልጅነቱ ሚሲዮን ነበር የሚማረው። ለዚህ ይሆን?



@BOOKALEM

# ሶስት

## ሲልቪ
## ላይ ላዩን

ተመስገን ክፍል ውስጥ ቁጭ ብዬ ስሰራ አንዳንዴ ወቢቱ ሲልቪ ትመጣና «Salut, Castro noire» ትለኛለች:: («ሰላም፣ ጥቁር ካስትሮ») (ዒም ስላለኝ ነው::)

«Que la paix soit avec toi, O, Scheherazade Blanche,» እላታለሁ («ሰላም ላንቺ ይሁን፣ ፃእዳይቱ ሻህራዝድ ሆይ»)

ትስቃለች:: በምስራቃውያን አነጋገር እንቀጥላለን:: ቀልድ ነው:: ከሲልቪ ጋር ሁልጊዜ ቀልድ ነው:: እውነተኛ ፈረንሳዊት ናት፡ ስለምንም ነገር ቢሆን «Moi, je m'en fous!» ነው 'ምትለው («እኔ ስለዚህ ነገር ደንታ የለኝም») ታድያ ደስ ትላለች:: ስሬ አፏ ሳሙኝ ሳሙኝ ይላል:: አብረሀት ስትሆን ሳቅ ቀልድ ታበዛለህ፣

«ዡማንፉቲዝሚ» ይጋባብሀል፡ ስለምንም ነገር ደንታ አይኖርሀም

አንድ ቀን ግን

«ምንድነው ሁልጊዜ ስትፅፍ 'ማገኝህ?» አለችና ደብተሬን አየችው:: «የምን ፅህፈት ነው ይሄ? ያገራችሁ ነው?» አለችኝ

«አዎን»

«ምኑም አይገባም»

«ቀላል ነው:: ሁለት መቶ አርባ የሚሆኑ ፊደላት አሉት»

«Quel horreur! (ኧረ የጉድ ያለህ!) እንግዲያው እታስረዳኝ ይቅርብኝ. . . ምንድነው 'ምትፅፈው?»



@BOOKALEM

«ምንም አይደለም—»

«ልብወለድ ነው?»

«ብጤ ነው»

«እንዴት ማለት— ብጤ?»

«እንዴት ልበልሽ? ልብወለድ ነው፣ ግን ፈጥሬው አይደለም፣ ያየሁትን የሰማሁትን ነገር ሰብስቤ ቅርጹን እለዋውጣለሁ 'ንጂ፣ ቀንበጢ እንዲጥም»

«ቆይ—ቆይ:: አሁን መፃፍ አለብህ ወይስ ለጊዜው ልትተወው ትችላለህ»

«ልተወው እችላለሁ»

«እንግዲያው ከዚህ እንሂድና ቡና ልጋብዝህ:: እና ስለድርሰት እናውራ:: ይስማማሀል?»

«ብደምብ ነዋ! ቆንጆ ሴት ቡና ስትጋብዘኝ ሁልጊዜ ይስማማኛል»

«Malin Castro noir, va!» («ሂድ ወድያ! ሎሌ ጥቁር ካስትሮ!»)

Deux Chevaux መኪናዋ ውስጥ ከገባን በኋላ

«ኤክስ ውስጥ የምወደው ካፌ የለኝም:: ማርሰይ እንሂድ?» አለችኝ

እየቀለድን እየሳቅን ደጋግማ «Moi, tu sais, je m'en fous!» እያለች፣ በሆዴ ውበቷን እያደነቅኩ፣ ማርሰይ ደረስን:: የንግድ ሳይሆን የግል የመደሰቻ ልዩ ልዩ አይነት ጀልባዎች ከተደረደሩበት ወደብ አጠገብ አንድ ካፌ ገብተን ቢራ ካዘዝን በኋላ፣ ጉልህ ሰማያዊ አይኖቿ በፈገግታ እያዩኝ

«ንገረኛ ስለምትፅፈው» አለችኝ

«ምን ልንገርሽ?»

«ስለሰዎቹ፣ ስለጊዜው፣ ስለግንኙነታቸው፣ ማን ማንን እንደ ሚወድ፣ ማንስ ማንን እንደሚጠላ፣ መፅሀፍህ እንዴት እንደ ሚጀመር፣ አሁን የት እንደደረሰ፣ በኋላ እንዴት እንደሚያልቅ፣ ምን ምን ነገር እንደሚያስቸግርህ፣ መፅሀፍህ ምን እንዲል እንደ



@BOOKALEM

ምትፈልገው፣ ሁሉን ንገረኝ»

ቆንጆ ስለሆነች ይሁን፣ አጠያየቁን ስላወቀችበት ይሁን ወይስ ሌላ ያልተገለፀልኝ ምክንያት ይኑር እንጃ፣ ስለመፅሀፌ ሁሉን ነገርኳት:: ለማንም ነግሬ የማላውቀውን ለሷ አጫወትኳት:: ችግሩን፣ ደስታውን፣ ብስጭቱን፣ የድል አድራጊነት ስሜቱን፣ ምንም ሳልደብቅ አዋየኋት:: ፈረንሳይኛው ሲያስቸግረኝ ልክ ልናገረው የፈለግኩትን ቃላት ታቀብለኛለች፣ ምክንያቱም ሀሳቤ ቃላቱን ቀድሞ ደርሷት ይቆያል:: አንዳንድ ቦታ አንድ ሀሳብ ተናግሬ ጨርሼ ሌላ ሀሳብ አልመጣልህ ሲለኝ አንድ ጥያቄ ትጠይቀኛለች፣ እሱን ጥያቄ ስመልስ፣ ሌላ ሀሳብ ይመጣልኝና እቀጥላለሁ:: እንደዚህ ብዙ ካወራሁ በኋላ

«ይገርምሻል፣ ይህን ለማንም ነግሬ አላውቅም» አልኳት

«J'en suis flattée» አለችኝ («ክብር ይሰማኛል»)

«እኔ እውነቴን ነው»

«እኔም እውነቴን ነው»

«አሁን ተራሽን አውሪልኝ»

«ቆይ» አለችና ከያዘችው የመፃህፍት ቦርሳ አንድ አስር የሚሆኑ ባንድ በኩል ብቻ በታይፕ የተፃፈባቸው ነጠላ ወረቀቶች ሰጠችኝ:: አንብበው አለችኝ:: አነበብኩት:: አጭር ልብ ወለድ ታሪክ ነው:: ስጨርስ

«ምን ይመስልሀል?» አለችኝ

«አንቺ ነሽ የፃፍሽው?» አልኳት

«አዎን» አለችኝ

«አዝናለሁ:: ጥሩ ታሪክ አይደለም»

«ምንድነው የጎደለው?»

«እርግጠኛ አይደለሁም:: አየሽ፣ አንድ ሰው የሚወዳትን ሴት ሊገድል ይችል ይሆናል:: ግን ባስር ገፅ ውስጥ ይህን መናገር የሚቻል አይመስለኝም:: ቢያንስ ቢያንስ ሁለት መቶ ገፅ ያስፈልገዋል»

«ይህንንም አንብብ እስቲ» ብላ ሌላ አስራ ሶስት ገፅ ሰጠችኝ::



@BOOKALEM

አስነብቤት፡፡ ጥሩም ታሪክ ነበር፡፡

«ይህንንም አንቺ ነሽ የፃፍሽው?»

«አዎን»

«ታሪክ ይሉሻል ይሄ ነው! ይህን ጊ ደ ሞፓሳን ራሱ ነው የፃፈው ቢሉኝ አምናለሁ» አልኳት

ንፁህ ሰማያዊ አይኖቿ ልዩ አስተያየት ሰጡኝ፣ እንደማቀፍ ያለ አስተያየት፣ ሙቀት ያለው አስተያየት

«Merci» አለችኝ

«Je t'en prie, (እረ ምንም አይደለም) ይህን የመሰለ ለመፃፍ ስትችዪ፣ እንዴት አርገሽ የቅድሙን ፃፍሽው?» አልኳት

መሳቅ ጀመረች (ጥርሶቿ ትክክል ሆነው ነጫጭ ናቸው፡፡ ነጭ የፈረንጅ ጥርስ ብዙ አይታይም) «እኔ 'ንጃ» አለችኝ «በምፅፍበት ሰአት ሁሉም እኩል ጥሩ ሆኖ ይሰማኛል፡፡ ካንድ ሁለት ወር በኋላ ነው እውነተኛው ዋጋው የሚታየኝ»

«ይሄ መጥፎው መቼ ነው የተፃፈው?»

«ካንድ አመት ተኩል በፊት»

«እንግዲያው መጥፎ መሆኑ ድሮ ገብቶሻል፡፡ ለምን አስነበብሽኝ?»

«ላውቅህ ስለፈለግኩ፡፡ ማንም ሰው ቢሆን፣ እንደምፅፍ ካወቀ ወይም እንዲያውቅ ከፈለግኩ፣ መጀመሪያ መጥፎ ታሪኬን አስነብበዋለሁ፡፡ እንብቦት ጥሩ ነው ካለ በቃው፡፡ ሁለተኛ እኔ የፃፍኩትን አያነብም፡፡ እስካሁን ለአንድ ስምንት ሰው አስነብቤያለሁ፡፡ አንተና አንድ የፓሪስ ጓደኛዬ ብቻ ናችሁ መጥፎውን መጥፎ ያላችሁት፡፡ ስለዚህ ሁለታችሁ ብቻ ናችሁ ጥሩውን ያነበባችሁ»

«ሌላ የፃፍሽው አለ?»

«ሃያ ስድስት አለኝ፡፡ አስሩ እንዱ ጥሩ ይመስሉኛል፡፡ ሰባቱ በጣም መጥፎ ነው፡፡ አምስቱ ግን ጥሩም አይደል፣ መጥፎም አይደሉ– እንደኔ አስተያየት፡፡ ስለዚህ አንተ እነዚህን አምስት አንብበህ ምን እንደሚመስልህ ብትነግረኝ፣ ተስፋ የሌለውን አጥለውና ተስፋ ያለውን እየመከርከኝ አሻሽለዋለሁ»

«ክብር ይሰማኛል፣ ግን ልመክርሽ መቻሌን እንጃ»

«ትችላለህ። ታግዘኛለህ?»

«ከቻልኩማ በደስታ! አሁን ስለራስሽ ንገሪኝ። ቀድሞ እኔ እንደነገርኩሽ»

ነገረችኝ። የምንሰፍበት ቋንቋ ተለያየ 'ንጂ ሙከራችን፣ ችግራችን፣ አስተያየታችን በጣም ይመሳሰላል። ስንወያይ መሸ።

«እማውቃት ጥሩ ርካሽ ምግብ ቤት አለች» ብላ ሳን ሻርል ባቡር ጣቢያ አጠገብ ወሰዳ እራት ጋበዘችኝ። በፈረንሳይ ደምብ ከምግቡ ጋር አንድ ጠርሙስ ወይን ጠጣን። ሲኒማ ላስገባሽ አልኳት። ሁለታችንም እንደዚህ ልንጨዋወት የምንችልበት ጊዜ መቼ ተመልሶ እንደሚመጣ አይታወቅም አለችኝ። እውነትሽን ነው አልኳት

ወደ ወደቡ ተመልሰን በእግር እየተዘዋወርን ወሬያችንን ቀጠልን። በተርታ የቆሙ ጀልባዎች የሚወዛወዙበት ውሀ ውስጥ የማርሰይ መብራት ይጫወታል። የባህር ሽታ ይዞ ከባህር በኩል የሚመጣው ነፋስ ቅዝቅዝ ያለ ሆኖ ይለሰልሳል። እንደኛው እያወሩ የሚዘዋወሩ ሰዎች አሉ፤ አብዛኛዎቹ ተቃቅፈዋል። መንሸራሸር ሲበቃን አንድ ካፌ ገብተን ቁጭ ብለን ቢራ አዘዝን

«ስለ ኑሮ ምን ታስባለህ?» አለችኝ

«ኑሮ በጣም አጭርና በጣም ጣፋጭ ናት እላለሁ። አንቺስ ምን ይመስልሻል?»

«እኔም በጣም አጭር ናት እላለሁ። ስለዚህ ለመኖር መሽቀዳደም፣ መጣደፍ አለብን»

«በተቻለን መጠን ኑሮአችን ውስጥ ሀሴትን መጠቅጠቅ አለብን»

«ሀሴት» ስል bonheur የሚለውን ቃል ነበር የተጠቀምኩት

«Il n'y a pas de bonheur, tu sais» አለችኝ «Il n'y a que du plaisir.» («ሀሴት የሚሉት የለም'ኮ። የስሜት ደስታ ብቻ ነው ያለው»)

«እና አንቺ ምን አይነት የስሜት ደስታ ትወጂያለሽ?»

ሳቅ እያለች «ከምግባባው ሰው ጋር እንደዚህ ማውራት፣



@BOOKALEM

ከማምነው ሰው ጋር ማታ ባህር ዳር መንሸርሸር»

«ሌላስ?»

«ውብ ሙዚቃ መስማት፣ ጥሩ ትያትር ማየት፣ ጥሩ መፅሀፍ ማንበብ፣ እስክጠግብ ከበላሁ በኋላ ወይን እየጠጣሁ ማውራት. . .»

«ሌላስ?»

«ልንገርህ?»

«ንገሪኝ»

«አትደነግጥም?»

«ሞክሪኝ»

አመነታች:: «ለሰው ተናግሬው አላውቅማ»

እየሳቅኩ «እኔና አንቺ'ኮ ከሰው በላይ ነን:: ደራሲያን ነን፣ ፈጣሪዎች ነን» አልኳት

ሳቀች:: ሳቋ ጉሮሮዋ ውስጥ ይሰማል፣ በጣም ደስ ይላል:: ሁለመናዋ ደስ ይላል

«እንግድያው ልንገርህ»

«ንገሪኝ»

«J'aime faire l'amour,» («ከወንድ ጋር መተኛት እወዳለሁ»)

አየሁዋት:: እስካሁን የተመሰገን «ሚስት» በመሆኗ ስለሷ እንዲገለፅልኝ ያልፈቀድኩለት ስሜት አሁን የአእምሮዬን በር በርግዶ ገባ:: ሲልቪን በጣም ተመኘኋት!

«እ! ላ-ላ! እንደሱ አትየኝ!» አለችኝ:: አፍራለች፣ ጉንጮቿ ደም መልበስ ጀምረዋል፣ አይኖቿ ይርገበገባሉ:: የባሰውን አማረችኝ::

«ምናለበት ባይሽ?» አልኳት

«Tu me fais rougir» («ፊቴ እንዲቀላ ታደርገኛለህ»)

«በጣም ታምሪኛለሽ ፊትሽ ሲቀላ» አልኩና ጉንጮቿን በሁለት እጄ ይዤ አፏ ላይ ሳምኳት:: አፏ ይሞቃል::



@BOOKALEM

«እንሂድ ከዚህ?» አልኩዋት። Deux Chevaux መኪናዋ ውስጥ እንደገባን

«እኔም ከሴት ጋር መተኛት በጣም በጣም እወዳለሁ» አልኳት

«አውቃለሁ» አለችኝ

«እንዴት ታውቂያለሽ?»

«ምስጢር ነው። Secrèt professionnel» («የባለሞያተኞች ምስጢር»)

«Mais nous sommes de la meme profession» («ታዲያ የሁሊታችንም ሞያ አንድ ነው'ኮ»)

«እውነትክን ነው»

«ንገሪኝ። ሴት መውደዴን እንዴት ታውቂያለሽ?»

«እንደኛ አስተያየትህ። አይንህ ቆንጆ ሴት ላይ ሲያርፍ ሴትዮዋን በሙቀት ያጎናፅፋታል። ደሞ ቆንጆ ሴት አይንህን ጣል ሳታረግባት አታልፍም። ሁለተኛ ድምፅህ። ከወንዶች ጋር ስትነጋገር ሰምቼሀለሁ። ከሴት ጋር ስትነጋገር ግን ድምፅህ ልስልስ ይላል፣ ሙቀት ይሞላዋል። እንዴት ያለች ሴት ነው 'ምትመርጠው?»

«እንዳንቺ ያለች»

«የምሬን ነው 'ምጠይቅህ»

«እኔም የምሬን ነው 'ምመልስልሽ»

«እንዴት ነው እንደኔ ያለች ሴት ማለት?»

«አእምሮዋን ላከብረው ስችል፣ ጠባይዋን ልወደው ስችል፣ ገላዋን ልመኘው ስችል፣ በዚህ በሶስት በኩል በቂ ሆና ሳገኛት፣ ሴትዮዋ እንዳንቺ ያለች ናት ማለት ነው» ብዬ እንደገና ሳምኳት። መሳሙን በጣም ትችልበታለች፣ ሰፊ አፏ ይመቻል

«ተመስገን ጓደኛህ ነው?» አለችኝ

«ጓደኛ የለኝም» አልኳት። ሳመችኝ። ሙቅ እርጥብ አሳሳም ሳመችኝ

«ስለተመስገን እንዴት እናድርግ?» አለችኝ

«እንግደለው»

@BOOKALEM

እየሳቀች «እውነቴን ነው!»

«እንቺ እንደፈለግሽ:: ብትፈልጊ ተይውና እኔጋ ነይ:: ብትፈልጊ ሳትነግሪው በድብቅ እንገናኝ:: ብትፈልጊም የሚገባው ከመሰለሽ፣ ነገሩን አስረጂው:: እንደመሰለሽ አርጊ»

«ሳንተ እንዴት ይሻልሀል?»

«ለኔ ሁለም ያው ነው:: እናንተ ፈረንሳዮች እንደምትሉት 'Je m'en fous!' ብቻ አንቺን ላግኝሽ»

«አትቀናም?»

«አልቀናም:: ምን ያስቀናኛል? በማገኝሽ ጊዜ የተቻለሽን ያህል የስሜት ደስታ ስጪኝ እንጂ፣ ከኔ ጋር ባልሆንሽበት ጊዜ ምንስ ብታረጊ ሳንቺ ከተስማማሽ ምን ይጎዳኛል?»

«እውነትክን ነው?»

«እምና!»

«Mon Dieux! እንዴት ያለኸው ሰውዬ ነህ!» (ወይ አንተ እምላክ!)

«ምነው?»

መልሷ መሳም ነበር

«ወደ ኤክስ እንመለስ?» አለችኝ

ምናልባት አሜሪካኗ ሆቴሌ ትጠብቀኝ ይሆናል በማለት

«ለምን እዚህ አናድርም?» አልኳት

«ነገ በጧቱ ክፍል አለብኝ»

«ቅሪ ከክፍል»

«ትምህርቱስ?»

«ስሚኝ:: ዛሬ ከኔ ጋር ነው 'ምታድሪው:: ሌሊቱን ችዬ እንቅልፍ አላስወስድሽም:: ስለዚህ፣ ነገ ጧት ብትገቢም እንቅልፍ አጥቶ ማደሩና ድካሙ በደምብ አያስሩሽም:: ስለዚህ አንደኛውን ብትቀሪ አይሻልም? ቅሪ እባክሽን! ደሞ ጧት ልለይሽ አልችልም» ብዬ እቅፍ አድርጌ ሳምኳት:: እሺ አለች:: ሳን ሻርል አጠገብ አንድ ትንሽ ሆቴል ውስጥ አንድ ክፍል ተከራየን::



@BOOKALEM

እጅ ለእጅ ተያይዘን ሮቁን ወጣን:: የክፍላችንን በር ከፈትኩላት:: ገባን:: መብራቱን አበራችው:: አነስ ያለ ንፁህ ክፍል መሀል አልጋ ልብስ የተዘረጋበት ሰፊ አልጋ ይጠብቀናል:: ሁለታችንም ለአልጋው ቸኩለናል፣ ሁለታችንም አልጋውን ፈርተነዋል

በሩ አጠገብ እንደቆምን ወደኔ ሳብኳት፣ ተጠጋች:: ቀጭን ወገቧን እቅፌ፣ ደረቷ እየገፋኝ፣ ጭኖቿ እየተሻሹኝ አንገቷን ጉንጯን ስስም፣ ሰፊ አፏ ተከፍቶ ከጎን ታየኝ፣ አይኔ አጠገብ ከንፈሮቿ በጣም ወፍረው ቀይ እርጥብ ሆነው ታዩኝ፣ እየተንገበገብኩ ጎረስኩዋቸው:: እሷም ጎረሰችኝ በሰፊ አፏ፣ በእርጥብ ከንፈሮቿ፣ በፈጣን ምላሷ፣ በትኩስ ትንፋሿ፣ በሚያዳልጡ ጥርሶቿ ታኘከኝ ታላምጠኝ ጀመር

እፎቻችን እንደተቆላለፉ ልብሶቻችንን በሙሉ አወለቅኳቸው፣ በለስላሳው ሌሊት ራቁት ለራቁት ተቃቅፈን ቆመን መተሻሸት መሳሳሙን ቀጠልን:: ጡቶቿ ደረቴን ሲገፉ ልዩ ስሜት ተሰማኝ፣ ትንሽ ራቅ አደረግኳትና አየኋቸው፣ ኮረዳነት የገተራቸው የውበት ክምሮች የምኞት ሀውልቶች ይመስላሉ:: እጆቿን ዘርግታ ራሴን ወደ ደረቷ ሳበች፣ አንዱን አበባ ጡት አፌ ውስጥ ከተተችው፣ ራሴን አቀፈችኝ:: ሽቶና ኮረዳነት የተደባለቁበትን ጠረኗን ወደ ውስጥ ተነፈስኩት

በኋላ ቀስ አርጋ ገፋችኝ፣ ለብቻዋ ቆመች:: እየተያየን ብዙ ጊዜ ቆየን:: ሳኝካቸው የነበረ ጡቶቿ ቆመዋል፣ ከረዥም ቀጭን ሽንጧ በታች ሰፊ ዳሌዋ ወደ ረዣዥም ጭኖቿ፣ በልዩ ጥንቃቄ ወደ ተቀረፁ እግሮቿ ይወርዳል::

«እንዴት ቆንጆ ነሽ!» አልኳት

ፈገግታ አልሰጠችኝም:: ዙሪያችን የተንጠባጠቡትን ልብሶች ሰበሰበችና ወስዳ ወምበር ላይ ከመረቻቸው:: ጎንበስ ስትል፣ ቀና ስትል፣ ስትራመድ፣ የገላዋ ቅርፅ የዳሌዋ መወዛወዝ አቅበጠበጠኝ:: ቶሎ ሄጄ አቀፍኳት፣ አልጋው ላይ አጋደምኳት:: እጇን ወደ ራስጌ ዘርግታ መብራቱን አጠፋች:: በጨለማው እጆቿንም፣ እግሮቿንም፣ ከንፈሮቿንም ከፈተችልኝ፣ እቅፏ ውስጥ አፏ ውስጥ ሴትነቷ ውስጥ አስገባችኝ

የጉርምስና ስሜት ውስጥ እንደ ሀረግ ተገማምደን፣ በምኞት ትኩሳት እየተቀቀልን በስጋ ርጥበት ተጠበስን



@BOOKALEM

በተቃቀቁ ገላዎቻችን መቅደስ ውስጥ፣ ዘለአለማዊውን ጭለማ ለተጎናፀፈ፣ ጥንታዊ ለሆነ፣ ዘወትር አዲስ ለሆነ፣ ቅዱስ ለሆነ ህይወት በጠረናችን ከርቤ፣ በወጣት ልባችን ከበሮ፣ በማቃሰታችን መዝሙር ምስጋናችንን አቀረብንለት

በኋላ፣ እንሶላው ውስጥ ገባንና ክንዴን አንተርሻት

«አውሪልኝ» አልኳት

«ምን ላውራልህ?»

«ያስኘሽን»

«ተደስተክ?»

«እንዲህ ተደስቼ አላውቅም»

«እኔም:: አልጋ ውስጥ አርቲስት ነህ:: እንዳንተ ማንም አስደስቶኝ አያውቅም»

«ብጭራሽ? እውነት ተናገሪ»

«አንድ ብቻ ነበር:: እሱም ያንተን ግማሽ ያህል አይችልበትም»

«ታድያ እንዴት አስደሰተሽ?»

«የመጀመሪያዬ ነበር:: ፍቅር ይዞኝ ነበር»

«እሱስ?»

«እሱም በጣም ይወደኝ ነበር:: ግን ፍቅር አልያዘውም ነበር:: ፍቅር ሊይዘው አይችልም:: ፍቅሩን በሙሉ ለነፃነት ሰጥቷል:: አንድሬ ማልሮን አንብበሀል? La Condition Humaine የሚባለው ልቦለዱ ውስጥ ያሉትን ጀግኖች ተስታውሳቸዋለህ?»

«ቻይና ሄደው ለሬቮሉሽኑ እውቀታቸውንና ህይወታቸውንም ጭምር ይሰጣሉ::»

«አዎን! እንደነሱ አይነት ነው እሱም:: ፖል ይባላል:: መልኩ ይህን ያህልም አይደለም:: ደቃቃ ብጤ ነው:: ግን የአስር ሰው ድፍረት ተሰጥቶታል:: አይኑ ውስጥ ደሞ 'ነፃነት' ባለ ቁጥር ቦግ የሚል ነበልባል አለ:: ያባቱን ሀብት ወርሶ ነበር:: ግን እሱን ለታናሽ

እህቱ ትቶላት ሄደ»

«ወዴት ሄደ?»

«ወደ ኩባ። እንካስትሮን ለማገዝ»

«አሁንም እዚያው ነው?»

«አይ! እንካስትሮ አሸንፈው የለም'ንዴ?»

«እንግዲያው የት ነው?»

«ቬየትናም። ቬየትኮንጎቹን ያግዛል»

«ኮሙኒስት ነው?»

«አይደለም። የነፃነት ነብይ ነው። የነፃነት አርበኛ ነው። ያን ጊዜ በ56 ዓ.ም. ሀንጋሪ ውስጥ ብጥብጥ አልተነሳም? ለሀንጋርያኖች ነፃነት ለመዋጋት ቀዩን ጦር ሰራዊት (የሶቭዬት ህብረት ጦር) ከሀንጋሪ ለማስወጣት እዋጋለሁ ብሎ ሀንጋሪ ሊሄድ ተነስቶ ነበር። በስንት መከራ አባቱ አስቀሩት። ያን ጊዜ ሀያ አንድ አመቱ ነበር።»

«እንዴት ያለ ሰው ቢሆን ነው?» አልኳት

«የአርነት ሰው ነው። የጭቆናን ቀምበር በያለበት እየዞርኩ መስበር አለብኝ ይላል»

«ይፅፍልሻል?»

«በስድስት በሰባት ወር አንዴ ይፅፍልኛል። አሁን በሱ እናውራ 'ባክህን። አለዚያ ማዘን እጀምራለሁ። ዛሬ ማታ በጭራሽ ማዘን አልፈልግም»

ወሬውን ተውነው፣ ግን ሊሊቱን አልተኛንም። የወጣትነት ትኩሳት እያቃጠለን፣ በህይወት ርጥበት ውስጥ ተነክረን አደርን

ሊነጋጋ አቅራቢያ እንቅልፍ ወሰደን። እስከማታ አልነቃንም

ከእንቅልፌ ስነቃ ሰውነቴ ታድሷል፣ አስተያየቴ ተለውጧል። ሲልቪ አጠገቤ በመሆኗ ትልቅ ፍስሀ ተሰማኝ። እቅፍ እያደረግኳት

«ስለተመስገን ጉዳይ እንዴት ልታረጊ ነው?» አልኳት



@BOOKALEM

«እንዴት ላድርግ?» አለች

«ተይው!»

«ምን?»

«ለብቻዬ ነው 'ምፈልግሽ»

«ትላንት ስናወራ ከኔ ጋር ባልሆንሽበት ጊዜ ምንም ብትሰሪ የራስሽ ጉዳይ ነው አላልከኝም ነበር?»

«ትላንት ፍቅር አልያዘኝም ነበራ!»

በሀይል እቅፍ አደረገችኝ

* * *

ካንድ ስምንት ቀን በኋላ፣ ማታ ተመስገን ክፍል ቁጭ ብዬ ስሰራ፣ ተመስገን መጣና አልጋው ላይ ዘጭ ብሎ ተጋደመ:: እፎይ! ብሎ ተነፈሰ

«ሲኒማ የገባችሁ መስሎኝ» አልኩት

«ሌሎቹ ገቡ፣ እኔ ግን ተውኩት»

«ለምን ተውከው?» አልኩት:: ድምፄ «አንተ ተንኮለኛ!» እንደሚል አይነት ነበር

«ደስ አላለኝማ!» አለኝ:: ትንንሽ አይኖቹ ሊደበቁ ጀምረዋል፣ ግን ጥርሶቹ ገና መታየት አልጀመሩም

«ውሸታም! ቀጠሮ ቢኖርህ ነው 'ንጂ» አልኩት

«ከማን ጋር?»

«እኔ አውቃለሁ 'ንዴ ያንተን ተንኮል? ወይ ካንዷ ብሎንድ (ፀጉሯ ብጫ ወይም ነጭ ብጤ) ጋር፣ ወይ ከሲልቪ ጋር»

«ሲልቪ!? አላወቅክምና!»

«ምን?»

«ተርቶ!»

«ምንዋ?»

«ምን እባክህ የሴት ነገር» አለ «እግር ጤና ብዬ እንደ

ሁልጊዜዎችን ወዲህ አመጣሁዋት:: ከስእት በኋላ ነበር:: የከስአት በኋላው እንዴት እንደሚጣፍጥ ታውቅ የለ? ልብሷን አወላለቀችና አልጋው ውስጥ ገባች:: እየተንገበገብኩ ተከትያት ልገባ ስል፣ ከትራሱ ላይ እንዲት ፀጉር አንስታ አቀበለችኝ:: ረዥም የፈረንጅ ፀጉር ነው፣ ግን ጥቁር አይደለም፣ ቡና አይነት ነው»

«ይሄ የኔ ፀጉር እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ» አለችኝ

«ዝም አልኩ:: አልገባኝም አየህ

«ተናገር 'ንጂ» አለችኝ:: እግዜር ያሳይህ:: በመጀመሪያ አልጋው ውስጥ ልገባ ጎምበስ እንዳልኩ አሁንም አለሁ:: ይታይሀል? ራቁቴን አልጋው ላይ ባራት እግሬ ቆሜ? እንደሚድህ ልጅ:: ልብሷን ስታወልቅ እያየሁና የሚጠብቀኝን ደስታ እያሰብኩ ግትር አድርጎ ቅንዝር ወጥሮኛል::»

የተመስገን አይኖች ጨርሰው ጠፉ፣ ጥርሶቹ ተገለጡ፣ ይስቅ ጀመር:: ከት ብሎ እየሳቀ፣ ሳቅ በሚቆራርጠው ንግግር

«ገና አሁን ታየኝ – ሀ! ሀ! ሀ! – እንዴት እንዴት – ሀ! ሀ! ሀ! – እንዴት እንደነበርኩ – ሁ! ሁ! ሁ! እንዲህ ነበርኩ» አለና በጀርባው ከተጋደመበት ተነስቶ ዞሮ በጉልበቱና በእጁ ተንበረከከ:: ከስሩ ትራሱን አስተካከለና፣ ሌባ ጣቱን እያነጣጠረበት

«እኔ 'ንዲህ ነኝ፣ ሂሂ!!» ትራሱን «እቺ ሲልቪ ናት:: ያቀበለችኝን ፀጉር ባንድ እጄ እንደዚህ ይዣለሁ:: እንዳትበጠስ ወይም ወድቃ እንዳትጠፋ እየተጠንቀቅኩ፣ ያቺን ነጃሳ ፀጉር እንዲህ ይዣለሁ:: ቁላዬ ደሞ እዚህ ጋ ቆሞ ሲልቪን ቁልቁል ያያታል:: አይ የኔ ቁላ! ቂል ነው'ኮ:: ያንተም ቂል ነው?» እንደገና ሳቁ አሸነፈው:: አልጋው ላይ ተንከባለለ:: ሳቁ ሲያልፍለት

«በኋላስ?» አልኩት

«በኋላማ ምን ልበልህ ልጄ? ቃል ሳትናገር ተነስታ ልብሷን መልሳ ለበሰች:: ረጋ ባለ ድምፅ 'የኔና ያንተ ነገር በዚሁ አለቀ!' ብላኝ ልትወጣ ስትል፣ እኔ እዚች ጋ ራቁቴን እንደቆምኩ

«ምን ነካሽ?» አልኳት:: ሲያቀብጠኝ'ኮ ነው:: እስቲ ዝም



@BOOKALEM

ብላትስ?

«ዘወር አለችና፣ እሱ ጠረጴዛ ላይ ያለውን መጽሀፍትና ደብተር በእጇ እንዴ ገፍታ መሬት ላይ አዝረከረከችው:: እና ጠረጴዛውን በተጨበጠ እጇ ደጋግማ እየመታች

«እኔ – የእስላም – ሀሪም – ሴት – አይደለሁም!» ብላኝ ስታበቃ፣ ወጥታ በሩን በሀይል ጓ! አርጋው ሄደች:: ልብሴን ለለብስ ካናቴራዬን ሳነሳ በሩ ብርግድ ብሎ ተከፈተ:: ማን ገባ መሰለህ?» አለኝ

«ማን?» አልኩት

«ሲልቪ ራሷ ነቻ! የሴት ነገር! ከመቼው ሀሳቧን ለወጠች?! እያልኩ ልገረም ስጀምር፣ አጠገቤ መጣች:: አቅፋ ልትስመኝ እንደሆነ ገባኝ:: ትንሽ ልኮራባት አሰብኩ:: ታድያ እሷ ምን አረገች መሰለህ? እወቅ 'ስቲ::»

«በጥፊ መታችህ?»

«በጭራሽ!»

«አቅፋ ሳመችህ?»

«ትቀልዳለህ?»

«እንግዲያው ምን አረገች?» አልኩት

«ጫማዋን አረገች»

«ምን?»

«በንዴት ጫማዋን ረስታው ሄዳ ነበር:: ተመልሳ አረገችውና ወጣች:: እኔ ራቁቴን ቆሜ ቀረሁ:: ቁላዬ እስካሁን ተኝቷል:: ከዚያ በኋላ አናግራኝ አታውቅም»

«ጥፋቱ ያንተ ነው» አልኩት

«እንዴት?» አለኝ

«ያመጣሀቸው ሴቶች ሊሄዱ ሲሉ 'ፀጉሮችሽን ሁሉ ይዘሻል? ቁጠሪ እስቲ' ለምን አትላቸውም?» አልኩት

«መቼ ሴት አመጣሁና?» አለኝ



@BOOKALEM

«እ–ሀ? ቡናማው ፀጉርሳ?»

«ከየት እንደመጣ 'ንጃለት። ምናልባት ቤት የምትጠብቅ አልጋ የምታነጥፈው አሮጊት ያን እለት ታማ ዋሮ፣ በሷ ምትክ ባለቡናማ ፀጉር ሴት አልጋዬን አንጥፋልኝ ይሆናል»

«ምስኪን ተመስገን!» አልኩት

«ምስኪን ትላለህ ምስኪን። ይኸው እስከዛሬ ፆም ላይ እገኛለሁ»

«ዛሬ ማታ ግን ለመግደፍ ያስብክ ትመስላለህ»

«ነበር እባክህን። ፀጉሯን እንደ ወንድ ነው 'ምትቆርጠው ቢሆንም ምንም አትል። ብቻ –»

«ብቻ ምን?»

«የት እንደምወስዳት ጨንቆኛል» (ሲመሽ ፈረንሳዮች concierge የሚሉት ዘበኛ ይመጣና፣ ወደመኝታ ቤቶቹ የሚያስገባው በር አጠገብ እንዲት ቢሮ አለችው፣ እዚያች ቁጭ ብሎ ወጪ ገቢውን ሁሉ ይመለከታል። ወንዶች መኝታ ቤት ሴት ማስገባት ክልክል ነው።)

«የኔ ሆቴል አለልህ አይደለም 'ንዴ?» አልኩት

«አትጠቀምበትም?»

«እዚሁ ልተኛ እችላለሁ»

«እሱማ ጥሩ ነበር»

«ብቻ እንዳታስጮሀት አደራ። ካስጮህካትም ፎጣ አጉርሳት» ብዬ የሆቴሌን ቁልፍ ሰጠሁት

ተመስገን ወደ ቀጠሮው ከሄደ በኋላ ተመልሼ ልሰራ አልቻልኩም። ሲልቪ ለኔ ስትል እንደተወችው ገባኝ። ይህ ሀሳብ በጠበጠኝ። ተነስቼ አሜሪካዊቷ ቤት ሄድኩ። ጉዳዬን አስረዳኋት፣ ከዚህ በፊት አገሬ እጮኛ አለችኝ ብያት ነበር። አሁን፣ እጮኛዬ ካንቺ ጋር ያለኝን ግንኙነት አወቀች። ማን እንደነገራት እንጃ፤ ወረቀት ፃፈችልኝ። በአንድ ሳምንት ውስጥ አሜሪካንህን ትተሀታል የሚል ወሬ ካልደረሰኝ ሌላ እጮኛ ፈልግ አለችኝ፣ ብዬ ነገርኳት።

«I understand የዚህ መጥፎ ዜና ምክንያት በመሆኔ በጣም አዝናለሁ» አለችኝ:: ያቀድኩት ይህን ነገሬያት ደህና አደሬ ብያት ሲልቪን ፍለጋ ለመሄድ ነበር:: ግን ልጅቱ ጥቁር ስስ የሌሊት ልብስ ለብሳ ስትራመድ በጣም ታስጎመጃለች፣ ገላዋን ታጥባ ቆዳዋን በታልከም ዱቄት አሻሽታው፣ ሽታው ይማርካል:: ከሷ ጋር አደርኩ

«ራሴን በጣም ታዘብኩት:: በጣም ፀፀት ተሰማኝ፣ ሲልቪን የበደልኳት መሰለኝ»

በነጋታው ሲልቪን ከምግብ ቤት ስትወጣ ጠብቄ አገኘኋት:: ቡና ልጋብዝሽ አልኳት:: ኢኩስ ውስጥ የምወደው ካፌ የለኝም አልኩህ፣ አለችኝ፣ እሺ ማርሰይ ልውሰድሽ አልኳት:: መኪናዬ ጋራዥ ናት አለችኝ:: በአቶቡስ ልውሰድሽ አልኳት:: አልፈልግም አለችኝ:: እንግዲያው ምን እናርግ? አልኳት:: እኔ ቡና ሳጠጣህ፣ ራሴ አፍልቼ፣ አለችኝ:: ቤቷ ወሰደችኝ፣ ከኢኩስ ትንሽ ወጣ ብሎ ባላገሩ ውስጥ ነው

«የሲዛን የነበረው ቤት በዚህ በኩል ነው:: መሄድ ትፈልጋለህ?» አለችኝ

«አልፈልግም» አልኳት

«እኔም ሄጄ አላውቅም» አለችኝ

እየሳቅኩ «Tu t'en fous, eh?» አልኳት («ደንታ የለሽም፣ እ?»)

እየሳቀች፣ «Je m'en fous épérdument!» አለችኝ («እቺን ያህል እንኳ ደንታ የለኝም»)

ቤቷ ገባን:: ሁለት ክፍል (አንድ መኝታ፣ አንድ ሳሎን) ወጥ ቤት፣ መታጠቢያ ክፍል:: በየግድግዳው የልዩ ልዩ አቢይ ስእሎች እትም ተለጥፏል:: የቤት እቃው ዘመናዊ ነው፣ ሰማያዊና ወይን ጠጅ ቀለማት ይበዙበታል

«ግሩም ቤት አለሽ» አልኳት

«ከርስዎ በፊት ሌላ ወንድ ገብቶበት እንደማያውቅ ስገልፅልዎት በትህትና ነው» አለችኝ:: አመንኳት:: እጅ እየነሳኋት

«ሻህራዛድ የኔ ፍቅር፣ የቀኔ ጨረቃ፣ የሌሊቴ ፀሀይ! ክብር ይሰማኛል» አልኩና፣ እንደ ፈረንሳዮቹ እጇን ሳምኳት:: ደስ የሚለኝ

ሳቋን እየሳቀች «ቁጭ በል ቡና ላፍላልህ» አለችኝና ወጥ ቤት ገባች

እንዱን ግድግዳ በሙሉ የያዘ ባለአምስት ተርታ የሆነ የመፃህፍት መደርደሪያ አለ:: በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ የተፃፈ መአት መፅሀፍ ተደርድሮበታል:: ባንዱ ተርታ የአርት መፃህፍት፣ ባንዱ የፊሎሶፊና የታሪክ የሶሲዮሎጂ መፃህፍት፣ በሶስተኛው ልዩ ልዩ አይነት መፃህፍት፣ በተቀሩት ሁለት ተርታዎች ደሞ ልብወለድ መፃህፍት:: መደርደሪያው አጠገብ መፅሄቶችና ጋዜጦች የተሸከመ ሰፊ ጠረጴዛ አለ:: ወድያኛው ግድግዳ ጥግ ትልቅ ራዲዮ-ግራማፎን፣ አጠገቡ እንደ መፃህፍቱ የተደረደሩ ሸክላዎች

ይህን ቆሜ ሳደንቅ መጣችና

«ቁጭ በል 'ንጂ» ብላ ከስማያዊዎቹ ሶፋዎች አንዱ ውስጥ አስቀምጣኝ «ምን አይነት ሙዚቃ ትፈልጋለህ?» አለችኝ

«የላቲን አሜሪካ አለሽ?»

«እንዴታ!»

ሙዚቃው ሲጫወት አጠገቤ ቁጭ ብላ እጄን ያዘችኝ:: ዝም ብለን ስንሰማ ከወጥ ቤቱ ቀጭን የባቡር መሳይ ፉጨት ጮኸ:: ዘላ ተነሳች

«ቡና ደርሷል:: ከወተት ጋር ነው 'ምትፈልገው?» አለችኝ

«አዎን፣ ውድ ሻህራዛድ ሆይ» አልኳት

ቡናውን ስንጠጣ «ተመስገን ቤት መሄድ መተውሽን ለምን አልነገርሽኝም?» አልኳት:: ጉልህ ሰማያዊ አይኖቿ በመልካም ብርሀናቸው አዩኝ፣ ውብ ሰፊ አፏ በፈገግታ ተከፈተ

«ኩራት እንዳይሰማህ ብዬ ነዋ» አለችኝ

ጥቁር ፀጉሯን ወደታች እየዳሰስኩ

«ስሰማ እንዴት ደስ እንዳለኝ ልነግርሽ አልችልም» አልኳት:: ጉንጮቿ መቅላት ጀመሩ፣ ወደታች አየች

«እንደሱ አትየኝ!» አለችኝ

አገጯን በግድ ወደላይ አንስቼ፣ አይን አይኗን እያየሁ



@BOOKALEM

«ምናለበት ባይሽ?» አልኳትና ግምባሯን ሳምኳት

ዝም ብለን ቡና በወተታችንን ፉት እያልን ሙዚቃውን እየሰማን ትንሽ ከቆየን በኋላ

«ለመሆኑ፣ ተመስገን ትራስ ላይ ቡና አይነት ፀጉር እንዴት አገኘሽ?» አልኳት

እየሳቀች «እኔው ራሴ ነኝ ይገኘው የሄድኩት» «እንዴት ቡናማ ፀጉር ያላት ጓደኛ አለችኝ:: ቤቷ ሄጄ ከወገር ብሩሿ ፀጉሮች ለቅሜ ይገኼ ሄድኩ»

እኔም እየሳቅኩ «ጫማሽን ሳታረጊ ወጥተሽ ነበር:: ረስተሽ ነው?» አልኳት

«ረስቼ አይደለም»

«ታዲያስ?»

«የእውነቴን የተናደድኩ እንዲመስለው ብዬ ነው:: ምናልባት 'ቡና አይነት ፀጉር እዚህ ሊገኝ በጭራሽ አይችልም' ብሎ ያሰበ እንደሆነ፣ ቀጥሎ 'እሷ ራሷ አምጥታው እንደሆነ ነው 'ንጂ' ብሎ ሊያስብ ይችላል:: ያን ጊዜ 'ራሷ አምጥታው ቢሆን ኖሮ፣ በንዴት መፅሀፎቼንም ከጠረጴዛው አትበትንም ነበር፣ ጫማዋንም ማድረግ አትረሳም ነበር' ብሎ ማሰቡ አይቀርም»

በአድናቆት ራሴን ነቀነቅኩ

* * *

ይሄ ሁሉ ሲሆን ባህራምን አልረሳሁትም ነበር

ከምሳ በኋላ Le Monde የተባለውን ስመጥሩ የፈረንሳይ ጋዜጣ እገዛና፣ ካፌ ዶርቢቴል ገብቼ petit créme (ቡና በወተት በሲኒ) አዝዤ ሀበሻቼ እጠገብ ቁጭ ብዬ ጋዜጣዬን ማንበብ እጀምራለሁ:: ጩኸት፣ ሳቅ፣ ወሬ፣ የሲጋራ ጪስ፣ የሴት ሽቶ ካፌውን ይሞላዋል:: በበጋው ሙቀት ምክንያት መስኮት ሁሉ ይከፈታል:: ሰማያዊ ካኪ የስራ ልብስ የለበሱ የፋብሪካ ሰራተኞች የቡና ማፍያው መኪና የተቀመጠበትን ረዥም ባንኮኒ በክንዳቸው ተደግፈው በተርታ ቆመው ፓስቲስ (ነጭ አረቂ) እየጠጡ፣ የፋብሪካ ዘይት ምናምን ያቆሸሸውን ቀያይ ፀጉራም እጃቸውን በብዙ እያንቀሳቀሱ፣

በእስቲኝ የደቡብ ፈረንሳይኛቸው ያወራሉ:: ከባንኮኒው ዳር፣ ከመስተዋት የተሰራው በር አጠገብ፣ የካፌው ባለቤት መስዬ ፖል የቂል ሳቁን እየሳቀ «Merci bien, monsieur» («እግዜር ይስጥልኝ ጌታዬ») እያለ የሚከፍሉትን ገንዘብ ይቀበላል፤ ቴምብርና ሲጋራ ይሸጣል

ከባንኮኒው ኋላ ቆንጆዋ የመስዬ ፖል ሚስት ባጭሩ የተቆረጠ ብጫ ብጤ ቀለም የተቀባ ፀጉሯ እያብለጨለጨ ለሰዎቹ ቡና ወይም ፓስቲስ እያቀበለች፣ ከወጣቶቹ ጋር ፈገግታና ቃላት ትቀባበላለች፣ ትሽኮረመማለች፣ በማርሰይ ዜማ ታወራለች:: ሽርሞጥሞጥ የምትል ሴት ናት:: ድምፅዋ፣ አስተያየቷ፣ አረማመዷ፣ ሁለመናዋ ወንድ ይጣራል:: መስዬ ፖል በብስጭት ነው የሚኖረው ሲባል እሰማለሁ:: ግን ተማሪ ውሽማ የላትም ይላሉ:: ተማሪዎቹ መስዬ ፖልን ይወዱታል፣ ሚስቱን ሊነኩበት አይፈልጉም:: እሷም ተማሪ የምትፈልግ አትመስልም:: ውሽሞቿ ጎረምሶችና የፋብሪካ ወይም የኩባንያ ሰራተኞች ናቸው — በበጋው ሙቀት ኮታቸውን አውልቀው የሸሚዛቸውን ቁልፍ በሙሉ ፈተው፣ የደረታቸውን ፀጉርና ጡንቻ እያሳዩና እጅጌያቸውን ሰብስበው ጡንቸኛ ፀጉራም እጃቸውን እያወዛወዙ ካፌ ዶርቢቴል የሚመጡ ጎረምሶች

አጠረጴዛዎቹ መሀል ሁለቱ ሴት ቦዮች ቡና፣ መጠጥ፣ ሲጋራ እየያዙ ይዘዋወራሉ

ሀበሾቹና ባህራም ካንድ ሁለት አፍሪካውያን ወይም ፈረንሳዮች ጋር ካርታ ሲጫወቱ፣ አጠገባቸው ቁጭ ብዬ ጋዜጣዬን አነባለሁ:: በካርታ የተሸነፉት ሁለት ልጆች፣ ሌሎች ሁለት ተሸንፈውላቸው ተራቸውን ለመጫወት እስኪችሉ ድረስ መጥተው ከኔ ጋር ያወራሉ

ተካ ይመጣና ጋዜጣዬን ሳነብ «የማታነበውን ገፅ ልመልከተው 'ስቲ» ብሎ ጋዜጣዬን ነጥሎ ግማሹን ይወስድብኛል:: የማነበውን ጨርሼ ወደሌላ ገፅ መሄዴ ሲሆን፣ ተካ «ቆይ እቺን ልጨርስና 'ስጥሃለሁ» ይለኛል:: «አምጣ 'ንጂ» ስለው «ጋዜጣው ካንተ ጋር ይውላል፣ ትንሽ ባነብ ምናለበት?» ይለኛል:: ብሽቅ ብዬ አየዋለሁ:: ጥፍሩን እየነከሰ ያነባል:: ጋዜጣው ውስጥ ያሳቀውን ወይም ያስገረመውን ነገር ያሳየኛል፤ በጭራሽ አያስቅም፣ አያስገርምም:: አይ ተካ ብሽቁ! ግን ጥሩ ልጅ ነው:: እሱ ራሱ ጋዜጣ ገዝቶ ያነብ እንደሆነ፣ ጋዜጣውን ይሰጠኝና «የማታነበውን ገፅ ስጠኝ:: ሌላውን ካንተ በኋላ ቀስ ብዬ አነበዋለሁ» ይለኛል



@BOOKALEM

አንዳንዴ ሀበሾቹ ተሰብሰበው ካርታ ሲጫወቱ ወዳጆቻቸው ሴቶች አንድ ጠረጴዛ ይዘው እያወሩ ይጠብቁዋቸዋል:: ሲያሰኘኝ ከነሱ ጋር ትንሽ አወራለሁ

ከኒኮል ጋር ማውራት እሞክራለሁ፣ ያቅተኛል:: በጣም ታፍራለች፣ ያልለመደችውን ሰው ማናገር አይሆንላትም:: ለጊዜው በጭራሽ ላውቃት አልቻልኩም:: በለዚህ ባህራም ምን አይቶባት ይሆን? ለሚለው ጥያቄ የመልስ ጫፍ እንኳ አላገኘሁለትም:: መልኳን አይቶ እንዳልሆነ ግን ግልፅ ነበር:: ውሀ አረንጓዴ አይኖች፣ የተዘረዘሩ ጥቃቅን ጥርሶች፣ ትኩሳት እንደያዛቸው አይነት ቆዳቸው የደረቀ ከናፍር:: ድምፅዋ ደስ ይላል:: ባህራም ምን አይቶባት ይሆን? እውነት ለገንዘቧ ሲል ይሆን?

ከአማንዳ ጋር ግን ብዙ እናወራለን:: ሀበሾቹ አማንዳ ዱቤ ነው የሚሏት:: ሉልሰገድ ይዟት ሊሄድ ሲል፣ ተካ «እንግዲህ ሂድና ዱባህን አገላብጥ!» ይለዋል:: ሉልሰገድ «አንተ ደሞ ከዱባ የተሻለች እስከታገላብጥ ድረስ በለዱባ ባታወራ ጥሩ ነው!» ብሎት አማንዳን አቅፎ ይሄዳል:: አማንዳ በእንግሊዝኛ «ምንድነው 'ሚለው?» ትለዋለች:: «ተይው ዝም ብሎ ነው» ይላታል::

ጋዜጣዬን አንብቤ፣ ሰዉን አይቼ፣ ባህራምን ተመልክቼ፣ በለራሱ ለማውራት ዝግጁ እንዳልሆነ ከተገነዘብኩ በኋላ፣ ከካፌው ወጥቼ ወደ ኩር ሚራቦ በኩል ትንሽ እራመዳለሁ:: ወደኋላ ዞሬ፣ ማንም ሀበሻ እንዳልተከተለኝ ካረጋገጥኩ በኋላ፣ እታጠፍና ወደ ሲልቪ ቤት አመራለሁ

አንድ ቀን «ባህራምን ያዘከው?» አለችኝ

«የለም» አልኳት

«የምትይዘው ይመስልሀል?»

«እርግጠኛ ነኝ»

«የምስራቅ ሰው እንደሆንክ ያስታውቃል:: ጊዜ የሚያመጣውን ጊዜ እስኪያመጣው ትጠብቃለህ 'ንጂ ጊዜን ልታጣድፈው አትሞክርም:: የምእራብ ሰው ብትሆን ግን ባህራምን ሂደህ በብልሀት ታዋሪው ታወጣጣው ነበር»

«እንደሱ ካረግኩማ እሱን ራሱን ላውቀው አልችልም:: የማስብና



@BOOKALEM

የሰጥሽው ችሎታውን ብቻ ነው ሳውቅ 'ምችለው»

«ምን የሚል ይመስልሀል?»

«ምን እንደሚልማ ማወቅ ቀላል ነው»

«እንግዲያው ምንድነው 'ምትጠብቀው?»

«ያ ያልኩሽ ጊዜ ሲመጣ፣ ተጠንቅቄ 'ምሰማው ቃላቱን አይደለም'ኮ»

«ታድያስ?»

«ድምፁን ነው:: ዜማውን:: እጁ እንዴት እንደሚንቀሳቀስ:: ምን ሲል ድምፁ እንደሚለሰልስ፣ ምን ሲናገር ግምባሩ እንደሚቋጠር:: አንዳንድ ጊዜ እኛ ሳናውቅ ፊታችን ላይ ፈገግታ ወይም ሀዘን በገዛ ራሱ ይጫወት የለ? ያንን ነው 'ምጠብቀው:: አንድን ሰው የምናውቀው በሚናገረው ቃላት አይደለም፣ ያን ቃላት ሲናገር በሚያሳየው ገፅ፣ በሚያሰማው ድምፅ ነው:: እሱን እሱን ለማየት ነው ባህራምን አድፍጬ 'ምጠብቀው»

ከሰአት በኋላውን ከሷ ጋር አሳልፈዋለሁ:: እንቅልፍ ከወሰደን ወይ አስራ አንድ ላይ እንነቃለን:: ወይ እናወራለን፣ ወይ እናነባለን፣ ወይ ሙዚቃ እንሰማለን:: ሰኞና አርብ በአስር ሰአት ላይ ክፍል አለባት:: አንዳንዴ ተኝቼ ትታኝ ሄዳ ስትመለስ ትቀሰቅሰኛለች:: አንዳንዴ ነቅቼ እንደ ሌላ ቀን ከአርት መፃህፍቷ አንዱን እየተመለከትኩ፣ ወይም እያነበብኩ፣ ወይም ሙዚቃ እየሰማሁ እቆያታለሁ

ሲመሽ ተሰይቻት እሄዳለሁ:: «A demain, cheri» («እስከ ነገ ደህና ሁንልኝ») ምግብ ቤት ሄጄ እራቴን በልቼ፣ ከዚያ ወጥቼ የቴሌቪዥን ዜና አይቼ ሳበቃ፣ ሆቴሌ ሄጄ ስራ እጀምራለሁ:: (አሜሪካዊቷ መምጣት ትታለች) ወይም ሲኒማ እገባለሁ:: ከሲኒማ በኋላ ለመስራት እሞክራለሁ:: እምቢ ካለኝ፣ የሌሊት ፀጥታ የጥጣቸውን የእክስን ጠባብ መንገዶች እዘዋወርባቸዋለሁ:: ንጉሳቸው ነኝ

ጧት ተነስቼ፣ ቁርሴን ሁለት croissant በልቼ፣ ቡና በወተት ጠጥቼ፣ ወደ ቤተመፃህፍት ሄጄ እስከምሳ ሰአት እሰራለሁ:: (ክፍል መግባት ከተውኩ መቸስ ዘመን የለኝም)



@BOOKALEM

ከምሳ በኋላ ካፌ ዶርቢቴልን ኅብኘቼ ወደ ሲልቪ አሄዳለሁ:: በስፌ አፏ እየሳቀች ትቀበለኛለች

አያሌ ቀናት ካለፉ በኋላ፣ ተመስገንን እየሳቅኩ

«ሲልቪ እንደወጣች ቀረች?» አልኩት

«ቀረች!» አለኝ «አሁንማ ብትመለስም አልፈልጋት»

«ምነው?»

«እንጎሏ ምላጭ የሆነ ሴት መቶ በመቶ ሴት አትመስለኝም:: አሁን አንዲት ጅል ብጤ ፈረንሳይ ይዣለሁ:: በጣም ተስማምታ ኛለች:: እጄን ሰደድ ሳረግ መከፈት ነው:: ዝብዝብ የለም:: ፖለቲካ፣ ሊትረቸር፣ ምናምን የለም:: ያቺ ግን! ስለኢትዮጵያ የምትጠይቀኝን ጥያቄ ለመመለስ ብቻ ስንትና ስንት አስጥሮ መዋጥ ያስፈልገኝ ነበር:: ያውም አብዛኛውን ለመመለስ አልችልም ነበር»

«እኔ ግን በጣም ደስ ትለኛለች ልጂ» አልኩት «እውነት በጭራሽ አትፈልጋትም?»

«በጭራሽ:: አንተ 'ምትወዳት አይነት ሴት ናት:: ሞክራት»

«በኋላ ይቆጭህና መልስልኝ ትለኛለህ ልባርግ» አልኩት

«እርም ይሁንብኝ!»

«ተው!»

«ኡዎ! ይልቅ አንዱ ጭልፊት ፈረንሳይ ሳይሞጨልፋት ቶሎ አብስላት»

«ታድያ አንተ የተጠቀምክበትን ዘዴ ንገረኛ፣ እንዲረዳኝ ያህል» አልኩት

ነገረኝ፣ መከረኝ፣ አብረን ፕላን አወጣን:: በመጨረሻ

«አንድ ምክርና አንድ ማስጠንቀቅያ ልስጥህ መሰለኝ» አለኝ

«እሺ»

«ምክሩ ይኸውና፣ ልጅቱን እንደፈለግካት ጊታው ተካ



@BOOKALEM

እንዳያውቅብህ»

በዚህ ስቀን ስንጨርስ

«ማስጠንቀቂያውስ?» አልኩት

«እቺ ሲልቪ አንዳንዴ ሌላ ሰው ትሆንብኛለች፡፡ አልጋ ውስጥ ያለልማዷ እንደማበድ ትላለች፣ ወሬፍ ያረጋታል፡፡ እና በያሰታ ታሳብድሀለች፣ ታድያ—»

«ታድያ?»

«ታድያ ነገሩ ካለቀ በኋላ ታኮርፋለች፡፡ ወይዚያ ፊንጠር ብላ ራሷን እጇ ውስጥ ትደፋለች፡፡ አንዳንዴም ታለቅሳለች»

«ምን ሆንሽ ስትላትስ?»

«አትነግርህም፡፡ እና ግራ ያገባሀል፡፡ አውቀህ ብትገባበት ይሻላል ብዬ ነው»

«ይገባኛል» አልኩት

ተመስገን እንዳልዋሸ አውቄያለሁ፡፡ ግን ሳቂታዋ ሲልቪ አኩርፋ ወይም ስታለቅስ -- በጭራሽ ሊታየኝ አልቻለም

ካንድ ሳምንት በኋላ እኔና ሲልቪ በይፋ አብረን እንወጣ ጀመር፡፡ ሀበሾቹ «አልጋ ወራሽ» አሉኝ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አልጋ ወራሽነቴን ረሱት፤ በነሱ አይን ሲልቪ የኔ ሆነች

ተመስገን «የነገርኩህ ብልሀት ሰራ መሰለኝ» አለኝ፡፡ የደስ ደስ ቢራ ጋበዝኩትና ሲኒማ አስገባሁት፡፡ የያዛትን «ጅል ብጤ» ፈረንሳይ አስተዋወቀኝ፡፡ ብሉንድ (ነጭ) ፀጉሯን እንደ ወንድ ተቆርጣለች፡፡ በጣም ቁንጅ ናት፡፡ ይሄ ተመስገን ሴት አመራረጥ ያውቃል፡፡

ደሞ ሴቶች የሚወዱት ይመስላል፡፡ ታድያ የሚገርመኝ ነገር አለ፡፡ አዲስ አበባ በነበርንበት ጊዜ የምትጠጋው ሴት አልነበረችም



@BOOKALEM

# አራት

## ባህራም
## ከቅርብ

ማክሰኞ ነበር እስታውሳለሁ:: ከምሳ በኋላ Le Monde ጋዜጣዬን ገዝቼ ካፌ ዶርቢቴል ገብቼ እንደ ልማዴ petit créme አዝዤ ካርታ የሚጫወቱት ሀበሾች አጠገብ ቁጭ አልኩ:: ትንሽ ቆይቶ ባህራም መጣ:: ሳየው የተለወጠ መሰለኝ:: ልማዱ በፍጥነት እርምጃው ከተፍ ብሎ ሲያበቃ፣ ሀበሾቹን «እናትክን! ሀለላሲ ሙት! Je veux jouer aux cartes.» («ካርታ አጫውቱኝ») ብሎ ቁጭ ማለት ነበር:: ዛሬ ግን በቀስታ እርምጃ መጣ:: እንደ ድሮው አልቀለደም:: እንደ አጋጣሚ ለካርታ ጨዋታው አንድ ሰው ጎድሏቸው ስለነበረ «ባህራም! ና ካርታ እንጫወት» አሉት

«ካርታ ጨዋታ አላሰኘኝም» አለና ዝም ብሎ ቁጭ አለ:: የተበሳጨ ይመስላል

«ምን ሆነሀል?» አለው ሉልሰገድ

«በፈተና ወደቅኩ» አለ

ሁሉም የሚሉትን አጡ

እንግዲህ በፈረንሳይ ዩኒቨርሲቲዎች ደምብ፣ አንድ ተማሪ የሰኔ ወር ፈተናውን የወደቀ እንደሆነ፣ በእረፍት ጊዜው ሲያጠና ይከርምና፣ በጥቅምት (ትምህርት ቤት ሲከፈት) እንደገና ይፈተናል:: ስለዚህ ተመስገን

«አይዞህ በጥቅምት ፈተና ታልፋለህ» አለው

ባህራም አልተፅናናም:: ሁሉም ዝም አሉ:: ካርታ ጨዋታቸውን



@BOOKALEM

ቀጠሉ

ባህሩም «ዞላለም ካርታ ጨዋታ ምን ያረጋል? እንውጣ ትንሽ እንንሸርሸር» አለ:: ማንም መልስ አልሰጠውም:: ትንሽ መውጣት ፈርተዋል:: ካርታ ጨዋታቸውን ቀጠሉ – አብረውት ብቻ ሳይሆን ከባህሩም ብስጭት ለማምለጥም ጭምር:: ለጨዋታው ተነስቶ ብቻውን ወጣ:: ተከትዬው ወጣሁ:: ወደ መናፈሻው በኩል ገባው:: እያመለከትኩ

«ወደዚያ እንሂድ?» አልኩት:: መልስ ሳይሰጠኝ ወደዚያው አመራ:: ትንሽ እንደተራመድን

«ያውና ተካ:: ወደኛ በኩል ይመጣል» አለኝ «አደራህን አብሮን እንዳይመጣ:: ዛሬ እሱ ሁለት ቃላት ቢያናግረኝ አብዳለሁ»

«አትስጋ» አልኩት

ተካ አቆመንና በፈረንሳይኛ

«ከየት ነው የምትመጡት?» አለን

«አሁን ከየትም ብንመጣ ደንታ የለህ:: ለምንድነው 'ምትጠይቀን?» አልኩት በአማርኛ

«ከዶርቢቴል ነው 'ምትመጡት?» አለኝ ባማርኛ

«አዎን» አልኩት ባህሩም እጁን ኪሱ ከቶ ወደዚያ ይመለከታል

«ወዴት ነው 'ምትሄዱት?» አለኝ ተካ

«ወዴትም:: ምን ያረግልሀል?»

«ወደ ሲቴ ነው 'ምትሄዱት?»

«ምነው? ከኛ ጋር ሲቴ መሄድ አማረህ?»

«አይ! እኔ ለራሴ ከዛ መምጣቴ ነው:: ቡና አምሮኛል»

«እንግዲያው ሂድና ቡናህን ጠጣ»

«ጋዜጣህን አሁን አታነበው እንደሆነ ስጠኝ»

ጋዜጣዬን ሰጠሁትና መንገዳችንን ልንቀጥል ስንል

«ይሄ አቃጣሪ ገንዘብ እንዳያጭበረብርህ ተጠንቀቅ» አለኝ

«ሂድ ቡናህን ጠጣ» አልኩት:: ሄደ



@BOOKALEM

እኔና ብሁሉም አንድ ቃል ሳንነጋገር መናፈሻው ደረስን፡፡ ዛፎች ጥላ ስር አንድ አግድም ወምበር ላይ ቁጭ አልን

«ፈተና መውደቅ የተለመደ ነገር ነው፡፡ በጥቅምት ታልፋለህ» አልኩት

በተለመደ ፈረንሳይኛው፣ በመፍራም ልዝብ ድምፁ መናገር ጀመረ

«መውደቁ አይደለም የሚያበሳጨኝ፣ አወዳደቁ ነው፡፡ ትምህርቱን በደምብ ይዤዋለሁ፡፡ በምን እንደጣሉኝ ታውቃለህ? በፈረንሳይኛዬ ጉድለት፡፡ አያስቅህም? ፈተናውን የወደቅኩት እኔ ፈሊ ባልሆን ያስቀኝ ነበር

«እኔንና ፈረንሳዮቹን የክፍሌን ልጆች አስተያየን እስቲ፡፡ ትምህርቱን እኩል እናጠናቀው፡፡ ፈተና እንገባና ጥያቄው ይሰጠን፡፡ መልሱን እኔም እነሱም እኩል እንወቀው፡፡ እነሱ ምን ያረጋሉ? መልሱን በፍጥነት ይፅፋሉ፣ አስካኩንና አገባቡን ያማርጣሉ፡፡ ተቃቅኗን ነገር ጭምር ያስገቢታል፡፡ ሀያ-ሀያ አንድ ገፅ ዕፈው ይወጣሉ፡፡ ያልፋሉ፡፡ እኔም መልሱን ከነሱ እኩል አውቀዋለሁ፡፡ ታድያ ፈረንሳይኛው ከየት ይምጣ? ከሱ ጋር ስታገል የጊዜዬን ግማሽ እጠፋለሁ፡፡ ለዚያውም እምጩ የማመጣው ፈረንሳይኛ እንካሳ ሽባ ስለሆነ፣ በደምብ የማውቀውን መልስ ልክ እንደማላውቀውና በግምት ወይም በነሲብ እንዳገኘሁት ያስመስልብኛል፡፡ ዘጠኝ አስር ገፅ ዕፌ እወጣለሁ፣ በመጥፎ ፈረንሳይኛ፡፡ ትምህርቱን እያወቅኩት ፈተናውን እወድቃለሁ

«ፈረንሳዮች ደሞ ታውቃቸዋለህ፡፡ በቋንቋቸው የመጣ በጣም እንክለ-ጠባብ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አስተውለህ እንደሆን በፍጥነትና ያለ ስህተት ያነጋገርካቸው እንደሆነ ያከብሩሀል፣ «Intelligent» ይሉሀል፡፡ እየተንተባተብክ ያነጋገርካቸው እንደሆነ ግን ምንም ቁም ነገር ብትናገር መሃይም ነህ ማለት ነው፡፡ በቋንቋህ ብታናግራቸው እንደ ቂል አፋቸውን ከፍተው እንደሚቀሩና፣ የነሱም ቋንቋ ላንተ ያንን ያህል እንግዳ እንደነበረ፣ የሚሉት ሁሉ «ዠበበቢ» ይመስልህ እንደነበረ፣ በስንት ልፋት በመጠኑ ልታውቀው እንደቻልክ፣ በቋንቋቸው መንተባተብ ስለቻልክም ሊያመሰግኑህ እንጂ ሊንቁህ እንደማይገባቸው፣ ይህን ለመገመት ያህል ስፊ እንጎል የላቸውም፡፡



@BOOKALEM

ተራውስ ሰው እንዲህ ቢሆን አልፈርድበትም:: የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮቹ እንዲህ ሲሆኑ ግን በጭራሽ አይገባኝም:: እንግዲያው የነሱ ትምህርት የታል? እቺን ያህል ቀላል ነገር ማመዛዘን ካልቻሉ፣ እንነሳቸውስ ትምህርታቸውስ ምን ትርጉም ይኖረዋል?

«እማናውቀው አገር መጥተን፣ በማናውቀው ቋንቋ የማናውቀውን ህዝብ ባህልና ታሪክ ለመማር ስንታገል፣ ለምን አስተያየት አያደርጉልንም?»

«ምን አይነት አስተያየት ሊያደርጉልን ይችላሉ?» አልኩት

«ፈረንሳይኛችን ትንሽ የተጣመመ እንደሆነ፣ የቋንቋውን መጣመም ችላ ብለው የፍሬ ነገሩን እዚያ መገኘት ለምን አያስቡልንም? አገራችን ስንመለስ በራሳችን ቋንቋ ነው 'ምንጠቀመው፣ ስለዚህ ፈረንሳይኛውን እንደነሱ ቻልነውስ በመጠኑ ተንተባተብንበትስ ምን ያህል ልዩነት ያመጣል? እንግዲህ ስንሆን፣ ፈረንሳይኛውን በሀያ ሶስት፣ በሀያ አራት፣ በሀያ አምስት አመታችን ስንጀምረው፣ እንዴት ከናታቸው ጡት ጋር ሲጠቡት ካደጉ ሰዎች እኩል ካልሆን ተብለን እንቀጣበታለን? ቅጣት መሆኑ ይታይሀል? ፍሬ ነገሩን እንደማውቀው ግልፅ ሳለ፣ የተጠቀምኩበት ፈረንሳይኛ የተቀመመ ፈረንሳይኛ ባለመሆኑ ፈተናዬን ስወድቅ፣ አንድ አመት ሙሉ የለፋሁበትን ስከለከል፣ ይሄ ቅጣት ነው እንጂ ምንድነው? ፍትህ የሌለው ቅጣት

«አንድ አመት ምን ያህል እንደሆነ ይገባሀል? አስበው:: የዘጠኝ የአስር አመት ልጆች ሳለን ክፍል በመድገም አንድ አመት ብናጠፋ ምንም አይደለም:: በሀያ ስድስት፣ በሀያ ሰባት አመታችን አንድ አመት ማጥፋት ግን ሌላ ነገር ነው:: ምክንያቱም እነዚህ አመታት ከሀያ አምስት እስከ ሰላሳ አምስት ሰፈር ያሉት አመታት፣ የሌሎቹን አመታት ሶስት አራት እጥፍ ዋጋ አላቸው:: አሁን ነው ህይወታችንን ለመጨረሻ የምንቀርፀው:: አሁን ነው ያለ የሌለንን ለሀገራችን ልናበረክትላት የሚገባን:: አሁን ነው የኑሮ ስራችንን የምንመርጥበት የምንጀምርበት ጊዜ:: አሁን ነው የኑሮ ጓደኞቻችንን የምንመርጥበት፣ ትዳራችንን የምንቆረቁርበት ጊዜ:: አሁን ነው፡ አሁን! አሁን! አሁን ነው ልጅነትም የማያታልለን፣ እርጅናም የማይጫጫነን:: አሁን ነው ፍሬ ለመስጠት ዋጋ ለማስገኘት የምንችለው»

ሬጋ ባለ ድምፅ

«አሁን ነው ፈረንሳዮች 'ለምን ቋንቋችንን ከኛ እኩል አልቻላችሁም?' ብለው ወርቅማ አመታችንን የሚያጠፉብን

«ጠፉች በቃ እቺ አመት:: እኔም፣ ቤቶቼም፣ አገሬም አንድ ወርቃማ አመት ተነጠቅን:: ታድያ የነጠቁን ሰዎች አልተጠቀሙበትም:: እንደነጠቁንም አላወቁም:: በጫካ ስታልፍ አንድ ትል ብትጨፈልቅ አይታወቅህም፣ የትሉ ሚስት ግን አለም ይጨልምባታል:: ፈረንሳዮቹ አመቴን አጠፉብኝ:: አንድ አመት ሙሉ!»

«ፈተናውን ባታልፍበትም እውቀቱን አግኝተህበታል» አልኩት

«እኛ አገር ምስክር ወረቀት የሌለው እውቀት ከእውቀት አይቆጠርም:: ስለዚህ ያገኘሁት እውቀት በምንም ሊጠቅመኝ አይችልም:: የህግ ትምህርት እንደ ፍልስፍና ወይም እንደ ስነ-ጽሁፍ ትምህርት አይደለም:: ጥቅሙ እስራ ላይ ሲታውለው ከቻልክ ብቻ ነው:: በስራ ላይ እንድታውለው ደሞ የምስክር ወረቀት ያስፈልግሃል:: የምስክር ወረቀት ለማግኘት የፈረንሳይኛ ቋንቋን እንደ ፈረንሳዮቹ ማወቅ አለብህ:: በፈረንሳይኛ እርሳስ ተባእታይ ፆታ ነው፣ ብእር ግን አንስታይ ፆታ ነው:: ለምን? ምክንያት የለውም:: መኪና፣ አውቶብስ፣ መፅሀፍ፣ ደብተር፣ ሰማይ፣ መሬት፣ ፀሀይ፣ ኮከብ፣ ደመና፣ ነፋስ – እነዚህ ተባእታይ ይሁኑ አንስታይ ፈረንሳይ ያልሆነ ሰው ቢያሳስት ይህን አሳሳትክ ተብሎ ፈተናውን ይወድቃል? ይሄ የሚገባ ነገር ነው?»

እውነቱን ስለሆነ ምንም ልለው አልቻልኩም

«አይዞህ በጥቅምት ወር ተፈትነህ ታልፋለህ» አልኩት

«እንዴት አድርጌ?» አለኝ «ትምህርቱ ቢሆን ያቃተኝ፣ ሌት ተቀን አጥንቼ እፈተን ነበር:: ፈረንሳይኛውን ግን በሶስት ወር ውስጥ ከምን ላደርሰው እችላለሁ? ከእንግዲህ ልጅ አይደለሁም:: ሀያ አምስት አመቴ አልፏል:: እስከ መቼስ ቢሆን ፈረንሳይኛውን ከነሱ እኩል ላውቀው እችላለሁ እንዴ?

«ጠፉች እቺ አመት:: እንደ ሌሎቹ አመታት ጠፉች፣ ተከተለቻቸው»

«ሌሎቹ አመታት?» አልኩት

«በይሩት ነበር የምማረው። በህክምና ትምህርት ሁለተኛ አመት እንደጨረስኩ ነው ወዲህ የመጣሁት»

(«ለምን መጣህ? መጥተህስ በህክምና ትምህርት እንደመቀጠል እንደገና ሀ ብለህ ህግን ለመማር ለምን ቆረጥክ?» ልለው ፈለግሁ፣ ግን አሁን የመጠየቅ ጊዜ አልነበረም፤ ዝም ብሎ የመስማት ጊዜ ነበር)

ዝም ሲል ጊዜ ንግግሩን እንዲቀጥል ለመቆስቆስ ያህል «አይዞህ በርታ፣ ሁሉም ሰው ችግር ያጋጥመዋል» አልኩት

ሳቅ አለ። አስተያየቱ «በምቾት ቁጭ ብለህ በችግር የሚፍጨረጨረውን ሰው 'አይዞህ፣ ረጋ በል' ማለት ምንኛ ቀላል ነው!» የሚል ይመስላል

«ችግሩ ይህን ያህልም ከባድ አይደለም» አለ «እንዲህ የሚያስለፈልፈኝ ከሌላ ችግር ጋር ተጋግዞ ስለሚያጠቃኝ ነው። በፈተና ስለወደቀ ያለቅሳል ብለህ እንዳትታዘበኝ. . .»

«ሌላ ችግር አለብህ?»

«ቤቶቼ ናቸው ሌላው ችግር። አየህ፣ አባቴና ከሁሉ ታላቅ ወንድሜ ነጋዴዎች ናቸው። እንዴ ገንዘብ ይተርፋቸዋል፣ እንደ ደሞ የተገዛው እቃ መሸጥ እስኪጀምር ጥሬ ገንዘብ ከእጃቸው ያጣሉ። በዚህ ምክንያት፣ በይሩት ስማር ሳለሁ በሶስት በአራት ወር ነበር ገንዘብ 'ሚልኩልኝ። ሳኩልኝ ስላቸው 'ከጓደኞችህ ተበደር፣ በኋላ እንከፍላለን' ይሉኛል

. . እንግዲህ በይሩት ውስጥ መአት ሰው ያውቀኛል። ይበደራል። እስከ ስድስት ሺ ፍራንክ ድረስ (3,000 ብር) ይበደር ነበር። ቤቶቼ ሲመቻቸው አንድ ስምንት ሺ ፍራንክ ይልኩለታል። እዳውን ከፍሎ ሲጨርስ ሁለት ሺ ያህል ይተርፈዋል። እነ እስኪታልቅ ካልላኩለት እንደገና ሌላ ይበደራል። እንደዚህ ነበር የሚኖረው

እዚህ ኢክስ እንደመጣ አድራሻውን ላኩላቸው «እንግዳ እኔ ስለሆንብኝና የማውቃቸው ሰዎች ስለሌሉ፣ ገንዘብ ቶሎ እንድትልኩልኝ አደራ» አላቸው። «እንደተመቸን እንልክልሀለን» አሉት። መበደር ጀመረ። እንደገና ደብዳቤ ፃፈ። በቀን በቀን



@BOOKALEM

ደብዳቤ መጥቶልኝ እንደሆነ ኢያለ እየተንገበገበ ይጠብቃል። አራት ወር ሙሉ ምንም መልስ ሳይልኩለት ቆዩ። ብድሩ እየበዛ ሄደ። ቴሌግራም ላከ «ምን ሆናችኋል? ስግቻለሁ፣ እዳ ተጠራቅሞብኛል፣ ረሀብም አጥቅቶኛል» አላቸው። መልስ ይጠብቅ ጀመር

ማታ ሲተኛ ስለነሱ ያስባል። ነገ ደብዳቤ ይደርሰኛል ይላል። ጧት ሲነሳ ስለነሱ ያስባል። ዛሬስ ደብዳቤ አገኛለሁ ይላል። ደብዳቤ ሳይደርሰው ቀኑ ሲመሽ ይገርመዋል። ይሰጋል። ምን ሆነው ይሆን? ይፈራል። ነገ ደብዳቤ ይደርሰኛል ይላል።

እዳው እየከበደው ሄደ

እንግዲህ የኤክስ ፖስታ በቀን ሁለቴ ነው የሚታደለው። የጧቱ ባምስት ሰአት ሰፈር ይመጣል። ባህራም ከክፍል ወጥቶ ሲጣደፍ ቤቱ ይሄዳል። ምንም ደብዳቤ አይጠብቀውም። ኩም ይላል። በአስር ተኩል ላይ ይመጣልኝ ይሆናል ይላል። እስከ አስር ተኩል ይጠብቃል። በአስር ተኩል ምንም ደብዳቤ አይመጣለትም። እነዚህን ሰአቶች ይፈራቸው ጀመር። ተስፋ ልቡ ውስጥ እየተጠራቀመ ይቆይና፣ ምንም ደብዳቤ እንዳልመጣለት ሲያይ፣ ነብሱ በኩምታ ሽምቅቅ ትላለች። በዛበት። ስለዚህ፣ ሁለቴ ኩም ከማለት ብሎ ከቤቱ ጧት የወጣ እስከ ማታ አይመለስም። ማታ ወደቤቱ ሲራመድ «ጧት ደብዳቤ መጥቶልኝ ይሆናል፣ ወይም ከሰአት በኋላ መጥቶልኝ ይሆናል፣ ከሁለቱ በአንዱ ሳይመጣልኝ አይቀርም» እያለ ያሰላስላል። ታድያ ደብዳቤ የሚሏት የለችም። ተስፋና መንገብገቡ ድንገት አፈር ይሆናል። ራሱን ማመን ያቅተዋል። «እንዲህ ሊሆን አይችልም፣ ደብዳቤ ሳይኖረኝ አይችልም!» ይላል። «ነገ» ይላል። እስከ ነገ በብዙ ይሰጋል። «ቤቶቼን ምን ነክቷቸው ይሆን? አባቴና ወንድሜ ከሰረው ይሆን? ግን ቢከስሩ ዕፈው አይነግሩኝም? መፃፍ አልቻሉ ይሆን? ታስረው ይሆን? ሞተው ይሆን? ምን አግኝቷቸው ይሆን?»

ይሄ ሁሉ ሲሆን እዳው እየተከማቸ ሄደ

«ከማውቃቸው ሰዎች ከአብዛኛዎቹ አምስት አስር፣ ሀያ ፍራንክ ተበድርያለሁ ይመስለኛል። አሁንማ ስንት ፍራንክ ከስንት ሰው እንደተበደርኩ እርግጠኛ አይደለሁም። ሰዎቹን በቀን በቀን አገኛቸዋለሁ። በቅርቡ እመልስልሀለሁ እያልኩ ነበር የተበደርኳቸው። እና ሳያቸው እፍራለሁ። ሲያሳፍር የሰው አይን! አይተውህ

ሲያልፉና፣ ካለፉህ በኋላ አይናቸው ውስጥ ያየኸውን ንቀት ሲታስታውሰው ማሳፈሩ!»

የሚገባበት ይጨንቀዋል:: ግን ምን ለማድረግ ይችላል? እፍረቱና ስጋቱ ሲፈራረቁበት እያየ «ይሄ ሁሉ መጨረሻው ምን ይሆን?» ማለት ብቻ ነበር

ከሁሉ የሚጎዳው ስለቤቶቹ ማሰብ ነበር:: ማታ እንቅልፍ እምቢ እያለው ስለነሱ ሲያስብ፣ እንነሱ እንደ ወሬኛ የመንደር ሴት ክፉ ክፉ ሀሳቦችን እየለቃቀመ የጭካኔ የጭቆና ትርኢቶችን ያሳየው ነበር

«ለጊዜው አንተን ችግር አያጥቃህ እንጂ፣ ቤቶችህስ ምንም አይሆኑም አይባልም» አልኩት

«አንተ የኛን አገር አታውቀውም:: ስንት ጭቦ እንደሚሰራ፣ ስንት በደል እንደሚፈፀም፣ እንኳን ልትገምት ልትጠረጥር አትችልም»

ሌሊት ሲሆን የሚመጡብህ ሀሳቦች አሉ:: ሀልም አይደሉም፣ ምክንያቱም እንቅልፍ አይወስድህም:: ግን ጤነኛ ሀሳቦች አይደሉም፤ የሌሊቱን ጭለማ ይለብሱና እንደ ጉንዳን ይወሩሀል. . . ያስፈራሩሀል. . . ቀን ቢመጡብህ ትስቅባቸዋለህ፤ እነሱም በቀን ደፍረው አይመጡብህም:: ሌሊት ግን እውነት ይመስሉሀል:: ብቻህን በጭለማ በረሀ ውስጥ ስትፈራ እንደምታየው ቁጥቋጦ ናቸው:: በመጥፎ ህልምና በውን መካከል አንድ የሀሳባችን ጫካ አለ:: ብቻህን ነህ፣ ጭለማ ውጦሀል፤ የቁጥቋጦ መአት ከቦሀል. . . መሰረት የሌለው ሀሳብ ሁሉ የመጨረሻ እውነት መስሎ ይመጣብሀል. . . እና በዚህ ጊዜ ባህሩም ስለቤቶቹ ሲያስብ፤ እንደ ቤታቸው ተቃጥሎ፣ ሁሉም ሞተው ይታየዋል፤ እንደ አባቱና ወንድሙ ከብረው በእጁ ተይዘው ታስረው፣ ወንድሞቹና እህቶቹ መጠጊያ አጥተው ሲጨነቁ ይታየዋል

በተለይ ከሁሉም አብልጦ የሚወዳት እህት አለችው:: የመጨረሻ ልጅ ናት:: ቤቶቹ ሁሉም እሷን ነው የሚወዷት:: ታድያ እሷ አልጋዋን ነው 'ምትወደው:: ስታጠና አልጋዋ ላይ ሆና፣ ስትጫወት፣ ስታዝን፣ ስትደሰት – ሁልጊዜ አልጋዋ ላይ ሆና ነው የሚያገኙዋት:: ይህን አልጋ ገረዶቹ እንዳያነጥፉት አይፈቀድላቸውም፤ ልጅቱ ራሷ ናት የምታነጥፈው:: በቀን አራት አምስት ጊዜ

ይነጠፋል

«እህቴን ያመጣት እንደሆን እማማ ብቻ ናት እንድታንጥፈው የሚፈቀድላት። ይሄ አልጋ በአመት ስድስት ሰባት አልጋ ልብስ ይገዛለታል። ብቻ ምን ልበልህ፣ እህቴ ያለአልጋዋ መኖር አትችልም። ታድያ በሀሳቤ ቤታችን ከነእቃው ሲወረስ፣ የእህቴ አልጋ በሀራጅ ሲሸጥና፣ እሷ ይህን ስትመለከት ይታየኛል። አይኖቿ ይታዩኛል። ሆዴን ያመኛል»

አንዳንዴ ደሞ አባቱ በፖለቲካ ምክንያት ተይዘው ወታደሮች እየዱፉ ሲወስዷቸውና ሌሎቹ ወታደሮች ደሞ እህቶቹን ሲደፍሩዋቸው፣ ወንድሞቹን በሰደፍ ራሳቸውን ሲፈነክቷቸው ይታየዋል። «ይሄ ሁሉ እኛ አገር በየቀኑ የሚደረግ ስለሆነ፣ እነዚህ የሌሊት ሀሳቦች በጣም ያስፈሩኛል፣ ያስጨንቁኛል»

አንዳንዴ ስጋቱ ከመጠን በላይ ይበዛበትና፣ ተነስቼ አገሬ ልግባ ይላል። ግን እንዴት ለመሄድ ይችላል? ባንድ በኩል ተስፋ የሚሉት አለ –

«ይሄኔ'ኮ ይህን ሁሉ ዝምታ የሚያስረዳ ደብዳቤና እዳዬን በሙሉ ለመክፈል የሚያስችለኝ ገንዘብ መንገድ ላይ ይሆናል፣ ነገ ወይ ተነገ ወድያ ይደርሰኝ ይሆናል» ይላል። በሌላ በኩል «ለመሄድ ብቆርጥስ በምን እሄዳለሁ?» ብሎ ሲያስብ፣ በኤሮፕላን፣ በመርከብ፣ በባቡር ወይም በአውቶቡስ እንዳይሄድ፣ ምን ከፍሎ? በእግሩ እንዳይ ሄድ፣ አመት ወይም ሁለት አመት ይፈጅበታል፣ ለዚያውስ ስንቅ ከየት ይመጣል? ሲመሽስ የት ይተኛል? በሌላ በኩል ደሞ፣ የመሄጃ ዘዴ ቢያገኝስ እዳውን ሳይከፍል እንዴት አድርጎ ለመሄድ ይችላል?

«እስረኛ ነኝ በቃ። በእዳና በተስፋ ታስሬ፣ በእፍረትና በስጋት የምገረፍ እስረኛ ነኝ»

«እንዴት ጎበዝ ነህ!» አልኩት

«እንዴት?» ለማለት ያህል አየኝ። ከቅንድቦቹ ጥቁር ሻካ ጥላ ስር ቡናማ ትንንሽ አይኖቹ ያዩኛል፣ ሀዘን ሞልቷቸዋል፣ ግን ተስፋ አልከዳቸውም፣ እንዲያውም ሳቁን የረሱ አይመስሉም

«እኔ አንተን ብሆን ድሮ ተስፋ ቆርጫለሁ» አልኩት። እፍንጫው ትልቅና ሸካራ መሆኑን ገና አሁን አስተዋልኩ



@BOOKALEM

«በይፋት ሳለሁ እንዲህ አይነት ኑሮ የሚኖር ሰው አለ ቢሉኝ ኖሮ፣ እኔም 'እንዴት ተስፋ አይቆርጥም!?' ብዬ ይገርመኝ ነበር። ስትገባበት ግን ሌላ ነው። አየህ፣ የሰው ልጅ በጣም ጠንካራ ነው፤ ምንም ያህል መከራ ቢናድበት አይሸነፍም፣ መቸም ቢሆን ተስፋ አይቆርጥም»

ዝም አልኩ። አፍንጫው ምን ያክላል!

«እኔ ተስፋ እንዳልቆርጥ የደገፈኝ ምን መሰለህ?» አለኝ

«ምን?»

«ሉልሰገድ፣ ተመስገንና፣ ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን። እንደዚህ ያሉ ሰዎች አጋጥሞኝ አያውቅም። ፈረንሳዮችን ታውቃቸዋለህ – እግራቸው ስር ወድቀህ እየተንፈራገጥክ በራብ ሞትኩ ብትላቸው፣ እጃቸውን ብድግ አርገው ትከሻቸውን አንቀሳቅሰው 'ኸአ! መሰዩ፣ ታድያ ይህ የኔ ጥፋት ነው? ለምን ወደ ኢምባሲዎ አያመለክቱም?' ብለውህ መንገዳቸውን ይቀጥላሉ። ኢክስ ውስጥ ተበድሬ ተበድሬ፣ የማውቃቸውን ሰዎች ጨረስኩ። የቀረኝ ጥቅልል ብሎ በረሀብ መሞት ነበር። ተመስገንና ሉልሰገድ አበሉኝ። ያገሬ ልጆች ማጣቴን አይተው ፊት በነሱኝ ሰአት፣ እንግዳ የሆኑ ሰዎች፣ ቋንቋቸውን ባህላቸውን የማላውቀው ሰዎች፣ ቆዳቸውና ፀጉራቸው ሳይቀር ከኔ የተለየ ሰዎች ጠርተው አበሉኝ። በሀበሾቹ ጓደኞቹ ምክንያት፣ በሰው ልጅ ላይ ያልነበረኝ መተማመን አደረብኝ። ምግብ ብቻ አይደለም የሰጡኝ። ስሙን እኔ እማላውቀው፣ ከምግብ የበለጠ ነገር ነው የሰጡኝ። ሌላ ሰው ሰጥቶኝ እማያውቀው ነገር ነው የሰጡኝ»

አይኖቹ ብርሀን ሞሉ – ብርሀን አይደለም፣ እንባ ነው – የሀዘን እምባ አይደለም፣ ሌላ አይነት እምባ ነው። ወደዚያ አየ። እኔም ወደ ሌላ በኩል አየሁ

ሀበሾቹ እንደዚህ ጥሩ ሰዎች መስለው የታዩት ምንኛ የዋህ ቢሆን ነው? ብዬ አሰብኩ

ከጥቂት ጊዜ በኋላ

«ችግሬን ትከሻህ ላይ ጫንኩብህ፤ ይቅርታ አርግልኝ» አለኝ። ዘወር ብዬ አየሁት። አይኖቹ ውስጥ እንባ የለም

«አታምነኝም ይሆናል» አልኩት «ግን ችግርህን ስላዋየኸኝ ክብር



@BOOKALEM

ይሰማኛል:: ደሞ አይቼው የማላውቅ ጉብዝና ዛሬ አየሁ»

ሳቅ አለ

«አንድ ነገር ልንገርህ» አለኝ «ይሄ ስጋት፣ ፍርሀትና በእዳ ተይዞ ማፈር እየከበደኝ እያስጨነቀኝ ሲሄድ ጊዜ፣ ብቻዬን አልችለውም በማለት ለሰው ልናገረው ሞክሬ ነበር:: ደጋግሜ ሞክሬ ነበር:: ግን ልናገረው አልቻልኩም:: አብዛኛውን ጊዜ ሰሚ አጣለሁ:: የሚሰማኝ ሳገኝ ደሞ ልናገር እንደጀመርኩ እፍረት ይይዘኛል:: መናገሩን እተውቀዋለሁ:: ላንተ መናገር ግን በፍፁም አያሳፍርም:: የማጽናኛ ስጦታ አለህ:: ቄስ ለመሆን አስበህ ታውቃለህ?»

እፍረት ተሰማኝና ሳቅ ስል፣ እሱም ሳቅ እያለ

«ህለላሲ ሙት!» ብሎኝ ተነሳ:: እኔም ተነሳሁ

«Vive l'amitié Irano-Ethiopienne!» አለኝ:: ይስቃል:: («የኢራንና የኢትዮጵያ ጓደኝነት ለዘለአለም ይኑር») አሁን አሁን ያን ሁሉ ችግሩን ሲያወራልኝ እንደነበረ ለማመን አመነታሁ

«Vive!» አልኩት «A bas les Yankees!» («ይኑር! . . . ያንኪዎች ይውደሙ!»)

«A bas!» አለኝ:: («ይውደሙ!»)

ወደ ካፌ ዶርቢቴል በኩል ስንራመድ መንገዳችን ላይ ምናምን ሲለቃቅሙ ከነበሩት ወፋፍራም እርግቦች አንዷን በእግሬ ቃጣሁባት:: አልበረረችም:: እንዲያውም አልዘለለችም:: እንደ ሞጃ ወይዘሮ ደበልበል እያለች ከመንገዳችን ወጣ አለች:: ባህራም

«የከይ ኮስሮ እርግብ ብትሆን ይህን ጊዜ በራ ጠፍታ ነበር» አለ::

«ከይ ኮስሮ?»

«የጥንት የኢራን ሻህ:: አየህ ከይ ኮስሮ በሰረገላ መሄድ ሰለቸው:: በአየር መሄድ አማረው:: የሌላ አገር ንጉስ ቢሆን መብረር እንዳማረው ይቀር ነበር:: ከይ ኮስሮ ግን የኢራን ሻህ-ን-ሻህ ነው:: መብረር ካለኝው መብረሩ አይቀርም:: ስለዚህ አንድ አምስት መቶ ወሮች ሰበሰበና ከአልጋው ጋር አስሯቸው ሲያበቃ፣ በማእረግ አልጋው ላይ ወጥቶ ተጋደመና፣ እንዴ ጅራፉን ሲያስጮህባቸው



@BOOKALEM

ጊዜ ተነስተው በረሩ። ከይ ኮስሮ አሊጋው ላይ እንደ ተቀመጠ ወደላይ ወጣ፣ ግን የልጓሙን ጉዳይ ሳያስብበት ቀርቶ ኖሮ፣ ወፎቹ ወደ ልዩ ልዩ አቅጣጫ መብረር ስለጀመሩ፣ ሩቅ ሳይሄዱ አሊጋው ወደታች መዝኗቸው ወደቁ። ከይ ኮስሮ እግሩን ተሰበረ። ከሚኒስትሮቹ አንድ አምስቱን አስገደለ»

«ለምን?»

«መጀመርያውኑ ተው እንዳትሰበር ብለው ስላልመከሩት። ግን መጀመርያውኑ ተው እንዳትሰበር ቢሉት ኖሮ ደግሞ ያስገድላቸው ነበር»

«ምክንያቱስ?»

«እኔ መብረር ሲያምረኝ፣ ለምናባታችሁ ነጃሳ ቃል ትናገሩኛላችሁ? ብሎ ነዋ!»

«ግሩም ንጉስ ኖሯል!»

«እንዴታ! ተራ ንጉስ መስሎህ ኖሯል እንዴ? የኢራን ሻህ - ን-ሻህ ነው'ኮ»

«እና ከዛስ?»

«ከዛ እግሩ ሲድንለት ሰራዊቱን አስከተተና ወደ ህንድ ዘመተ»

«ከህንድ ጋር ጠብ ኖሯቸኋል?»

«የምን ጠብ? ህንድ መቼ ጠብ ያውቃል?»

«እህ! እንግዲያው ከይ ኮስሮ ለምን ወደ ህንድ ዘመተ?»

«የደምቡን ለማድረስ ነዋ»

«በጭራሽ አልገባኝም»

«ላስረዳህ። በዚያን ዘመን ማንም የኢራን ንጉስ ገንዘብ ሲያስፈልገው ወይም ጉልበቱን ማሳየት ሲያምረው፣ ትንሽ ሰራዊት ይሰበስብና ወደ ህንድ ብቅ ይላል። እንግዲህ ህንዶች ለቡድሀ ወይም ለሺቫ ይሁን፣ ለሌላ አምላክ ይሁን፣ ያለ የሌላቸውን አልማዝ፣ ወርቅ፣ ብር፣ ሉል፣ ምናምን ቤተ መቅደስ ውስጥ ያከማቻሉ። የኢራን ሰራዊት ይመጣና ለደምቡ ያህል - ማለት ጦርነት አርገናል ለማለት ያህል - ጥቂት የህንድ ወታደሮች ገድሎ፣ ሌሎቹን አባሮ፣



@BOOKALEM

ሴቶቹን ትንሽ ተደስቶባቸው ሲያበቃ፣ ቤተ መቅደሱ ውስጥ የተከማቸለትን ሀብት ተሸክሞ ወደ አገሩ በሰላም ይመለሳል

«ማንም ሻሁ-ን-ሻህ በዘመነ መንግስቱ አንድ ጥያቄ ይገጥመዋል:: ይኸውም፣ የኢራንን ህዝብ አዲስ ግብር ማስከፈል ይቀላል፣ ወይስ አንድ ሁለት ሺ ወታደር አስከትሎ ህንድ አገር ደርሶ መመለስ ይቀላል? የሚል ጥያቄ ነው:: አንዳንድ ነገስታት አሉ፣ የኢራን ታሪክ የሚያስታውሳቸው ህንድ አገር ባለመዝመታቸው ነው»

እንደዚህ እየቀለደ ካፌ ዶርቢቴል ደረስን:: ሀበሾቹ አሁንም ካርታ ጨዋታቸውን ይዘዋል:: ባህራም እንደልማዱ

«እስቀያሚ! ሽርሙጣ! ሀላለሴ ሙት! Je veux jouer aux cartes!» እያለ መሀላቸው ቁጭ አለ:: (ካርታ አጫውቱኝ)

እንደ ወጣት ረኸም ባህር ዛፍ ሆኖ ታየኝ - የመከራ ነፋስ ይነፍሳል፣ ባህራም ይታጠፋል፣ መሬት እስኪነካ ይታጠፋል፣ ግን አይሰበርም፣ ተመልሶ ቀጥ ይላል፣ እስከሚቀጥለው ነፋስ ድረስ . . .

. . . በስንት ጭቅጭቅ ጋዜጣዬን ከተካ ተቀብዬ ወደ ሲልቪ ቤት ሄድኩ

ባህራም የነገረኝን ሁሉ አጫወትኳት:: ለረዥም ጊዜ ዝም ብላ ከቆየች በኋላ

«ይገርምሀል:: እኔ'ኮ gigolo ይመስለኝ ነበር» አለችኝ

«ዢጎሎ? ምንድነው እሱ?» አልኳት

«ዢጎሎ አታውቅም? ገና አልሰለጠንክማ!»

«እኮ ምንድነው እሱ?»

«ሴቶችን እያስደሰተ ገንዘብ የሚቀበል ወንድ ነው»

«ታድያ ባህራም ምኑ ያምራልና ዢጎሎ ይሆናል?» አልኳት

«አያምርም:: ግን ከሚያምሩ ወንዶች ይበልጥ ደስ ይላል»

«አይ! እንግዲህ ወሬ እንለውጥ»

«እሺ:: ግን እሱ የነገረህን ሁሉ ባታምን ይሻላል»

«ለምን?»



@BOOKALEM

«በውጪው አሪፍ ውሸታም እንደሆንስ?»

«ይመስልሃል?»

«ይመስለኛል»

«እኔ ግን አይመስለኝም»

«እስቲ እናያለን» አለችኝ

እንዲህ በማለቷ በሸቅኩ። ግን መብሸቁን አላሳየኋትም።



@BOOKALEM

# አምስት

## ሲልቪ
## ውስጥ ውስጡን

በነጋታው ሟት የመኝታዬ በር በኃይል ሲንኳኳ ነቃሁ:: ማነህ ሳልል በሩን ከፈትኩ:: ሲልቪ እየሳቀች ዘላ ተጠመጠመችብኝ:: ተንገዳግደን አልጋዬ ላይ ወደቅን:: የፀጉሯ ሽታ ደስ አለኝ

«ዛሬ ምን ሆነሻል?» አልኳት

«ፈተናዬን በማእረግ አለፍኩ:: ተነስ እንሂድ»

«የት?»

«ፓሪስ:: ቀጥሎ ጄኖቫ፣ ከዚያ ሮማ፣ ናፖሊ፣ ፊሬንዜ፣ ከዚያ ኒስ፣ ማርሰይ፣ ኤክስ:: ፕላኑን በሙሉ አውጥቻለሁ:: ጎበዝ አደለሁም?»

«ጎበዝ ነሽ:: መቼ ነው 'ምንሄደው?»

«አሁኑኑ:: ተነስ ተጣጠብ» አለችኝ፣ በሰፊ አፏ እየሳቀች

«ለባለሆቴሉ 'ምከፍለው ገንዘብ አልያዝኩማ»

«እኔ ይገባለሁ»

«በምንድነው 'ምንሄደው?»

«በባቡር:: ባቡራችን ልክ ከዘጠና ሁለት ደቂቃ በኋላ ከማርሰይ ይነሳል:: ቶሎ በል»

እንደዚህ አጣድፋ፣ ማንንም ለመሰናበት ሳልችል ፓሪስ ወሰደችኝ:: ከሁሉ ቅር ያሰኘኝ አማንዳ ዱቤን ሳልሰናበት መሄዴ



@BOOKALEM

ነበር ስለጫወት ቀናቸው አስር ሳምንት ውስጥ ስለባህሪዋ በብዙ

በሚቀጥለው አስር ሳምንት ውስጥ ስለባህሪዋ በብዙ ነገር በብዙ አላሰብኩም:: ሀሳቤን ሲልቪ አላሰብኩም:: ስለ ምንም ነገር በብዙ አላሰብኩም:: ሀሳቤን ሲልቪ ሞልታው ነበር

ባቡሩ ሞልቶ ቆይቶን አንድ ላይ ቦታ ለማግኘት ባለመቻላችን ፊት ለፊቴ ተቀመጠች:: ሁለታችንም መፅሀፍ ማንበብ ጀመርን:: ረዥምና ወተት ነጭ ፊቷን ትንሽ አነብና ሰርቄ አያታለሁ:: ረዥምም ፀጉሯ ውብ ነጭ ፊቷን እንደ ጥቁር ሀር ከቦታል:: በጣም ቆንጆ ናት፣ የደስ ደስ አላት:: እንዳንድ ጊዜ ሳያት ትይዘኛለች:: ትጠቅሰኝና ሳቅ ትላለች:: መልሼ እጠቅሳታለሁ:: ንባባችንን እንቀጥላለን:: አልፎ አልፎ እንድ ያልገባኝን ቃል እጠይቃታለሁ:: ፈረንሳዮቹ ብርቱካን ይበላሉ፣ ያወራሉ፣ ፖም ይበላሉ፣ ጋዜጣ ያነባሉ፣ ሳንድዊች ይበላሉ፣ ወይን ይጠጣሉ፣ ባቡሩን ያዝረከርኩታል፣ ያቆሽሹታል፣ ዝነኛውን «የፈረንሳይ ባቡር ግማት» ይሰጡታል

አቪኞን ስንደርስ አንዲት አሮጊት ከአጠገቤ ተነሳችና፣ ገና ከመነሳቷ ቦታዋ ላይ አንድ ሰውዬ ተቀመጠ:: ከአቪኞን እንደወጣን የሲልቪ አይኖች ደጋግመው እዚህ ሰውዬ ላይ ያርፉ ጀመር:: ሰውዬውን አየሁት:: ፀጉሩ ላይ ነጭ ዘርቶበታል፣ ምናልባት ያርባ አምስት አመት ሰው ይሆናል:: አይኖቹ ንፁህ ሰማያዊ ሆነው፣ ቀጠን ያለ ፊቱ በጣም ቆንጆ ነው:: ሳየው ጠላሁት:: ንባቤን ቀጠልኩ፣ ግን የማነበው ሊገባኝ አልቻለም:: ሰርቄ ሲልቪን አየኋት:: ሰውዬውን በሰማያዊ አይኖቿ ብርሀን ታየዋለች:: እሷ እሱን ስታይ፣ እኔ እሷን ሳይ፣ ንዴቱ ውስጤ ሲጠራቀም፣ ብዙ ጊዜ ሄድን

ሳያት ያዘችኝ:: አይኖቿ ተርገበገቡ፣ ወደ ታች አየች፣ ጉንጮቿ ደም ለበሱ:: ማማሯ! የንዴቴን ጥቁር ደመና የፍትወት ብልጭታ ሲሰነጣጥቀው ተሰማኝ:: «ድንገት ሳብ አድርጌ ቀሚሷን ገልቤ ጭኖቿን ፈልቅቄ - - -»

በመስኮቱ ወደ ውጭ ማየት ጀመርኩ:: ለጥ ያለ ሜዳ መሬት ወደኋላ ይኅርፋል:: ከሩቅ አንድ መንደር ይታየኛል፣ መሀሉ የቆመ ረዥም ቀጭን የቤተ ክርስቲያን ደወል-ቤት ሰማዩን እንደ መርፌ ወግቶታል፣ አንድ ቀጭን መንገድ ከሹሉ ደወል ቤት ስር ወጥቶ እየተጠማዘዘ ሄዶ እድማሱ ውስጥ ገብቷል፣ ሰማይና ምድር የተሰፋበት ክር ይመስላል:: መንደሩ እንደ ልጅነት ቀስ እያለ ወደ

ኋላ እየተንሸራተተ ጠፋ

ዘወር ብዬ ሲልቪን አየኋት፡፡ ራሷን ወደ መፅሀፉ ደፍታለች፣ ፊቷ ደም እንደለበሰ ነው፡፡ መፅሀፌን ማንበብ ጀመርኩ፡፡ አሁንም ቃላቱ አይኔን ዘልቆ አንጎሊ ውስጥ መግባት አቅቶት፣ አይኔ ብቻውን ያነባል፡፡ ሲልቪን አየኋት፡፡ አየችኝና ፈገግ አለች፡፡ ሰማያዊ አይኖቿ ሳቂታ ናቸው፡ በጣም ቆንጆ ፈገግታ አላቸው፡፡ እናቷን!

ንባቤን ቀጠልኩ፡፡ ከዚያ በኋላ እንደገና ደጋግሜ ስታየው አየኋት፡፡ አንድ ሶስት ጊዜ ያህል፡ ስታየው እንዳየኋት አይታ በጣም አፈረች፡ አይኖቿ ተርገበገቡ፣ ጉንጮቿ ቀሉ፡ ንዴቴና ምኞቴ ውስጤ እየታገሉ አስጨነቁኝ

ሶስት ሰአት ያህል አለፈ.

ከሊዮን በኋላ አንድ ሁለት ትንንሽ ከተማ እንዳለፍን ሰውየው እግሮቼን የሚዘረጋ አስመስሎ የሲልቪን እግር ነካ፡፡ ቀና ብላ በውብ አይኖቿ ፈገግታ አየችው፡፡ በሰፊ አፏም ሳቅ አለችለት፡፡ ሰውዬው በእግሩ እግሯን ማሻሸት ጀመረ፡፡ ቀላች፡፡ ውስጤ ሲጋዊ ፍትወትና ንዴት ታገለ፣ ንዴቱ አሸነፈ፡፡ እግሬን የምዘረጋ አስመስዬ የሰውዬውን ቅልጥም በኃይል መታሁትና፣ ዘወር ብዬ እያፈጠጥኩ

«Pardon, monsieur» አልኩት («ይቅርታ መስዬ»)

«Je vous en prie» አለኝ («ኧረ ግድ የለም»)

እግሩን ሰበሰበ፡፡ ፊቱ በንዴት ይሁን በእፍረት ደም ለብሷል፡፡ ሲልቪን አየኋት፡፡ መፅሀፏን ታያለች፡ ፈገግታ ብጤ አፏ ዙሪያ ይርበተበታል፡፡ ሰውየው የሲጋራ ፓኮ ከኪሱ አውጥቶ ወደ ሲልቪ ዘረጋ፣ እየሳቀች ተቀበለችው፡፡ አቀጣጠለላት

«ወደ ፓሪስ ነው 'ሚሄዱት?» አለችው

«አዎን ማድሟዜል፡፡ እርስዎስ?» አላት

ወሬ ጀመሩ፡፡ ብሽቅ አልኩ፡፡ ተነስቼ ትቻቸው ወጣሁ

መተላለፊያው ዘንድ አልፎ አልፎ የቆሙትን ፈረንሳዮች እየገፈሁ «Pardon!» እያልኩ፣ አንድ አስር ሰረገላዎች አቋርጬ ሄጄ ባቡሩ መጨረሻ ደረስኩ

ስመለስ ግማሽ መንገድ ላይ ቆምኩ፡፡ «. . . እቺ ንፍጣም!



@BOOKALEM

ሊታስቀናኝ ፈልጋ አይደለም? እንደማልቀና ማወቅ አለባት፡፡ ግማሽ ሰአት እስኪያልፍ ወደሷ አልመለስም፡፡ ምን ያህል ግድ እንደሌለኝ ይግባት. . .»

ግማሽ ሰአት እንዴት ረዥም ነው! ስአቴን አስር ጊዜ አየኋት፡፡ አምስት ደቂቃ እንኳ ገና አላለፈም፡፡ እሷ ታድያ አትንቀሳቀስም፡፡ ወደ ጆሮዬ አስጠጋኋት፡፡ ተኝታለች፡፡ የለም የለም፣ የባቡሩ ጩኸት ድምፅዋን አላሰማ ስላለኝ ነው፡፡ . . . እኔና ሰአቷ ስንተያይ ሩብ ሰአት አለፈ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን መቆየት አልቻልኩም፡፡ ሰዎቹን እየገፋሁ «Pardon!» እያልኩ ወደነዚያ ውሾች መመለስ እንደ ጀመርኩ፣ በመስኮቶቹ በኩል ቤቶች ብቅ እያሉ ወደኋላ ሽው ብለው ሲያልፉ ይታዩኝ ጀመር፡፡ አንድ ትንሽ ከተማ ደርሰናል፡፡ ባቡሩ በቆመልኝ! ማቆያ እንዲሆነኝ ጋዜጣ እገዛ ነበር. . . ጎሽ! ባቡሩ ቆመ፡፡ ወረድ ስል አንድ መለዮ የለበሰ የባቡሩ ኩባንያ ሰራተኛ «መስዬ፣ አይውረዱ፣ ሁለት ደቂቃ ብቻ ነው ያለን» አለኝ

«Je m'en fous!» አልኩትና ወረድኩ («ደንታ የለኝም!»)

አንድ Le Monde ጋዜጣና ሁለት ሳንድዊች ገዝቼ እስክመለስ ባቡሩ ተነሳ፡፡ ሮጬ ለትንሽ ደረስኩበት፡፡ «. . . ጋዜጣውን እንብቤ ሳልጨርስ ወደሷ አልመለስም፡፡ ሳገኛት ደሞ ሳንድዊች እሰጣታለሁ፡፡ እየሳቅኩ፡፡ ጭራሽ አለመቅናቴ እንዲገባት. . .» ጋዜጣው ውስጥ የክሩስቼቭና የኬነዲ የቤንቤላ ስም አለ፤ የቪየትናምም ሁኔታ ተጠቅሷል፣ ግን በደምብ አልገባኝም፤ የሲልቪ ፈገግታ፣ ለሌላ ያበራችው ፈገግታ አንጎሌን በጥብጦታል፡፡ የሆነ ሆኖ፣ ያልኩት ግማሽ ሰአት አለፈልኝ፡፡ ኧረ ሰላሳ ሶስት ደቂቃ ነው ያለፈው! እኔ የሰውዬው ልጅ! . . . ወደኛ ሰረገላ አመራሁ

ሲልቪ የለችም፡፡ ሰውዬውም የለም፡፡ ሁለቱም የሉም፡፡ የታባታቸውን ሄዱ? እንደገና ፈረንሳዮቹን እየገፋሁ «Pardon!» እያልኩ አንድ አምስት ሰረገላ ካቋረጥኩ በኋላ፣ ራሴን «የት ነው ምትሄደው?» አልኩት፡፡

ቆምኩ «በቁላህ ሳይሆን በጭንቅላትህ አስብ» የሚል ሀሳብ ውስጡን አሳቀኝ፡፡ ለመሆኑ፣ ባገኛቸውስ ምን ላደርጋቸው ኖሯል? ብዬ አሰብኩ፡፡ ተመልሼ ቦታዬ ቁጭ ብዬ ልጠብቃቸው ቆረጥኩ፡፡

«እቺ ውሻ! ከኢክስ አጣድፋ ያመጣችኝ ለዚህ ኖሯል? ማን



@BOOKALEM

መስያታለሁ!? ፈረንሳይ መስያታለሁ? አበሻ መሆኔን ማን በነገራት! ቆይ አሳያታለሁ! - - - ግን አልቸኩል:: ዝግ ብዬ ረጋ ብዬ ላስብ:: እንደ ልጅ መጮህ መፍጨርጨር አያስፈልግም. . . እሷ አሁን አስቀናሁት ብላለች:: እስቲ ማን ማንን እንደሚያስቀና እናያለን:: እቺ ቅሊታም ፈረንሳይ!. . . ዋናው ነገር፣ አሁን እንዳልቀናሁ ማሳየት ነው:: ስትመጣ ልክ እንደ ድሮ አናግራታለሁ:: ልክ ባለሽበቱን ሰውዬ እንዳላየሁት መሆን አለብኝ:: . . . ሌላ ቀን ታድያ፣ ከሁለት ወይ ሶስት ሳምንት በኋላ፣ መኖር እስኪያስጠላት ድረስ አስቀናታለሁ:: ያኔ እናያለን. . .»

እንዲህ የበቀል ሀሳብ እያሰላሰልኩ ወደ ቦታዬ በኩል ስራመድ፣ መመላለሻው ዘንድ እያጨሱ፣ እያወሩ ወይም ፈዘው በመስኮቶቹ በኩል ወደ ውጭ እየተመለከቱ ከቆሙት ሰዎች አንዱ ከሩቅ ስመጣ ጀምሮ ያየኛል

ፀጉሩ ላይ ሽበት ዘርቶበታል፣ ፊቱ ቀጭን ቆንጆ ብጤ ነው:: አይኑ ሰማያዊ ባይሆንም ሽበቱና የቆንጆ ፊቱ መቅጠን አበሸቀኝ:: አጠገቡ እስክደርስ በብሩህ ቡናማ አይኖቹ ያየኛል:: እየገላመጥኩት

«ምነው ያዩኛል?» አልኩት:: እንደ መደንገጥ ብሎ

«ምንም መስየ» አለኝ

«ፀጉርዎ አስር ጊዜ ሽበት ቢኖረው je m'en fous!» አልኩት:: («ደንታ የለኝም»)

ስለምን እንደማወራ አልገባውም፣ ግን ፈርቷል:: ዝም አለ:: ሰውዬው ምንም እንዳልበደለኝና አሁን የማወርድበት ቁጣ ፈጽሞ የማይገባ ጭቦ እንደሆነ ይሰማኛል፣ ግን ራሴን ለመግታት አልቻልኩም:: መልኩንና እድሜውን እያየሁ በንዴት ተቃጠልኩ

«በሉ 'ንጂ ይንገሩኝ:: ለምን ያፈጡብኛል? ሰው ሳንድዊች ይዞ ሲሄድ አይተው አያውቁም? ወይስ ርቦዎታል? እንኩ ብሉት!» አልኩና የያዝኩትን ሳንድዊች በድንገት አስጨብጬው ወደ ቦታዬ በኩል በንዴት ስራመድ፣ መተላለፊያው ውስጥ ያሉት ሰዎች ሁሉ በፀጥታ እኔን እንደሚመለከቱ ድንገት ታየኝ:: ንዴቴ ወደ እፍረት ተለወጠ፣ ሽበታሙ ሰውዬ በጣም አሳዘነኝ:: ይኸኔ'ኮ ወጣት ቢሆን አይታገሰኝም ነበር፣ አሁን ወጣትነቱን በህዘንና በናፍቆት ያስታውስ ይሆን? ኧረ ምን በደለኝና ነው ያዋረድኩት? መባለጌ በጣም



@BOOKALEM

ቆጨኝ:: ቀኝ ኋላ ዞሬ ወደሱ ተራመድኩ:: ሳንዲውቾቹ የተጠቀለሉበትን ወረቀት በሁለት እጁ እንደጨበጠ ይመለከተኛል:: ፊቱ ላይ የመደናገር እንጂ የንዴት ስሜት አይታይም

«መስዬ: እባክዎን ይቅርታ ያድርጉልኝ:: ጤና አልያዘኝም» አልኩት:: ታችኛ ከንፈሬ ሲንቀጠቀጥ ተሰማኝ፡ ግን መንቀጥቀጡን ላስተወው አልቻልኩም:: ሲጨንቀኝ ጊዜ አፌን በእጄ ያዝኩት

ረጋ ባለ ድምፅ “Ça va, jeune homme. N'y pensons plus” አለኝ:: («ግድ የለም ጎበዝ:: እንርሳው») “Merci, monsieur” ብዬው ብሄድ ጥሩ ነበር:: ግን አሁንም ራሴን ለመግታት አልቻልኩም:: ሳልወድ በግድ ለፈለፍኩ

«ጤና ስላልያዘኝ ነው እንጂ አገሬ ብሆን፣ እንኳን እኔው ራሴ ሸበት ያለው ሰው ልሰድብ፣ ማንም ወጣት እንዲህ ሲያደርግ ባየው እጣላዋለሁ» አልኩት

«አውቃለሁ» አለኝ

«ያውቃሉ?»

«የናንተን አገሮች ባህል በደምብ አውቀዋለሁ:: ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የአንትሮፖሎጂ ፕሮፌሰር ነኝ:: ደሞ፣ ካደጉበት አገር ወጥቶ እንግዳ አገር ሄዶ፣ ባእድ ህዝብና ባይተዋር ባህል ሲያጋጥም፣ በመጠኑ ግር እንደሚል አውቃለሁ:: ደጋግሜ ካገሬ ወጥቼ አይቼዋለሁ:: ስለዚህ አሁን እኔን ይቅርታ መጠየቅ በጭራሽ አስፈላጊ አይደለም:: ይልቅ ቡና ልጋብዝዎትና ትንሽ እንጫወት» ብሎ ቡና ወደሚጠጣበት ስረገላ ወሰደኝ

ሰውዬው ሊቅ ከመሆኑም በላይ ብልህና ደግ ነበር:: ኮኛክ እየጠጣን ሳንድዊቾቹን በላናቸው

«ከኮኛክ ጋር እንኳ ሳንድዊች አይበላም፤ ብቻ ግድ የለም» አለ ሰውዬው እየሳቀ:: ብዙ ብዙ ወሬ አወራን:: በተለይም ስለአልጄሪያ ጦርነት በሰፊው ነገረኝ:: ጄኔራል ደጉል ባይኖር ኖሮ፣ ይህን ጊዜ ፈረንሳዮች በአልጄሪያው ሁከት ምክንያት እርስ በራሳቸው ተከፋፍለው ተዋግተው ተፋጅተው፣ ፍራንስ ራሷ ገደል ገብታ ነበር አለኝ:: እስከ ፓሪስ እያወራን ብንሄድ ደስታዬ ነበር:: ግን ፕሮፌሰሩ ዲዦን ወራጅ ነበር

ሲለየኝ፣ መውረጃው በር አጠገብ እንደቆምን፣ ሳላስበው እጆቹን

ትከሻዬ ላይ አሳረፈና፣ ደግነት በተሞሉ የአዋቂ አይኖቹ እያየኝ፣ አንቱ ማለቴን ትቶ ለመጀመሪያ ጊዜ አንተ እያለኝ

«ይገርማል፡ ጠቆርክ እንጂ ልክ የመጀመሪያ ልጄን ነው ምትመስለው። እንግዲህ ልጄ ትዝ ባለኝ ቁጥር አስታውስሀለሁ። ትናፍቀኛለህ። Enfin, c'est la vie. Au revoire, jeune homme" («ይኸ ነው የኑሮ ነገር። በል ደህና ሁን፣ ጉበዝ») አለና፡ ፈረንሳዮቹ የሚወዱትን ሰው ሲሰናበቱ እንደሚስሙት ጉንጭና ጉንጩን ሳመኝ። በእጁ ራቅ አድርጎ በናፍቆት አይን አየኝ። ፀጉሬን በእጁ በተን በተን አድርጎ፣ እንደገና ሳብ አድርጉ በኃይል እቅፍ አደረገኝና፣ ከባቡሩ ወረደ። ሻንጣውን ሳቀብለው፣ አይኑ ውስጥ እንባ አየሁ

ባቡሩ ቀስ ብሎ ተነሳ። «ልጄ ትዝ ባለኝ ቁጥር» እንዳለኝ አስታወስኩ

ከባቡሩ በላይ ጮኩኬ

«ልጅዎ የት ነው?» አልኩት

«ሞቷል። አልጄሪያ» አለኝ፣ እጁን የስንብት እያራገበ

እጁን ሳወዛውዝለት፡ ተሰምቶኝ የማያውቅ አይነት ሀዘን ልቤንሞላው። አልቅስ አልቅስ አለኝ። እዚያ ቆሞ እጁን ሲያወዛውዝልኝ፣ እየራቀና እያነሰ ስሄድ፡ በሀይል አሳዘነኝ። በመጨረሻ ከአይኔ ተሰወረ። ምን ያህል እንደወደድኩት ገና አሁን ገባኝ. . .

መሬት መሬቱን እያየሁ፡ ማንንም ሳልገጭ፣ በዝግታ ወደ ቦታዬ ሄጄ ቁጭ አልኩ። በመስኮት ወደ ውጭ እያየሁ በብዙ አዘንኩ። ሲልቪ ደጋግማ ታወሰችኝ፡ ግን ንዴቱ ለቆኛል። ቅድም አሰላስል የነበረው የበቀል ሀሳብ ከንቱ ሆኖ ታየኝ። ምስኪን ሲልቪ! አሁን ምን አጠፋች? ካንዱ ጋር በሳወራች ነው? ታድያ ያገራቸው ባህል ነው። ደሞ ባህላቸው ባይሆንስ ምን አለበት? አሁን ባቡር ውስጥ ምን እንዳያደርጉ ነው?. . . ኧረ የፈለጉትንስ ቢያደርጉ ምን እንዳይቀርብኝ ነው?. . .

ሰዎቹ ሻንጣቸውን ከየተሰቀለበት ማውረድና መተራመስ ጀመሩ። ፓሪስ መድረሳችን ነው። ሲልቪ ከሄደችበት ተመለሰች (ሰውዬው ግን አልመጣም) ሻንጣዋን አወረድኩላት። እንዴት እንደም እንጃ፣ በጣም አሳዘነችኝ። ታናግረኝ ጨንቋታል። ለምን እንደሆነ



@BOOKALEM

እቅፌ እይዞሽ ሌላት ፈለግኩ። ግን ጊዜውም ቦታውም አይፈቅድም

«በሀይል ርቦኛል። አልራበሽም?» አልኳት እየሳቅኩ። ፆ ባዶ ፊቱ ላይ ምን እንደሚመስል ብቻ እግዜር ይወቀው

«አዎን፣ በሀይል ርቦኛል» አለች

«ነይ፣ እራትሽን ሳብላሽ» አልኳት

ከበርግ ማብያው ትርምስምስ ወጥተን፣ እዚያው አጠገብ እንዳ ከፍል ተከራይተን፣ ገላችንን ያረጀ ብጤ ሆቴል ውስጥ አንድ ርካሽ ብጤ ምግብ ቤት ውስጥ ገቡ ታጥበን፣ እዚያው ሰፈር አንድ ርካሽ ብጤ ምግብ ቤት ውስጥ ገባ እራት በላን። ከሶስት ጠርሙስ ቀይ ወይንና፣ ከብዙ ብዙ ወሬ በኋላ፣ ሁለታችንም በጣም ሞቅ ብሎን ሳለ፣ እጇን ይዛ በቀንጆ ስሟያዊ አይኖቿ እያየችኝ

«ትፈልገኛለህ?» አለችኝ። የቀኑ ንዴት አሁንም ልቤ ውስጥ አንድ ጊዜ ተግላበጠ። ግን በጭራሽ እንዳልተበሳጨሁ ማስመሰል አለብኝ በማለት፣ ጥቁር ፀጉሯን እየዳበስኩ

«በሀይል በሀይል እፈልግሻለሁ» አልኳት። እውነቴን ነበር።

«ና ቶሎ እንሂድ» አለችኝ

እንግዲህ እኔና ሲልቪ ስንተቃቀፍ በመብራት እየተያየን፣ እያወራን፣ እየሳቅን ነው። ዛሬ ግን አልጋ ውስጥ ስንገባ መብራቱን አጠፋችው፣ በጭለማው ስታቅፈኝ ያለልማዷ ቸኮለች፣ ተንገበገበች። አንድ ቃል አልተናገረችም። በጭለማው እየሳመችኝ ማቃሰት ብቻ ሆነ። ደስታው መሀል ላይ እንደደረስን፣ ያለልማዷ ከንፈሬን ነክሳ አሳበጠችኝ። ጠረኗ ብቻ የራሷ ሆነ እንጂ፣ እግር እንሳሷ ሳይቀር ተለወጠብኝ፣ በጠቅላላው ከሌላ ሴት ጋር እንደመተኛት ያህል ነበር። መጨረሻ ላይ፣ በሀይል እየተንቀጠቀጠች፣ ፊቷን እንገቴ ውስጥ ቀብራ

«Oh, pitié, monsieur! Pitié! Pitié!» እያለች አጉረመረመች። («አይ! ይማሩኝ፣ እባክዎን ይማሩኝ! ይማሩኝ!»)

ከጨረስን በኋላ ማልቀስ ጀመረች። ከዚህ በፊት አልቅሳ አታውቅም። ተመስገን ሲያስጠነቅቀኝ፣ እንዳንዴ ነገሩ ካለቀ በኋላ ቃኮርፋለች፣ ታለቅሳለች ያለኝን አስታወስኩ

«አይዞሽ የኔ ቆንጆ፣ ምን ሆንሻል?» እያልኩ ሳቅፋት



@BOOKALEM

«አይ ውርደት! እንዴት ነው ያፈርኩት!» እያለች ለቅሶዋን ቀጠለች

አሳዘነችኝ:: ተጨነቅኩላት:: እቅፍ እያደረግኳት

«ምንድነው የኔ ሲልቪ? ንገሪኝ:: ሰው አዋርዶሽ እንደሆነ እረግጠዋለሁ»

«እኔው ነኝ እንጂ የተዋረድኩት:: እኔው ራሴ!»

«ንገሪኝ:: ይኸኔ ባልሆነ ነገር ነው 'ምታለቅሺው:: ንገሪኝ 'ስቲ»

«ትወደኛለህ?»

«በሙሉ ልቤ»

«ከበሽታዬ አስጥለኝ!»

«የምን በሽታ?»

«ታስጥለኛለህ?»

«ከቻልኩ»

«ትችላለህ:: ትችላለህ»

«እንግዲያው ንገሪኝ»

«እምቢ ያልከኝ እንደሆንስ? የከዳኸኝ 'ንደሆንስ? ሞት ይሻለኛል»

«ሞኝ አትሁኚ:: እኔ እንዴት አንቺን ልከዳሽ እችላለሁ? የማይሆን ነገር ነው»

«መጥፎ ብሆንም?»

«ሴጣን ብትሆኚም እወድሻለሁ:: ንገሪኝ፣ ምን ሆነሻል?»

«አሁን ካንተ ጋር አይደለም የተኛሁት» አለችና ድንገት ለቅሶዋን አቆመች:: ጭለማው ውስጥ ሙሉ ፀጥታ ሆነ:: መተንፈስም አቁማለች::

በጭራሽ አልገባኝም:: ንግግሯን ትቀጥላለች ብዬ ነበር፣ ግን ዝም ስትል ጊዜ

«ምን ማለትሽ ነው? አልገባኝም» አልኳት



@BOOKALEM

በሹክሹክታ

«አሁን አንተ ነህ የተኛኸኝ:: በሀሳቤ ግን ሌላ ሰው ነበር የተኛኝ:: በጭለማው አንተ እያቀፍከኝ፣ ሌላ ሰው ሲያቅፈኝና ሲስመኝ ነበር የሚታየኝ:: ገላዬን የሰጠሁት ለሌላ ሰው ነበር»

ስካሬ ባንዳፍታ ጠፋ

«ለዚህ ነው መብራቱን ያጠፋሽው?» አልኳት::

«አዎን»

«አሁን እናብራው?»

«የለም እፈራለሁ:: አሁን አይንህን ማየት አልችልም» ብላ ተጠመጠመችብኝ

«እሺ ይቅር:: አይዞሽ፣ አይዞሽ. . . ግን እኔን ማፈርሽ ቂልነት ነው:: ይልቅ አስረጂኝ»

«እኔም ለራሴ አይገባኝማ!»

«ምስጢሩን አስረጂኝ ማለቴ አይደለም:: አሁን ለምሳሌ ስንተቃቀፍ ሳለን፣ በሀሳብሽ ውስጥ ምን ምን ተደረገ?. . . ንገሪኝ አይዞሽ፣ የኔ ሲልቪ»

«ያው ያደረግነው ነገር ነው የተደረገውስ:: ብቻ. . .»

«ብቻ?»

«ሰውዬው አንተ አልነበርክም»

«ማን ነበር?»

አፍራ ዝም አለች

«ያ ባቡር ውስጥ የነበረው ሽበታም ሰውዬ ነው?»

በሹክሹክታ

«አዎን:: አባክህን ይቅርታ አድርግልኝ:: ወድጄ አይደለም» አለችኝ:: ምንም ቅናት አልተሰማኝም:: ሲጋዬ ሲጋዋን ስለጠገበው ይሆን?

በጭለማው ከጉኔ አስነስቼ እላዬ ላይ አስተኛኋትና፣ ባንድ እጄ

ጀርባዋን፣ በሌላው እጄ ፀጉሯንና አንገቷን እያሻሸሁና አይኗን እየሳምኩ

«አሁን ምን ይሰማሻል?» አልኳት

«እንደምትወደኝ ይሰማኛል»

«አውቀሻል:: እንግዲህ ይትርታ ምናምኑን እርሺውና፣ ስለዚህ ነገር የተቻለሽን ያህል ግለጪልኝ»

«እሺ:: በመጀመሪያ ሰውዬን ሳየው ትንሽ ደስ አለኝ»

እየሳቅኩ፣

«ውሸታም! በሀይል ነው ደስ ያለሽ» አልኳት

እሷም እየሳቀችና በሀይል እያቀፈችኝ

«እቤት እንዴት ነው 'ምወድህ! እባክህን አግባኝ! አውቃለሁ አውቃለሁ:: አገርህ እሎኛ አለችህ:: ደሞ ባትኖርህም ጥቁርና ነጭ ቢጋባ ትርፉ ብስጭት ነው:: አውቃለሁ:: ጋብቻውን እንርሳው»

«ንገሪኝ»

«ሰውዬው ደስ አለኝ»

«ስጋዊ ምኞት አሳደረብሽ»

«አዎን:: በሀይል ተመኘሁት:: ግን. . .»

«ግን ምን?»

«እሱ ራሱ በስጋው እንዲገናኘኝ አልፈለግኩም»

«እንግዲያውስ?»

«አንተ እሱን ሆነህ እንድትተኛኝ ነው የፈለግኩት»

«ትንሽ አብራሪልኝ»

«እሱ ነው ያማረኝ:: ግን እሱ ራሱ ቢገናኘኝ አልፈቅድም:: አንተ ብትተኛኝ ነው 'ምፈቅደው:: ግን አንተ ስትተኛኝ አንተን ሆነህ አይደለም፣ እሱን ሆነህ ነው:: የሱ ገላ ነህ»

«እሱ በገላዬ እንዲያቅፍሽ ነው 'ምትፈልጊው?»



@BOOKALEM

«አውቀሀል»

«ነገሩን ብናለዋውጠውስ?»

«እንዴት?»

«እሱ የኔ እንደራሴ ቢሆንና፣ የሱን ገላ እያቀፍሽ ስለኔ ብታስቢ»

«በጭራሽ አይሆንም»

«እሺ ቀጥይ»

ቀጠለች:: ግን ምንም ሌላ አዲስ ነገር አልነገረችኝም:: ያው ነበር:: አንድ ወንድ ያማራት ጊዜ፣ እሱ ራሱ ከሚተኛት ይልቅ ስለሱ እያሰበች ሌላ ወንድ ቢተኛት ትመርጣለች

ገረመኝ:: ግን ሊገባኝ አልቻለም::

ሁለት ሰአት ያህል ከተወያየንበት በኋላ እንደገና ሞቅ አለኝና ጭኗን ማሻሸት፣ ሰፊ አፏን መሳም ጀመርኩ:: አሁንም ያለ ልማዷ ተንገበገበች፣ በብዙ አቃሰተች፣ ጀርባዬ እስኪደማ ድረስ ቧጨረችኝ፣ ስትጨርስ እየተንቀጠቀጠች፣ «Ah, vous alors! Quel homme!» እያለች አጉረመረመች:: («አይ አንቱ! አይ ወንድ!»)

ከኔ ጋር እንዳልሆነች እያወቅኩ ውስጥ ውስጡን ተቃጠልኩ፣ የኔን ገላ ተውሶ ሌላ ሰው እንደተኛት እያወቅኩ ውስጥ ውስጡን ጦፍኩ:: ግን የሴት ገላ እንደዚያን ቀን ልቤን አጥፍቶኝ አያውቅም:: በነጋታው አያለሁ፣ ለካ ሳይታወቀኝ አንገቷን ሶስት ቦታ ነክሼያት ኖሯል:: ለሚቀጥሉት አምስት ቀናት ረዥም አንገቷ ዙሪያ ሻሽ ጠምጥማ መዞር ግድ ሆነባት:: ለጌጥ የለበሰችው ይመስል ነበር

በዚህ አኳኋን ከቅናት ጋር ተዋወቅኩ:: ግን ቅናት ምን አይነት ግሩም ስሜት መሆኑን ለመገንዘብ ብዙ ሳምንት ወሰደብኝ. . .

በነጋታው ሲልቪ ቤቶቿ ዘንድ ዋለች፣ እኔ ፓሪስን በአቶቡስና በእግር ስዞር ዋልኩ:: ማታ ሆቴላችን ተገናኘን:: ሁለታችንም ደክሞን ስለነበረ፣ አልጋ ውስጥ እንደገባን እንቅልፍ ወሰደን:: ሲነጋ ተነስተን ቁርስ በልተን ፓሪስን ዞርን:: ምሳ በልተን ፓሪስን ዞርን:: እራት በልተን ፓሪስን ዞርን:: አያልቅም የፓሪስ ውበትና የሲልቪ ሳቅ ጨዋታ:: ከሌሊቱ በስምንት ሰአት ሆቴላችን ተመለስን:: ስንተኛ

«ፓሪስ እንዴት ቆንጆ ናት!» አልኳት

«ይገርምሀል:: ባንተ አይን ሳየው ጊዜ ሌላ ፓሪስ አየሁ:: ነገም ስንዞር እንዋል?»

«አመት ሙሉ እንዞር ብትይኝ ደስ ይለኛል»

«አንድ ሳምንት ብቻ ነው 'ምንዞረው:: ከዚያ የት እንደምንሄድ ታውቃለህ?»

«የት?»

«ጄኖቫ:: የክሪስቶፎ ኮሎምቦ ከተማ»

«እኔ አንድ ሺ ፍራንክ ብቻ ነው ያለኝ ልብ አርጊ»

«ግድ የለህም:: እኔ ሁለት ሺ አምስት መቶ አለኝ»

«እሺ እንግዲያው»

«አሁን እቀፈኝ»

የድሮዋ ሳቂታ ሲልቪ ናት:: ከትላንት ወዲያ ሌሊት የነበረውን ማቃሰት፣ ማልቀስና መናከስ አሁን ሳስበው ህልም መስሎ ተሰማኝ:: እሷም ፊዕማ የረሳችው ትመስላለች:: ብቻ ሳላውቅ አንገቷን የነካሗት እንደሆነ «አይ!» ትላለች፣ ሁለታችንም እናስታውሳለን

ሮማ ከመሄዳችን በፊት ጄኖቫ ሶስት ቀን አደርን:: ሁለተኛውን ሌሊት በተለይ አስታውሳለሁ:: እራት ከበላን በኋላ፣ አንድ ሲጋራ የማይሸጥበት ቡና ቤት ገብተን ስናወራ ቆይተን፣ ሲጋራዋ ስላለቀባት ልገዛላት ወጣሁ

ስመለስ ከአንድ ረዥም ብሎንድ (ባለ ነጭ ፀጉር) ጎረምሳ ጋር ትተያያለች:: እሱ ቡና የሚቀዳበትን ባንኮኒ ተደግፎ ቆሞ ያያታል፤ ጥብቅ ያለ ጂንስ ሱሪና እጅጌው አጭር የሆነ ነጭ ሸሚዝ ለብሷል:: እሷ ጠረጴዛችን ጋ ቁጭ እንዳለች ሽቅብ ታየዋለች፤ ውብ አይኖቿ ፊቱና ገላው ላይ ይንከራተታሉ:: ትንሽ ከተያዩ በኋላ ሳቅ አለች፤ ጉልህ አይኖቿና ሰፊ አፏ የምኞት እስክስታ ይወርዳሉ - ማማር! አይኔን አንዴ ወደ ጎረምሳው ጣል አደረግኩ፤ ጥርሱን ሳያሳይ ነው ፈገግታ የሚልክላት:: እሷን አየኋት፤ ቀያይ ከንፈሮቿን ለመግጠም ትሞክራለች፤ ፈገግታው ግን ሊፈለቅቃቸው ይፈልጋል፤ ታዲያ



@BOOKALEM

ይርበተበታሉ:: (ምኞቱ ሲያሳብጠኝ ከናፍሯ በሚያስጎመጅ አኳኋን ከፍርሀት ጋር ነው፣ ምክንያቱም የተመኘኋት ቆንጆ ተብሜን፣ ታድያ ከፍርሀት ጋር ነው፣ ሰውየውን ስትመኘው ስላየኋትም ነው፡፡ ስለሆነች ብቻ ሳይሆን፣ ሰውየውን ስትመኘው ስላየኋትም ነው፡፡ ነው?)

ድንገት እጇ ወደ አንገቷ ሄደ:: ያን ጊዜ የነከሰኳትን አስታወስኩ:: ፊቷ ቀስ ብሎ ደም ለበሰ፡ አይኖቿ ተርገበገቡ፡ የሰውየውን አይን ለመሸሽ ወደኔ በኩል አየች - ከኔ ጋር አይን ለአይን ተጋጠምን!

ቅናቱ ደረቴን ያሳምመኛል፡ ግን ምንም እንዳላስተዋልኩ ያህል (አሁን አሁን ከውጭ እንደመጣሁ አስመስዬ) ወደሷ ሄድኩና ተቀመጥኩ:: ሰውየው ወደ ጓላዬ ሆነ:: ሲጋራ እያቀጣጠለች

«ስንት ሰአት ነው?» አለችኝ «አምስት ተኩል::»

«እንደ መድከም ብሎኛል:: ሄደን አልጋ ውስጥ ተጋድመን እናውራ?» አለችኝ:: ገብቶኛል:: እሺ አልኳት:: ስንሄድ ቃል አልተናገርንም:: የክፍላችንን በር ቆለፍኩት፣ መብራቱን አጠፋችው:: በፀጥታ ልብሳችንን አወለቅን፡ አልጋ ውስጥ ገባን፣ ተቃቀፍን:: እንደ አንድ ቀኑ ሌሊት ተንገበገበች፡ ስስማት አፌ ውስጥ እያቃሰተች ጭኖቿን ከመጠን በላይ ፍርክክ አድርጋ አቀፈችኝ፡ ደምበኛው ፍቅር ሳይሆን፣ ቆሻሻ ብልግና የምንሰራ መስሎ ተሰማኝ:: የባሰ ቆሻሻ እንዲሆን አማረኝ፡ ጭኖቿን የባሰውን በለቀቀኋቸው:: ወደ መጨረሻው ልንደርስ ስንል ወፈፍ አደረጋት፡ በሚያስደነግጥ፣ በሚያስቀነዝር ሹክሹክታ «አፌ ውስጥ ይትፉ!» አለችና፡ መላ አፉን ጎርሳ እስኪያመኝ ድረስ ጠባችው. . . «ኡ! ገደልከኝ!» ስትለኝ ነቃሁ - ለካ እኔም ወፈፍ አርጉኝ ያለሁበትን ረስቼ፣ በሀይል አቅፌ ይገርያት መተንፈስ ተስኗታል:: ለቀቅ አደረግኳት:: ቁና ቁና መተንፈስ ጀመረች፡ እኔም ቁና መተንፈስ ጀመርኩ፡ ሁለታችንም በላብ ታጥበናል:: በጭለማው ከግርጌ ፎጣ ሳብኩና ግምባሯን፣ መሀል ጡቶቿን፣ ብብቶቿንና ሆዷን አደረቅኩላት፡ «Merci,» ብላ ፎጣውን ተቀበለችኝ፣ እኔንም አደረቀችኝ

ያን ጊዜውኑ እንቅልፍ ወሰደን

* * *

ፈረንዚ ውብ ከተማ ናት፣ የነዳንቴ የነሚኬላንጀሎ ከተማ!



@BOOKALEM

እንዲት ትንሽ ሬስቶራንት ውስጥ እራት ስንበላ ነበር:: ሲልቪ ምግቧን ረስታ ወደ ኋላዬ በኩል ትኩር ብላ ማየት ጀመረች:: ሳይታወቃት በግራ እጇ ፀጉሯን አስተካከለች - ብቻ መስተካከል አያስፈልገውም ነበር:: ገባኝ:: የምትንመጀው ወንድ አይታ መሆን አለበት:: ሹካና ቢላዋን ቁጭ አድርጋ ወይን እንስታ ፉት አለችና፣ ብርጭቆውን መልሳ እንደማስተመት፣ በእጆቿ ውስጥ በዝግታ እያሽከረከረችው ወደዚያው ወደ ኋላዬ ማየቷን ቀጠለች:: ቀይ ከንፈሮቿ ገርበብ፣ በወይን ረጠብ ብለው ያስጎመጃሉ

እሷ ወደዚያ ስታይ እኔ እሷን ስመለከት፣ ቀንጆ ፊቷ ቀስ ብሎ ፈገግ አለ፡ ስማያዊ አይኖቿ ስልምልም ማለት ጀመሩ:: ምኞቱ ውስጤ ሲያድግ ተሰማኝ:: አይኖቿ ከአይኖቼ ጋር ተጋጠሙ፣ ፊቷ መቅላት ጀመረ፡ አይኖቿ ተርገበገቡ:: ሰውየው ማን እንደሆነ ማወቅ ፈለግኩ፡ ግን ወደኋላ ከተገላመጥኩ ነገሩ ይበላሻል፣ ስለዚህ ተውኩት

«ፍሬ ይምጣልሽ?» አልኳት

«የለም በቃኝ:: አንተ ብላ»

«እኔም በቅቶኛል»

«እንግዲያው እንሂድ?» አለችኝ፣ ወደ ቅድሙ በኩል እያየች

ስንወጣ እሷ ታተኩርበት ወደነበረው በኩል ተመለከትኩ:: በየጠረጴዛው የተበታተኑ አንድ አምስት ወንዶች አሉ፡ የትኛው ፍላጎቷን እንደ ቀሰቀሰ ለማወቅ አልቻልኩም:: ግን ፍላጎቷ በሀይል ተቀስቅሷል:: አልጋ ውስጥ ስንገባ መብራቱን አጠፋችው፡ እየተንገበገበች አቀፈችኝ፡ በመጨረሻ ላይ በእንግሊዝኛ ቃዠች

«Please, my lord! Please, have mercy!»

ሌላ ሰው ሆኜ፣ ግን ማን እንደሆንኩ ሳላውቅ፣ በቅንዝርና በቅናት እየተቃጠልኩ፣ ጥልቅ የሆነ ስጋዊ ደስታን ተደሰትኩ:: በነጋታው ቀኝ ጡቷን እያመማት ዋለ:: ሳይታወቀኝ ጨፍልቄው ኖሯል

በሌላ ቀን፣ «ማን ሆኜ ነበር?» አልኳት:: ስንበላ በስተኋላዬ አንድ ሰውዬ አይታ ኖሯል:: «ልክ ስመ ጥሩውን ባለቅኔ ሎርድ ባይረንን ይመስል ነበር» አለችኝ

እንደዚህ ስንል፡ እሷ ደስ የሚላትን ወንድ ስታይ፣ እኔ በጭለማ

እሱን እየሆንኩ ሳቅፋት፣ እሷ ስትቃኘኝ፣ እኔ ስንከላት ስጨፈልቃት፣ እንደዚህ ስንል፣ በሰማያዊ አይኖቿ ብርሀንና በሰፊ አፏ ሳቅ እየሞቀችኝ፣ በውብ ወጣት ገላዋ እያቃጠለችኝ፣ የጣልያንን ከተማዎች እያዞረችኝ፣ «Je m'en fous» እያለች እያሳቀችኝ፣ እንደዚህ ስንል የቢጋው እረፍት ወደ ማለቂያው ተቃረበ:: ከፊሬንዜ ሮማ፣ ከሮማ ናፖሊ፣ ከናፖሊ ኒስ (ፈረንሳይ) ከኒስ ማርሰይ ተጓዝን::

ከማርሰይ እሷ ቤቶቿን ጥየቃ ፓሪስ ሄደች:: ባቡር ጣቢያው ሄጄ ስሸኛት «ልክ የዛሬ ዘጠኝ ቀን ማክሰኞ ኤክስ እገባለሁ፣ ማታ ቤቴ እጠብቅሀለሁ» አለችኝ

የሲልቪ ናፍቆት የሚገድለኝ መስሎኝ፣ ዘጠኝ ቀን ሙሉ እንዴት ሊያልፍልኝ ነው? እያልኩ ስሰጋ ነበር:: ግን ባቡሩ ይዟት እንደሄደ፣ በሀዘን ፈንታ እፎይታ ተሰማኝ:: ማታ አልጋ ውስጥ ገብቼ ብቻዬን እንደ ልቤ ስገላበጥ፣ ብቸኝነት ሳይሆን ምቾት ተሰማኝ:: ምቾቴ በደምብ እንዲታወቀኝ ስል በብዙ ተገላበጥኩ:: ጧት ስነቃ ሲልቪ የለችም፣ ብቻዬን ነኝ:: በናፍቆት ፈንታ ደስታ ተሰማኝ:: ሲልቪ ሰልችታኝ ኖሯል? ወይስ ከሰው ጋር ለመኖር አልተፈጠርኩም? ሊገባኝ አልቻለም

ኤክስ ሄጄ ሲቴ (ዩኒቨርሲቲ) ውስጥ አንድ የመኝታ ክፍል ተቀበልኩ:: ሁለተኛው አመት ወደ መጀመሩ ነበር

ጧት ስነሳ በመስኮቱ ደማቅ ሰማያዊ የሆነ ንፁህ ሰማይ ታየኝ:: ደስ አለኝ:: ሳይታወቀኝ የኤክስ ውብ ሰማይ ናፍቆኝ ኖሯል

@BOOKALEM

# ክፍል ሁለት

## ስድስት
## ባህራም ከቅርብ

ኤክስ እንደተመለስኩ መጀመሪያ ያገኘሁት ተካን ነበር:: ያው እንደ ልማዱ ጥፍሩን እየነከሰ፡ የት ነበርክ? ከማን ጋር ነበርክ? ምን አደረግክ? ምን አየህ? እያለ በጥያቄ አጣደፈኝ:: ግን ሳየው የጥርሱ መበለዝ የቀነሰ መሰለኝ:: አፉም አልገማኝም:: ጊዜው ከእራት በኋላ ነበር፡ ና ቡና ሳጠጣህ ብሎ ወደ ክፍሉ ወሰደኝ:: ቤቱ በጭራሽ አይገማም!

እንግዲህ፣ የዩኒቨርሲቲው መኝታ ቤቶች ባለ ሶስት ፎቅ ሲሆኑ፣ እያንዳንዱ ፎቅ ላይ ለሚገኙት ሰላሳ ያህል ክፍሎች የጋራ የሆኑ አንድ የገላ መታጠቢያ ክፍልና፣ አጠገቡ ደግሞ (ልክ ደረጃው መጨረሻ ላይ) አንድ የቡና ማፍያ ምድጃ ያለው ክፍል አላቸው:: ተካ ቡናውን ሊጥድ ወደ ማፍያው ክፍል ሲሄድ እኔ የሱን መኝታ ክፍል ተመለከትኩ:: ንፁህ ነው:: ፊት መታጠቢያው ዘንድ፡ ግማሹ ያለቀ ኮልጌት የጥርስ ሳሙናና አንድ የጥርስ ብሩሽ አለ:: ተካ ጥርሱን ይቦርሻል! ምን ነካው?. . . ምን ይነካዋል? ያው



@BOOKALEM

የተለመደው መሆን አለበት! አንድን ነሬምባ ጥርሱን ሲያስቦርሽው የሚችል ምንድነው? ሴት አይደለችም? ግምቱ ልክ ይሆን? ልክ መሆን አለበት። አለዚያ ምኑን ደፋሪ ሆንኩት?

እንትቴን በበሩ ብቅ አድርጌ አየሁ። ጨለም ያለው ረዥም መተላለፊያ ኮሪደር ባዶውን ነው። ኮሪደሩ መጨረሻ ላይ ያለው የቡና ማፍያ ክፍል ተዘግቷል። ተካ ገና ቡናውን በመጣድ ላይ ነው ማለት ነው። ጊዜ አለኝ። በሩን ዘጋሁ። ቶሎ ወደ አልጋው ራመድ አልኩ። እንስላውን ላመሉ ገለጥ አደረግኩት። ነምበስ ብዬ ትራሱን አሸተተኩት። የሴት ጠረን። ያለጥርጥር። እንዴት ያለች ትሆን?

ቶሎ አልጋውን አስተካከልኩና፣ ቁጭ ብዬ ጋዜጣ እያነበብኩ ቆየሁት

ቡና ከጠጣን በኋላ ሌሎቹን ሀበሾች ፍለጋ ወጣን

ተካ «ተመስገንን ግን አታገኘውም» አለኝ «ወደ ፓሪስ ተዛውሯል። ለምን እንደተዛወረ ታውቃለህ?»

«ለምንድነው?» አልኩት

«ነጭ ሴት ስለቸገኘ አለ»

«ምን?»

«ጥቁር ሴት ካላገኘሁ ልማር አልችልም አለ። እዚህ ኤክስ ውስጥ ሁለት ጥቁር ሴት ብቻ ነው ያለው፣ ሁለቱም አስቀያሚ ናቸው። ስለዚህ ፓሪስ መሄዱ ነው። ቢሆን እግዜር ብሎ አንዲት ሀበሻ ልጅ ታጋጥመኝ ይሆናል። ባይሆን ደሞ ሌላ ጥቁር ሴት አላጣም፣ ብሎ ሄደ»

ተመስገን እውነቱን ነው። ኤክስ ውስጥ ጥቁር ሴት አይገኝም፣ ሀበሻ ሴት ይናፍቃል። ያገራችን ሴቶች ትዝ ይሉናል፣ አነጋገራቸው፣ አሳሳቃቸው፣ መሽኮርመማቸው ይናፍቀናል፣ ጥቁር ቆዳቸው፣ ነጭ ጥርሳቸው እንቅልፍ ይነሳናል፣ በሀሳባችን «እረ ንሺ» ሲሉ ይሰማናል።

እንዳንድ ጊዜ ተሰብስበን ስለነሱ እናወራለን። ናፍቆት ሲበዛብን እየሳቅን እየጮህን እንዘፍናለን

«አንቺ ጥቁር ድንጋይ ፍቅር አይገባሽ
በሰው አገር ሆኜ ተቃጠልኩልሽ»

ለሉሲንድማ «ልጆችዬ፣ አብረን እንዴት እምስ የተቀረጠባት ቅጥ ለቀለብሎ እናብራለትና» አለን «እምስ በፖስታ ሳክልን፣ መጋረጃ እናስገባልሀለን፣ እንበለው:: እውነቴን'ኮ ነው! ያገሩ ልጆች ነን፣ ይስማናል:: ኧረ 'ናታችሁን! ይሄ ምኑ ያስቃል?»

እኔና ተካ ሀበሾቹን ሉሲንድ ቤት አገኘናቸው:: ባህራምና አንድ ሌላ ኢራናዊ አብረዋቸው አሉ:: ይህ ሌላ ኢራናዊ ጆምሺድ ይባላል:: ረዥም መልከ ቀና ወጣት:: ጥቁር ሱፍና ነጭ ሸሚዝ ከቢራቢሮ ከራቫት ጋር ለብሷል:: ግብዣ ለመሄድ የተዘጋጀ ይመስላል:: ረዘም ያለ ፊት፣ ቀጥ ያለ ረዥም አፍንጫ:: ከሀር መሳይ ውብ ቅንድቦቹ በታች ሰማያዊ ትንንሽ አይኖች ሁልጊዜ ይጨፍራሉ:: ብርሀን፣ ሳቅ፣ ብልጠት የሚፈራረቅባቸው፣ ህይወት የሞላባቸው አይኖች ናቸው:: በኋላ እንደተረዳሁት፣ ጆምሺድ ፈረንሳይ አገር ከመጣ አመት አልፎታል:: ታድያ ቢበዛ ስምንት መቶ የፈረንሳይኛ ቃላት ቢያውቅ ነው (የቋንቋ ስጦታ የለውም) ግን እነዚህ ስምንት መቶ ቃላት ለንግግር ኮርተው ይበቁታል:: ምክንያቱም፣ ቀጭን ኮሚክ ድምፁና ትንንሽ ብልጮ አይኖቹ፣ ያለ ቃላትም ቢሆን የፈለገውን ይገልፁለታል

እኔና ተካ ስንገባ ጆምሺድ አንድ ታሪክ ጀምሮላቸው ኖሮ፣ ጨብጠናቸው ቁጭ ካልን በኋላ እንደገና ጀምርልን አሉት:: ስብርብር እንቅሽቅሽ ባለ ፈረንሳይኛ ጀመረ:: ሁለት እንካሳ አረፍተ ነገር ያህል እንደተናገረ ቃል ይጠፋዋል:: በፋርስ ቋንቋ ባህራምን ይጠይቃል:: ባህራም ፈረንሳይኛውን ቃል ይነግረዋል:: ጆምሺድ ታሪኩን ይቀጥላል::

«ከአስራ ስስት ወር በፊት» አለ ጆምሺድ «እኔና ሆዚ ከኢራን እንመጣለን:: ወደ ፓሪስ:: ሆዚ ፈረንሳይኛ አይችል:: እንዳች በፍፁም! እኔ ግን 'ዊ-ዊ' ማለት እችላለሁ:: ደሞ 'ሜርሲ ቦኩ' አውቃለሁ:: ግን 'ሜርሲ ቦኩ' አልልም 'መርስ ባኩ' እላለሁ:: እኔና ሆዚ ሀሳብ፣ ሶርቦን ዩኒቨርሲቲ ለመማር:: ለመማር መመዝገብ:: ለመመዝገብ ሶርቦን መሄድ:: ሶርቦን ለመሄድ ሜትሮ መግባት:: ('ሜትሮ' ፓሪስ ውስጥ ከምድር ስር የሚሄድ የህዝብ ማመላለሻ ባቡር ነው)

ሟት በሁለት ሰአት ሜትሮ ገባን:: ሆዚ ፈረንሳይኛ አያውቅም::



@BOOKALEM

እኣ ግን ፈረንሳዮቹን፣ የትኛቸው ባቡር እንሳፈረው? ብዬ ጠየቅሁ። በቃላት አይደለም፣ በእጅ፣ በራስና በድምጽ። በምልክት። 'ዠ ሽ ኳ ዢ፣ ኝም፣ ዥም!'። ይሉኛል። ሆዚ ዝም ይላል። ፈረንሳይኛ አያውቅ። እኣ ግን 'ዊ - ዊ! መርስ ባኩ' ይላል - እላለሁ ማለቴ - ማለቱ። እኣና ሆዚ አንድ ባቡር መሳፈር ሲቆም መውረድ። ሌላ ባቡር መሳፈር። እንደዚህ በመሳፈር የምሳ ሰአት ማለፍ። ፈረንሳዮቹ እንጠይቃለን። 'ዠ ሽ ዥ ዢ! ኝም! ዢም!' ይሉናል። ሆዚ ዝም። እኣ 'ዊ - ዊ! መርስ ባኩ!'። መሬት ውስጥ ገብተን መምሸት። እሑን ወደ ሆቴላችን። ሌላ ባቡር። ሌላ ባቡር። ሌላ ባቡር። ሆዚ ድካም፣ ራብ፣ ብስጭት - እምባ! እኔ የሆዚ እምባ ያሳዝነኛል። እኔ እምባ! ሁለት ኀረምሶች ሜትሮ ውስጥ እምባ!!

«አንዷት አሮጊት መምጣት። ታየናለች። 'ዠ ሽ ዥ ዢ?' ትለናለች። ሆዚ ፈረንሳይኛ አያውቅ። ዝም። እምባ ብቻ። እኔ 'ዊ ማዳም፣ መርስ ባኩ!' አሮጊት ሆዚን ማቀፍ፣ ማልቀስ። ሶስታችን ተቃቅፈን ማልቀስ። በኋላ እኔ አሮጊትን 'መርስ ባኩ ማዳም' ብሎ መሳም። እሷ ሆዚን 'አሙር ቦኩ' ብላ መሳም

እኣና ሆዚ ከሜትሮ መውጣት። በታክሲ ወደ ሆቴላችን። ዋጋ አስራ ስምንት ፍራንክ

«በነገ - በንጋት - ከሌላ የኢራን ልጅ ጋር ወደ ሶርቦን። በሜትሮ ባንድ አፍታ ከተፍ!»

ጆምቪድና ሆዚ ስተት ብለው ወደ አንድ ትልቅ ቢሮ ገቡ። የፐሬዚዳንቱ ሳይሆን አይቀርም። ሲረግጡት ስምጥ የሚል ምንጣፍ ወለሉን በሙላ ሸፍኖታል። ከሰፊው ዴስክ በስተኋላ ተቀምጦ ፒፓ ያጨስ የነበረው መላጣ ባለትልቅ ሙስታሽ ሽማግሌ ዘሎ መጥቶ ጨበጣቸውና፣ በእጁ መቀመጫ ሰፋ አመልክቷቸው ሲያበቃ፣ እስኪቀመጡ እንኳ ሳይጠብቅ፣ ከጠረጴዛው ወደ በሩ፣ ከበሩ ወደ መስኮቱ፣ ከመስኮቱ ወደ ጠረጴዛው እየነጠረ መለፍለፍ ጀመረ። ይለፈልፍ ይለፈልፍና ቆም ይላል። N'est-ce pas? (አይደለም?) ብሎ ፒፓውን እየማገ በመነፅሩ ሲያያቸው፣ ጆምቪድ ልክ ንግግሩና [illegible] ነገሩ እንደገባው ሰው ራሱን እየነቀነቀ

«ዊ! ዊ!» ይለዋል

ሽማግሌው መንሰፋንና መላጣውን እያብለጨለጨ መለፍለፉንና እንደ ፊልም ባቡር እየተዘዋወረ የፒፓውን ትምባሆ ቡልቅ ቡልቅ ማድረጉን ይቀጥላል:: አልፎ አልፎ ቆም ይልና እያያቸው «N'est-ce pas?» ሲል፣ አሁንም ጆምቢድ ራሱን እየነቀነቀ «ዊ! ዊ!» ይለዋል:: አንድ አሰር ደቂቃ ከተዘዋወረና ከለፈለፈ በኋላ፣ አሁንም «N'est-ce pas?» ብሎ ፒፓውን እያቦነነ ሲያያቸው፣ ጆምቢድ እንደ ደምቡ «ዊ! ዊ!» አለው::

«Comment oui?» («እንዴት ማለት አዎን?») ብሎ ሮጣበት «ኖ!» ማለት ነበረበት:: ጆምቢድ ተደናገጠ

«ኖ! ዊ! ኖ! መርስ ባኩ! ዊ?» እያለ ከተቀመጠበት ተነስቶ፣ ከኪሱ የሲጋራ ፓኮ አውጥቶ ጋበዘው:: ሽማግሌው በሀይል እየሮጠ ፒፓውን ከአፉ አወጣና ጆምቢድ አፍንጫ ስር ደቀነው:: ጆምቢድና ሆዜ ከዚያ የሮጡ፣ ከዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ሲወጡ ቆሙ

«ፋሚችንን ጨርሰን ቆመን:: ያን ጊዜ ፒፓው ገማኝ» አለ ጆምቢድ ለካ በድንጋጤው የሽማግሌውን ፒፓ መንጭቆ ይዞ ሸሽቶ ኖሯል:: ፒፓውን ሊሰጡት ቢሮው ተመልሰው ሲገቡ፣ ሽማግሌው እንደ ቡድሀ እግሮቹን ከስሩ አጣጥፎ ጠረጴዛው ላይ ተቀምጧል:: ፊቱ ወደ መስኮቱ በኩል ስለሆነ ሲገቡ አላያቸውም:: ለማአት እንደሚቀርብ የስለት ስጦታ ፒፓውን እግሮቹ አጠገብ አስቀመጡለትና፣ እንዳይቀሰቅሱት በእግራቸው ጫፍ እየረገጡ ወጡ

ሆዜ አገሩ ተመለሰ:: ጆምቢድ ወደ ኤክስ መጣ

ጆምቢድ ሌላ ብዙ የደረሰበትን ኮሚክ ነገር በኮሚክ ድምፁና በብልጮ ሰማያዊ አይኖቹ፣ በእጆቹና በእግሮቹ ትንሽ ትንሽ ደሞ በፈረንሳይኛው ሲያወራልን ስንስቅ ቆየን:: ሶስት ሰአት ሲሆን አብዛኛዎቹ ወደ ሲኒማ ሄዱ:: እኔ ባህሩምን ወደ ካፌ ሰንትራ ወሰድኩት

ከሰንትራ ፊት ለፊት ወዳለው «ሲኒማ ካዚኖ» ለመግባት ሰዎቹ ቲኬት ሲያስቆርጡ እያየናቸው ቀዝቃዛ ቢራ ካዘዝን በኋላ

«Alors, comment vas tu?» («ታዲያስ እንደምነህ?») አልኩት

ያው እንደድሮው ቀልደኛ ነው፣ ቡናማ ትንንሽ አይኖቹ ይስቃሉ:: ግን ከስቷል፣ ጉንጮቹ ጎድጉደዋል፣ አፍንጫው ከድሮው



@BOOKALEM

የበለ ትልቅ መስሏል:: በጣም ጥቁር ፀጉሩ ከጎንና ከጎኑ - አለፍ አለፍ - አንዳንድ ሽበት ማውጣት ጀምሯል:: ደህና ነኝ አለ፤ ግን እየለመደኝ ከሄደ በኋላና ለስተኛ ጠርሙስ ቢራችንን ከጠጣን በኋላ ሊነግረኝ ጀመረ

«ቤቶችህ ፃፉልህ?» አልኩት

«የለም»

«ታድያ የእረፍት ጊዜውን እንዴት አሳለፍከው?» አልኩት:: ሲልቪ ልብሷን ስታወልቅ ታየችኝ:: በልዩ ጥንቃቄ የተቀረፁ ውብ እግሮቿ ሀሳቤ ውስጥ ድቅን አሉብኝ:: ውስጤ ሙቀት ተሰማኝ:: እስክትመለስልኝ ቸኩልኩ:: እንዴት ያለ ግሩም የእረፍት ጊዜ ነበር!... የባህሩም የእረፍት ጊዜ ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነበር

እኔ ሲልቪን ተከትዬ በሄድኩ በሳምንቱ፣ ኒኮል ለእረፍቴ ወደ ቤቷ ስትሄድ (ቤቶቿ ሰሜን ፈረንሳይ ለሀብር የተባለው ወደብ ከተማ ውስጥ ነው የሚኖሩት) ጥቂት ፍራንክ ልትተውለት ፈለገች:: ግድ የለም አያስፈልገኝም፡ ቤቶቼ ካሁን ካሁን ይልኩልኝ ይሆናል፣ ባይልኩልኝም ስራ መያዜ ነው አላት:: ስራውን እስክትይዝ ምን ትበላለህ? ቤቶችህ ባይልኩልህስ? አለችው:: እምቢ በማለቱ አፈረ:: ተቀበለ:: በመቀበሉ የባሰውን አፈረ

ከኒኮል ቀጥሎ ሀበሾቹ ሄዱ:: ብቻውን ቀረ:: ስራ ፍለጋ ጀመረ:: ኒኮል የተወችለት ፍራንክ እንዳለቀ ከሷ ደብዳቤ ደረሰው:: አንድ መቶ ፍራንክ ልላክልህ ወይ አለችው:: አትላኪልኝ፣ አያስፈልገኝም ብሎ ፃፈላት

ይርበው ጀመር:: ምግብ ቤቱ ሰፈር ይዞራል:: ምናልባት በሁለት በሶስት ቀን የሚያበላው ሰው ያገኛል:: (በዚያውም ሲጋራ ይጋብዙታል) ያን ጊዜ ከምግብ ቤቱ ዳቦ በኪሱ ይዞ ይወጣል:: ዳቦው በበጋው ሙቀት ቶሎ ይደርቃል:: ደረቁን ዳቦ በሻይ እየነከረ ይበላል:: ያለስኳር:: ስኳሩ አልቋል:: ሻይ ቅጠሉም ወደ ማለቁ ነው:: ያንኑ ቅጠል አምስት ስድስት ጊዜ ያፈላዋል:: ቅጠሉ ይቀቀልና የሻይ ቃናው ጠፍቶ ሌላ አስቀያሚ ብረት ብረት የሚል ጣእም ይሰጣል

በምግብ ሰአት ባህሩም ምግብ ቤቱ አጠገብ ይዞራል:: በሳምንት ቀን አንድ ጊዜ ያህል አንዱ ምሳ ወይም እራት ይጋብዘዋል:: በሳምንት

ቀን አንድ ሙሉ ምግብ ማግኘቱም ድንገት ተቋረጠ:: የምግብ ቤቱ ሰራተኞች የእሙት እረፍታቸውን እንዲያገኙ ተብሎ ምግብ ቤቱ ለአንድ ወር ተዘጋ:: እንግዲህ ወዴት ይሄድ?

አንድ የዘይት ፋብሪካ ውስጥ፣ እቃ መኪና ላይ መጫንና ማውረድ፣ እና ይህን የመሳሰለ የጉልበት ስራ አለ አሉት:: ግን ስራው ከነድ ሳምንት በፊት አይጀመርም:: እስከዚያው ምን ይብላ? ጨነቀው:: የሲጋራ ጥምም በበኩሉ የመፍዘዝ ስሜት ያሳድርበታል:: ሙሉ ምግብ እንዳያስፈልገው በማለት አልጋው ላይ ተጋድሞ መዋል ጀመረ

ድረት ዳቦ በጠነሻ ሻይ ከበላ ሁለት ቀን አለፈው:: ራብ ሲገድለኝ እንዴት ዝም ብዬ ልተኛ? ብሎ ከቤቱ ወጣ:: በተስፋ ላይሆን እንደዚሁ ወጣ:: ትንሽ እንደሄደ ቆሻሻ መጣያ አጠገብ የወደቀ የሰርዲን ቆርቆሮ አገኘ:: በደህና ቀን ሰርዲን በጣም ይጠላል:: አሁን ግን ቤቱ ወስዶ እየተንገበገበ ከፈተው:: ዘይቱ አሳስበላ አለው:: ዳቦ ቢያገኝ! ዳቦ መግዣ ፍራንክ ፍለጋ ቤቱን ይበረብር ጀመር:: አልጋው ስር፣ መጻህፍቱ መካከል፣ ኪሶቹ ውስጥ፣ የተወሻሸሹ የተረሱ ሳንቲሞች አገኘ:: ለዳቦ መግዣ ሶስት ሳንቲም ነደለው:: ግን ሲበረብር አንድ እንደ ድንጋይ የደረቀ ቁራጭ ዳቦ አግኝቶ ነበር:: እሱን ውሀ ውስጥ ነከረው:: ሲርስ ከውሀው አውጥቶ ከሰርዲኑ ጋር ፈተፈተው:: በላው::

ትንሽ ቆይቶ ሆዱን አመመው:: አቅለሸለሸው፣ አስታወከው:: ላብ አጠመቀው:: የማስታወኩ ከፍና ዝቅ ያችን የተረፈችውን ሀይሉን ጨረሰበት፣ ደከም አለው፣ አቅሙ ውሀ ሆነ፣ ወደ አልጋው ሲራመድ ጉልበቱ ከስር ታጠፈ፣ አልወደቀም፣ ቀስ ብሎ ወደ ወለሉ ወርዶ ተዘረጋ:: አይኑን ዘጋ:: ትንሽ ቆይቶ ብርድ ብርድ አለው:: እየተንፏቀቀ አልጋው ደረሰ:: አንሶላው ውስጥ ገባ:: አይኑን ዘጋ:: እንደማገር አለው:: ራቡ ብቻ አይደለም፣ ሲጋራ ማጣቱም ጭምር ነው:: በረደው:: በዚህ በጋ ሙቀት? ትኩሳት መሆን አለበት:: እናቱ ትዝ አሉት:: «አመመህ?» ብለው ግምባሩን ሲነኩት፣ አልጋው ዳር እንደተቀመጡ ወደታች ሲያዩት፣ ትራሱን ሲያመቻቹለት፣ አስታወሰ:: ድንገት ብቸኝነት ተሰማው:: ውስጡ አንድ ድምፅ «ብቻዬን ነኝ፣ ማንም የለኝ! ማንም አይደርስልኝ!» ብሎ ጮኸ:: አስፈራው:: ከውስጡ፣ የድሮ የልጅነት ድምፁ «እማማ!» ብሎ



@BOOKALEM

ሲጣራ ተሰማው:: «ወይኔ፣ ማበዴ ይሆን እንዴ? አሜሪካኖቹን ሳላባርር?» ብሎ አሰበ:: የባሰውን ፈራ:: ብርድ እንቀጠቀጠው:: ጥቅልል ብሎ ተኛ:: በቅዠት ህልሙ እናቱ ትልልቅ ለስላሳ ትራስ ላይ አስደግፈውት ሾርባ በማንኪያ ሲያጠጡት፣ አሜሪካኖችና የሻ ሰዎች መጥተው ሊያርዱት ሲሉ፣ ሲሸሽ፣ በጫካ በሽለቆ ሲያባርሩት፣ ሲሮጥ፣ ሲሮጥ፣ ሲሮጥ፣ አሊጋው ውስጥ እያቃሰተ ሲገላበጥ፣ በላብ ሲታጠብ፣ በብርድ ሲንቀጠቀጥ አደረ

ጧት በማለዳ ነቃ:: ጉልበቱ ትንሽ ተመልሶለታል:: ተነስቶ ወጣ:: ከቤቱ ትንሽ ሄድ እንዳለ፣ የወተት መኪና መጣና እንድ የምግብ ሸቀጥ ሱቅ ደጃፍ ላይ ሶስት ደርዘን የወተት ጠርሙስ አስቀምጦ ሄደ:: ባህራም ሁለቱን ጠርሙስ አንስቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ፣ መንገዱ ዳር አንድ ተገምጦ የተጣለ ፖም አገኘ:: የተገመጠውን በቢላ ቀርፎ ጥሎ፣ የቀረውን ግማሽ ፖም በውሀ አጥቦ በልቶ ወተቱን እየጠጣ ዋለ

ሲመሽ ራብ አንገበገበው:: ኩራቱን ክብሩን ረሳ:: እንድ የሚያውቀው ፈረንሳይ ቤት ሄደ:: በቀጥታ «በራብ ልሞት ነው» አለው:: ፈረንሳዩ ቤቱ አስገባና ጭቅና ከድንች ጥብስ ጋር፣ ስፓጌቲ፣ ሰላጣ፣ ቺዝ፣ ወይን አቀረበለት:: ተንገብግቦ አምስት ጉርሻ ያህል እንደ ጉረስ ሆዱ ተዘጋ:: እስኪጠግብ ከበላ ሳምንት አልፎታል:: ራቡ ሊገድለው ነው፣ ከዛሬ በኋላ መቼ ምግብ ሊያገኝ እንደሚችል አያውቅም፣ አሁን ታዲያ ሆዱ እምቢ አልቀበልም አለው:: በጣም ተበሳጨ፣ እምባ ተናነቀው፣ እዚያው ራሱን ደፍቶ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ:: ፈረንሳዩን «እግዜር ይስጥልኝ፣ ይቅርታ ያድርጉልኝ» ብሎት ወጣና ቤቱ ተመለሰ:: ተኛ

በማለዳ ተነስቶ ከሌላ የምግብ ሱቅ ደጃፍ ሶስት ጠርሙስ ወተት አንስቶ ወሰደ:: ተጋድሞ እሱን እየጠጣ ዋለ:: ሊሊት ተቅማጥ ያዘው

ሲነጋ እንደምንም እየተጎተተ ዘይት ፋብሪካው ሄደ:: ስራውን ነገ ትጀምራለህ አሉት:: አለቃው አንዲት አሮጌት ያለች ሴትዮ ናት:: ሲያያት ፊቷ በጣም ርህሩህ መሰለው:: ችግሩን አጫወታት:: ከደመወዝህ ትከፍለኛለህ ብላ ሃምሳ ፍራንክ አበደረችው:: ምግብ ገዝቶ ቤቱ ወሰደ:: ትንሽ ቀማመሰ:: ለመጀመሪያ ጊዜም ሲጋራ አጨሰ:: ትልቅ እፎይታ ተሰማው:: ተኛ:: ነቅቶ እንደገና ትንሽ



@BOOKALEM

በላ፣ አንድ ሲጋራ አጨሰ:: ተመልሶ ተኛ:: ሲነጋ ደህና ቁርስ በልቶ፣ አንድ ሲጋራ አጭሶ ወደ ስራው ሄደ::

ከባድ እቃዎችን ከመኪና ማውረድና መኪና ላይ መጫን ነበር ስራው:: ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ መጠነኛ ሳጥን ከመኪናው አንስቶ ተሸክሞ ወደ ግምጃ ቤቱ ሲወስድ፣ ጥቂት እርምጃ እንደሄደ ጉልበቱ ከስሩ ታጠፈበት:: ሳጥኑን ትከሻው ላይ እንደተሸከመ ተምበረከከና፣ በዚያው ቀስ ብሎ ቁጭ አለ

አሮጊት ብጤ አለቃው መጥታ ሳጥኑን ከላዩ ላይ አነሳችለት:: አፍሮ ቁጭ እንዳለ ቀረ:: ውሀ አምጥታ አጠጣችው:: ብርጭቆውን ሲመልስላት፣ በርህሩህ ገፅዋ አስተያየት በጣም እንዳዘነችለት ታወቀው:: ለሚቀጥለው አራት ቀን፣ ማለት ጉልበቱ እስኪመለስለት ድረስ፣ ጡንቻ የማያስፈልገው ስራ ሰጠችው:: በኋላ ከባድ እቃዎችን መሸከም ጀመረ::

ትከሻውን ያመዋል፡ ወገቡ የሚቆረጥ ይመስለዋል፣ መዳፉ ይላላጣል፣ በበጋው ሙቀት ከባድ እቃ መሸከሙ አንዳንዴ ራሱን ያዞረዋል:: ግን ማታ እራቱን ጥስቅ አርጎ ይበላል፣ ቡና ጠጥቶ ሲጋራ ያጨሳል:: አልጋው ውስጥ ይገባል:: ከመቅፅበት እንቅልፍ ይዞት ጥርግ ይላል

ልክ አራት ሳምንት እንደሰራ ስራው አለቀ:: አሰናበቱት:: ቅዳሜ ነበር:: ባለውለታ አለቃውን አመስግኖ ሲሰናበታት እራት ጋበዘችው:: ቤቷ አመሸ:: ሲያያት፣ እርጅና አፋፍ ላይ ደርሳለች:: ወንድ ካገኘች ብዙ ጊዜ ሳይሆናት አይቀርም:: ከእንግዲህ ማግኘቷንም እንጃ:: ሲያስብ ጊዜ፣ እሷ ደግ ባትውልለት ኖሮ ይህን ጊዜ በራብ ሞቶ ነበር:: ሆን ብሎ ብዙ ወይን ጠጣና ሰከረ:: አብሯት አደረ

«ስራ ከተውኩ ይኸው ዛሬ አንድ ሳምንት ሆነኝ:: ግን የተሸከምኩበት አሁንም ትከሻዬን ወገቤን ያመኛል» አለ:: ከዚህ በፊት የጉልበት ስራ ሰርቶ አያውቅም ነበር

«ይሄ ሁሉ ሲሆን ጀምሺድ የት ነበር?» አልኩት

«ሞንቴ ካርሎ»



@BOOKALEM

«የት?»

«አታውቅም' ንዴ? ቁማርተኛ ነው'ኮ:: ቅዳሜ ቅዳሜ እዚያ ካዚና ነው 'ሚያመሸው»

ከተቀመጥንበት ካፌ ሰንትራ ፊት ለፊት መንገዱን ተሻግሮ «ሲኒማ ካዚና» በብዙ መብራት አሸብርቆ ይታያል:: የሲኒማ ህንፃው ቀኝ ጎን ቁማር ቤት ነው:: ይኸኔ እዚያ ውስጥ ጥቁር ልብስ የለበሱ ወንዶችና ከበር ጌጣጌጥ ባንገታቸውና በእጃቸው ያሰሩ ሴቶች የመጠጥ ብርጭቆ ወይም ሲጋራ እንደያዙ አይኖቻቸውን የሚሽከረከረው ሩሌት ላይ ተክለዋል:: የጆምሺይ አይኖችም ሩሌቱ ላይ ተተክለዋል:: እንደ ቅድማቸው ሳቅና ቀልድ ይጨፍርባቸው ይሆን? ወይስ ፍዝዝ ብለው ይሆን?

ባህራምን «ብዙ ይበላል?» አልኩት

«አዎን ይበላል:: ግን የበላውን ወስዶ መልሶ ያስበላል:: አንድ ቀን ሰባት ሺ ፍራንክ ሲበላ አይቼዋለሁ:: ታድያ እዚያው መልሶ ተበላ::. . . እውነተኛ ቁማርተኛ ነው:: ማለቴ፣ የሚጫወተው ገንዘብ አገኛለሁ ብሎ ተስፋ በማድረግ አይደለም:: ለቁማር ፍቅር ነው:: ከሚያገኘው ገንዘብ የሚያጠፋው ይበልጣል:: ከሁለት ወር በፊት ሲነግረኝ፣ ኢክስ ከመጣ ብቻ ሰላሳ ሰባት ሺ ፍራንክ ተበልቷል»

«ገንዘብ ከየት ያመጣል?»

«ቤቶቹ በጣም ሀብታም ናቸው»

ይህን ጊዜ ወደ ውጭ በኩል ስመለከት፣ ተካና አንዲት ግዙፍ ብጤ ሴት እጅ ለእጅ ተቆላልፈው ሲሄዱ አየሁ:: ባህራምን

«ተካ አገኘ 'ንዴ?» አልኩት

ሳቁን ለመቋጠር እየሞከረ «አዎ:: ጀርመን» አለኝ

«እንዴት ያለች ናት?» አልኩት:: ቡናማ አይኖቹ ያስቃሉ፣ ግን ጥርሶቹን እንደምንም ከድኗል

«ከንፈሮቿ በጣም ውብ ናቸው:: እንደ ዕጌሬዳ ናቸው» አለ

«እና?»

አሁንስ ሳቁ እያመለጠው «እና ከከንፈሯ በላይ ምን የመሰለ ጥቁር ሙስታሽ አላት:: ለምን እንደማትላጨው አይገባኝም» አለ፡



@BOOKALEM

መሳቅ ጀመርኩ። ከኪሱ አንድ ወረቀት አውጥቶ አቀበለኝ። «ሉልሰገድ ነው ባማርኛ የፃፈልኝ። የናንተ አገር ምሳሌ ነው። ምን ብለህ እንደምትተረጉምልኝ ልሰማው እፈልጋለሁ» አለኝ። እንዳነበብኩለት

«ለአፈ ግም አፍንጫ ድፍን ያዘለታል»

እየሳቀ «ምን ማለት ነው? በደምብ አስረዳኝም» አለኝ። ባስረዳው የባሰውን ሳቀ። በመጨረሻ

«ምንድነው 'ሚያስቅህ?» አልኩት። እየተንከተከተ

«ምሳሌው ነው 'ሚያስቀኝ» አለ «ብፌት— ተካ— አፉ— ይሸትህ ነበር?»

«አዎን። ታድያ ይሄ ምኑ ያስቃል?» አልኩት

«ባለሙስታሿ ጀርመን ልጅ— አፍንጫዋ— አያሸትም!— ድፍን ነው!» አለኝ። ሁለታችንም በሳቅ ተንፈራፈርን።

«እውነትክን ነው ግን?» አልኩት

«ሀለሳሴ - ሙት!»

ከዚያ እንግዲህ የኩምክና ወሬ መጣ። አብረን ስንስቅ አመሸን።



@BOOKALEM

# ሰባት

# ባህራም
# ምጥ

ባህራም በሰኔ ወር የወደቀውን ፈተና እንደገና ለመፈተን ማጥናት ጀመረ:: የራሱ መኝታ ቤት ያረጀና የከረከሰ ሆኖ፣ ደምበኛ ጠረጴዛና ወምበር የለውም:: እዚያ ማጥናት አልቻለም:: የዩኒቨርሲቲው ቤተመፃህፍት እየሄደ እንዳያጠና፣ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች ውር ውር እያሉ ሀሳቡን ይሰርቁታል:: ከቀኙ፣ ከግራው፣ ከፊቱ፣ ከኋላው ደሞ አስር፣ አስራ አምስት ፍራንክ ያበደሩት ሰዎች ያዩታል፣ ይከብዱታል:: እንሉልሰገድ ቤት ሄዶ እንዳያጠና ወሬና ጫጫታ ይበዛል:: እኔ ቤት እየመጣ ያጠና ጀመር:: ከስአት በኋላ ሲኒማ እሄድለታለሁ፣ ሲያጠና ይውላል:: ማታ እፅፋለሁ ወይም አነባለሁ፣ ሲያጠና ወይም የማአ-ትዜ-ቱንግን መፃህፍት ሲያነብ ያመሻል:: ጧት ግን ምንም ያህል አይሰራም:: ወሬ እናበዛለን::

ጧት ገና ከእንቅልፌ ሳልነቃ መጥቶ፣ በቀስታ በሩን ከፍቶ ገብቶ፣ ጠረጴዛው ዘንድ ተቀምጦ ሲሰራ ይቆያል:: ስነቃ "Bon jour" እለዋለሁ:: Bon jour ብሎኝ ቡና ይጥድና ስራውን ይቀጥላል:: አልጋዬ ውስጥ እንዳለሁ ትላንት የፃፍኩትን እመለካከታለሁ፣ አርማለሁ፣ እሰርዛለሁ፣ እቀዳለሁ:: ሙሉ ሰአት ሲሆን ባህራም «አንድ ጊዜ ዜና ብንሰማ ይረብሽሀል?» ይለኛል:: (የፈረንሳይ ራዲዮ በየሰአቱ አጫጭር ዜና ያሰራጫል) ራስጌዬ ያለችውን ራዲዮ እከፍታታለሁ:: ባህራም ያፈላውን ቡና በዱቄት ወተት እየጠጣን፣ ስለቪየትናም ወሬ እንሰማለን:: ቪየትኮንጎ የደፈጣ ተዋጊዎች አሜሪካኖቹን አጥቅተዋቸው እንደሆን ባህራም ደስ ይለውና ደስታው አላስጠና ይለዋል:: መናገር ይጀምራል:: ቬየትኮንጎቹ ድል



@BOOKALEM

ማድረጋቸው አይቀርም ይላል:: ንግግሩ ቀስ ብሎ ወደ ኢራን ይወሳስደዋል:: ስለኢራን ሊነግረኝ ይጀምራል:: ስለኢራን፣ ስለኮሙኒዝም፣ ስለማኦ-ትዜ-ቱንግ፣ ስለአሜሪካን ወራሪነትና አጥቂነት፣ ስለካፒታሊዝም ስናወራ እንቆይና፣ ሙሉ ሰአት ሲደርስ እንደገና ራዲዮ እንከፍታለን:: ዜናው ያስደስተዋል ወይም ያበሳጨዋል:: ወሬያችንን እንቀጥላለን:: የምሳ ሰአት እስኪደርስ እናወራለን፣ እናወራለን — ማለት፣ በአብዛኛው እሱ ሲያወራ እኔ አዳምጠዋለሁ፣ አንዳንድ ጊዜ ጥያቄ እጠይቀዋለሁ:: የነገረኝን እያንዳንዱን ማታ ልተኛ ስል አንድ ትልቅዬ ደብተር ውስጥ አስፍረው ነበር

አሁን ያንን ደብተር ሳነበው ባህራም ይታየኛል:: እኔ አልጋ ውስጥ ትራስ ተደግፌ ቁጭ ብዬ፣ እሱ በሽተኛ ሊጠይቅ የመጣ ይመስል አጠገቤ ወምበር ላይ ተቀምጦ፣ በብልህ ቡናማ አይኖቹ እያየኝ፣ ፀጉራም እጆቹን በብዛ እያንቀሳቀሰ፣ በወፍራም ልዝብ ድምፁና በተሰባበረ ፈረንሳይኛው ሲያወራልኝ፣ ቁልጭ ብሎ ይታየኛል

ወሬው አንድ መስመር ይዞ አይሄድም:: ኢራን፣ ኒኮል፣ የባህራም ቤተሰብ፣ የባህራም ጓደኞች፣ ፈረንሳዮች፣ ጥቁሮች፣ «ወጣት ኮሙኒስቶች» የተባለ የኢራን አገር ማህበር፣ ትምህርት ቤት፣ ሴቶች፣ ቡሽቲዎች፣ ጋዜጠኞች — ብቻ ባህራም ያየውንና የሰማውን ነገር፣ በህይወቱ የደረሰበትን ወይም በሌሎች ላይ የደረሰባቸውን ነገር - አሳዛኝ ነገር፣ አስደሳች ነገር፣ አስቂኝ ነገር፣ የሆነ ነገር ያወራልኝ ነበር:: ስንቱን ብዬ ልናገረው እችላለሁ? ጥቂቱን ብቻ ባጭሩ ላስፍረው፣ እንደ ባህራም ካንዱ ወደ ሌላው እየዘለልኩ. . . እንደሚከተለው. . .

አሜሪካኖቹ ይወድቃሉ (ይላል ባህራም) ታያለህ:: ስንቱን ህዝብ ጨቁነው፣ ስንቱን አገር ፈትፍተው፣ ስንቱን መንግስት ገዝተው ይችላሉ? አንድ ቀን ይወድቃሉ:: እንኳን እንደነሱ ያለ ቂል ፈረስ ይቅርና፣ እንደ እንግሊዝ ያለ ተንኮለኛ ቀበሮም ወድቋል:: ተነስቶ ሌሎች ህዝቦችን ጨቁኖ መውደቅ የሚቀርለት የለም:: አሜሪካኖችም ይወድቃሉ:: ይወድቃሉ:: ታይቶ የማይታወቅ



@BOOKALEM

እወዳደቅ ይወድቃሉ:: ያን ጊዜ የአለም ህዝቦች እልል ይላሉ:: በአሜሪካ እግር ተረግጠው ደክመው እልል ለማለት ያህል አቅም ያነሳቸው ደሞ እርይ ይላሉ

አሜሪካኖቹን መጀመሪያ ሆ-ቺ-ሚን ከቬየትናም ያባርራቸዋል:: ቀጥሎ እነ ማኦ-ትዜ-ቱንግ ወይም ወራሾቹ ከሩቅ ምስራቅ ያስወጡዋቸዋል:: ቀጥሎ እንግዲህ ማን ከየት እንደሚያስወጣቸው አላውቅም:: ብቻ እርግጠኛ ነኝ ያስወጡዋቸዋል:: ይህን የሰው አገር ደም ጠጥቶ የወፈረ ቂጣቸውን በካልቾ እየመቱ "Yankee go home! And stay home!" («ያንኪ ወደ አገርህ ግባ– እና እዚያው ቅር!») እያሉ ያስወጡዋቸዋል:: ከሰው እድሜ በላይ በኖርኩ! አሜሪካ ስትወድቅ ለማየት እንድችል ብቻ!. . .

ምን ማለትህ ነው? ለምን አልጠላቸውም? አሜሪካኖችን ያልጠላሁ ማንን ልጥላ? የነፃነትን ዋጋ እያወቅኩ፣ የተጨቆነ ህዝቤን እየወደድኩ፣ አሜሪካኖችን ካልጠላሁማ ሰው አይደለሁም ማለት ነው:: ድንጋይ ነኝ ማለት ነው

አሜሪካኖች አንድ የተቀደሰ ተግባር አላቸው:: ይኸውም፣ እባብ ያንዲትን ወፍ እንቁላል መጠ ጨርሶ ቅል ብቻ እንደሚያስቀርላት፣ እነሱም ያንዲትን አገር ሀብት መጠው ጨርሰው፣ አፈርና ድንጋይ ይተዉላታል:: የኔን አገር ውሰድ:: ዋና ሀብቷ ነዳጅ (ፔትሮል) ነው:: ነዳጁን ከመሬት መጠ የሚወስደው አሜሪካ ነው

አንድ ቀን ሞሳዴግ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነ:: ተነሳና የኢራን ሀብት ለኢራን ህዝብ ነው አለ:: አሜሪካኖቹ ተሳስተሀል አሉት:: በቃል ሳይሆን በተግባር፣ የኢራን ሀብት ለአሜሪካ ነው፣ የኢራን ሀብት ለኢራን ነው ካልክ ኮሙኒስት ነህ ማለት ነው አሉት:: ሲ.አይ.ኤ ልከው ገለበጡት:: ሞሳዴግ ተይዞ ሞት ተፈረደበት:: ግን ሽማግሌ በመሆኑ፣ የሞት ፍርዱ ወደ እስራት ተሻሻለለት:: አሁንም ታስሯል:: የኢራን ሀብት ለአሜሪካኖቹና ለሻህ ነው ያለ ሰው ግን ይሾማል ያሸልማል:: ሻህ ማለት በነሲሩስ፣ በነዳርዩሽና በነካሻር ያገር ስመ ጥሩ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ኢራንን የሚጨቁን ጋንግስተር ማለት ነው:: አጋሮች አሉት:: ህዝቡ ያረሰውን ለመንጠቅ የእርሻ ሚኒስትር ያገዘዋል:: ህዝቡ ሲነግድ ከነጋዴው ለመቀማት የንግድ ሚኒስትር ያገዘዋል:: ለልዩ ልዩ አይነት ጭቆና ልዩ ልዩ ሚኒስትር አለው::

ህዝቡ በደስታ እንዲጨፈቅን፣ ማለትም ተጨፈቅንኩ ብሎ እንዲያጉረምርም፣ ፀጥ የሚያሰኙ ያገር ግዛትና የፍርድ ሚኒስትሮች አሉት

የሻህን-ሻህ ሚኒስትሮች፣ በተለይም የውጭ ጉዳይና ያገር ግዛት ሚኒስትሮቹ፣ ትእዛዛቸውን በቀጥታ ከዋሽንግተን ይቀበላሉ:: ምክንያቱም ኢራን የአሜሪካ የነዳጅ ማእድን ናት:: ደሞ ኢራን የሩሲያ ጎረቤት ስለሆነች፣ አሜሪካኖቹ ለኢራን በጣም ይጠነቀቁላታል:: አንድ ገበሬ ብዙ የምትታለብ ላም ብትኖረው አይጠነቀቅላትም?

ሻህ ማለት ውሻ ነው:: አሜሪካኖቹ ኢራንን አርደው ብልቷን ሲያወጡ አፉ ምራቅ እየሞላ በአይኑ ይከተላቸዋል፣ ሳምባ ወይም ሌላ ቁራጭ ስጋ ጣል ያረጉለታል:: እሱ ደሞ ህዝቡን ጨፈቆ ይይዝላቸዋል:: እየሀ፣ ህዝቡ ተጨፈቆ ካልተያዘ፣ እንደ ሞሳዴግ ተነስቶ «የኢራን ሀብት ለኢራን ሰዎች» ይላል:: ስለዚህ አሜሪካኖቹ ለህዝቡ የማይቆረቆር፣ ጥቂት ሚልዮን ብር ቢሰጡት የሚበቃው፣ ህዝቡን ጨፈቆ የሚይዝላቸው ገዥ ይፈልጋሉ:: ለዚህ ነው ዙፋኑን የሚጠብቁለት

በሞሳዴግ ጊዜ ረብሻ ተነሳ:: ሻህ ሸሽቶ ከአገር ወጣ:: አሜሪካኖች መጥተው «የኢራን ሀብት ለኢራን ሰዎች» የሚሉትን የሞሳዴግ ተከታዮች ፈጅተው፣ በዚያውም ያለ የሌለውን ኮሙኒስት አርደው ጨርሰው፣ አገሩን ጸጥ ካደረጉ በኋላ፣ ና ወደ ዙፋንህ ተመለስ አሉት:: ወደ ዙፋኑ ተመለሰ

ሻህ መሸሽ ልማዱ ነው:: ቴህራን ከተማ ውስጥ አራት ቤተ መንግስት አለው:: እና ሁለቱ ውስጥ ለመብረር ዘወትር ዝግጁ የሆኑ ሁለት ኤሮፕላኖች አሉት:: ትንሽ ረብሻ የተነሳ 'ንደሆነ፣ ወድያው ኤሮፕላኑ ውስጥ ይገባና ካገር ይጠፋል:: ብቻ እሱ ያምልጥ እንጂ፣ ስዊስ፣ አሜሪካ፣ እና ምናልባት ኢንግላንድ ባንኮች ውስጥ ብዙ ሚልዮን ብር ስላለው፣ እንዴት እኖራለሁ ብሎ አይሰጋም

እንግዲህ ሻህ ይሸሻል:: ረብሻው አልፎ ሰላም ሲመለስ፣ ወደ ውድ አገሩ ይመለሳል፣ ለውድ ህዝቡ ንግግር ያደርጋል

አንድ ቀን ግን የሚያስደንቅ ስራ ሰራ:: ማለቴ፣ ረብሻ ሲነሳ አልሸሸም:: አይገርምም? አንተማ ምን ይገርምሀል? ሀለላሴ ረብሻ

ሲነጋ ወደሀገሩ ይገሰግሳል፣ እንጂ አይሸሽም:: የሆነ ሆኖ ያን ጊዜ — ሻህ ሳይሸሽ የቀረ ጊዜ — ለህዝቡ በሬዲዮ «ህዝቤ ሆይ፣ ዛሬም አረኞችን ትቶን ይሄድ ይሆን? ብለህ አትስጋ:: ዛሬስ እዚችው እሞታታለሁ እንጂ አልሄድም!» አለ

እዚህ አለም ላይ እንደ ኢራን ተራ ወታደር የመሰለ ጀግና አታገኝም:: በጭራሽ አታገኝም:: አየህ፣ ጦርነት የተፋፋመ ጊዜ፣ የኢራን ተራ ወታደር ጄኔራሉንም አይታዘዝ፣ ሻለቃውንም አይታዘዝ:: ማንንም አይታዘዝ:: በገዛ ራሱ እንዳሰኘው ይዋጋል:: ምክንያቱም ጄኔራሉም የለ፣ ሻለቃውም የለ:: በጦርነት ጊዜ፣ የኢራን ሰራዊት ተራ ወታደር ብቻ ነው 'ሚዋጋው

የኢራንን ጄኔራሎች የሚመስል የለም:: ከነመለዮዋቸው፣ ከነሊሻናቸው፣ ከነሙስታሻቸው፣ ከነእስተያየታቸው፣ አቤት ደስ ማለታቸው! አረማመዳቸው ሲያኮራ! ግርማቸው ሲያስፈራ! እነሱም ይህን ያውቃሉ:: መለዮዋቸውንና ሊሻናቸውን በሰላም ጊዜ ፈፅመው አያወልቁም:: ጦርነት ሲመጣ ታዲያ፣ መለዮና ሊሻናቸውን አውልቀው፣ የወታደር ሳይሆን የሰላማዊ ሰው ልብስ ይለብሳሉ:: ይሄ 'ንግዲህ የቤት ልብስ ያጡ እንደሆን ነው:: የቤት ልብስ ካገኙ ግን፣ እሷን ይለብሱና እልም! ይጠፋሉ፣ በቃ:: ተራው ወታደር ያለ አለቆቹ ይዋጋል

ጦርነቱ አልቆ የሰላም ውል ከተፈረመ በኋላ፣ ጄኔራሎቹ መለዮአቸውን ለብሰው፣ ሊሻናቸውን ደርድረው፣ አንድ በአንድ ከተፍ ይላሉ:: በየመፅሄቱ ስለጦርነቱ ይፅፋሉ:: አንዳንዶቹም ሙሉ መፅሀፍ ይደርሳሉ:: ጦርነቱ ላይ እንዴት እንደተዋጉ፣ እንዴት እንደተከበቡ፣ እንዴት በጣጥሰው እንደወጡ፣ በመጨረሻም ወታደራቸው ሁሉ አልቆ እንደተማረኩ፣ እንደታሰሩ፣ ስቃይ እንዳዩ፣ ምናምን ይዘበዝባሉ:: ሻህ ውሸታቸውን እንደሆነ ያውቃል:: ግን የበለጠ ማእረግና ሊሻን ይሸልማቸዋል:: ሲሞቱ ብሄራዊ የቀብር ስነ ስርአት ያውጅላቸዋል:: ይሄ ሁሉ ለምንድነው? ንጉሳቸው ሲሸሽ፣ አርአያውን ተከትለው ስለሸሹ ነው

ግን ያልሸሹ፣ በጀግንነት ተዋግተው፣ ብዙ ተጋድሎን አድርገው፣ ድልን ያስገኙ አንድ አራት ጄኔራሎች ይኖራሉ:: እነሱ ማእረግም፣ ክብርም፣ ሊሻንም አይጨመርላቸውም:: ስማቸውም



@BOOKALEM

አይጠራም:: ስእላቸው በየጋዜጣው አይወጣም:: ወደ ቤተመንግስትም አይጋበዙም:: ምክንያቱም ሻህ እነሱ እንደሚበልጡት ስለሚገነዘብ፣ እሱ ጋንግስተር ሆኖ እነሱ ግን እውነተኛ ኢራናውያን መሆናቸው በጣም ስለሚከብደው፣ ሊያያቸው አይፈልግም

ጄኔራሎቹ መለዮዋቸውን

እንግዲህ ሰላም መጣ፣ አይደለም? ጄኔራሎቹ መለዮዋቸውን ለብሰው፣ ሊሻናቸውን ደርድረው፣ እንደ ውሀ በሚፈስ የአሜሪካን መኪና እየተዘዋወሩ ለህዝቡ ይታያሉ:: ቀን ቀን:: ሌሊት ሌሊት ደሞ ሲበዱ ያድራሉ:: የራሳቸውን ሚስቶች አብዛኛውን ጊዜ ሌላ ሰው ነው ነሚበዳቸው:: እነሱ ነሚበዱት የሌላ ሰው ሚስት ነው

እኛ ከተማ ውስጥ አንድ ጄኔራል ነበር:: ከዋናው ፖሊስ አዛዥ ጋር ሸርክ ነው:: ታድያ አንድ ግብዣ ላይ ደስ የምትለው ሴት ሲያይ፣ ለፖሊስ አዛዡ ይነግረዋል:: ፖሊስ አዛዡ የሴትዮዋን ባል ለምርመራ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይወስደውና፣ ባልየው ሲመረመር ያድራል:: ጄኔራሉ ሄዶ ያችን ሴትዮ ሲበዳት ያድራል:: ታዲያ እየህ፣ ከቆሻሻነታቸው የተነሳ፣ ሴትዮዋን እንኳ ወደ ጄኔራሉ ቤት ወይም ወደ ሌላ ቦታ አይወስዷትም:: እዚያው የባልየው አልጋ ላይ ጄኔራሉ ሲበዳት ያድራል:: ምን ይሄ ብቻ? እዚያ ቤት የጄኔራሉ ዘብ ይቆማል:: የጄኔራሉ ደስታ የሰው ሚስት በጉልበት መብዳት ብቻ ሳይሆን፣ የባልየውንም ክብር ማዋረድ ነው:: ሰውየው ልጆች ይኖሩታል፣ ሽማግሌ ወላጆች ይኖሩታል፣ ከጄኔራል ጋር ለመጋጨት ያህል ሀይል አይኖረውም:: ውርደቱን ውጦ ዝም ይላል

አቤት ኢራን ውስጥ ስንት ሰው አለ ውርደቱን ውጦ ዝም ያለ! ሞሳዴግ እንደ ወደቀ፣ የኢራን ፖሊስ ሰራዊት በሲ.አይ.ኤ. ትእዛዝና እርዳታ ኮሙኒስቶችን መፍጀት ጀመረ:: ዘዴው እንደዚህ ነበር

የጠረጠሩትን ሰው ይይዙና ፖሊስ ጣቢያ ወስደው «ኮሙኒስት ነህ?» ይሉታል:: አይደለሁም ይላል:: ያሰቃዩታል:: ውስጥ እግሩን በማስመሪያ ይጠፈጥፉታል፡ ጥፍሮቹን አንድ በአንድ ከስር ይነቅሉለታል:: ቂጡ ውስጥ እንቁላል ይከቱበታል:: ስቃዩ ሲበዛበት ኮሙኒስት ባይሆንም «አዎን፣ ኮሙኒስት ነኝ» ይላል:: በል አሁን የኮሙኒስት ጓዶችህን ስም ንገረን ይሉታል:: ያሰቃዩታል:: እንደ በረዶ የቀዘቀዘ ውሀ ውስጥ ይነክሩትና በአለንጋ ይገርፉታል:: እጁን ጠምዝዘው ይሰብሩታል:: ጥርሱን ቀጥቅጠው ያወላልቁታል:: በመጨረሻ ስቃዩን አይችለውም:: ስለዚህ ስም ይሰጣቸዋል::



@BOOKALEM

ኮሙኒስት ከሆን እውነተኛ ስም ሊነግራቸው ይችላል:: ኮሙኒስት ካልሆን ግን የሆን ስም ይነግራቸዋል:: እነዚያ ሰዎች መሀል ያንተ ስም ይገኛል:: ትያዛለህ:: ይሄኔ አንተ ኮሙኒስት አይደለህም፣ እንዲያውም ኮሙኒስት ትጠላለህ:: ግን ወስደው «ኮሙኒስት ነኝ» እስክትል ያሰቃዩሀል:: በኋላ፣ ስቃዩ ስለሚበዛብህ አንተም የመጣልህ ስም ትናገራለህ:: በዚህ አኳኋን ኮሙኒስቶቹ አለቁ:: ኮሙኒስት ያልሆኑም ብዙ ብዙ ታሰሩ፣ ተሰቃዩ፣ በስቃይ ላይ ሞቱ

መንገድ ላይ አንዱ ሊላውን እየደበደበ «አንተ ውሻ ኮሙኒስት፣ አንተ ነህ የኛን ሻህ 'ምትሰድብ?» ይለዋል:: ሲደበደብ የነበረው ፖሊስ ጣቢያ ይወሰዳል:: ኮሙኒስት ነኝ እስኪል የተለመደውን ስቃይ ይቀበላል

ግን ይሄ ሁሉ ስቃይ የሚደርስህ ገንዘብ ከሌለህ ብቻ ነው:: ገንዘብ ካለህ ኮሙኒስት ብትሆንም ትድናለህ:: እንደታሰርክ አባትህ ወይም ወንድምህ ሄደው ጉቦ ይሰጡልሀል:: ፋይልህ ላይ «በስህተት የተያዘ» ተብሎ ይጻፍና አንተ ነፃ ትለቀቃለህ:: መጥፎነቱ፣ አብዛኞቹ ኮሙኒስቶች ድሀ ነበሩ

ታሰረው ከተፈቱት ጥቂቶች አንዱ የደረሰበትን ነገረኝ:: መጀመሪያ ደበደቡት፣ ገረፉት:: ኮሙኒስት ነኝ አለ:: በኋላ የሌሎች ኮሙኒስቶች ስም ተናገር፣ አሉት:: እምቢ አለ:: ቀዝቃዛ ውሀ ውስጥ ነክረው በአለንጋ ገረፉት:: እምቢ አለ:: ቂጡ ውስጥ እንቁላል ጨመሩበት:: እምቢ አለ:: ልብሱን በሙሉ አስወለቁና ሁለት እጁን በገመድ አስረው፣ እግሩ መሬት እንደማይነካ አድርገው ሰቀሉት:: ተንጠለጠለ:: ሩብ ኪሎ ብረት አምጥተው ብረቱን በሲባጎ አስረው ከቆለጡ ላይ አንጠለጠሉት:: ብረቱ በየደቂቃው ክብደት እየጨመረ የሚሄድ ይመስል ስቃዩ እያደገ ሄደ:: ሀሳቡን ለግማሽ ሰከንድ እንኳ ከቆለጡ ህመም ለማራቅ አልቻለም:: ህይወቱ በሙሉ ቆለጡ ውስጥ ያለ መሰለው:: ከግማሽ ሰአት በኋላ «ተናገር» አሉት:: ዝም አለ:: ክብደቱ ላይ አስር ግራም ብረት ጨመሩለት:: ቀስ እያሉ አምስት አምስት ግራም እየጨመሩ፣ ስቃዩ እየበዛ፣ ጩኸት የእብድ ሰው ይመስል እየቀጠለ፣ አስር ኩዊንታል ብረት ከቆለጡ የተንጠለጠለ እየመሰለው ሲጮህ፣ እነሱ ትንሽ በትንሽ ክብደቱ ላይ እየጨመሩ «ተናገር» እያሉት፣ እሱ «እምቢ!» ብሎ እየጮኸ፣ ድንገት ህመሙ ተወው፣ ጭለማ ዋጠው::

ልቡ ሲመለስለት፣ እሱ አሁንም ተሰቅሏል፡ ግን ብረቱን ከቆለጡ ላይ እንስተውለታል:: ትንሽ ቆየ:: መጡ:: «ተናገር» አሉት:: እምቢ አለ:: በሲባጎ የታሰሩትን ብረቶች አመጡዋቸው:: ብረቶቹን በአይኑ ሲያይ ብቻ በሀይል ቆለጡን አመመውና ጮኸ «ፈታቱኝ! እናገራለሁ!» አለ:: ፈትተው አወረዱትና ልብሱን አልብሰው ወደ አለቃቸው ቢሮ ወሰዱት:: እንጠልጥለው ወሰዱት:: ምክንያቱም ሲራመድ ቆለጡ ትንሽ ሲወዛወዝ ሊገድለው ሆነ:: ቢሮ ሲደርስ ለመናገር ዝግጁ ነህ ወይ? ተባለ:: አይደለሁም አለ:: ምነው እናገራለሁ ብለህ? አሉት:: ሲቀዩን ፈርቼ ነው ’ንጂ፣ የማላውቀውን ዘቶ እምጥቼ ልናገር? አላቸው

ይህን ጊዜ አንድ ጓደኛው መጣ:: የታሸገ ደብዳቤ ለፖሊስ አለቃው ሰጠው:: አለቅየው ደብዳቤውን አነበበ:: ጓደኝየውን ወደ ልዩ ቢሮ ወሰደው:: ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ተመለሱ:: የፖሊሱ አለቃ፣ እስረኛውን ወደ ስቃዩ ቦታ ሳይሆን፣ መኝታ ወዳለበት ክፍል አስወሰደው:: በነጋታው ጓደኛው መጥቶ ወደ ቤት ወሰደው:: ፋይሉ ውስጥ እንግዲህ «በስህተት የታሰረ» ወይም «ተመርምሮ የተጣራ - ኮሙኒስት አይደለም» ተብሎ ተፅፏል፣ ማለት ነው

ልጁ እንዴት ሊፈታ እንደቻለ ገርሞታል:: ጓደኛው ድሀ ነው፡ ዘመዶቹ በሙሉ ድሀ ናቸው:: ጉቦ ከየት ተገኘ? . . . ታድያ ልጁ ድሀ ይሁን ’ንጂ፣ የከተማችን ኮሙኒስቶች ሶስተኛ አለቃ ነው:: ብቻ ኮሙኒስት የሆንን ሁላችን አዋጥተን ነው ጉቦውን የከፈልንለት:: ብቻ ኮሙኒስት የሆንን ሁላችን አዋጥተን ነው ጉቦውን የከፈልንለት:: ብቻ

ኮሙኒስት የሆንን ሁላችን አዋጥተን ነው ጉቦውን የከፈልንለት:: ብቻ ካለቆቻችን አንዱን ለማስፈታት ገንዘብ አዋጡ ተባልን እንጂ፣ ማን እንደሆነ አናውቅም (እኔም ከብዙ አመታት በኋላ ነው ያወቅኩት) አየህ፣ ኮሙኒዝም እንደ ወንጀል የሚቆጠርበት አገር ውስጥ፣ አለቆቻችንን እኛ ሌሎቹ ኮሙኒስቶች አናውቃቸውም:: ሳስረዳህ

ኮሙኒስት ፓርቲ በፍሬ (cell) ነው ’ሚሰራው:: ከሁሉ በላይ አንድ «ፍሬ» አለ:: በድስት አባላት አሉት:: በድስቱ ሰዎች እያንዳንዳቸው የአንድ ሌላ «ፍሬ» አለቃ ናቸው:: የዚህ የሁለተኛው «ፍሬ» እምስቱም ሌሎች አባላት እያንዳንዳቸው የአንድ «ፍሬ» አለቃ ናቸው:: እነዚያ ደሞ ተራቸውን አንዳንድ «ፍሬ» አላቸው:: አንተ የምታውቀው ’ንግዲህ ሁለት ፍሬ ብቻ ነው:: የአንድ ፍሬ አባል ነህ፣ የፍሬው አለቃ ያንተ አለቃ ነው:: ሌላው ፍሬ ደሞ አለቃው አንተ ነህ:: አንተ አለቃቸው የሆንክ ሰዎች፣ እያንዳንዳቸው

ካንተ በታች የአንድ ፍሬ አለቃ ናቸው:: እንዲህ እያለ ይቀጥላል:: ገባህ?

ደሞ ኮሙኒስቶቹ ሁሉም የኮድ ስም አላቸው:: እርስ በራሳቸው የሚጠራሩት በኮድ ስማቸው ብቻ ነው:: የእውነት ስማቸው ማን እንደሆነ አይተዋወቁም:: እንዲህ የሆነ 'ንደሆነ፣ አንተ ብትያዝ እና ፈሪ ብትሆን፣ እና ስቃዩን ፈርተህ መናገር ብትፈልግ፣ ለፖሊሶቹ የምትነግራቸው የኮሙኒስቶቹን የኮድ ስም ብቻ ነው:: ምክንያቱም የእውነት ስማቸውን አታውቅም:: ይህም ሲሆን፣ የአንድ «ፍሬ» አባሎች አንድ ሁለቱ ያንድ ሰፈር ወይም ያንድ ትምህርት ቤት ልጆች ስለሚሆኑ፣ የእውነት ስማቸውን ይተዋወቃሉ:: ይህም ፖሊሶቹን ይረዳቸዋል::

ኮሙኒስት ፓርቲ አንድ ነገር ለማድረግ ሲወስን፣ ውሳኔው ከላይ ወደ ታች፣ ከፍሬ ወደ ፍሬ ይተላለፋል:: አንድ ሀሳብ ታች ሲፈጠር፣ ከታች ወደ ላይ፣ ከፍሬ ወደ ፍሬ ይተላለፋል

የኔ የፍሬ አለቃ አንድ ቀጭን፣ መነፅር የሚያደርግ ማኑ የምንለው ልጅ ነበር:: አምስታችንም የፍሬ አባሎች እንወደው ነበር:: እኔ ግን በጣም በጣም ነበር 'ምወደው:: አደንቀው ነበር:: አቤት ሲፅፍ! ስለህገራችን አስተዳደር ጉድለት፣ ስለጉቦው፣ ስለጭቦው፣ ስለከይሲነቱ ይፅፋል:: ታድያ ሲፅፍ ልዩ አይነት ነው:: የፃፈውን ስታነበው፣ ፍሬ ነገሩ በጣም አያናደደህ፣ አፃፃፉ በጣም ያስቅሀል:: በሳምንት በሳምንት አንድ ሙሉ ገፅ ይፅፋል

አንድ በከተማው የታወቀ፣ የማይጠረጠር ሀኪም አለ:: ትልቅ ቤት አለው:: ቤቱ ውስጥ ከመሰረቱ ስር የሚገኝ አንድ ክፍል አለ:: እዚያ ውስጥ በስቴንስል የሚያባዛ መኪና አለ:: የከተማችን ኮሙኒስቶች ፅሁፋቸውን ሁሉ የሚያባዙት እዚያ ነው:: ብዙ ሰው ለመታከም ስለሚመላለስ፣ ለመጠርጠር ያስቸግራል:: እኔና ማኑ ያችን የፃፋትን ገፅ እናትማለን:: ሁለት ሺ ኮፒ እናትምና፣ በየቡና ቤቱ፣ በየመንገዱ፣ በየአደባባዩ፣ ብቻ ምን ልበልህ፣ ሰው ሊያያቸው በሚችልበት ቦታ እንነዛቸዋለን:: በስርቆሽ:: ሌሊት እየዞርን በየግድግዳው እንለጥፋቸዋለን

አንድ ሌሊት በጭለማ እንደዚህ ስንለጥፍ፣ ሳናስበው ሁለት ፖሊሶች ከተፍ አይሉም?! ደንግጬ ልሮጥ ስል፣ በወድያ በኩልም

የመጣ መሰለኝ። ግን ጨለማ ነው፣ በደምብ አይታይም። ማት ድንገት አቀፈኝና በሹክሹክታ «ለጊዜው ማምለጫ የለም። እቀፈኝ!» አለኝ። ሁልጊዜ ስለማያዘኝ በልማድ ታዘዝኩት እንጂ ነገሩ አልገባኝም። ተቃቀፍን። ፖሊሶቹ አጠገባችን ሲደርሱ፣ ማት በቀጭን ድምፅ «እኔ ፈራሁ፣ ቤት ውሰደኝ» አለኝ «አይዞሽ ምንም አይደለም። ፖሊሶች ናቸው» አልኩት። «ዝም በል! እፈራለሁ!» አለ «አይዞሽ አይዞሽ» እያልኩ ሳባብለው፣ ፖሊሶቹ ትንሽ ተለያይተው ቆመው ሲመለከቱን፣ ማት የሴት ድምፁን ትቶ በእውነት ድምፁ

«በለው!» አለኝ

ሁለታችንም ተወረወርን። በኔ በኩል ያለውን ፖሊስ በጭንቅላቴ ፊቱን መታሁትና፣ ሲወድቅ ትቼው ተፈተለክኩ። ትንሽ እንደሮጥኩ ማት አጠገቤ እንደሌለ ታወቀኝ። በሩጫ ተመልሼ አጠገቡ ስደርስ «ሂድ መጣሁ» አለኝ። ፖሊሶቹ ተጋድመዋል፣ ግን በጨለማው በደምብ አይታዩኝም። በቀስታ ስራመድ ማት በፍጥነት እርምጃ ደረሰብኝ። ይስቃል

«ምነው ቆየህ?» አልኩት

«ቀበቶና ቁልፋቸውን ስበጥስ» አለኝ እየሳቀ። ብርሀን ጋ ስንደርስ ከቦርሳ ገንዘብ አወጣና ቆጠረ። ሰሞንት መቶ ቲማን (ብር 250,000)።

«ሰማን ነጥቀውት ይሆን?» አለ «ሰሞንት መቶ ቲማን። ነገ ወረቀት የማተሚያ ቤታችን ወረቀት ወደማስቀ ተጻርጓል። ነገ ወረቀት እንገዛለን»

የታተሙትን ወረቀቶች አስረጭተን ከጨረስን በኋላ፣ የደስ ደስ ኬኪ ገዛተን በና በገጠማ ሳቅ እያለ፣

«ሰመሮ» የትናንቱን ፖሊስ ፍንገል እርፐኸው ነበር ለካ የሮጥከው» አለኝ

«እምን» አልኩት

«ተጎስቆ ቢከተልህስ? እና ካንተ የፈጠነ ሮጭ ቢሆንስ? ወይም ከተሮጥ ውጋት ቢይዝህስ? ወይም ቢተኩስብህስ? ወይ ፊሽካ ቢነፋና ሌሎቹ ፖሊሶች ከያለበት ወዳንተ ቢሮጡስ?»



@BOOKALEM

«ታድያ 'ንዴት ማድረግ ነበረብኝ?» አልኩት

«አታውቅም?»

«አላውቅም»

«እንግዲያው ነገ ጧት ባስራ አንድ ተኩል ቤቴ ና»

ከዚያ በኋላ አራት ወር ሙሉ ጧት ጧት ካስራ አንድ ተኩል እስከ አንድ ተኩል ድረስ የሚያውቀውን ሁሉ አስተማረኝ:: ከሱ እኩል ከሆንኩ በኋላ፣ አንድ ሌሊት ማጅራት መቺዎች የሚበዙበት ሰፈር ወሰደኝና «እኔ 'ንግዲህ አላግዝህም፣ ዝም ብዬ ማየት ነው:: ይሄ የመጨረሻ ፈተናህ ነው» አለኝ

አንድ ቦታ ስድስት ዱርዬዎች ከበቡና! ማኑ «ወዲህ በኩል ያሉት ሁለቱ የኔ ናቸው፣ አራቱን ውሰድ» አለኝ በእንግሊዝኛ:: የኔን ሶስቱን አጋደምኳቸው፣ አንዱ ሸሸ:: ፈተናዬን አለፍኩ

(ግን አንድ ሌሊት ኢክስ ውስጥ ብቻዬን ስዘዋወር፣ ሰስት አሜሪካኖች ግድግዳ ላይ ሲፅፍ ይዘውት፣ ሊደበድቡት እንደ ጀመሩ ድንጋይ በመወርወር አስጥዬዋለሁ:: ይህን የአምባዢር ችሎታውን ለምን ከነሱ ለማምለጥ አልተጠቀመበትም? ማወቅ ፈለግኩ፣ ግን አልጠየቅኩትም:: ከፈለገ እሱ ራሱ እንደሚነግረኝ አውቃለሁ)

ማኑ አንድ ሌላ ነገር አስተምሮኛል (አለ ባህሪም) እየሁ፣ ድሮ ሻህ ግርማ ሞገስ ያለው፣ ከነሲሩስ ከነዳርዮሽ የሚስተካከል ንጉስ ይመስለኝ ነበር:: እና እየጠላሁትም አከብረው እፈራው ነበር:: በማኑ ቀልድ እየሳቅኩ በማኑ አይን ሳየው ግን ሻህ ምንም ግርማ ሞገስ የለውም:: በነዳርዮሽ ዙፋን ላይ ተቀመጠ 'ንጂ፣ የነዳርዮሽ ደም ወይም ክብር ወይም ጀግንነት የለውም:: የአንበሳ ቆዳ የለበሰ ውሻ ነው

ብቻ እሱን ተወው. . . .

አንድ ጊዜ የኮረምሻህር ወደብ ከተማ የስራተኞች ማህበር ሰላማዊ ሰልፍና ንግግር ለማድረግ በህግ ተፈቀደለት:: የኛ ፓርቲ ሊያግባቸው ወሰነ፣ እኔና ማኑ በባቡር ሄድን:: ስነ ስርአቱ የሚካሄደው በታጠረ የኳስ ሜዳ ውስጥ ነበር:: ቦታ ቦታችንን ይዘን ንግግሩ የሚደረግበት ሰአት ጥቂት ደቂቃ ሲቀረው፣ ብዙ ብዙ ፖሊሶች በትልቁ በር ሲገቡ አየሁ:: እንደገቡ ፊታቸው ያገኙትን



@BOOKALEM

በዱላ መጨፍጨፍ ጀመሩ

ማኑን «እንሂድ?» አልኩት

«አንተ ሂድ» አለኝ

«አንተስ?» አልኩት

«እኔ ደህና ቦታ እንድይዝና ካለቆቻችን ትእዛዝ ካልመጣ በስተቀር እንዳልለቅ ታዝዣለሁ»

ይህን ጊዜ ሜዳውን ጨኸትና ትርምስምስ ሞልቶታል

«አለቆቻችን የተፈቀደላቸው መስሏቸው ነበር:: ግን ፈቃዱ ወጥመድ ነው:: ስለዚህ አሁን እዚህ መቆም ምንም ጥቅም የለውም:: ና 'ንሂድ» አልኩት

«አልሄድም:: ኮሙኒስት ነኝ:: አለቆቼ ሽሽ ካላሉኝ ልሸሽ አልችልም» አለኝ

«እዚህ መቆምህ ጥቅም የለውማ!» አልኩት

«ምን ታውቃለህ? ይልቅ ሂድ ፖሊሶቹ እዚህ ሊደርሱ ነው:: በወዲያ በኩል ዝለልና አምልጥ» አለኝ

«አንተ ካልሄድክ አልሄድም» አልኩት

«እኔ አለቆቼን እታዘዛለሁ:: አንተም አለቃህን ታዘዝ:: አለቃህ እኔ ነኝ:: በል አሁን ሂድ:: ሂድ!» አለኝ

ሄድኩ:: አጥሩን ልዘል ስል ዘወር ብዬ አየሁት:: ዙሪያውን ፖሊሱና ሰዉ ሲተራመስ ሲከታተት፣ እሱ ሁለት እጆቹን ደረቱ ላይ አጣምሮ እንደ ሀውልት ቆሟል:: በአጥሩ ዘለልኩ

ማኑ ፖሊሶቹ ደብድበውት ሶስት ሳምንት ሙሉ ሀኪም ቤት ተኛ:: መሀል ጣቱ ተሰብሮ ቀረ:: አሁን ሊያጥፈው አይችልም

ማኑ እንዴት ኮሙኒስት እንደሆነ ልንገርህ?

አንድ የትምህርት ቤት ጓደኛ ነበረው:: ጓደኛየው በጣም ጥሩ ልጅ ነው:: ቆንጆ ቆንጆ ግጥሞችን ይደርሳል:: ግን ድሀ ብጤ ነው:: ከዚህም በላይ እጅግ የተዋበ!

አንድ ቀን የዚህ ልጅ አባት ታሰሩ:: በሽተኛ ሚስት፣ ስድስት ትንንሽ ልጆች አሏቸው:: እሱ የመጀመሪያ ልጃቸው ነው:: አባትየው

ታስረው ልጆቼ ምን ይብሉ? ልጁ ጨነቀው:: ያባትየውን ጉዳይ የሚከታተለው የፖሊስ ሹም ቢሮ ሄደና እያለቀሰ የቤቱን ችግር ነገረው:: ፖሊሱ ደግ ነበር:: የልጁ ችግር ገባው:: «ጉዳዩ በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ፣ አባትህን ዝም ብዬ ነፃ ብለቃቸው፣ የበላይ ሹማምንት ይቀጡኛል:: ብቻ ለማንኛውም ዛሬ ማታ ለእራት ቤቴ ብቅ በልና እንመካከርበታለን» አለው

ሲመሽ ልጁ ፖሊሱ ቤት ሄደ:: እራት ከበሉ በኋላ ፖሊሱ ልጁን ያሻሽው ጀመር:: ልጁ በመጀመሪያ ደነገጠ፡ በኋላ ተቆጣ:: ይኼኔ የፖሊሱ ፊት ተለወጠ:: ደግ የነበረው በሀይል ክፉ ሆነ:: ረጋ ባለ ድምፅ ልጁን እንዲህ አለው

«አባትህ በኔ እጅ ነው:: ላስገድለውም እችላለሁ፣ ላሳስረውም እችላለሁ፣ ላስፈታውም እችላለሁ:: ስለዚህ አባትህ ባንተ እጅ ነው ማለት ነው:: እዚህ ከኔ ጋር ካደርክና ካስደሰትከኝ፣ ነገ አባትህ ለምሳ ቤቱ ይመጣል፣ ተነገ ወዲያ መስሪያ ቤቱ ይሄዳል፣ በስህተት መያዙን አስመሰክርለታለሁ፡ ቤቶችህ የሚበሉትን ያገኛሉ:: እኔን እምቢ ካልከኝ ግን አባትህ ወየውለት! ትንንሽ ወንድሞችህና እህቶችህም ምን እንደሚውጣቸው አላውቅም:: ባንተ እጅ ናቸው:: ሁሉም ባንተ እጅ ነው»

ልጁ እሺ እርስዎ 'ንዳሉኝ አደርጋለሁ አለ:: አባትየው ተፈታ:: መስሪያ ቤቱም ተቀበሉት

ልጅየው ውርደቱን ተሸክሞ መጣና የተፈፀመበትን ግፍ እያለቀሰ ለማኑ አጫወተው:: ምን ባደርግ ይሻለኛል? አለው

አየህ፣ ሲለያዩ ፖሊሱ ምን ብሎታል «እኔ የተገደልኩ ወይም የተጎዳሁ 'ንደሆነ፣ ሁለት ሌሎች የፖሊስ ሹማምንት አሉ፡ ጓደኞቼ ናቸው፡ አንተ እንደጎዳኸኝ ያውቃሉ፡ ስለዚህ አባትህን እነሱ መልሰው ያሳስሩታል:: ያን ጊዜስ አባትህን አያርገኝ! ስለዚህ በኔ ላይ የበቀል ሀሳብ ባታስብ ጥሩ ነው» ብሎታል:: ልጁ ምን ይሁን? የተዋረደ ክብሩን ሊበቀል አልቻለም:: ግን ውርደቱ ሊረሳ የሚችል አይነት አይደለም:: ልጁ አልቻለም:: በዛበት:: ከሚችለው በላይ በዛበት:: አበደ:: አበደ በቃ! እብድ ሆነ:: ቤቶቹ በድህነታቸው ላይ ሀዘን ተጨመረባቸው:: ደግሞስ ማን ያውቃል? ኢራንም አንድ ታላቅ ደራሲ ባጭሩ ተቀጨባት ማለት



@BOOKALEM

ይሆናል'ኮ

አይ ኢራን! ስንቱን ጉድ ትችያለሽ! ኢራን ውቢቱ! እንዴት መሰለችህ! አቤት ህዝቡን ብታውቀው! ቋንቋውን ብትሰማው! አይ ህዝብ! እንደ ምንም ብዬ ከሻህና ከጋንግስተሮቹ ነፃ ባወጣው'ኮ የኢራን ህዝብ በደስታ ሊኖር የሚችል ህዝብ ነው:: ክብሩን ልመልስለት ብችል፣ ማንንም ሳይፈራ ሰርቶ ለመብላት ቢችል፣ ሆማ ካልጣሰ ማንም ሊያስረው እንደማይችል እርግጠኛ ለመሆን ቢችል፣ ሻህና አሜሪካኖቹ ሀብቱን ባይነጥቁት! — ብቻዬን እንዳልመስልህ! በጭራሽ ብቻዬን አይደለሁም:: እኔ ያየሁትን ያዩ፣ እንደኔ የሚቀረቀሩ፣ እንደኔ የተናደዱ፣ እንደኔ ደም ለማፍሰስ ዝግጁ የሆኑ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ኢራናውያን አሉ:: አሉ! አሉ! የሚመራቸውን ይጠብቃሉ! (አለ ባህራም)

ባህራምና እኔ ከተዋወቅን ጀምሮ እስከተለያየን ድረስ ስለኢራን ያወራልኝ ነበር:: ኢራን፣ ኢራን፣ ኢራን:: አልሰለቸኝም ግን ይበዛብኝ ነበር:: ይልቁንም የአገሩ መበስበስ ያንገሸግሸኝ ነበር:: ሁሉ ነገር በጉቦ ነው:: ፖሊሱ፣ ዳኛው፣ አስተማሪው ሳይቀር ጉቦ ይበላል:: ልጅህ ፈተናውን የሚያልፈው ለአስተማሪው ጉቦ ከሰጠኸው ነው:: ወዘተርፈ. . . የመጥፎውን ያህል ብዙ ጥሩ ነገር ይነግረኝ ነበር:: ብቻ አብዛኛው ጥሩ ነገር በናፍቆት ቀለማት ያጌጠ በመሆኑ የመጥፎውን ነገር ያህል እምነቴን አይማርከም ነበር

ለምን ስለኢራን ይህን ያህል እንደሚለፈልፍ ቀስ በቀስ እየገባኝ ሄደ:: ካገሩ ከወጣ ብዙ ጊዜው ነው:: አገሩና እዚያ የሚደረገው ነገር አልተረሳውም፣ ግን ሩቅ ከመሆኑ የተነሳ እንደ ህልም እየሆነበት ሄዷል:: ጊዜ ሊያሸንፈው ሆነ:: ስለዚህ ስለ አገሩ ብዙ ማውራት አለበት:: ቃላቱ የጊዜ ወንዝ ዳር የተተከሉ ሳሮች ናቸው:: ወንዙ እንዳይወስደው ሳሮቹን እየተቆናጠጠ ይከራከራል. . . እስከ መቼ ድረስ?

አንዳንድ ጊዜ ተስፋ ይቆርጣል:: እዚህ ቁጭ ብዬ ምን እሰራለሁ? ወይ ጠበንጃ አልቀሰቀስኩ፣ ወይ አገሬ ገብቼ ሬቮሉሽን አላገዝኩ:: ታድያስ? ቁጭ ብዬ እንጠልጥዬ ሄጄ ቪየት ኮንጎችን አላገዝኩ::



@BOOKALEM

ይላል:: እዳ አከማቻለሁ፡ ጊዜዬን አሳልፋለሁ፡ እድሜዬን እገፋለሁ፣ ያ የማይበገር መንፈሱ ለጊዜው ይሸነፋል

ያን ጊዜ እኔ አወራለታለሁ:: ስለሌኒን፣ ስለማኦ፣ ስለ ሆ-ቺ-ሚን፣ ስለ ካስትሮ እነግረዋለሁ:: በጊዜያቸው ከሱ የባሰ ብቸኝነት እንዳጠቃቸው፣ ከሱ የከፋ ጭንቀት እንዳፈናቸው፣ ከሱ ለረዘመ ጊዜ ስራ ፈትተው መቀመጥ ግድ እንደሆነባቸው፣ ከዚያ በኋላም ያን ሁሉ ችግር ጥሰው፣ ያን ሁሉ ተስፋ መቁረጥ ዘልቀው፣ በድል አድራጊነት ብቅ እንዳሉ፣ ብቅ ብለውም አለምን እንዳናወጡ፣ ጠላታቸውን አፈር እንዳስጋጡ፣ ለተጠቃ ህዝባቸው እንጀራና ክብር እንደሰጡ፣ አልሸነፍ ባይ ተስፋ አልቆርጥ ባይ በመሆናቸው ታሪክ ውስጥ ስማቸውን በደምና በእሳት እንደፈረሙ፡ — ይህን ሁሉ ደጋግሜ እነግረዋለሁ

እሱ ራሱ ከኔ ይበልጥ የሚያውቀውን ከኔ አፍ ሲሰማው ይፅናናል

«ለሁሉ ጊዜ አለው» እለዋለሁ «የልብን ለማድረስም ጊዜ አለው፣ ያ ጊዜ እስኪመጣ ቁጭ ብሎ ለመታገስም ጊዜ አለው:: አሁን አንተ ልታረግ 'ምትችለው አንድ ነገር ብቻ ነው:: እጅህን አጣምረህ ጊዜህን ጠብቅ:: ተዘጋጅ:: የሬቮሉሽን ጊዜ፣ ቆሻሻ ደም የማፍሰስ ጊዜ፣ ለተጠቃ ህዝብህ ነፃነትን በገፍ የማደል ጊዜ ይመጣል:: ስለዚህ ያ የተባረከ ጊዜ ሲመጣ ተገቢውን ዝግጅት ሳታደርግ ይደርስብህና ወየውልህ!»

«ምን ዝግጅት ለማረግ እችላለሁ?»

«ውስጣዊ ዝግጅት:: ዋናው ዝግጅት እሱ ነው:: ለንጉሥ ለነካስትሮ የወጣው ቀይ የንጋት ኮከብ ላንተም ይወጣልሀል»

ዝም ይላል:: ዝም ሲል የኢራንን ሻህ ይመስላል

አንድ ቀን «የኢራን ሰው ብትሆን እንዴት ጥሩ ነበር!» አለኝ

«ለምን?» ስለው

«ታስፈልገኛለህ» አለኝ «በጣም ታስፈልገኛለህ:: እኔ መፃፍ አላውቅም:: ማድረግ ብቻ ነው:: ግን ለሬቮሉሽን ማድረግ በቂ አይደለም:: ማድረግ ግማሹ ነው:: ሌላው ግማሽ መፃፍ ነው:: አዋቂዎቹን ለማሳመን ሀቁን መፃፍ፡ ተራውን ህዝብ ለማሳመን



@BOOKALEM

ፕሮፓጋንዳ መፃፍ:: ይህን እኔ የማሳውቅበትን ግማሽ ትሰራልኝ ነበር:: እኔ ደሞ የማድረጉን ግማሽ አንተ ለሁለት ግሩም ገድል እንጀምር ነበር:: እንደኛ ያሉ ስድስት ሰባት ሌሎች እንፈልግና በቃ ነገሩ ተጀመረ ማለት ነበር:: ያን ጊዜ ማን ያቆመን ነበር!?

«በፊት ከማኑና ከሌሎቹ ጋር ነበርኩ:: ብዙ እትድ ብዙ ተስፋ ነበረን:: አሁን ማን የት እንደደረሱ ወይም ምን እንደዋጣቸው 'ንጃ:: ማኑ ለንደን ነበር:: ጠፋ:: ሞተ 'ሲ.አይ.ኤ' ገደለው? እንጃ:: ብቻዬን ነኝ በቃ:: እዚህ ያሉት ያገሬ ልጆች 'ንደሆኑ ጀግንነታቸው እምስ ማደን ብቻ ነው:: አገሬ ገብቼ እንዳንተ አይነት ሰዎች እንዳልፈልግ እንዴት እገባለሁ? ብገባስ የት አገኛቸዋለሁ? የለም'ኮ እንዳንተ አይነት ሰዎች፣ ይገባሀል? የሉም:: ኢራን ውስጥ አሁን የሉም:: ጥቂት ነበሩ፣ 'የሲ.አይ.ኤ' ሰዎች ከሻህ ጋር ሆነው አረዷቸው:: አሁን የቀሩት መሪ ካገኙ የሚከተሉ ናቸው፣ እንጂ ራሳቸው ለመነሳት የሚችሉ አይደሉም

«እንዴት ነው የደከመችው ኢራን! እንዴት ነው የቆሸሸችው አገሬ!

«መለወጥ አለባት:: ኢራን መለወጥ አለባት:: ጋንግስተሮች እየገዙዋት መኖር አትችልም:: መለወጥ አለባት:: ህዝቡ ዘለአለም ተጨቁኖ መኖር አይችልም:: ዘለአለም በፍርሀት እየተርበተበተ መኖር አይችልም:: ዘለአለም አንገቱን አቀርቅሮ መሄድ አይችልም:: ገዢዎቹ ተወግደው መሪዎች መምጣት አለባቸው:: ህዝቡ ቀና ብሎ የመሪዎቹን አይን በማይፈራ አይን ለማየት የሚችልበት ቀን መምጣት አለበት

«ይህ ቀን ይመጣ ዘንድ ስንቶቹ ህይወታቸውን ሰውተዋል! እቤት ስንቶቻችን በተጨማሪ መሰዋት ይኖርብናል!

«ደም መፍሰስ አለበት:: ብዙ ቆሻሻ የተመረዘ ደም መፍሰስ ይኖርበታል! ሳስበው ያሳዝነኛል፣ ያስፈራኛል. . .

«ግን አንተ በጣም ታስፈልገኝ ነበር» አለ ወደፊተኛው ሀሳቡ እየተመለሰ

«እኔኮ በሬቮሉሽን አላምንም» አልኩት

«ኢራን ተወልደህ ኢራን አድገህ የኢራንን መበስበስ አይተህ ቢሆን ኖሮ በሬቮሉሽን ማመንህ አይቀርም ነበር:: ሌላ ምርጫ አይኖርህማ!»

«በጭራሽ!» አልኩት «አንተ'ኮ ሬቮሉሽን ለማድረግ «በጭራሽ!» የምትፈልገው፣ በሰው ልጅ ጥሩነት የፀና እምነት ስላለህ ነው:: የሰው ልጅ ካልተጨቆነና ካልተጠቃ ሰርቶ ይበላል፣ ብጤውን ይወዳል፣ ብለህ ታምናለህ:: እኔ ግን የሰው ልጅ በተፈጥሮ መጥፎ፣ ግፍ መሆኑን እርግጠኛ ነኝ:: ሻህና አሽከሮቹ ቢሻሩ፣ የሚከተሉት መሆኑን እርግጠኛ ነኝ:: ሻህና አሽከሮቹ ቢሻሩ፣ የሚከተሉት ገዢዎች ያው ተመልሰው ህዝቡን ይጨቁናሉ

«ፖሊሱንና ጥቃቅኑን ዳኛ ውሰድ:: በሁሉ ነገር ተራ ሰው ናቸው:: ግን ትንሽ ስልጣን ስለተሰጣቸው፣ በዚያች በትንሽ ስልጣናቸው ህዝባቸውን ያጠቃሉ፣ ይጨቁናሉ:: ይህ ያስቆጣሀል:: ግደላቸው ይልሀል:: ግን ልብ አድርግ:: የሚጨቆነው ተራው ሰው፣ የነሱ ስልጣን ለሱ ቢሰጠው፣ ልክ እነሱ የሚሰሩትን ግፍ ይሰራል:: ጭቦና ጭቆና ሊቀር የማይችል የሰው ልጆች እጣ ነው:: እንግዲህ ጥያቄው 'ማን ይጨቁን፣ ማንስ ይጨቆን?' ነው 'ንጂ 'እንዴት አድርገን ጭቆናን እናጥፋ?' አይደለም:: ሰው ከስረ መሠረቱ እስቀያሚ፣ መጥፎ፣ ክፉ ነው:: ስለዚህ፡ ለሰው ልጆች ብዬ እንኳን ሀይወቴን ልሰዋ ይቅርና፣ ያንድ ቀን እንቅልፌን አልሰጥም::»

«ውሸትክን ነው» አለኝ «ውሸትክን ነው 'ንዲህ 'ምትለው:: የፈረንሳዮቹ ፍቅር-የለሽነት በመጠኑ ተላልፎብህ ነው:: ከልብህ ሰው እንዲህ ክፉ ከመሰለህ፣ ለምን እኔን ትመማበኛለህ? ለምን ተስፋ ስቆርጥ ታፅናናኛለህ? ሀብታም አይደለህም:: ግን፣ እንደማልከፍልህ እያወቅክ፣ ካቅምህ በላይ የሆነ ገንዘብ ለኔ ታወጣለህ:: ለምን?»

«አንተማ አንድ ሰው ነህ:: የሰው ልጆች በጠቅላላው አይደለ ህም:: አንተን ብቻህን ሳይህ ጎበዝና ብርቱ ሆነህ ትታየኛለህ:: በሚል ዮን ውስጥ እንዳንተ ያለ አንድ እንደማይገኝ ይሰማኛል:: ደሞ ላንተ ስል አይደለም:: ካንተ ጋር ስሆን ደስ ስለሚለኝ፣ ለራሴ ስል ነው::»

«አይምሰልህ:: አይምሰልህ:: እንግዲያው ለምን መፃፍ ትፈልጋለህ? እውነቱን ንገረኝ 'ስቲ::»

«መፃፍ ደስ ይለኛል::»



@BOOKALEM

«ለምን? እውነትን በምታየው አኳኋን ለመግለጽ ስለምትፈልግ አይደለም?»

«እምን»

«ለምን? እውነትን ካወቅካት አይበቃህም? ለምን እንዚህን ለመግለፅ ጊዜህን ታጠፋለህ?»

«እኔ 'ንጃ»

«ለሌሎች ማጋራት ፈልገህ ነው፡፡ እውነትን ላላወቁ ለማሳወቅ፣ ውበትን ላላዩዋት ለማሳየት፣ ስለህይወት የሚሰማህን አድናቆት ለሌሎች ለማካፈል፡፡ ለዚህ ነው 'ምትፅፈው፡፡ ምክንያቱም ወገኖችህን ትወዳቸዋለህ፡፡ ሰውን ትወዳለህ፡፡ ባትወድ ኖሮ እንደዚህ አትሆንም ነበር፡፡ ለኔ የተሰጠኝ እድል ለሰዉ ሁሉ ቢሰጠው ኖሮ እንደኔ ይሆን ነበር፡፡ ሰው ሁሉ እንደኔ ቢሆን፣ ሀያ ሚልዮን እንደኔ ያሉ ሰዎች በባርነት በጭቁና ሲኖሩ ብታይ፣ ሬቮሉሽን ልትቀሰቅስላቸው አትሞክርም ነበር?

«አየህ ሰው በመሰረቱ ጥሩ ነው፡፡ የትም አገር ሄደህ መንገድ ይጥፋህ፡፡ ያገኘኸው ሰው ሁሉ ሊመራህ ዝግጁ ነው፡፡ እኔ እንደ ፈረንሳዮች ለሰው ግድ የሌለው ህዝብ አይቼም ሰምቼም አላውቅም፡፡ ግን የፈለግከውን ፈረንሳዊ ተማሪ፣ ትምህርት እምቢ አለኝ፣ እንዴት ላድርግ በለው፡፡ ከልቡ ሊረዳህ ይሞክራል፡፡ ያስተማሪዎቹን ፀባይ ይገልፅልሀል፡ ምን ምን መፅሀፍ ማንበብ እንደሚጠቅምህ ያስረዳሀል፡ የራሱን መፃህፍትና ደብተሮች ያውስሀል፡፡ . . . ሰው መጥፎ የሚሆነው ጥቅሙን የነካህበት 'ንደሆን ብቻ ነው ወይም ነገርዎቹ መጥፎነቱን ለማረም እንደመጣር፣ ክፋቱንና ጭካኔውን በብልሀት እየኮተኮቱ ያሳደጉት እንደሆን ነው፡፡...»

«እሱን ተወውና፣ ስለካስትሮ የማታውቃት እንዲት ትንሽ ታሪክ አለች፡፡ ልንገርህ?» አልኩት

«ንገረኝ». . .

. . . እየህ፣ ካስትሮ የአብዮቱ መልካም ሂደት በአለም እንዳይታወቅ በአሜሪካ mass media ስለታፈነበት፣ ሚዛናዊና በህዝባቸው ተደማጭ የሆኑ ምእራባውያን ጋዜጠኞችንና ደራሲያንን



@BOOKALEM

በአክብሮት ጋብዞ መጥተውለት፣ ኩባን እያዞረ በሚያስጎበኘበት ጊዜ፣ በጂፕ ሲሄዱ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ እንደደረሱ፣ ድንገት አንድ ትልቅ ደንደሳም ጡንቻኛ ጥቁር ሰውዬ ከየት መጣ ሳይባል መንገዳቸው ላይ ቆመ

መትረየስ እያነጣጠረባቸው፣ ካስትሮን

«የት ነው 'ምትሄደው?» አለው

ካስትሮ «እንግዶች ይገርለሁ፡ ለማስጎብኘት ነው» አለው

ሰውየው «በዚህ በኩል መሄድ አትችልም» አለው

«ለምን»

«አደገኛ ነው:: እንግዶችህ ቢፈልጉ በዚህ ሊሄዱ ይችላሉ:: አንተ ግን በወዲያ በኩል ዞረህ መሄድ አለብህ::»

ካስትሮ «በዚያ በኩል መሄድ ብዙ ብዙ ሰአት ያጠፋብናል:: ስለዚህ በዚህ መሄድ አለብን» አለው::

ሰውዬው በጣም ተቆጣ:: «አደገኛ ነው እያልኩህ እንዴት በዚህ ልሂድ ትላለህ? ለኛ አታስብም 'ንዴ? አንተን አደጋ የደረሰብህ 'ንደሆን፣ እኛ ምን እንሆናለን? የት እንገባለን? ምን ይውጠናል? አይገባህም?» አለው

ካስትሮና እንግዶቹ በዙሪያ መንገድ መሄድ ግድ ሆነባቸው::»

የባህሩም ቡናማ አይኖች በልዩ ብርሀን ተሞሉ — ብርሀን አይደለም፡ እምባ ነው — የሀዘን እምባ አይደለም፡ ሌላ አይነት እምባ ነው:: ከዚህ በፊት አንድ ጊዜ እንዲህ አይነት እምባ አይኖቹ ውስጥ አይቼ ነበር

በነጭ መሀረብ አይኖቹን እያዳበሰ

«እንደዚህ ውብ ታሪክ ሰምቼ አላውቅም» አለኝ. . .

. . . ባህሩም ስለኢራን ሲያወራልኝ አርፍዶ፣ በየሙሉው ሰአት ስለቪየትናም ወሬ ስንሰማ አርፍደን፣ የምሳ ሰአት ሲደርስ ወደ ዩኒቨርሲቲው ምግብ ቤት እንሄዳለን:: አንዳንድ ጊዜ ባጋጣሚ ከአሜሪካን ተማሪዎች ጋር ስንቀመጥ፣ ወሬ መጀመሩ አይቀርም:: አብዛኛውን ጊዜ እየሳቀና እነሱንም እያሳቀ፣ እንደማይረቡና ተስፋ

እንደሊላቸው ይነግራቸዋል:: ሳይንሳችሁ የሚራመደው በጀርመኖች እውቀት ነው፣ በሲኒማ አሰራር ጣልያኖንና ስዊድን ይበልጧችኋል ይላቸዋል በስነፅሁፍና በፖለቲካ እንግሊዞች ያስከነዷችኋል፣ በአርትና በአእምሮ ስልጣኔ ፈረንሳዮች ያፐፏችኋል ይላቸዋል::

ስለምንም ቢያወራ ዞሮ ዞሮ ወደ ኩባና ቬየትናም ይመጣና «ብጦርነት ኩባን ለመውረር ስትሞክሩ፣ ካስትሮ በኩርኩም ብሎ መለሳችሁ – "Bay of Pigs ውጊያ ላይ ሽንፈትን፣ ውርደትንና እፍረትን አከናነባችሁ:: – የBay of Pigs ቅሌት!» አለ ነፃው አለም ሁም:: ከስህተታችሁ የመማር ፀጋ አልተሰጣችሁማ! "The bigger they come, the harder they fall" በምትሉ ጊዜ'ንኳ ስለገዛ ራሳችሁ መተንበያችሁ አይታያችሁም:: አሁን ደሞ ቬየትናምን ለመውረርና ለመግዛት ትሞክራላችሁ፡ ግን ጀግናው ሆ-ቺ-ሚን ገትሮ ይዟችኋል» ይላቸዋል

ንግግሩን ሁልጊዜ በኢራን ይደመድማል «እኔ ደሞ ትምህርቴን ጨርሼ አገሬ ስመለስ፣ ከኢራን እየነዳሁ አስወጥቼ፣ ህንድ ውቅያኖስ ውስጥ እጨምራችኋለሁ:: ምን አለ በሉኝ!»

ይስቃሉ

ይህን ሁሉ ሲልና ከአሜሪካኖቹ ጋር ሲከራከር፣ እኔ ዝም ብዬ እሰማለሁ:: ምሳዬን ወይም እራቴን እየበላሁ:: አንድ ጊዜ ግን ከአንድ ጉረኛ አሜሪካን ጋር ክርክር ገጠመ

ባህራም እንደ ልማዱ ከሙግቱ ጋር ቀልድና ሳቅ ሊቀላቅል ሞከረ:: አሜሪካኑ ግን በሀይል አምርሮ ስለ አሜሪካን የጦር ሀይል ሲሸልል፣ ስንት የጦር መርከብ፣ ስንት የጦር ኢሮፕላን እንዳላቸው ሲያወራ፡ እንኳን ሆ-ቺ-ሚን፣ ክሩስቾቭና ማኦ፡ እንደዚሁም ሌሎቹ ችጋራሞች ኮሙኒስቶች ተሰብስበው ቢመጡ፣ አሜሪካ ብቻዋን ድምጥማጣቸውን እንደምታጠፋቸው፣ የዚህም ማስረጃ በ61 ዓ.ም. የኩባ ፍጥጫ ላይ ኬነዲ ኮሙኒስቶቹን ፈሳቸውን አስረጭቶ ከኩባ እንዳባረረ – እንደዚህ እያለ ጉራ ሲነፋ አበሸቀኝ:: ባህራምም መሳቁን ትቶ ዝም ብሎ ይሰማዋል:: አሜሪካኑ

«አሁን ብንፈልግ ሆ-ቺ-ሚንንና ቬየትኮንጎቹን በአንድ ሳምንት



@BOOKALEM

ውስጥ እናስፈሳቸዋለን!» ሲል፣ ምን እንደነካኝ ሳላውቅ

«እዚህ ላይ አንድ ነገር አለ» አልኩ:: እየሳቅሁን አንዴ ቃል ሳልተነፍስ ስለቆየሁ፣ ባህራምም፣ አሜሪካኑም፣ ሌሎቹም ገበታችን ላይ የነበሩት፣ ወደኔ አዩ:: አጭር ዝምታ

«ታሪክን ብናስታውስ» አልኩ «በ480 አመተ አለም፣ ብዙ በሚሊዮን የሚገመት የፋርስ ጦር ሰራዊት ግሪኮችን ለመውረር መጣ:: ቴርሞፒሌ ላይ ሌዎኒዳስ የተባለው የስፓርታ ንጉስ አራት መቶ ወታደሮቹን አሰልፎ ሲጠብቅ፣ ከፋርስ ንጉስ ወይም ከጦር አበጋዙ እንዲህ የሚል ማስፈራሪያ ደረሰው:: 'እጅህን ብትሰጥ ይሻልሀል:: የኛ ቀስተኞች ሲተኩሱ፣ ፍላጻዎቹ ከመብዛታቸው የተነሳ፣ ፀሀይዋን ይሸፍኗታል::'

እና ሌዎኒዳስ ምን አለ ይመስላችኋል?»

አሜሪካኑ «ምን አለ?» አለኝ

«መልካም ነው:: እኔና አራት መቶዎቼም ጥላ ውስጥ ሆነን ብንዋጋ እንመርጣለን» አለ

ዝም አሉ:: የምግብ ቤቱ ጩኸት ከቦናል

ባህራም «ቀጥል» አለኝ

«ምን እቀጥላለሁ? ታውቁታላችሁ'ኮ:: ሌዎኒዳስና አራት መቶው አለቁ:: ሆኖም ግን የፋርስን ቁጥር-የለሽ ሰራዊት ጉትረው በመያዛቸው የውጊያው ሚዛን በነሌዎኒዳስ መስዋእትነት ወደነሱ ስላደላ፣ ግሪኮቹ ወራሪውን ሰራዊት ድል አድርገው አበረሩት። ታድያ በጦር ብዛት ቢሆን ኖሮ፣ ፋርስ ያን ጊዜ የአለምን ጦር በሙሉ ሊያሸንፍ ይችል ነበር:: ግን የሰው ልጅ ለነፃነት ሲዋጋ በጦር መሳሪያ ብቻ ሳይሆን በወኔው፣ በንዴቱ፣ በወንድነቱ ጭምር ስለሚዋጋ፣ ማንም ትልቅ ጦር አይችለውም:: ለዚህ ነው እነሆ-ቺ-ሚን ሊሸነፉ የማይችሉት::»

ይህን ጊዜ ምሳችንን ጨርሰን ስለነበረ ባህራም እየሳቀ አሜሪካኑን «ለዚህ መልስ ለማግኘት አትሞክር:: እውነት በሉን መልስ አይገኝለትም» አለው «ይልቅ ለኬኔዲ ሀቁን ንገረው:: እና አንድ ሌላ ነገር አለ ለኬኔዲ መንገር ያለብህ:: ማኦ የቻይናን ህዝብ በሙሉ ለጦርነት ተዘጋጅ ብሎ ማዘዙን ታውቅ የለ? ደሞ የቻይና

ህዝብ በማኦ ትእዛዝ ዋና በመሻገር ላይ ይገኛል። በየቀኑ ሰባት ሚልዮን ቻይናዎች የዋና ልምምድ ያደርጋሉ። እርጊትና ሽማግሌው ሳይቀር ባኞ ውስጥ ይዋኛል። ልምምዳቸውን ከጨረሱ በኋላ 'ንግዲህ ምን እንደሚያደርጉ ታውቃለህ? ማኦ እየመራቸው የፓሲፊክን ውቅያኖስ በዋና ያቋርጡና፣ እናንተን በአለንጋ አርባ ገርፈው ሲያበቁ፣ አሻንጉሊቶቻችሁን በሙሉ ይቀሟችኋል። «ጥሩ ልጆች የሆናችሁ እንደሆን፣ አሻንጉሊቶቻችሁን እንመልስላችኋለን፣ አለዚያ ግን መጫወቻ ታጣላችሁ። ልባርጉ!» ብለዋችሁ ሲያበቁ፣ ወደአገራቸው ተመልሰው በሰላም ይኖራሉ። ይህን ለኬነዲ ንገረው» አለውና እኤን እንሂድ አለኝ። አሜሪካኑ ለመሳቅም አልቻለ፣ ለመናደድም አልቻለ። ግራ ገብቶት ባህራምን አየው

እኤና ባህራም ትተነው ከምግብ ቤቱ ወጣን። መኝታ ቤት ሄደን ቡና ከጠጣን በኋላ፣ እንዲያጠና ወይም ስለሬቮሉሽን እንዲያነብ ትቼው ወጥቼ ሲኒማ ለመግባት ወደ ኩር ሚራቦ በኩል አመራሁ

ግን ሲኒማ አልገባሁም። በካፌ ዶርቢቴል በር ሳልፍ፣ ውስጥ ሲልቪን አየኋት። ፊቷን ወደበር በኩል አርጋ ተቀምጣ ጋዜጣ ስታነብ ነበር፣ አየችኝ። የፈገግታዋን ውበት ረስቼው ኖሯል፤ አሁን ሳየው በጣም ደስ አለኝ። ወደኔ መጣች። ስትራመድ አንገቷን እያወዛወዘች ስለሆነ፣ ከረዥምም ነጭ አንገቷ በስተኋላ የተለቀቀው ጥቁር ሀር ፀጉሯ ዠው ዠው ይጫወታል። ይህንንም ረስቼው ኖሯል። መጣችና ጉንጩን ስማኝ

«ከነገ ወዲያ ነበር ልመጣ ያቀድኩት፣ ግን በሀይል ናፈቅከኝ» አለችኝ። እሷ ስትናገረው ፈረንሳይኛው መጣፈጡ! ወደ ቤቷ በኩል እየተራመድን፣

«እንኳን መጣሽ! በሀይል ናፍቀሽኝ ነበር» አልኳት

እንደ ልማዷ «ዣማንቴ» ሳቋን እያሳቀች «እኤን የምታስረሳህ ሴት አላገኘህም?» አለችኝ። እንዳላገኘሁ ታውቃለች። መቸም እንደማላገኝ እርግጠኛ ነች።

«ሴት የሚሉት ነገር ዘወር ብዬም አላየሁ» አልኳት

«እንግዲያው ምን ስትሰራ ሰነበትክ?» ጫማዋ መንገዱን ኳ! ኳ!

«እንግዲያው ምን ስትሰራ ሰነበትክ?» ጫማዋ መንገዱን ኳ! ኳ! ቢያረገው ይሰማኛል፣ ከጎኔ ድምፅዋ ይሰማኛል፣ ስፊ አፏ ላይ ውብ



@BOOKALEM

ፈገግታዋ ይታየኛል፤ ደስታ ይሰማኛል

«ሲኒማ ሳይ። እና ከባህራም ጋር ሳወራ»

«ምን ምን አወራችሁ?»

«እ —! ብዙ ነው»

«ንገረኝ»

«ጊዜ የለኝም። ዛሬ ካንቺ ጋራ ማውራት አልፈልግም» አልኳት ምኞቱ ውስጧ ማበጥ ጀምሯል። ቤቷ እስክደርስ ቸኩያለሁ

«ማውራት አለብህ፤ ሌላ ነገር ለመስራት አትችልም» አለችኝ

«ለምን?» ብዬ አየኋት። ከጎኔ ስትራመድ ጭንቅላቷ ይወዛወዛል ወደኔ አታይም። ፊቷ በጣም ቀልቷል። አፍራለች። ዝም አለች

«ለምን? ለመመንከስ ቆርጠሻል 'ንዴ?» ዝም አለች። «ምን ሆንሻል?»

«አሞኛል»

«ምንሽን?»

«አንተ 'ምትጠይቀውን ጥያቄ መችስ የመንደር ቂል እንኳን አይጠይቀውም።»

«አትቆጪ። ምን ሆንሽ ነው? ማለቴ —»

«ነገሩ ትንሽ ነው። ሀኪም አይቶኝ መድሀኒት ሰጥቶኛል። ከአንድ አምስት ቀን በኋላ ይድናል ብሎኛል።» ድንገት ሳቀች። «ብቻ ቂጥኝ ወይም ጨብጦ እንዳልሆነ እርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ» አለችኝ፣ ሳቋን ትታ «ይልቅስ ስለባህራም ንገረኝ።»

ስለባህራም ሳጫውታት፣ ተንሳስቶ የነበረ ስሜቴን ረሳሁት። ቤቷ ገብተን፣ ቡና በወተት አፍልታ ጠጥተን፣ ለብዙ ጊዜ አወራሁላት። ስጨርስ እስተያየቷን ባጭሩ ገለፀችልኝ

«ይሄ ባህራም እንደ ፖል አይነት ሰው ይመስላል» አለች

«ለመሆኑ ስለፖል ትሰሚያለሽ?»

«ፓሪስ ስሄድ አንድ ደብዳቤ አገኘሁ። ፖል በቬየትናምና በላኦስ መካከል እየተመላለሰ የደፈጣ ተዋጊዎቹን ያግዛል። በደፋ ባይታወቅ ነው 'ንጂ፣ አሜሪካኖቹ ላኦስ ውስጥም ይዋጋሉ። የደፈጣ

ተዋኒዎቹ ፖልን ኮሎኔል ነው የሚሉት። በጣም ይወዱታል።»

«ሌላስ ምን አለ?»

«ምንም አላለ። እሱን ተወውና ናፍቄህ እንደሆን አሳየኝ እስቲ» አለችኝ። ውብ ፊቷ ላይ ቅንዝረኛ ፈገግታ ይርበተበታል። ባንዳፍታ ረሳኋቸው። እሷ እንደተቀመጠች ከፊቷ ተምበርክኬ አንገቷን እስመው ጀመር። አንገበገበኝ። ተለይታኝ ስለቆየችና እሁንም ላገኛት ባለመቻሌ፣ ስሜቱ እንደ እብድ አደረገኝ። ምንም ማድረግ እንደማልችል እያወቅኩም ልብሷን አስወለቅኳት። የነበረውን ውብ ገላዋን ማየትና መቃጠል አማረኝ። ናፍቆኝ የተቀረፀ ድንቅ እግሮቿን መሳም ጀመርኩ። ቀስ እያደረገ ስሜቱ ሁለታችንንም እንደ አዙሪት እያቃጠለ ያሽከረክረን ጀመር። ከስአት በኋላውን በሙሉ በስሜት ስንቃጠል አሳለፍነው። ሁለታችንም አንድ ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ተገንዘብን። ወጣት ሆኖ አልጋ ውስጥ መተቃቀፍና፣ እየተያዩ፣ እየተሻሹ፣ እየተሳሳሙ፣ እየተናከሱ፣ እየተላላሱ መቃጠል፣ የስሜትን ጥም ከማርካት የበለጠ ደስታን ሊሰጥ ይችላል. . .

* * *

ባህራም ፈተናውን በጭራሽ አልፋለሁ አላለም ነበር። ግን አለፈ። በጣም ገረመው። እኔን «አንተ ነህ የቀናኸኝ» አለኝ። «እስቲ ና ስራ አፋልገኝ። አሁንም ያንተ ውቃቢ ይቀናኝ ይሆናል'ኮ።»

ትምህርት ተጀምሮ አንድ ወር ያህል እንዳለፈ፣ ባህራም ከኤክስ ውጪ፣ ጋርደን የምትባል መንደር አጠገብ አንድ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎች ሞግዚትነት ስራ አገኘ። ብዙ ትርፍ ጊዜ ስላለው፣ ትምህርቱን ሊያጠና ይችላል። በየሁለት ሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ እረፍት ስለሆነ፣ ኤክስ መጥቶ ከኒኮል ጋር ያሳልፈዋል፣ እኛንም ያገኘናል፣ ስለተማሪዎቹ ብዙ ኮሚክ ነገር ያወራልናል። እነ ሉልሰገድን ምን ምን አንዳንድ ጊዜ በስራ ቀንም ብቅ ይልና፣ እንደተማሩ ጠያይቆ፣ ደብተርና መፃህፍት አውስውት ይሄዳል

አንድ ቀን ትምህርት ቤቱ ልንበኘው ሄጀ «ያንተ እድል በጣም ቀንቶኛል» አለኝ «ስራዬ ከልጆች ጋር መኖር ነው። ጂምናስቲክ አሰራቸዋለሁ፣ አልጋቸውን እንዲያነጥፉ፣ ንፅህናን እንዲጠብቁ አደርጋለሁ፣ ዲሲፕሊን አስከብራለሁ። እነሱም በጣም ይወዱኛል።



@BOOKALEM

እንዳንዴ በፈረንሳይኛዬ ይቀልዳሉ:: ለጥናት ብዙ ጊዜ አለኝ:: ጥናቱ ደሞ መቅለሉ! እንብቦ መረዳቱ ሁለት ሰአት ይወስድብኝ የነበረ ምእራፍ፣ አሁን ግማሽ ሰአት ይበቃዋል:: ግማሽ ሰአት! ለምን ብትል፣ በዙሪያዬ ገንዘብ የተበደርኩት ሰው የለም፡ ካገሬ ደብዳቤ መጥቶልኝ ይሆን? ብዬ አላስብም — ቢመጣልኝም ኤክስ ይጠብቀኛል እንጂ እዚህ ስለማይመጣ::

ስለዚህ ኤክስ እስክሄድ ሰላም ውስጥ እስነብታለሁ:: ከሁሉ የበለጠ ግሩም ስሜት የሚሰማኝ መቼ መሰለህ? ከተማሪዎቼ ጋር ምሳ ወይም እራት ስበላ:: ሰው አይደለም የሚጋብዘኝ፣ እኔው ራሴ ነኝ የምመገበው:: በሰው ደግነት ሳይሆን በራሴ ልፋት ነው እስከጠግብ የምበላው:: አቤት እንዴት ያለ ግሩም ስሜት ነው! ይመስለኛል፣ ችግርን መቅመስ ብዙ ጥቅም አለው:: ለምሳሌ ሰው ብዙ ሰርቶ ለፍቶ መኖር ይመረዋል:: ግን ስራ አጥቶ መንቀዋለልንና፣ ምን አበላ ይሆን ብሎ መስጋትን የቀመሰ ሰው፣ ሰርቶ፣ ለፍቶ ለመኖር መቻል ትልቅ እድል መሆኑ ይገባዋል:: ስለዚህ ደስታን ያገኛል:: . . . አንዳንድ ጊዜ ምን ብዬ አስባለሁ ይመስልሀል? ይህን የደረሰብኝን ችግር መቀበሉን ብችልበት፣ አስተያየቱን ብችልበት፣ የተሻልኩ ሰው ሊያደርገኝ ይችል ይሆናል'ኮ፣ ብዬ አስባለሁ::»

@BOOKALEM

# ቡክ - አለም

@BOOKALEM

የመፅሐፍት መንደር

የቴሌግራም ቻናሉን

SUBSCRIBE

ያድርጉ

@BOOKALEM

## ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

# ትኩሳት



# ቡክ - አለም

@BOOKALEM

የመፅሐፍት መንደር

የቴሌግራም ቻናሉን

SUBSCRIBE

ያድርጉ

@BOOKALEM

# ሰምንት

## ኒኮል
## ፍትወት

ባህራም ወደ ጋርደን ሲሄድ ኒኮልን ብቻናንት እንዳታሰማት አደራችሁን ብሎን ሄደ። በተለይም ሉልሰገድን አደራ አለው። ኒኮል አይናፋርና ሰውን ቶሎ የማትላመድ በመሆኗ፣ ከሉልሰገድና ከጆምሺድ ጋር ብቻ ነበር በመጠኑ የምትጫወተው

አንድ ምሽት ከእራት በኋላ፣ እኔ፣ ሉልሰገድ፣ ጆምሺድ፣ ተካ ካፌ ዶርቢቴል ቁጭ ብለን የሲኒማ ሰአት እስኪደርስ ስናወራ፣ ኒኮል ግራጫ ሱፍ ኮትና ጉርድ ከአረንጓዴ ሸሚዝ ጋር ለብሳ መጣች። ሉልሰገድ ተነስቶ ከሌላ ጠረጴዛ ወምበር ሲስብላት፣ ጆምሺድ ተነሳና Bon soir ብሎ ሊጨብጣት እጁን ዘረጋ። Bon soir ብላ እጇን ሰጠችው። ጨበጣት

«እይ!» ብላ እጇን ማሻሸት ጀመረች

«ምንድነሽ?» አላት «ምን ሆንሽ?» ማለቱ ነው

«ወጋሽኝ» አለችው፣ ሉልሰገድ ያመጣላት ወምበር ላይ እየተቀመጠች

«እንዴት ወጋሁሽ?»

«በሀይል ጨበጥከኝና ቀለበቴ ወጋኝ»

«ኦ!» አለና፣ ይቅርታ እንደመጠየቅ «ዛሬ ከሰአት በኋላ የሚከራይ አፓርትመንት ቤት እየፈለግኩ ብቻዬን» አለ። ትንንሽ ሰማያዊ አይኖቹ እንደልማዳቸው በሳቅ ይጨፍራሉ። ቀጠለ፡- ማለቴ ወጥቼ፣ የባለቤት የበር

አንድ አፓርትመንት ፎቅ ወር...



@BOOKALEM

ደወል:: በእጀ መግፋት:: ውስጥ ደወል:: ተጭን ደወል ኪል! ኪል! ቆንጆ ደወል:: በር ከፍት! የደወልኩት በር አይደለም:: ሌላ በር-ከግራ በኩል ከበሩ ብቅ:: አንድ ሽማግሌ ዶክተር:: ነጭ የዶክተር ልብስ:: በአይኑ መነፅር በራሱ መላጣ:: በከንፈሩ ሙስታሽ:: በእጁ መርፌ

ዶክተር እኔን «ወዲህ ይግቡ፣ ልውጋህ»

እኔ «እኔ መርፌ አይፈልጉም:: እኔ በሽታ የለም:: እኔ ጤነኛ:: እኔ ቤት መፈለግ:: የአፓርትመንት ባለቤት መፈለግ:: ለቤት ኪራይ::»

ዶክተር «ግድ የለህም:: ና ግቡ ልውጋህ:: እኔ አዋቂ መርፌ ወጊ» ብሎ መርፌ እንደ ጋንግስተር ሽጉጥ ወደኔ

እኔ «ዶክተር! እኔ አሁን መርፌ አይፈልጉም:: ነገ እመጣለሁ፣ እሺ?»

ዶክተር «እኔ ነገ አይሰሩም:: አሁን ና ልውጋህ:: በኋላ ይቆጭሀል:: አላስከፍልም:: አሁን ልውጋህ:: ነገ ሀይድሮጅን ቦምብ ፓሪስ ላይ — ፑፍ!»

እኔ «ዶክተር፣ አሁን መጣሁ» ብዬ በሩጫ ፎቁን መውረድ

ዶክተር በሀይል ጩኸት ድምፅ «ታድያ እኔ ማንን ይወጋል? አንተ ከሄድክ እኔ ማንን ይወጋል?»

እኔ መልስ አልሰጥም ለዶክተር:: በልቤ «እንጃ፣ ምናልባት ከ... በኋላ ሌላ ሰው አፓርትመንት ፈላጊ:: ደወል ሲደውል ኪል! ኪል! ዶክተር ቀስ ብሎ መርፌ ጠቅ! ከኋላ::»

ጆምቪድ ሲያስቀን ከቆየ በኋላ ሁላችንም ሲኒማ ሄድን:: አንድ ነገር አስተዋልኩ:: ሉልሰገድ በትልልቅ ጥቋቁር አይኖቹ ኒኮልን ያያታል:: ኒኮል በአረንጓዴ አይኖቿ ጆምቪድን ታየዋለች:: ጆምቪድ በብልጭ ሰማያዊ አይኖቹ ማዳም ፖልን ያያታል:: ማዳም ፖል ብጫ ቅብ ፀጉሯን እያብለጨለጨች ወፍራም ዳሌዋን እያወዛወዘች በጠረጴዛዎቹ መሀል ጉድ ጉድ ትላለች:: አንድ ጊዜ ከጆምቪድ ጋ ስታልፍ መንገዷን የዘጋባት አስመስላ ትከሻው ላይ እጇን አሳረፈችና "Pardon, monsieur" አለችው:: "Derien, madame" ብሎ አሳለፋት:: ብዙ ጊዜ እየከበበው ሲያስቀን ስለምታይ፣ አይኗን



@BOOKALEM

አድርጋበታለች፡፡ መስየ ፖል በሩ አጠገብ ቆሞ ገንዘብ እየተቀበለ ሀጂውን ሰው በየዋህ ድምፅ "Au revoir!" ወይም "A bientôt" ይላል

* * *

አማንዳ ወደ አገሯ እንድሄድች ሉልሰገድ አንዲት ኢጣልያዊት ልጅ ያዘ፡፡ ትምህርት ተጀምሮ ጥቂት ሳምንት እንዳለፈ ልጂቱ አረገዘች፡፡ የፈረንሳይ ህግ ማስወረድ ስለሚከለክል፣ ሉልሰገድ ከኔ፣ ከጀምሺድና ከሌሎች ገንዘብ ተበድሮ ልጅቱን ወደ ስዊስ አገር ላካት፡፡ በዚያው አገሯ ገባች፡፡

አንድ ቀን፣ ባቡር ጣቢያው አጠገብ ያለችው ትንሽ ካፌ በረንዳ ላይ ቁጭ ብለን፣ ሉልሰገድ የሚወደውን ቡና አይነቱን የስኮትላንድ ቢራ እየጠጣን ስናወራ፣ ድንገት ተነሳና «ቆየኝ መጣሁ፡፡ ካልመጣሁ ቤትህ እንገናኝ» ብሎኝ፣ ባቡር መንገዱን ተሻግሮ ሁለት ኮረዳዎችን አቆመና ትንሽ አነጋገራቸው፡፡ ተለይተውት ሲሄዱ መሬት መሬቱን እያየ ወደኔ ተመለሰ

«እምስ የሸተተኝ መስሎኝ ነበር፡፡ ተሳስቼ ነው» አለኝ፡፡ አንድ ነገር ሊነግረኝ እንደፈለገ ታወቀኝ፡፡ ዝም አልኩና ቢራውን ቀዳሁለት፡፡ ጎልዋዝ ሲጋራ አፉ ላይ ሲሰካ፣ ክብሪቱን ከጠረጴዛው ላይ አንስቼ አቀጣጠልኩለት

«መከራ ነው ʼባክህ፡፡ ሴቶቹ እምቢ አሉኝ፡፡ እንደዚህ ስሞን እምስ ቸግሮኝ አያውቅም፡፡ እኔ ደሞ እንደምታውቀኝ ነኝ፣ ያለሱ መኖር አልችልም፡፡ ለኔ መንግስተ ሰማያት ማለት በየሜዳው ላይ፣ በየዛፉ ስር፣ በየመንገዱ ዳር፣ በየግድግዳው ጥግ እምስ የሚበቅልበት አገር ነው፡፡ ገሀነም ደሞ ፈፅሞ እምስ የማይገኝበት እርኩስ ቦታ ነው፡፡ እምስ ዘርተውት ቢበቅል ኖሮ ገበሬ እሆን ነበር፡፡»

ሌላ ቢራ አዘዝኩለት

«እኔ ʼምልህ! ስለኒኮል ምን ይመስልሀል?» አለኝ

«ምንም»

«ምንም? እንግዲያው አታውቅም»

«ምን ማለትህ ነው?»

«እኔ እንደሷ ያለች ሴት አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ አየህ፣ አመዳም ፀጉር፣ የኔ መጀመርያ ስታያት ስሜት አትሰጥህም፡፡



@BOOKALEM

ከንፈር። ታድያ እየለመድካት አይነት ጥቅቅን ጥርስ፣ የደረቀ ትሄዳለች። ልዩ አይነት ሴት ነች። የበለጠ ስትሄድ እያማረችህ ስትሄድ ደሞ ስትለያት ትናፍቅሀለች። ታድያ ጤነኛ እየለመድካት ናፍቆት አይደለም።»

«ዋ! አንተ ልጅ፣ ፍቅር የያዘህ ትመስላለህ»

«ፍቅር አይደለም። ቅንዝር ነው። የሚያቅበጠብጥ ቅንዝር። ባህራምን እወደዋለሁ። ጎበዝ ስለሆነ አደንቀዋለሁ። ደሞ አምኖኝ እደራ ኒኮልን አጫውታት ብሎኝ ነው የሄደው። ግን አልቻልኩም። በጭራሽ አልቻልኩም። እኔ ልለምናት ነው»

«እምቢ ብትልህስ?»

«የምትለኝ አይመስለኝም። እሷም የምትፈልገኝ ይመስለኛል። ትላንትና ማታ ሲኒማ ወስጃት፣ ፊልሙን አላየሁትም። ሽቶዋ ከለከለኝ። ቀስ አድርጌ እጄን ጭኗ ላይ አሳረፍኩ፣ አልገፋችኝም። ትንሽ ቆይቼ እጄን አመጣሁና የተገተረ ቁላዬ ላይ አስቀመጥኩት። በሱሪው ላይ። እጇን እዚያው ተወችው። ታድያ ከፋቱ፣ በጭራሽ አላሻሸችኝም። እጄን ወደ ቀሚሷ ውስጥ ላስገባ ስል ከለከለችኝ። ለመከልከል እጇን ከቁላዬ ላይ አነሳች። እንደገና መድፈር አልቻልኩም። . . . ስቃይ ነው የኒኮል ነገር።»

ከአራት ቀን በኋላ ሉልሰገድ ኒኮልን አፍ አውጥቶ፣ «ፍቅር ይዞኛል ቤትሽ መጥቼ ልደር?» አላት

«እኔ እሺ አልልህም። ግን እሺ ብልህም በኋላ ለባህራም እነግረዋለሁ» አለችው። ለምን ቢላት «ባህራምን ሳታልለው አልፈቅድም» አለችው

«ከባህራም ጋር መፋረስ አምሮሽ እንደሆነ አንቺው ራስሽ ምክንያት ፈልጊ እንጂ እኔን ሰበብ እንድታደርጊኝ አልፈቅድልሽም» አላት

ሉልሰገድ ይህን ሲያጫውተኝ «ሆ! ባህራምን ለምን እንጀራ ከምታበላው ሴት ጋር ላጣላው? ምን በደለኝ?» አለ

«እንግዲያው ምን በደለህና ኒኮልን ልትበዳበት ትፈልጋለህ?» አልኩት እየሳቅኩ

«በጭራሽ እንድ አይደለም» አለኝ «መጀመርያ ነገር ብበዳት



@BOOKALEM

አያልቅበትም:: እንኳን ልጨርስበት አላሰፋበትም:: አንድ ቀን ገላውን ታጥቦ ሙታንቲውን ሲቀይር አይቼ፣ ጆላ ነው የተሸከመው:: የኔ ግትር ብሎ ቆሞ 'ንኳ ያንን አያክልም:: ታድያ ተኝቶ ተንጠልጥሎ ነው ያየሁት:: እናትክን! ምናባክ ያስቅህል? እኔን አይቶ ሊቆምበት ኖሯል?»

«መጀመሪያ ነገር አያልቅበትም አልክ:: ሁለተኛ ነገርስ?»

«ሁለተኛ ነገር፣ ካላወቀ በጭራሽ ሊጎዳው አይችልም::»

ከሶስት ቀን በኋላ ሉልሰገድ ኒኮልን ደገመና ለመናት

«እኔ እሺ አልልህም:: ግን እሺ ብልህም በኋላ ለባህራም እነግረዋለሁ:: ብቻ አንተ መሆንህን አልነግረውም» አለችው

«ያወጣጣሻላ»

«አያወጣጣኝም»

ሉልሰገድ ቀፈፈው:: «እንግዲያው ከፈራህ ተወው» አለችው

ከሁለት ቀን በኋላ ከምሳ ስወጣ ሉልሰገድን አገኘሁትና፣ ና ያችን ቡና አይነት ቢራ ልጋብዝህ አልኩት:: ራሱን ነቀነቀ:: ትልልቅ አይኖቹ በጣም ቀልተዋል:: ሰክረሀል? አልኩት:: የለም፣ እንቅልፍ አጥቼ አድሬ ነው:: አሁን ሄጄ ልተኛ ነው፤ አደራህን ለእራት ቀስቅሰኝ አለኝ:: ወደ መኝታው እየሄድን

«የማይጠገብ እምስ አጋጥሞኝ ሌሊቱን ሙሉ አደርኩበት» አለኝ:: «በህይወቴ እንደሷ አይነት እምስ ቀምሼ አላውቅም:: ያቺ ልጅ መንግስተ ሰማያትን አጣጥፋ ጠቅላ በጭኖቿ ውስጥ ደብቃ ነው 'ምትዞረው ልልህ እችላለሁ::»

እርግጠኛ ለመሆን «ማነች እሷ?» አልኩት:: ኒኮል ናት

ይህ የሆነው ማክሰኞ ነበር

የሚቀጥለውን ቅዳሜና እሁድ ባህራም ኤክስ ውስጥ አሳለፈ:: እሁድ ከምሳ በኋላ ሉልሰገድ ተራውን ባቡር ጣቢያ አጠገብ ያለችው ካፌ ወሰደኝ:: (እኔና ሉልሰገድ «ካፌ ኒኮል» ብለን ስይመናታል) ቡና አይነቱን ቢራ ጋበዘኝና ወሬ ስናወራ ቆይተን

«እኔ ተሰቃየሁ» አለኝ



@BOOKALEM

«አሁን ደሞ ምን ሆንክ?» አልኩት

«ቀናሁ፡፡ ይሄ ባህራም ለምን አይሄድም? ለምን አይሞትም?»

«ምን ነካህ?»

«እኔ 'ንጃ ባክህ፡፡ ስለእምስ አንድ ነገር አለ በኒኮል ምክንያት የተገለፀልኝ፡፡ ይሄኔ'ኮ ሌላው ሰውዬ ያለፋዋል፣ ይሞላዋል፣ ብለህ ስታስብ፣ ያ እምስ የባሰውን ያምርሀል፡፡ እንዴት እግሯን ከፍት አርጋ ዋጥ እንዳረገችህ እያስታወስክ፣ በሀሳብህ ያንን እርጥብ እምሷን ስታየው፣ ሽታው ሲታወስህ፣ ግትር ብሎ ይቆምብሀል፡፡ ምግብ መብላት፣ መሬት መርገጥ አትችልም፡፡ በምኞት ላይ ትንሳፈፋለህ፡፡ በፍትወት ትዋጣለህ፣ አንተ ራስህ ፍፁም ቅንዝር ትሆናለህ፡፡ ቁላህ ይቆምና፣ ቀስ እያለ ሌላው የተቀረው ሰውነትህም ቁላ ይሆናል፡፡ ነብስህም የቁላ ነብስ ይሆንና፣ እምነት፣ ጓደኝነት፣ ግብረ ገብነት፣ ይሄ ሁሉ ጥሎህ ይጠፋል፡፡ እንዲያውስ ቁላ ምን ጓደኛ ሊኖረው ይችላል? ብቻውን አይደል? አያሳዝንህም? ብቸኛ ነው'ኮ!

«እኔ ምለው፣ ነገ መቸ በደረሰልኝና ያ ባህራም በሄደልኝ፡፡ እና ያንን ጉድዋን ተወርውሬ በገባሁበት! አቤት ሰኞ ሌሊት የምበዳት አበዳድ! ይታየኛል፡፡»

«ለምንድነው ይህን ያህል ያንገበገበችህ?» አልኩት

«እኔ 'ንጃ» አለኝ

«እሱን ተወው! አሁን 'ንግዲህ መናገር ጀምረሀል፡፡ እንደጀመርክ ለምን አትጨርስም? ላንተም ጥሩ ነው፡፡ ስትናገረው ቀለል ይልሀል፡፡»

በጥቃቅን ጥርሶቹና በጉልህ አይኖቹ ሳቅ እያለ «እንዲህ ነው» አለኝ «መጀመሪያ ነገር እምሷ ራሱ ልዩ ነው፡፡ እውነቴን ነው፡፡ እንደሷ የሚጣፍጥ የለም፡፡»

«ደግሞስ?» አልኩት፡፡ አፈረ፡፡ «አይዞህ» አልኩት

«ደግሞ አየህ፣ እጅግ በጣም አይናፋርና ጨዋ ልጅ ናት፡፡ አልጋ ላይ ስትወጣ ታዲያ፣ ባለጌ ናት! ብልግ ያለች የወጣላት ባለጌ ናት፡፡ እና ይሄ ብልግናዋ ግሩም አይነት ደስታ ይሰጥሀል፡፡ ልብሷን አስወልቀህ ስታቅፋት፣ እናንተ ብቻ ሳትሆኑ ፍጡር በሙ ልብሷን... ሰማይና ምድር ራሳቸው እምስና ቁ መባዳት የጀመረ ይመስልሀል፡፡



@BOOKALEM

የሆነን የተቆላለፉ መሰሉ ይሰማኝ ነበር። እንግዲህ የቤተሰብ ሳቅም የምን ቅጽል የሆነ ባለጌ ሀፃን አለቃይ [illegible] [illegible] ከተፈጠርኩ እንደዚያ ያለ አለቃይ [illegible] [illegible] [illegible] ባህሪም ለምን አይገባኝም?»

ባህሪም ከዚያ በኋላ ሰባ ወደ [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] ለመስበር ቆርጫለሁ፣ ንብረቱን [illegible] [illegible] [illegible] አባረሽኝ» አለኝ

«ምነው?» አልኩት

«ብንግርህ አታምነኝም»

«ምንድነው የሆንከው?»

«እንደዚያ ሰንዝሮብ ሰንብቼ፣ እኔ በእጆቼን ሰቅዬ፣ [illegible] ትር - ትር - ትር እያለ በጣቶቼን ሲቆጥር [illegible] [illegible] እምበ፣ እያልኩ እንደ በሽተኛ ስመለስ ሰንብቼ፣ ባህሪዬን [illegible] በኋላ እየሮጥኩ ሄጄ ሰጨኝ አልኳት»

«እና?»

«ሞት ነው፣ እዚህ ልፈነዳ ነው፣ ሰጨኝ አልኳት። እምቢ አለችኝ»

«እምቢ?»

«እመ እምላክን!»

«እሱን ተወው!»

«እኔም እሱን ተይው አልኳት። በጭራሽ አይሆንም አለች።»

«ምነው አለች?»

«ያስፈውም ይቆጨኛል አለችኝ። ባህሪዬን ከምበድል ራሴን ብበድል እመርጣለሁ አለች። ይስ ትለኛለህ ግን አይሆንም፣ በጭራሽ አይሆንም ብላ አባረረችኝ።»

ጊዜው መምሸቱ ነበር። እኔና ሉልሰገድ ማርሰይ ወረድን ሳለ፤ እንዲት አረብ ሸርሙጣ ተኛ። ከዚያ ወጥተ እንደ [illegible] ከዚያ ወደ [illegible] ተመለስን ጣጣ፤ እንዲት ፈረንሳይ ሸርሙጣ ተኛ። ከዚያ [illegible]

ስንመለስ «ይገርምሀል» አለኝ «እንሱን ሰበዳ የማታየኝ [illegible]

@BOOKALEM

እምስ ነበር:: እምስ እንደዚህ ገዝቶኝ አያውቅም። ድንገት የገንዘ
ጡንቻ ቀብቶ እርጎ ያዘና

«እሬ ‘ንጂት ልሆን ነው? ያለ ኒኮል እምስ እንጂት አ
ልኖር ነው?» አለኝ:: ሳቅኩ:: እሱም እየሳቀ

«ስክሬል ብለህ ትስቅብኛለህ? እኔ ግን እውነቴን ነው:: ነ
ጭለማ ሆኖ ነው ‘ማታየኝ» አለኝ

መኝታ ቤቱ ወስጄ አስተኛሁት

ይህ የሆነው ሰኞ ማታ ነበር

ሀሙስ ከሰአት በኋላ ወደ አስራ አንድ ሰአት ላይ አሊጋዬ ላ
ተጋድሜ ሙዚቃ ሳዳምጥ፣ የመኝታዬ በር ሳይንኳኳ ተከፈተ
ሉልሰገድ ገባ:: ቃል አልተናገረም:: ወምበር ላይ ተቀመጠ:: አይኖ
አንድ ጊዜም አይጨፈኑም:: እንደ መፍዘዝ ብሏል:: በህልም ው
ያለ ይመስላል

«ምን ሆንህል?» አልኩት:: መልስ አልሰጠኝም:: ሲጋራ አውጥ
አቀጣጠለ:: እጁ ይንቀጠቀጣል:: ሲጋራውን በረጅሙ ስቦ አይኑ
ዘጋ:: ቆየ:: አይኑን ሳይከፍት ጭሱን ወደ ውጭ ተነፈሰ

«ምን ሆንህል?» አልኩት

ትልልቅ አይኑን ከፍቶ ለመጀመሪያ ጊዜ አያየኝ

«እምስ» አለ:: ድምፁ ከቅል እንጂ ከሰው ጉሮሮ የሚወ
አይመስልም

«ምን?» አልኩት

«ኒኮል»

«ምን ሆነች?»

«ልታሳብደኝ ነው:: ሳብድ ነው:: እብድ ልሆን ነው»

«ምን አረገችህ? ንገረኝ ‘ስቲ:: ከመጀመርያ ጀምር:: እያ
ስትናገረው እየተሻለህ ይሄዳል:: በል:: የት አገኘችህ?»

«እኔ ነኝ ያገኘኋት»

«የት?»



@BOOKALEM

«ቢድ»

«ለምን ሄድክ?»

«አላስችል አለኝ:: እምስ እመጣለሁ:: ግን እንደዚህ አርጓኝ አያውቅም::»

ሲናገር መጥዘዙ እየተወው ሄደ

«ሌላ እምስ ማባረር አልቻልኩም:: ሌላ እምስ ሁሉ ጨው የሌለው አልጫ ሆኖ ይታየኝ ጀመር:: ብሪዢት ባርዶ ራሷ መጥታ ብትለምነኝ እሺ ማለቴን 'ንጃ:: ይገባሀል 'ምልህ? የኒኮል እምስ ግን ከጧት እስከ ማታ ይታየኛል፡ ከማታ እስከ ጧት በትዝታ ጠረኑ እየሸተተኝ እንቅልፍ ይነሳኛል:: አሁን መጥታ ኢትዮጵያዊነትህን ትተህ የፈረንሳይ ዜጋ ሆነህ አግባኝ ብትለኝ፣ አንዲት ደቂቃ አላመነታም:: እሺ ነው 'ምላት:: ታዲያ'ኮ ልጅቷን አልወዳትም፣ አላውቃትምም:: እምሷ ብቻ! እንዲህ ሆነህ ታውቃለህ? እኔ 'ምልህ፣ ድግምት አስደግማብኝ ይሆን?»

ሳቁ አመለጠኝ:: ተናደደ:: «በፈረንሳይኛ ስታስደግምብህ ታየኝ» አልኩት:: ሳቀ፤ ተንከተከተ:: ትንሽ ደነገጥኩ:: ሳቁ የእብድ ሳቅ ይመስላል:: ብዙ ከሳቀ በኋላ «ና 'ንሂድ» አለኝ

«ካፌ ኒኮል» ሄደን ቡና አይነቱን የስኮትላንድ ቢራ አዘዘን:: ስለ ኒኮል ነገረኝ

«አየህ፣ ወድጄ ሳይሆን ተገድጄ ነው ቤቷ የሄድኩት:: ከተኛኋት ሳምንት ያልፋል:: በጣም ረጅም ሳምንት:: እና አንተን ቢራ እንድጋብዝህና እንድታጫውተኝ ብዬ ወደዚህ ስመጣ፣ እሷ ከሊቴ ወደ ቤቷ በኩል ስትሄድ አየኋት

«አለፍኳት:: ግን ሀሳቤ ሊያልፋት አልቻለም:: እሷ ሳታየኝ ተከተልኳት:: ነጭ ሸሚዝና በጣም አጭር የሆነ በጣም ጥብቅ ያለ ዐና አይነት ጉርድ ለብሳለች:: የጉልበቷ መታጠፊያ ራቁቱን ይታያል:: ልስመው ልልሰው ፈለግኩ:: ስትራመድ ዳሌዋ ይወዛወዛል፣ በጉርዱ ስር የሙታንቲዋ ቅርፅ ይታያል:: ቂጧ ከፍ ዝቅ ሲል ያስታውቃል:: እዚያ ውስጥ 'ንግዲህ ያ ግሩም እምስ አለ:: ይኸኔ በሙቀቱ ትንሽ ረጠብ ብሏል፣ ገና ቢያደርጉት ያጂልጫል:: እንጋሌ ላልፈትድለት ይሆን እያሰበ፣ ቁላዬ ተንትሮ እንዳያዋርደኝ እጄን



@BOOKALEM

ሲሉ ከትፎ ተከተልኳት። ላልነገሩኝ እንዴት እችላለሁ?

«ቤቷ ገባች። አንድ አምስት ሪጃጅም ደቂቃ ቆይቼ፣ እንደሰ...
ገባሁ።

«'አትምጣ አላልኩህም ነበር?' አለችኝ። ድምፅዋ እንዴት
ልዝብ እንደሆነ አስተውለሀል? አይኗ ንፁህ ውሀ አረንጓዴ መሆኑን
ተገንዝበሀል? አይኗ ውስጥ ያለው ሀዘን አይማርክህም?»

«'አይዞሽ ምንም አላረግሽም። ተስፋ ቆርጫለሁ' አልኳት።»

«ደስ ያላት መሰለች። 'ቁጭ በል ቡና ላፍላልህ' አለችኝ
ቡናውን ልትጥድ ወጥ ቤት ስትሄድ በሩን ቆለፍኩት

«ቡናውን ከጠጣን በኋላ፣ ቆማ ሳለ ድንገት ከኋላዋ አቀፍኳትና
አንገቷን እየሳምኩ በቆመ ቁላዬ እየተሻሸኋት ጡቶቿን በእጆቼ
መዳበስ ጀመርኩ። ሊታመልጥ ሞከረች። አልቻለችም። ያልቀ...
የቁጧ መወዛወዝ የባሰውን አቆመብኝ። በግድ ፊቷን ወደኔ ...
መዘዝኩና ከንፈሯን ጎረስኩት። አፏ ሲስመኝ ተሰማኝ። ቀስ አድርጌ
አምርኳትና በስነ ስርአት አቅፌ እየሳምኩ፣ ሸሚዟንና ጉርዷን
አስወለቅኳት። የውስጥ ቀሚስ አልለበሰችም። ተሸክሜ አልጋው ላይ
አጋደምኳትና እየሳምኳት ልብሴን አወለቅኩ። ጡት መያዣዋን
ሙታንታዋንም አስወለቅኩና ታድያ፣ በቀጥታ እንደመኩ...
ሁለመናዋን እስማት ጀመር። እያገላበጥኩ ከእግር እስከ ራሷ እስማ...
ጀመር። አይገርምህም? እንደዚያ ስንገበገብ ስንብቼ፣ አሁንም እን...
መብዳት እስማታለሁ። ግን በኋላ ስታስበው ያሳፍራል። ያልሳምኩ...
ቦታ የለም'ኮ። ግን እውነት መናገር ይሻላል፣ እሷም ያልሳመች...
ቦታ የለም። ስድ ባለጌ ናት ብዬህ የለ? የባለጌ መጨረሻ ናት። ...
እኔም ዋና ባለጌ ነኝ። ገና ዛሬ ገባኝ። ብቻ ምን ልበል...
ያልሰራነው ብልግና የለም። ኒኮልን ሳላውቃት በፊት መብዳ...
ማለት ቁላን እምስ ውስጥ መክተት ይመስለኝ ነበር። ለካስ ነገሩ ...
ሌላ ኖሯል። አየህ፣ በዚያን ጊዜ ኒኮል ሁለመናህን
ታደርገዋለች። እና እምሷን ብቻ ሳይሆን፣ ሁለመናዋን ትበዳ...
አይ ሴት!

«በመጨረሻ ያቃሰትነው ባቡር መንገድ ድረስ ሳይሰ...
አይቀርም። ስናበቃ የሞትኩ መሰለኝ። አላይዋ ላይ እንዳለሁ እ...
ዘጋሁ። ታድያ ደረቷና ሆዷ በኃይል ሲንቀጠቀጥ አይኔን ከፈት...



@BOOKALEM

አየችኝ፡፡ እምባዋ ይወርዳል

«ምነው ምን ሆንሽ?» አልኳት

«እየተንከባከበችኝ ‹ሂድልኝ እባክህ ሂድልኝ› ማለት ብቻ ሆነ፡፡ ጨርሶ ግራ ገባኝ፡፡ እየተንከባከበችኝ ‹የምትፈልገውን አገኘህ፡፡ አሁን ደሞ አትሄድልኝም?› አለችኝ፡፡ ህሊናዬ በጣም ይቆረቁረኝ ጀመር፡፡ ልብሴን ለበስኩና ቆምኩ፡፡ መሄድ አቃተኝ፡፡ እሷ ራቁቷን እንዳለች በሆዷ ተኝታ ራሷን ትራሱ ላይ ደፍታ እያለቀሰች አሁንም ‹ሂድልኝ ሂድልኝ፡ እባክህ ሂድልኝ› አለችኝ፡፡ በሩን ከፍቼ ወጣሁና ዘጋሁት፡፡ ወዲያ ስመጣ መኪና ሊድጠኝ ነበር፡፡ ለትንሽ እግዜር አወጣኝ

«ታዲያ የሚገርመኝ ምን መሰለህ? ወዳንተ ስመጣ ሳለ፣ ስለሷ እያሰብኩ፣ ስለበደልኳት ከልቤ እያዘንኩ፣ እዚያ ትራሷ ላይ ተደፍታ ያለቀሰችው ሆዴን እየበላኝ፣ እሷ እያለቀሰች ቂጧ ሲንቀጠቀጥ እንዴት ቆንጆ እንደነበረ እያስታወስኩና ቆመብኝ

«እንግዲህ እንደማታስጠጋኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡ እኔ ደሞ ያለሷ ሌላ ቤት ማቀፍ የምችል አይመስለኝም፡፡ እና ግራ ገብቶኛል፡፡ ጨንቆኛል፡፡ እንግዲህ እርን እምስ ገዝተህ ያውቃል?»

በሚቀጥለው እሁድ ባህሩም «ማመን የሚያስቸግር ነገር ልንገርህ» አለኝ «ሉልሰገድ ኒኮልን ሊተኛት ሞከረ»

«ሙጀትክን ነው!» አልኩት

«እኔም ለጊዜው ማመን አቃተኝ፡፡ ግን ኒኮል አትዋሽም፡፡ ለሌላው ብትዋሽ ለኔ አትዋሽም፡፡ ብዙ ብዙ ተለማመጣት፡፡ እምቢ አለችው፡፡»

«ምን ነው ‹ብዙ›?»

«እሱ'ኮ ነው ‹ሚገርመኝ፡፡ ሁላችሁንም አደራ፣ ኒኮልን ማንም እንዳይደርስባት፣ ብያችሁ ሄድኩ፡፡ ከዘበኞቹ ሁሉ ሉልሰገድን ነው ‹ምወደው› ብላኝ ስለነበረ፣ በተለይ እሱን አደራ አልኩት፡፡ … ሊሰራት ማዘጋጀት፣ ንዴቱ ትዝታ እሱ ሆኖ፣ ገና ዘመር ከማለቱ ይዘለዝለኛል» አለ ሆዱን እያሻሸ፡፡ እንደ ቤቱ እዚህ ጋ ያርደኛል፣



@BOOKALEM

«ከዚህ በፊት የዋለልኝ ውለታ ባይገታኝ ኖሮ፣ አሁን ሄጄ እሩን ባበላው እንዴት ደስ ባለኝ!»

«አሁን እንዴት ሊታረግ ነው?»

«ምንም አላረግም:: እንዲያውም ማወቄን አላሳየውም:: ልክ ምንም ነገር እንዳልጠረጠርኩ መሆን አለብኝ:: አየህ፣ ምንም ቢሆን ውለታውን ልረሳው አልችልም:: ብቻ ያሳዝናል:: በጣም ያሳዝናል::»

ዝም ብሎ ሲያስብ ከቆየ በኋላ «እኔ ራሴ አንድ ነገር ለማድረግ ብፈልግም አልችልም» አለ «ምክንያቱም ኒኮል ይህን የነገረችኝ፣ ምንም ቢሆን ምንም፣ ስለዚህ ጉዳይ አንዳች እርምጃ እንዳልወስድ ካስማለችኝ በኋላ ነው:: 'እንዲያውም ጓደኞችህ ጥቂት ናቸው:: እነዚሁኑ በኔ ምክንያት እንድትጣላቸው አልፈልግም' አለችኝ::»

እቺ ኒኮል እንዴት ያለች ሴት ነች! ውስጡን አደነቅኳት

ባህራምን «ልጠይቅህ እያልኩ:: ከኒኮል ጋር ፍቅር ይዞሀል!» አልኩት

«ፍቅር አይደለም:: መዋደድና መግባባት ነው:: ጠባይዋ በጣም ይስማማኛል:: እኔ እንዳየሽኝ ነኝ:: መሯሯጥ መንቀዥቀዥ አበዛለሁ:: እሷ ግን ረጋ ያለች ዝምተኛ ልጅ ናት:: እና ከሷ ጋር ስሆን ሰላም ይሰማኛል:: ታውቃለህ፣ ገንዘብ የሚሏት አይደን እንኳ ካየሁ አመት ሊሆነኝ ነው:: ኒኮልን ካወቅኳት ጀምሮ፣ ከህበሾቹ ጋር ካልበላሁ ወይም ከነሱ ጋር ሲኒማ ካልገባሁ በቀር፣ እሷ ናት 'ምታበላኝ፣ ካፌ 'ምትወስደኝ፣ ሲኒማ 'ምታስገባኝ፣ መፅሀፍት 'ምትገዛልኝ:: ታዲያ ይህን ሁሉ ስታረግልኝ በጭራሽ አይከብደኝም:: ግሩም ልጅ ናት እልሀለሁ::»

ከትንሽ ፀጥታ በኋላ፣ ፈገግ ብሎ፣ «ደሞ ሸጋ ልጅ ናት:: ከሩቅ እያስታውቅም 'ንጂ ብዙ ውበት ተሰጥቷታል:: የብቻዋ የሆነ ልዩ ውበት አላት

«እኔ በአንዲት ሴት መርጋት አልወድም:: አይሆንልኝም:: ቶሎ ካንዲት ሴት ጋር ቢበዛ ሁለት ወር መቆየት ብችል ነው:: ቶሎ ይሰለቹኛል:: ኒኮል ግን አትሰለችም:: በጭራሽ አትሰለችም:: አሁንማ መዞሩን ትቼ በሷ ረግቻለሁ::»



@BOOKALEM

«ለምን?»

«እኔ 'ንጃ:: እሷን ከማወቁ በፊት ከመጠን በላይ ጦርኑ የማትስለች ሲያጋጥመኝ ጊዜ፣ እርዴ አልኩና አረፍኩ

«ታድያ' ኮ በእስተባሰብ ጨርሶ አንስማማም:: እሷ በጦርነት አታምንም:: እንጃ ከአሜሪካኖቹ የሚታገስ ካፒታሊስት ነች:: አንዳንዴ ስንከራከር እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ እስር ሰአት እንቆይና፣ እቺን ያህል እንኳ ሳንስማማ መብራቱን አጥፍተን እንተቃቀፋለን:: እና ይገርመኛል:: ከርክራችን የከረረውን ያህል መተቃቀፋችን ይጠ ብቃል

«አንድ ሌሊት እንደዚህ ስንከራከር ቆይተን መብራቱን አጥፍቼ በደንብ ካቀፍኳት በኋላ 'ይኸውልሽ፣ አሁን እኔ አንቺን እንደ ምበዳሽ፣ ኮሙኒዝም ደግሞ ካፒታሊዝምን ይበዳዋል' ስላት ጊዜ፣ ሲቃ ልትሞት! እኔም እሷ ስትስቅ ጊዜ የተናገርኩት በሀይል ኮሚክ ሆና ታየኝና ሆዴን እስኪያመኝ ሳቅኩ:: ሳቁ ሲበዛብን መብራቱን አቋረጥነው:: ከዚያ በኋላ ለአንድ ሁለት ወር ያህል፣ በተቃቀፍን ቁጥር ሳቃችን ይመጣል:: . . .»

«እኔ ፍቅር የያዘህ መስሉ ነው 'ሚሰማኝ» ስለው ሳቀብኝ

«የሴት ፍቅር ሊይዘኝ አይችልም:: የኢራን ፍቅር ይዞኛል::» ራቱ ድንገት እየጠቆረ «ኢራንን ከሻህና ከጋንግስተሮቹ እጅ እስክስፈታት ድረስ፣ አሜሪካኖቹን ከኢራን እስክባርራቸው ድረስ፣ ያ ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ልቤ ውስጥ ለሴት ፍቅር ሊኖር አይችልም:: አልፈቅድለትም!» አለ

(አመንኩት:: ግን አንድ ነገር አስታወስኩ:: እነሉልሰገድን ሲወያያቸው፣ በይሩት ሆኜ ያስሚን ከምትባል ልጅ ጋር ፍቅር የያዘኝ፣ ዘመዶቿ ሊያስገድሉኝ ሲሉ ጊዜ ነው የሸሸሁት:: እኔ 'ንኳ አልሸሽም ብዬ ነበር፣ እሷ እያለቀሰች ለመነችኝ:: ሂድልኝ፣ ከምቀብርህ ባጣህ ይሻለኛል፣ አለችኝ:: ሸሸቼ ወዲህ ወደ አክስ መጣሁ፣ ብሎ ነግሯቸው ነበር:: ለምን ነገራቸው ይሆን?)

«ኒኮልስ ፍቅር የያዛት አይመስልህም?» አልኩት::

«አይመስለኝም:: አይናፋርና ዝምተኛ ስለሆነች፣ የኔ



@BOOKALEM

መንቀዥቀዥ መቀላጠፍ እንደ መጠለያ ያገለግላታል:: በሃዘኔም ይስማማታል:: እንጂ ፍቅር አልያዛትም::»

* * *

አንድ ማታ ኒኮልን ከተማ ሬስቶራንት እራት ጋበዝኳትና ብዙ ወይን እየጠጣኋት ስለልብ ወለድ መፃህፍትና ስለ ፊልሞች ጨዋታ አስጀመርኳት:: መጀመሪያ ስለምንወዳቸው ደራስያን፣ ስላየናቸው ፊልሞች፣ ስለምናውቃቸው ሰዎች እና በልብ ወለድ መፃህፍት ውስጥ ካገኘናቸው ሰዎች ጋር በምን እንደሚመሳሰሉ — ማለት ስለራሳችን ሳይሆን ስለ ሌላ ነገር ስናወራ፣ ወይን ስንጠጣ፣ ብዙ ጊዜ አሳለፍን:: እየለመደችኝ ሄደች:: ወይኑም እየሰራ ሄደ:: አይናፋርነቷ እየረገፈ፣ እንደ ልቧ ለማውራት እየቻለች ሄደች:: እኔም ፈረንሳይኛ እሷ ስትናገረው በጣም የሚጥም መሆኑን እያስተዋልኩ ሄድኩ::

ቀስ ብዬ ወሬውን ወደ ባህሪም ወሰድኩት:: እንዴት ጉበዝ ሆና እንደሚታየኝና፣ ምን ያህል እንደማደንቀው ከነገርኳት በኋላ፣ ባህሪም ላንቺ እንዴት ሆኖ ነው የሚታይሽ? አልኳት:: ደራሲ መሆን እንደምፈልግና ስለሰዎች ማወቅ እንዳለብኝ፣ ይልቁንም ሴቶች ወንዶችን እንዴት እንደሚያዩዋቸው ማጥናት እንደሚገባኝ፣ ስለዚህ፣ እሷ ስለራሷ ብትነግረኝ ለኔ ትልቅ ዋጋ እንዳለው፣ በሰፊው ዘረዘርኩላት:: ተቀበለችኝና ስትናገር፣ በቃላትዋ እየተንሳፈፍኩ የድምፅዋ ዜማ እየተመቸኝ አዳመጥኳት

«ደራሲ ባትሆንም ስለራሴ ብነግርህ ግድ የለኝም አለችኝ:: ባህሪም ስላንተ ብዙ ጥሩ ጥሩ ነገር ስለነገረኝ ነው መሰለኝ፣ በጣም የማውቅህ መሰሎ ይሰማኛል:: ደሞ እወድሃለሁ:: በጣም ተወዳጅ ልጅ ነህ:: ብዙ ሴቶች ይህን ነግረውህ የለ? ተናገር::» (ትስቃለች:: እሷ የተናገረችው በንፁህ ልብ ነበር:: እኔ ግን ምኞቴ ተቀሰቀሰ:: እግሮቼን አጣመርኩ:: የሉልሰገድንና የሷን ታሪክ ባላውቅ ኖሮ አሁን ምኞቴ ይቀሰቀስብኝ ነበር? እንጃ:: ኒኮል ቀጠለችልኝ

«በአስራ ስድስት አመቴ ማርሴል ከሚባል ልጅ ፍቅር ያዘኝ:: ማርሴልም ወደደኝ:: ቤቶቻችን ሁለቱም ሀብታም ቡርዧዎ በመሆናቸው ይከባበሩና ይዋደዱ ስለነበረ፣ በመዋደዳችን እጅግ ተደሰቱ:: እስክንጋባ ቸኩሉ:: ግን ሁለታችንም የዩኒቨርሲቲ ትምህርታችንን እስክንጨርስ ላንጋባ ቆረጥን:: ቤቶቻችንን ለማስደ



@BOOKALEM

ሴት ስንል ተማጨን:: በዚህ መካከል ማርሴል አየር ሀይል ገባ

«አንድን ደ ሴንት ኤግዙፔሪን ታውቀው የለ? በኤሮፕላን ስለመብረር፣ ስለአደጋው፣ ስለክብሩ፣ ስለጀግንነቱ የደረሳቸውን መፃሕፍት፣ ማርሴል ደጋግሞ ያነባቸው ነበር:: ከልቡ ሴንት ኤግዙፔሪን ያደንቀው ነበር፡ ይመልከው ነበር:: ለዚህ ይመስለኛል አየር ሀይል የገባው:: እኔ ተው አትግባ፡ እንደ ሴንት ኤግዙፔሪ በኤሮፕላን አደጋ ትሞታለህ፣ አልኩት:: መሞት የት ይቀራል? አለኝ:: የሰው ልጅ ተግባሩ ከሞት ለማምለጥ መጣጣር ሳይሆን፡ ሞት እስኪመጣ ድረስ ክብር ያለው፣ ኩራት ያለው ኑሮን መኖር ነው፣ አለኝ:: አለቀስኩ:: እምባዬን ጠረገልኝ:: ኤሮፕላን ነጂ ሆነ

«ይህ ሁሉ ሲሆን በግብረ ስጋ ሊገናኘኝ ይሞክር ነበር:: በብዙ ይለምነኝ ነበር:: ሳንጋባ አይሆንም ብዬ እምቢ አልኩት

«አንድ ቀን የኤሮፕላን አደጋ ደረሰበት:: ሁለት ወር ሙሉ ሐኪም ቤት ተኛ:: ከዚያ ወደ ቤቱ መጣ:: የአየር ሀይል ኑሮ፣ የሴንት ኤግዙፔሪ አይነት ኑሮ፣ ክብር፣ አደጋና ጉብዝና የሞላበት ኑሮ፣ የጀግኖች አይነት ኑሮ በቃው:: ከአየር ሀይል አሰናበቱት:: ምክንያቱም ወገቡ ተሰብሮ እግሮቹ ሽባ ሆኑ:: በተሽከርካሪ ወምበር ቁጭ ብሎ፣ እኔ ወይም እናቱ እየገፋነው ነበር አየር ለመቀበል 'ንኳ የሚወጣው

«አንጀቴ አዘንኩለት፡ በሀይል ወደድኩት

«እሱ ግን አሁንም ሽባ ሆኖ የሴንት ኤግዙፔሪን መፃህፍት ያነብ ነበር:: ስለአደጋ፣ ስለጀግንነት፣ ስለክብር ስለሞት ያነብ ነበር:: አንድ ቀን ሽጉጡን ጠጥቶ ሞተ

«ሀዘን ጀመረኝ:: ግን ሀዘን ይለመዳል:: ወጣት ከሆንክማ ትንሽ ቆይቶም ይረሳል:: በተለይ ያጠቃኝ ፀፀት ነበር:: ፀፀት አይለመድም፣ አይረሳም፣ የማይጠገብ የማይተኛ ሙስባዊ ትል ነው፡ እድሜ ልክህን ይበላሃል:: የቆጨኝ ማርሴል በግብረ ስጋ ሊገናኘኝ ሲፈልግ እምቢ ማለቴ ነው:: እወደው ነበር፡ ሲጋዬን ለሱ መስጠት እንዴት አቃተኝ? በሀይል ይቆጨኛል ይሞረሙረኝ ጀመር

«ካባቱ-እናቱ ጋ ሄድኩና ሁሉን ተናዘዝኩ:: የሠራሽው ልክ ነበር፣ አሉኝ:: እኔ ግን ፍፁም ስህተት እንደነበረ የበለጠ እየተገ



@BOOKALEM

ነዙብኩ ሄድኩ፡፡ ራሴን መቅጣት ጀመርኩ፡፡ ከጠየቀኝ ሁሉ መተኛት ጀመርኩ፡፡ ደሞ ብዙዎች ይጠይቁኝ ጀመር፡፡ ርካሽ ሴት ሆንኩ

«ግን አሁንም ፀፀቱ አልተወኝም

«በካሎሪያዬን እንዳለፍኩ ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት ወደ ኤክስ መጣሁ፡፡ ቤተቹም ማርሴልን ለመርሳት ከለአገር ከተማ መራቅ እንዳለብኝ ስላወቁ ሂጂ አሉኝ፡፡ ኤክስ መጥቼ በርካሽነቴ ላይ ጠጪነት ጨመርኩበት፡፡ የፈለገኝ እንግዲህ እስክሰክር ድረስ ማጠጣት አለበት፡፡ ብዙ ሰአት ካንዱ ጋር ስጠጣ አመሻለሁ፡፡ ሟት ወደ አምስት ሰአት ላይ ስነቃ አልጋው ውስጥ ነኝ፡፡ ሲደሰትብኝ እንዳደረ ይታወቀኛል፣ ግን ምን ምን እንደሰራን እንደ ህልም'ንጂ እንደ'ውን ሆኖ አይታየኝም

«ካንዲት የኔ ብጤ ርካሽ ጋር ገጠምኩ፣ አብረን መጠጥና ወንድ ስናሳድድ እናመሽ ጀመር

«እንዲህ ስል አመቱ አለፈ፣ ፈተና ወደቅኩ፣ ክፍል ደገምኩ፣ ሁለተኛው አመት ተጀመረ፣ ያንኑ ኑሮዬን ቀጠልኩ

«አንድ ረቡእ ሟት እንደ ልማዴ አንዱ እማላውቀው መኝታ ቤት ነቃሁ፡፡ ሰውየው ቁርስ ያቀርባል፡፡ ልዩ ሰው ሆኖ ታየኝ፡፡ ሳይነካኝ አድሯል፡፡ ከመስከሩ የተነሳ ሊነካኝ ባይችል ነው እንዳልል፣ ትላንት ማታ ፓርቲው ጋ ልሰክር ትንሽ ሲቀረኝ «ጠጣ 'ንጂ» ስለው «ሁለታችንም ከሰከርንማ ማን ማንን ይደግፋል?» ሲለኝ አስታወስኩ

«አልጋ ውስጥ እንዳለሁ ቁርስ ከበላን በኋላ፣ ሰውየው በተሰባበረ ፈረንሳይኛ

«እንቁላል አንድ ጊዜ ከተሰበረ ወድያ ምንም ሞያ እንደማይሆን ታውቂ የለ?» አለኝ፡፡ ምን እንደሚል ሳይገባኝ «አዎን» አልኩት፡፡ «ወጣትነትም አንዴ ከተሰበረ ሊጠገን አይችልም» አለኝ

«ምን ማለትህ ነው?» አልኩት

«ያንቺ ወጣትነት ገና አልተሰበረም፡፡ ግን ሊሰበር ትንሽ ነው የቀረው፡፡ እንደዚህ አይነት ኑሮ ከቀጠልሽ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ይሰበራል»

ተናደድኩ «ምን አገባህ?» አልኩት



@BOOKALEM

«ምን አገባህ አትበይኝ:: ፈረንሳይ መስልኩሽ 'ንዴ? እናንተ ፈረንሳዮች ፈሪ ናችሁ:: ግብዝ ናችሁ:: ተግባራችሁን መፈፀም አስቸጋሪ የሆነባችሁ 'ንደሆነ፣ እኔ ምን አገባኝ? Ça me regarde pas, ብላችሁ ትተዉታላችሁ:: እኔ ግን እንደሱ አይደለሁም::»

«እና በኔ ህይወት አንተ ምን አገባህ?»

«አንቺ አልጋዬ ውስጥ ምን ትሰሪያለሽ? በኔ ህይወት ውስጥ ገባሽ ማለት አይደለም?» አለኝ:: መልስ ስላጣሁ ዝም አልኩ

መጥቶ አልጋው ላይ አጠገቤ ቁጭ አለና፣ አይን አይኔን እያየኝ

«አሁን 'ስቲ ለሁለት ደቂቃ ፈረንሳይ መሆኑን ተይና ሰው ሁኚ:: ለሁለት ደቂቃ ብቻ፣ እሺ? አለዚያ ለመናገር አልችልም» አለኝ:: አንድ አይነት ደግ ፈገግታ አሳየኝ:: ረስቼው የነበረ አይናፋርነቴ ድንገት ተመልሶ ሸፍን አደረገኝ:: ወደታች ሳይ ፊቴን በእጆቹ ይዞ ቀና አደረገኝና ግምባሬን ሳመኝ

«አገሬ አንቺን የሚያካክሉ ታናናሽ እህቶች አሉኝ:: አንቺ 'ምታረጊውን ሲያረጉ ባያቸው ዝም አልላቸውም:: ስለዚህ አንቺንም ዝም አልልሽም:: ይገባሻል?»

ዝም ብዬ ሳየው ቀጠለ «አሁን እንግዲህ ባንቺ ቤት አደግኩ ብለሻል:: አልኮል ጠጥተሽ ስለሰከርሽና፣ የማታውቂው ሰው አልጋ ውስጥ ስላደርሽ የበሰልሽ ይመስልሻል:: ግን ዋናው መብሰል ራስን ማወቅ ነው:: ራስሽን ብትመረምሪ ደሞ ርካሽ ሴት እንዳልሆንሽ ትገነዘቢያለሽ:: ታድያ ርካሽ ሳትሆኚ እንደ ርካሽ ሴት መኖር ምን ይባላል? እኔ መቸስ ህፃንነት ነው እላለሁ::»

ዝም አልኩት:: እውነትክን ነው አላልኩትም

«ትምህርት አለብኝ መሄዴ ነው:: መሄድ ካለብሽ ሂጂ:: መሄድ ከሌለብሽ ግን እዚሁ ቆይኝና አብረን ምሳ እንበላለን» ብሎኝ ሄደ:: ተመልሶ ለምሳ ወሰደኝ:: ከተመገብን በኋላ ካፌ ገብተን ቡና ስንጠጣ ስሙን ነገረኝ

እና ባህሪም ምንሽ ነው? ብለህ ብትጠይቀኝ፣ ቀላል መልስ ልሰጥህ አልችልም:: የስጋ ወዳጄ ነው፣ የመንፈስ ጓደኛዬ ነው፣ የህይወቴን አቅጣጫ ለበጎ ያስለወጠኝ ጠባቂዬ ነው»



@BOOKALEM

የኒኮል ውበት ጉም እንደሸፈነው ተራራ ነው፡ ጉሙ በፀሀይ ሙቀት ቀስ እያለ ሲተን፣ ተራራው መታየት ይጀምራል። በኔና በኒኮል መካከል የነበረው እንግዳነትና አይናፋርነት እየተገፈፈ እየተዋወቅን እየተለማመድን ስንሄድ፣ ውበቷ እየተገለፀልኝ ሄደ። አይኖቿ ንፁህ ውሀ አረንጓዴ ሆነው፡ ረገዥሮም ሽፋሎቿ አረንጓዴ ኩሬ ዙሪያ በተርታ የበቀሉ ሀር ጥቁር ቄጤማዎች ይመስላሉ። አስተያየቷ ልስልስ ያለ ሆኖ፡ ሀዘን የተሞላ ይመስላል። ድምፅዋ ውስጥ የማር ጠብታ አለ፡ ፈረንሳይኛዋ የታሳሳቆቹን ደራሲያን ቋንቋ ይመስላል። ይሀ ውበቷ ቀስ እያደረገ፡ ሳይታወቀኝ፡ ልቤ ውስጥ ገባ። በሌለችበት አስባት ጀመር። ስትራመድ ባየኋት ቁጥር፣ ሉልሰገድ «አልጋ ውስጥ የባለጌ መጨረሻ ናት» ያለኝን አስታውሳለሁ፡ እኔና እሷ ባለጌ ነገር ስንሰራ ይታየኛል. . . ካለችበት ቦታ መንጭቄ ወደ ሀሳቤ ጫካ እወስዳታለሁ፡ እንደ እንስሳ ዛፍ ስር አስጎንብሼ እሰራታለሁ፡ አፏን ትከፍታለች። ጣቶቼን አፏ ውስጥ እከታለሁ፡ ትጠባቸዋለች፣ ታኝካቸዋለች. . .

* * *

ሉልሰገድ ኒኮልን ሊተዋት ሞከረ። ከልቡ ሞከረ። አልቻለም። ይታገስ ይታገስና፣ ሄዶ ይለምናታል። ጥፋ ከፊቴ ትለዋለች። እኔ ጋ መጥቶ 'ካፌ ኒኮል' ይወስደኝና ቡና አይነት ቢራችንን እየጠጣን ስለኒኮል ያወራልኛል። ስለአሸዋ ጡቶቿ፣ ስለወተት ጭኖቿ፣ ስለነበልባል እምሷ፣ ስለቅዱስ ብልግናዋ፡ የቃላት ቃና ይፈጥራል። በቃላቱ ላይ እየተንሳፈፍን የኢክስን ፀሀይ እየሞቅን በሀሳባችን ኒኮል ጭኖች መሀል ገብተን እንጨማለቃለን። አንድ ሽባ አይነት ደስታ ልባችን ውስጥ ይንፏቀቃል

እስካሁን እንግዲህ በጋ አልፎ፣ በልግ ተጋምሷል። ቅጠሎቹ አረንጓዴ ስልችቷቸው በቡና አይነት፣ በብጫ ብጤ፣ በቀይ መሳይ ቀለማት አሸብርቀዋል። ፀሀይዋ ከኛ እየራቀች ትሄዳለች፣ ሙቀቷ እየተቀነሰና እየጣመን ይሄዳል። ከምሳ በኋላ ኩር ሚራቦ ላይና በየመናፈሻው ውስጥ የኢክስ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች አግድም ወምበሩን ሁሉ ሰፍረውበት፣ በፀሀይ እንደ ዶሮ ያንቀላፋሉ። ህፃናቱ አሸዋ እየሰፈሩ ወይም ባለሶስት እግር ብስኪሌት እየነዱ ይንጫጫሉ። አንዳንዶቹም ከእናታቸው ወይም ከአያታቸው ጋር ኳስ እየተወራወሩ ይጫወታሉ። የኢክስ አዛውንት «ቡል» የተባለውን



@BOOKALEM

ጨዋታ የብረት ኳስ እየወረወሩ ይውለበታል። ጎረምሶቹና ኮረዳዎቹ በየካፌው ተቀምጠው ያወራሉ፤ በየዛፉ ስር ሳር ላይ ተጋድመው ይሳሳማሉ። ንፁህ ውብ ሰማይ ከኢክስ በላይ ተዘርግቷል፤ ፀሀይዋ ፊቶቻችን እንደምትንሸራሸር ብጫ የእሳት ኳስ ናት። ሊመሽ ሲል፣ ለአንድ ሰአት ያህል ፀሀይዋ እንደ ትልቅ ብርቱካን ሰማዩ ዳር ላይ ትንጠለጠላለች፣ የኢክስ ውብ ሰማይ እንደ ልጃገረዶቹ ጉንጭ ቀይ ብርቱካን ደረቅ ቀለም ይለብሳል። ከዚያ የተንጠለጠለችው ቀይ ብርቱካን አድማሱ ውስጥ ትገባለች የኢክስ ሰማይ ቀስ እያለ ይጠቁራል፤ ኮከቦቹ ብቅ ብቅ ይላሉ።

አንዳንድ ቀን ግን «ሚስትራል» የተባለው ሀይለኛ ነፋስ ኢክስን በጥፊ ያጮላታል፣ ሽማግሌዎቹና ህፃናቱ በየቤታቸው ይሸሸጋሉ፤ የልጃገረዶች ፀጉር ይበታተንና ወደአንድ በኩል ይፈሳል፤ ቀሚሳቸው መጣት ገላቸው ላይ ይለጠፍና ቅርፃቸውን ወለል አርጉ ያሳያል። ሰዎቹ ሲሄዱ ጉምበስ ብለው፣ ፊታቸውን አጨማደው፣ የያዙትን እቃ አቅፈው፣ ከንፋሱ ጋር እየተጋፉ ነው። ሚስትራል ልክ ለሶስት፣ ለስድስት፣ ወይም ለዘጠኝ ቀን ነው የሚነፍሰው ይባላል። ነፍሶ ሲሰለቸው ይሄዳል። ኢክስ ውስጥ ሰላም ይመለሳል. . .

. . . ሲልቪ ትፅፈው የነበረው ረጅም ልብወለድ ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ እምቢ አላት። ከዚህ በፊት፣ አንድ መቶ ገፅ ያህል ከፃፈች በኋላ፣ ከደረሰችበት መቀጠል ፈልጋ ታሪኩ እምቢ ብሏት፣ እኔን በጣም አስቸግራኝ ነበር። አንዴ ማርሰይ ውሰደኝ ትለኛለች፣ አንዴ ሜካ አንዴ ናይት ክለብ ውሰድና አስክረኝ ትለኛለች፣ አንዴ ቤት መጥተህ ቁጭ በልና ውሰደኝና ፍቅር እንስራ ትለኛለች፣ አንዴ ቤት መጥተህ ቁጭ በልና እኔ ልፃፍ ትለኛለች። ይሄ ሁሉ ሲሆን፣ ድንገት ኩርፍ ኩርፍ እያለች ትእግስቴን ታስጨርሰኛለች።

በመጨረሻ፣ ከፊቴ ጥፋ፣ እኔ መጥቼ እስክፈልግህ ድረስ ፊትህን እንዳታሳየኝ አለችኝ። እሺ አልኳት። ከስድስት ቀን በኋላ መጣችና እየሳቀች «ስላስቸገርኩህ ይቅርታ አርግልኝ» አለችኝ

አሁን ደሞ መቶ ዘጠና ገፅ ላይ ካደረሰችው በኋላ፣ ታሪኩ ወደፊት አልቀጥልም እምቢ አላት። አሁንም አባረረችኝ። በሷ



@BOOKALEM

ምክንያት እኔም መፃፍ እምቢ አለኝ

ሉልሰገድን በበኩሉ የኒኮል እምቢታ ይጫወትበታል። ስለዚህ ሁለታችን «ካፌ ኒኮል» ሄደን ቡና አይነት ቢራ እናዛለን። ሉልሰገድ ስለኒኮል ያወራልኛል። በምኞት እየጋልኩ አዳምጠዋለሁ

«የኒኮልን ጡት እንግዲህ እንደ ነጭ ሰማይ ልታየው ትችላለህ። ሰማዩ መሀል ላይ ደማቅ ወይን ጠጅ ጨረቃ አለች። ወይን ጠጅን ጨረቃ ሮዝ ቀለም ብርሀን ከቧታል። ይታይሀል? . . . ታድያ ያንን ሞቃት ነጭ ሰማይ እየዳበስኩ፣ ጨረቃዋን መጉረስ ነው 'ሚታየኝ...»

የኒኮልና የሲልቪ ጡቶች ምናቤ ውስጥ ይደባለቃሉ፡ ሰላም ይነሱኛል፡ ሉልሰገድ ንግግሩን ይቀጥላል። . . .

በልግ ወደ ማለቂያው ተቃረበ



@BOOKALEM

# ዘጠኝ

## ባህራም
## ሞት

ያን ሰሞን ጀምሺድ ታሞ ተኛ:: ልጠይቀው ወደ ቤቱ ሄድኩ:: ሌሎቹ በሚጠይቁት ሰአት ብሄድ ምንም አልጠቅመውም በማለት፣ በትምህርት ሰአት ሄድኩ:: ፎቁን ውጥቼ በሩን ብሞክረው ተቆልፏል:: ደወሉን ተጫንኩት፣ ውስጥ ሲደውል ተሰማኝ:: ቆየሁ

የጀምሺድ ቤት ሳይሆን፣ በግራ በኩል ያለው የጎረቤቱ በር ተከፈተ:: መነፅር ያደረገ መላጣ ሽማግሌ ሀኪም አንገቱን ብቅ አርጎ አየኝ:: አየሁት:: ከበሩ ወጣ:: ነጭ የሀኪም ኮቱ በጣም ንፁህ ነው:: በእጁ መርፌ ይዟል:: ጀምሺድ የነገረኝን ታሪክ አስታወስኩ

ሀኪሙ ዙሪያውን ተገላመጠና ሲያበቃ፣ ማንም እንደሌለ ካረጋገጠ በኋላ፣ በሹክሹክታ

«ይምጡ ልውጋዎት» አለኝ

ዝም ብዬ አየሁት

«ካልፈለጉ ላስገድድዎት አልችልም:: ነፃነትሳ? ዱሩ፣ ለኔ ያው ነው:: ደሞ ደንታ የለኝም እንጂ» እያለ ለራሱ እያጉረመረመ ወደ ውስጥ ገባና በሩን ዘጋ

ጀምሺድ ተኝቷል መሰለኝ ብዬ ደረጃውን መውረድ ስጀምር በሩ ተከፈተ:: ዘወር ስል ኒኮል ነች

«ይቅርታህን:: አስጠበቅኩህ? ሽንት ቤት ነበርኩ» አለችኝ:: አመዳም ፀጉሯ ተሞነጫጭሯል:: ሸሚዟ በአንድ በኩል ከጉርዷ ወጥቷል:: ገባን:: ጀምሺድ አልጋው ውስጥ ትራስ ተደግፎ



@BOOKALEM

እንደተቀመጠ፣ እያሳቀ

«ዶክተር ሽናይትዘር መርፌ ይውጉህ!» አለኝ:: የሰው የ[illegible] ተምንጫጭር ግምባሩ ላይ ወድቋል:: ግን ፊቱ የታመ[illegible] አይመስልም::

ኒኮልና ጀምሺድ እየተኙ ስለዶክተሩ ነገሩኝ:: [illegible] የማይገኝ ሰላማዊ እብድ ነው:: የመጣውን ሁሉ መርፌ ሊወጋ[illegible] እያለ ይጠይቃል፤ አሉኝ:: እንጋገራቸው አንድ ነገር ለመደበቅ የ[illegible] ሰው እንጋገር ይመስላል

ትንሽ ቆይታ ኒኮል ክፍል አለብኝ ብላ ሄደች:: ጀም[illegible] ስለንረቤቱ ዶክተር ኮሚክ ወሬ እያወራ ሲያስቀኝ ቆየና ተነስቶ [illegible] ሽንት ቤት ገባ

በፍጥነት በፀጥታ ተነስቼ የራስጌውን ፍራሽ አነሳሁ:: እ[illegible] ሽቦ ላይ አንድ ጥቁር የቢት ሙታንቲ:: ሙታንቲው አጠገብ አ[illegible] አምስት የተጨማደደ ለስላሳ «ክሊኒክስ» ወረቀት:: ወረ[illegible] ዕጊረዳ አይነት ስለሆኑ ርጥበታቸው ለእይን ያስታውቃል:: [illegible] ብዬ ወረቀቶቹን አሸተትኩ:: የግብረ ስጋ ሽታ:: ያለጥርጥር::

ተመልሼ ወንበሬ ላይ ከተቀመጥኩ በኋላ፣ ተነስቼ የሰው [illegible] ሳሽት ታየኝና፣ ለራሴ «ሸርሎክ ሆምዝ!» ብዬ በሀይል [illegible] ጀመርኩ

ጀምሺድ ከሽንት ቤቱ «ለምን መሳቅ?» አለኝ

«መርፌ መውጋት» አልኩትና ሳቄን ቀጠልኩ

ሉልሰገድ ስለኒኮል ባይነግረኝ ኖሮ፣ ኒኮልንና ጀምሺድን [illegible] ሪጥር ነበር? አይመስለኝም

በጀምሺድ አገር ደምብ የሚያፈላው ሻይ በጣም ይጣፍ[illegible] እሱን እየጠጣን ወሬ ጀመርን

ጀምሺድ እንደሚለው ከሆነ፣ በቁማር መክበር አይቻል[illegible] በቁማር የሚከብር ቁማር ቤቱ ብቻ ነው:: ምንም ያህል ብ[illegible] ያችን የበላሀትን ተመልሰህ እስከታስበላ ያቁነጠንጥሀል:: በ[illegible] ለመክሰር እንጂ ለመክበር አይቻልም:: እንዲህ ከሆነ ጀምሺድ [illegible] ቁማር ይጫወታል? ስከሬው ለምን ይጠጣል?

ለጀምሺድ እንደሚታየው፣ ኑሮ ጨትጫቃ ሚስት ናት፣ [illegible]



@BOOKALEM

ሚስት፡ ና ምግብ ብላ፣ ና ተኛ፣ ና ሽንት ቤት ሂድ፣ ና ትምህርት ሥራ፣ ና ይህን አድርግ፣ ና ያንን ፈልግ፣ እያለች መጨቅጨቅ ነው። ታድያ የሰው ልጅ ከዚህ ሁሉ ጭቅጭቅ ለመገላገል አንዳንድ ጊዜ ቢሰክር ይፈረድበታል?

ጀምሺድ የኑሮን ችግሩን ሊረሳ የሚችለው ቁማር ቤት የሄደ እንደሆነ ነው:: ቁማር ቤት ውስጥ ያለችው ኑሮ፣ ነገሯ ችሎ ማስተ ልትምህን፣ የማትጠገብ፣ ለዛዋ ሁልጊዜ የሚታደስ ውሸታም ናት:: ኑት ምታለሽም ውብ ውሸታም!

«እኔ ቁማር ስጫወት መኖሬን ይረሳለሁ:: መኖሬን ሲረሳ፣ ያን ጊዜ ኑሮን ኖርኳት ነኝ ማለት ነው:: ሌላ ጊዜ ኑሮን ሲኖራት፣ እኔን እያታለለች ነው ችሎ ናት ደስታ የለም:: ቁማር ጊዜ ግን፣ ቁማር ሬሳም ሲውጠኝ ሳለ:: ኑሮ መሀል ውስጥ እገባ፣ ከንቱ አይደለች፣ አለሃትም እኖራታለሁ ማለት»

**ጀምሺድ ስለቁማር ሲያወራ አይኖቹ አይስቁም**

እንስሳ ኑሮ አይሰለቸውም (ይሄ የጀምሺድ አስተሳሰብ ነው) ምክንያቱም እንስሳ ይኖራል እንጂ መኖሩን አያውቅም:: ስለዚህ ኑሮ አይመረውምም አይሰለቸውምም:: ስለዚህ ነው እንስሳ ራሱን የማይገድለው:: «በሬ ወይም አህያ ወይም አይጥ ወይም ውሻ ወይም ሌላ፣ ራሱ ገደለ አሉ ሰምተህቻዋል ታውቃለህ?» ሰውን ከእንስሳ የሚለየው ማሰቡ አይደለም:: በመጠኑ ይሁን እንጂ እንስሳም ያስባል:: ሰው ከእንስሳ የሚለየው በመሳቁ አይደለም:: ዝንጀሮም ይስቃል:: ሰው ከእንስሳ የሚለየው፣ ህይወቱን እየኖራት እንደሚኖራት በማወቁ፣ ከህይወት በኋላ ሞት መከተሉን በማወቁ፣ እነዚህም እውቀቶች ለሰው ልጅ ኑሮን ከንቱ፣ ሞትን መራራ በማድረጋቸው፣ በዚህ ነው ሰው ከእንስሳ የሚለየው

በመሰረቱ ህይወት ግሩም ስጦታ ናት:: ኑሮ ግን ይሰለቻል:: ሀዘን ጥልቶበታል:: ብሶት ይበዛበታል:: በሽታ ወሮታል:: ሞት ሳይቀር፣ ደሞ ይቆያል እንጂ አይቀርም:: ስለዚህ፣ ብሶት ሊበዛ፣ ለምን አሁኑኑ እስኪሞቱ ደስታ ሳይገኝ፣ ብሶት ችሎ የሆነ ሀዘን፣ ብሶት እንሞትም? ለምን ራሳችንን እንገድልም? ራሳችንን የማንገድለው ሞትን የመረረው እውቀት ምን ይወደዳል? ይኸው ነው ለምንፈራ ብቻ ነው:: ፈሪ ነን በቃ::



@BOOKALEM

ስለዚህ፤ ልናደንቀው የሚገባ ሰው ማን ነው? ራሱን ለማጥፋት የደፈረ ሰው ነው፡፡ እሱ ብቻ ነው፡፡ እኛስ ዋናው አላማችን ምን መሆን አለበት? ይህን የመሰለችግት ቀሚስ አውልቀን ወዲያ መጣል፤ በተቻለ ፍጥንት ራሳችንን መግደል

«እኔ ራሴ ለመግደል ዋና ምኞት፡፡ ግን እስካሁን ድፍረት የለም፡፡ አንድ ቀን ግን ለመድፈር ተስፋ፤ ያን ጊዜ እኔ ሰው፤ እውነተኛ ሰው፡፡ እስከዚያ ድረስ ግን ከንቱ ቀማርተኛ፡፡»

ጀምሺድ ራሱን ስለመግደል ሲያወራ አይኖቹ አይሰቱም

በልግ ከዛፎቹ ላይ በሩማ፤ ቀይና ወርቃማ ቀለማቱን ሰብስቦ የሙቀትና የውበት ጓዙን ጠቅሎ ኢክሰን ለቆ ሊሄድ ተነሳ

የኢክስ አየር መብረድ ጀመረ፡፡ ሽማግሌዎቹ፤ አሮጊቶቹና ተቋሮቹ፤ ሹራብ መደረብ ካፖርት መልበስ ጀመሩ፡፡ ወጣቶቹ ፈረንጆች ግን ገና ብርዱ ሊሰማቸው አልጀመረም

ሉልሰገድን ኒኮል እምቢ ስትለው እኔጋ መጥቶ «ካፌ ኒኮል ይወስደኝና፤ እየቀረበን በመጣው የክረምት ብርድ ምክንያት፤ ቤት ውስጥ ገብተን ቁጭ ብለን ስለኒኮል ያወራልኛል፡፡ የጭገሯ ፀጉር እንደራሷ ፀጉር አመዳም ሳይሆን፤ ንፁህ ወርቅ ቀለም የተቀባ ነው፤ ወተት የመሰለው ነጭ ቆዳዋ ላይ ረገፍ ገፍም የተጠላለፈ ውብ ወርቃማ ሀረግ መስሉ በቅሏል፡፡ ታዲያ እምሷ ዳር የበቀሉት ፀጉሮች፤ ውሀ ዳር እንደበቀለ ቄጠማ ናቸው፤ አንዳንዶቹ ከሁለቱ ከናፍር ተንጠራርተው ተጠላልፈው፤ ጎምበስ ብለው እምሷ ውስጥ የፍቅር ውሀ ያጠጣሉ. . . ወዘተርፈ.

አንድ ቀን ግን፤ ስለሷ ያወራልኛል ብዬ ስጠብቅ ስለጀምሺድ ሊነግረኝ ጀመረ፡፡ ሁለቱ ጓደኛሞች ሆነዋል፡፡ ጀምሺድ ቁማር ለመጫወት ካዚኖ ሲሄድ ሉልሰገድን ይዞት ይሄዳል፡፡ ከዚህም በላይ ሉልሰገድ የጀምሺድ ሻይ ሱስ ይዞታል፡፡ ሁለቱም ሻይውን የሚጠጡት በኢራን አገር ወግ ነው፡፡ በፊት ከአራት ማእዘኑ ስኳር ላይ ይገምጡና፤ ቀጥሎ ሻይ ፉት ይሉበታል፤ እንጂ ስኳሩን ሻይ ውስጥ አይጨምሩትም

«ትላንት ማታ ጀምሺድ ሻይ ሳጠጣህ ብሎ ወሰደኝ» አለ



@BOOKALEM

ሉልሰገድ:: (ይህ የሚሆነው ጀምሺድ ድኖ ከተኑሳ በኋላ ነው::)

ጀምሺድ በተገማመደ ፈረንሳይኛው ኮሚክ ወሬ እያወራ ሻይውን ጨርሰው ሲያበቁ

«አንድ ነገር ሊያሳይህ?» አለው

«አሳየኝ» ሲለው፣ ከጠረጴዛው ኪስ ውስጥ ሽጉጥ ጥይቶችም አወጣና አጎረሰ:: አንድ ቃል ሳይናገር ሽጉጡን አቀባበለ

«አሁን መተኮስ ብቻ:: እንዲት ጣት:: እንደዚህ» አለና ሽጉጡን ሉልሰገድ ደረት ላይ አነጣጠረው

ሉልሰገድ ለመሳቅ እየሞከረ፣ ግን ላቡ ግምባሩ ላይ ብቅ ብቅ እያለ «ተው 'ንጂ:: ይባርቃል» አለ:: ድምፁ የሌላ ሰው ሆኖ ተሰማው

ጀምሺድ ሽጉጡን እንዳነጣጠረ

«አይባርቅ:: እኔ የፈለግኩ ይባርቅ:: እኔ ሳልፈለግኩ አይባርቅ» አለ:: ፊቱ ላይ ዝምተኛ አይነት ቁጣ ሰፍሯል፣ አይኖቹ ውስጥ ምህረት የማያውቅ ጭካኔ አድፍጧል

ሉልሰገድ በድንጋጤና በፍርሀት ውሀ ሆኗል:: ላቡ ከግምባሩ ወደ ጉን ይወርዳል:: መሀረቡን አወጣና ግምባሩን ጠረገ:: እጁንም ጠረገ:: እጁ ይንቀጠቀጣል:: ጀምሺድ አሁን ቢተኩስስ?

ጀምሺድ ሽጉጡን ወደ ሉልሰገድ ግምባር አነጣጠረ

«አሁን እተኩስ፣ ጥይት አይኖችህ መሀል» አለ

«ምን አረግኩህ?»

«ምንም»

«እንግዲያው ሽጉጡን ወደዚያ በለዋ»

«ቆይ አንድ ነገር ሊነግርህ»

«አሱን ወደዚያ በለውና ትነግረኛለህ»

«የለም:: እኔ ሊነግርህ፣ ሽጉጥ አይኖችህ መሀል:: ያን ጊዜ ጉሩ»



@BOOKALEM

ሉልሰገድ እንደገና ግምባሩን እያደረቀ

«እሺ ንገረኝ» አለ

«ኒኮል፡፡ ተው፡፡ በቃህ፡፡ ኒኮል ቤት መሄድ የለም፡፡ ነገ ስትሄድ በትልልቅ አይን ማየት፣ የኒኮል ቂጥ በአይን መብላት የለም፡፡ አለዚያ ጥይት! በአይንህ መሀል! እሺ?»

«እሺ»

«አሁን ተነሳ፡፡ ሂድ፡፡ ደህና እደር፡፡»

«ደህና እደር» ብሎ ሉልሰገድ ተነስቶ ወጣ፡፡ ባቡር መንገድ ሲደርስ አስታወከው፡፡ ብርድ ብርድ አለው

ሲቴ ሄዶ ግላውን ታጥቦ ጥርሱን በርሾ ወደ ከተማ ተመልሶ አንድ ቢራ ጠጣ፡፡ ይህን ጊዜ ስድስት ሰአት ይሆናል

«አሁን የምነግርህ በሙሉ የሆነ ነገር ነው» አለኝ ሉልሰገድ «ግን እኔ ራሴ በፈቃዴ የሰራሁት አይደለም፡፡ የማደርገውን ሁሉ ከማድረጌ በፊት አንድ ደቂቃ አስቀድመህ 'አሁን ምን ልታደርግ ነው?' ብትለኝ 'እንጃ' ነበር የምልህ፡፡ ምክንያቱም፣ አላውቀውም ነበር፡፡ እኔ አይደለሁማ ያደረግኩት! ውስጤ አንድ ባእድ መንፈስ ወይም አጋንንት ገብቶ ነው የሰራው፤ ሳላውቀው ይታወቀኛል

[«የሆነ ሆኖ ምን ሰራህ?» አልኩት፡፡]

ቢራዬን ከጠጣሁ በኋላ ሰአቴን አየሁ፡፡ ስድስት ከሩብ፡፡ በቀጥታ ኒኮል ቤት ሄድኩና አንኳኳሁ፡፡ «ክፈችኝ፣ የምነግርሽ አለኝ» አልኳት፡፡ ከፈተች፡፡ ገባሁና ወደ አንድ በኩል ገፋኋት በሩን ቆለፍኩት፡፡ ረዥም ስስ የሌሊት ቀሚሷን ለብሳ፣ ላይዋ ላይ ከሮጣ የተሰራ የቤት ውስጥ ካፖርት ደርባለች

«ሂጂ ውሀ አምጪልኝ ጠምቶኛል» አልኳት፡፡ ስታመነታ ገፈተርኳት፡፡ ቃል ሳትናገር ወደ ወጥ ቤቷ ሄደች፡፡ ወደ መኝታዋ ገባሁና በፍጥነት ልብሴን ማውለቅ ጀመርኩ፡፡ 'ለምን?' ብለህ ብትጠይቀኝ በጭራሽ አላውቀውም፡፡ ጋኔን ሰፍሮብኛል ብዬሀለሁ፡፡ ውሀውን ይዛ እንግዳ ቤት ስትገባ አጣችኝ፣ «የት ነህ?» አለች

«ነይ ወዲህ» አልኳት፡፡ ገባች፡፡ በሩ አጠገብ እንደቆመች ቀረች፡፡ ወለሉ መሀል እጆቼን ወገቤ ላይ አድርጌ ቆሜያለሁ



@BOOKALEM

ራቁቴን ነኝ:: ቁጣዬ ግትር ብሎ ቆሞ፤ ትር! ትር! ትር! እያለ ጓንቲራ ይረግጣል:: አስታውስ፤ ይህን የምሰራው አሁን የማወራልህ ሉልሰገድ እንዳልመስልህ:: ሌላ ሰው ነኝ

«አውልቂ!» አልኳት:: አቤት ድምጿ ውስጥ ያለው ትእዛዝ ምርጫ አልነበራትም:: የውሀውን ብርጭቆ ኮሞዲኖው ላይ አስቀመጠችና፤ የሮጣ ካፖርቷንና የሌሊት ቀሚሷን አውልቃ እዚያው ወለሉ ላይ ጣለችው:: ዝም ብዬ ሳፈጥባት ጡት መያዣዋንና ሙታንቲዋን አወለቀች

«ነይ ወዲህ!» አልኳት:: መጣች:: ፊቴ ተምበረከከች:: አቀፈችኝ::

ከዚያ በኋላ ያለውን እንዳልነግርህ 'ንግዲህ መናገር የሚገባ አይመስለኝም:: እየህ፤ ራቂታም ባለጌ ከመሆኗ የተነሳ ትዳሱ ምስጢር ይሆናል:: እና ብናገረው ቃላቱ ያረክሱታል:: ብቻ፤ ከተፈጠርኩ እንደ ትላንት ያለች ሌሊት አሳልፌ አላውቅም:: እኔ 'ምለው፤ እንደ ኒኮል ያለች ሴት እየበዱ ሁለት አመት ኖረው ቢሞቱ ምን አለበት?

ሟት ወደ አምስት ሰአት ላይ ነቃሁ:: ኒኮል ተኝታለች:: እንዳልቀሰቅሳት ቀስ ብዬ ልብሴን ለብሼ ወጣሁ

አሁንም የትላንት ሌሊቱ መንፈስ እየነዳ ጀምሺድ ቤት ወሰደኝ

ገባሁና ጀምሺድን «ሻይ አፍላልኝ» አልኩት:: ለምን እንደመጣሁ ግራ ገብቶታል:: ሻይውን ከጠጣን በኋላ ተነሳሁና ቆምኩ:: አይን አይኑን እያየሁ

«ትላንት ማታ የሸጉጥህን ቱዳዳ አይቼ ቆመብኝ» አልኩት

እየሳቀ «እና?» አለኝ

«እና እምስ አስፈለገኝ:: እና ሂጄ ኒኮልን በዳኋት»

ሳቁ ጠፋ:: አይኖቹ ውስጥ የትላንቱ ጭካኔ ብቅ አለ:: ተነሳ:: አቤት አይኖቹ ሲያስፈሩ! እዚህ ጀርባዬ ውስጥ ብርድ ተሰማኝ:: ተነሳና እጁን ትከሻዬ ላይ እያሳረፈ በጨካኝ አይኖቹ እያየኝ

«ጎበዝ ነህ:: በጣም ጎበዝ:: አንድ ቀን እገድልሀለሁ:: ሂድ» አለኝ:: ትቼው ሄድኩ:: አይኖቹን ሳስታውስ አሁንም ጀርባዬን ይበርደኛል [አለኝ ሉልሰገድ]



@BOOKALEM

ከዚህ ከሽጉጥ ፍጥጫ በኋላ ጆምቪድና ሉልሰገድ ብዙ ጊዜ ብዙ ቦታ አብረው ይታዩ ጀመር:: ማታ ሁለቱ በጆምቪድ መኪና ይሄዱና፣ ኒስ፣ ካን ወይም ሞንቴካርሎ ቁማር ሲጫወቱ ሰንብተው ስኛ ሟት ይመለሳሉ:: ከውጭ ለሚያየው ሰው ጓደኝነታቸው እየጠበቀ ሄደ . . .

ክረምት እየተንፏቀቀ መጣና፣ ከወርቃማው በልግ ጋር ተቃቅፋ የነበረችውን የኤክስ ከተማ እንደ ቀናተኛ ሌላ ውሽማ በብርድ ይገርፋት ጀመር:: ሽማግሌዎቹንና አሮጊቶቹን ከየመንገዱና ከየመናፈሻው አባረራቸው:: ልጃገረዶቹ ቆንጆ ስስ ቀሚሳቸውን ትተው ወፍራም ሱፍ ቀሚስ፣ ሱሪና ወፍራም ሹራብ፣ ካፖርት እየለበሱ፣ ውብ ቅርፃቸውን ከክረምቱ አይን እየሸሸጉ፣ በቢጫ ቀያይ ወይም ብር መሳይ የጥፍር ቀለም ተቀብተው ሲውለበለቡ የነበሩትን ጣቶቻቸውን በወፍራም ጓንቲ ውስጥ እየደበቁ፣ ከክፍል ወደ ምግብ ቤት፣ ከምግብ ቤት ወደ መኝታ ቤት በፍጥነት ኩስ ኩስ ይሉ ጀመር:: ውብ ዳሌያቸውን እያወዛወዙ በዝግታ መራመድ፣ ሰገረላ ጉንጫቸውን እያሳዩ፣ በቀያይ ከንፈራቸው እየሳቁ፣ በተኳለ አይን ጎረምሳውን መቃኘት ቀረ:: (ኩሉንና የከንፈር ቀለሙን ብርድ ስለሚያስንጣጥቀው ለአይን ደስ አይልም::) ደም የሸሸውን ነጭ ጉንጫቸውን ግራጫ ብጤ የሳሽ ፀጉር ወረረው

በየመንገዱ ዳር በተርታ የተተከሉት ዛፎች ራቁታቸውን ቆመው የኤክስን ንፁህ ሰማይ በጭራሮዎቻቸው ይቧጥጡታል:: ቅጠሎቹ በሙሉ ረግፈው የባቡር መንገዱን ዳርና የሰው መተላለፊያውን ሞልተውታል:: ሰው በፍጥነት ሲራመድ በቡት ጫማው ይፈጫቸዋል

አንዳንድ ቀን በረዶው እንደ ጥጥ በዝግታ ይወርድና ኤክስን በንፁህ ነጭ ሻሽ ይገንዛታል:: በሱፍ የተከናነቡት ልጃገረዶችና ጎረምሶች ሜዳ ወጥተው በረዶውን እያድቦለቦሉ ይፈነካከታሉ፣ ይሳሳቃሉ:: ትንፋሻቸው እንደ ጉም ከአፋቸው ቡልቅ! ቡልቅ! ሲል ይታያል:: ጥቁሮቹ በረዶው ላይ እየሆኑ ፎቶግራፍ ይነሳሉ

የኤክስ ሰማይ አብዛኛውን ጊዜ ብሩህ ሰማያዊ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ውሀ አረንጓዴ ይሆናል፣ ወደ ማታ ሰአት እንደ ልጃገረዷ ጉንጭ ይቀላል:: የኤክስ ሰማይ ደመና አይለብስም፣ ሁልጊዜ ራቁቱን ነው፣ ሁልጊዜ ውብ ነው፣ ሁልጊዜ ሰላማዊ ነው:: ማታ ማ



@BOOKALEM

የአልማዝ ከዋክብትና የፀጥታ ሰላም ይለብሳል

ክረምት ሲሆን ሌሊቶቹ ይረዝማሉ፣ ቀኖቹ ያጥራሉ፡ ፀሀይዋ ጧት ወደ አንድ ሰአት ተኩል ላይ ትወጣና ከሰአት በኋላ ወደ አስር ተኩል ላይ መጥለቅ ትጀምራለች፣ በሽታ እንደያዘው እየማቀቀች እየደከመች ትሄዳለች:: ፋት፣ ፋት፣ ፋት በጣም ፋት ሆና ኮሳሳ ብርሀን ትልካለች:: እቺ ፀሀይ በበጋው የሙቀት ምንጭ ነበረች፣ ለእክስ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች የህይወት ተስፋ ነበረች፣ አሁን ግን ሰማዩ ተበስቶ ከውጭ የብርድ ሙራዎች የሚያስገባ ይመስላል

ብርዱ መላውን ፍጥረት ጨብጦ ያዘ:: የሁላችንም ህይወት በክረምቱ ብርድ ታሰረ፣ በቆፈን ተቋጠረ:: ወይይና ፀሀይ መጥተው እስኪያስፈቱንና እስክንንቀሳቀስ ድረስ፣ የህይወታችን ታሪክ በያለበት ረጋ:: ተካና ጀርመኗ እኔ የማላውቀውን ግንኙነታቸውን ቀጠሉ:: ጀምሺድና ሉልሰገድ በኒኮል የፍትወት ገመድ ተሳስረው መለያየት አቅቷቸው፣ ጤና የለሽ ጓደኝነታቸውን ቀጠሉ፡ ለገና እረፍት ባሀሬም ወደ ኢክስ ሲመለስ ጊዜ፣ ኒኮልን ትተውለት ሁለቱ ተያይዘው ወደ ሞንቴ ካርሎ ሸሹ:: እኔና ሲልቪ አልፎ አልፎ እየተገናኘን፣ የቀረውን ጊዜ ስንፅፍ እንሰነብት ነበር

በብርዱ ምክንያት የህይወታችን ታሪክ መፍሰሱን መለዋወጡን ትቶ፣ በያለበት ረጋ

አዳሞ የተባለው ዘፋኝ

"Tombe la neige
Tu ne viendras pas ce soir
Tombe la neige
Me crie mon deséspoir…"

(በረዶው ይወርዳል
እንግዲህ ዛሬ ማታ አትመጪም
በረዶው ይወርዳል
ተስፋ መቁረጤ ይነግረኛል . . . »)

እያለ የክረምት እንጉርጉሮውን ያዜማል. . .

ፀሀይዋ ቀስ በቀስ የሸሸችንን ያህል ቀስ በቀስ ትጠጋን



@BOOKALEM

ጀመር:: እየተቀነሰ የሚሄደው ብርድ፣ ተጥሎም እየበረታ የሚሄደው ሙቀት፣ ፈግቶ የነበረውን የፍጥረት ደም ቀስ በቀስ ያሟሟቀው ጀመር:: መጀመሪያ አንዳንዷ ደፋር ቅጠል ብርዱን አሸንፋ እንገቷን ብቅ ታደርጋለች፣ ራቁታቸውን የከረሙት ቁራሮ ቅርንጫፎች ላይ ስትታይ ታስደንቃለች፣ ታስደስታለች፣ የድል አድራጊው ህይወት ፈታሞራፊ ነች፣ ምስጢራዊ ተአምር ነች:: እንግዲህ ሌሎቹ ቅጠሎች ይከተሏቸዋል፣ የኢክስ ዛፎች በራቁት ቁራሮቻቸው ሰማዩን መቧጨር ትተው፣ በለምለም አረንጓዴ ልብሳቸው ይወለውሉታል፣ ያፀዱታል:: የኢክስ ጎረምሶችና ኮረዳዎች መጀመሪያ ካፖርትና ጎንቴይኖቻቸውን አወለቁ፣ ቀጥሎ ሹራባቸውን አውልቀው መጣል ጀመሩ:: አንዳንድ ደፋር አሮጊት ወይም ሽማግሌ ካፖርቱን እንደለበሰ መንገድ ላይ ይታይ ጀመር:: ክረምቱ አለፈ.

ፀደይ መጣ:: የኢክስ ልጃገረዶች ከባድ የክረምት ልብሳቸውን ገፈው ጥለው፣ ክረምቱ አልብሷቸው የነበረውን አስቀያሚ ነጭ ጎሽ ፀጉር አራግፈው፣ የተፈጥሮ መብታቸውን መልበስ አመጡ:: በጉራቸው ቁንጅናቸው ላይ ተቆልሉ ወይም ወደ ኋላቸው እየፈሰሰ፣ ቆዳቸው ልስልስ ብሎ የስጌረጸ ቀለም እየለበሰ፣ በቀይ ከንፈራቸው የተከበበ ጥርሳቸው በፈገግታ እያብለጨለጨ፣ ተሸሽጎ የከረመው ወጣት ቅርፃቸው እየፋፋ፣ ሹል ጡታቸው ከፊት እየተንቀጠቀጠ፣ ያበጠ ዳሌያቸው ከኋላ እየተወዛወዘ፣ ይሄ ሁሉ ፀጋ የፀደይን መልካም ብርሀን ለብሶ በየመንገዱ እየተዘዋወረ፣ የኢክስን ጎረምሶች ምራቃቸውን ያስውጣቸው ጀመር:: በብርድ ተኮራምተው የከረሙት ኮረዳዎች አሁን በሙቀት ተዝናንተው፣ እየተፍነፈነፉ በሳሩ ሜዳ ይፈነጩ ይንከባለሉ ጀመር:: ከጎረምሶቹ ጋር ልፊያና መተቃቀፍ ተጀመረ

ሽማግሌዎቹና አሮጊቶቹ እየወጡ የኩር ሚረቦንና የመናፈሻውን አግዳሚ ወምበሮች ሰፈሩባቸው:: አረጅና ከወጣትነት ጋር እየተከበ የኢክስን መንገዶች በጎባጣ ጨምዳዳ እርምጃው ይንፏቀቅባቸው ጀመር

የክረምቱ ብርድ ገድቦ ይዞት የነበረው ታሪካችን አሁን በፀደይ ሙቀት እንደገና መፍሰስ ጀመረ

ፀደይ ለኢክስ ብርሀንና ሙቀት ከአረንጓዴ ቀሚስ ጋር ይዞላት ጀርመ ሲመጣ፣ ለተካ ችግር ይዞለት መጣ:: ባለሙስታፏ



@BOOKALEM

ታስቸግረው ጀመር:: ከአንድ ያገሬ ልጅ ጋር መውጣት ስትጀምር ተካ «ምን ትሽረሙጪያለሽ?» አላት:: «መሽርሞጥ አይደለም፣ ማማረጥ ነው» አለችው:: «እና የትኛችን ይሻላል?» አላት:: «በአንዳንድ ነገር እሱ ይሻላል፣ በሌላ ደሞ አንተ ትሻላለህ» አለችው:: ተካን ቅናት ይጦረሙረው ጀመር

ጥፍሩን እየነከሰ «አሁን ምን ማድረግ ይሻለኛል አባዘን?» አለኝ

«ትወዳታለህ?» አልኩት

«አዎን:: ብዙ ነገር ይገባታል::»

«እሷስ ትወድሃለች?»

«አዎን»

«እንግዲያው አግባታ»

«አብደሃል? ነጭ ማስት ይገቤ ብመለስ አባቴ አይታንቅም?»

«እንግዲያው ተዋት»

«እንዴት አድርጌ ልተዋት? በፊት እንኳ ቢሆን ልተዋት እችል ነበር:: አሁን ግን፣ ከዚያ ከንፍጣም ጀርመን ጋር መውጣት ከጀመረች ወዲህ፣ ከምተዋት ብገድላት እመርጣለሁ::»

«የሀበሻ ምቀኝነት ነው?» አልኩት

«አይደለም::»

«ታድያስ?»

«ኡ-ሀ! ስለቅናት አታውቅም 'ንጄ? እንግዲያው ልንገርህ:: ብትገድላት ፊታድህ እየህ፣ ስትቀና ልጅቷን በሀይል ትጠላታለህ:: ብትገድላት ፊታድህ አይሆን ሴትን ነው:: ግን በዚህ አለም ላይ ምን ትፈልጋለህ ቢሉህ፣ እሷን ነው 'ምትፈልገው:: ሁሉ ነገር ይቅር! ብቻ እሷ ትምጣ:: ገባህ 'ምልህ? ለምሳሌ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሱ ጋር የወጣች ጊዜ! ቤቷ ወስጄኳትና አንድ ጥፊ አላስኳት:: ወደ እስክትጠላ ልደበድባት ቆርጬ ኩቴን እወለቅኩ:: ታዲያ ጸግማጊ ጥፊ ሳወርድባት ስል ሰለ «Sauvage! አፍሪቃ ውስጥ ያለህ መሰለህ 'ንጄ?» አለችኝ:: እቅፌ እንደታጣሁ ቀረሁ:: ጸግማጊውን ጥፊ እንደማውረድ በታተገኩ ሳምኳት:: ስትፍጨረጨር በጉልበት ሙታንታዋን ቀድጄ



@BOOKALEM

ባት። ወደ አሊጋው 'ንኳ እስክመስዳት አላስቻለኝም። እዚያው ምንጣፍ ላይ በዳኋት። እንደጨረስኩ ታድያ በሀይል ቀፈፈኝ። እዚያው ወለል ላይ እንደተጋደመች ትቻት ወጥቼ ሄድኩ

«ይሄ ከሁለት ሳምንት በፊት ነበር። ከዚያ ወዲህ እንግዲህ ኑሮ መቃጠል ሆኗል።»

«ሰውየውን ተይው አልካት?» አልኩት

«እምን። 'እንዴት እተወዋለሁ? ላንተ ብዬ እንዴት እሱን ልተወው? አንተ ልትተኛኝ ነው 'ምትፈልገው። እሱ ግን ሊያገባኝ ነው 'ሚፈልገው። ባይሆን ለሱ ስል አንተን እተውሀለሁ 'ንጂ እሱንስ አልተወውም' አለችኝ።»

«ምን አልካት?»

«አንድ ሁለት ጥፊ አላስኳት። ስታለቅስ በግድ በዳኋት።»

«እንዲህ ከቀጠልክ ትተውሀለች» አልኩት

«ተሳስተሀል። በጥፊ መትቼ በጉልበት ስደፍራት በሀይል ነው ፍቅሬ 'ሚጥማት።»

«እንዴት ታውቃለህ?»

«ከሁኔታዋ ያስታውቃል»

«ዋ! ጥፊው ቢቀር ይሻለሀል» አልኩት

«አይገባህም። ቅናት ገና አላጋጠመህም» አለኝ

ግን አንድ ነገር ገብቶኛል። ልጅቷ ልታገባው ታጥቃ ተነስታለች

* * *

ክረምት አልፎ ፀደይ እንደገባ በፋሺስቶችና በኮሙኒስቶች መካከል ትልቅ አምባጓሮ ተነሳ። አምስት ስድስት ፋሺስቶች ይሆኑና አንዱን ኮሙኒስት ይዘው ይደበድቡት ጀመር። ኮሙኒስቶቹ ተማሪዎች፣ እጃቸውን ወይም ራሳቸውን በፋሻ ጠምጥመው ይታዩ ጀመር። ፋሺስቶቹ ወንድ ሴት ሳይሉ ያገኙትን ኮሙኒስት መደብደብ ሆነ። አንዷን ልጅ አራት ጎረምሶች ተጋግዘው

ደበደቧትና የአፍንጫዋን አጥንት ሰበሩት። ሆስፒታል ተኛች

ኮሙኒስቶቹ ከባድ የብረት መሳሪያ፣ አጭር የብረት ዱላ፣ ወይም ይህን የመሳሰለ ነገር እጅጌያቸው ውስጥ እየደበቁ ሶስት አራት እየሆኑ መዞር ግድ ሆነባቸው። ፌሌቢ ወይም ሽጉጥ እየያዙ የሚሄዱም ነበሩ

ባህራምን ልጠይቀው ትምህርት ቤቱ ሄድኩና የሆነውን ሁሉ አጫወትኩት። አብሮኝ ወደ ኢክስ መጣ። «የነገርከው ወሬ ያስ ያስኸ ይመስላል» አልኩት

«ለኮሙኒስቶቹ አዝንላቸዋለሁ። ግን ጥሩ ነው፣ ይጠቅማቸዋል። ለአምባገነር በቂ ዝግጅት የላቸውም፣ እያልኩ እጨቃጨቃቸው ነበር። ፈረንሳይ አገር አምባገነር አይሰራም። በስሁፍና በንግግር የሰውን ሀሳብ ማናወጥ ማንቃት ነው የሚያስፈልገው፣ ሲሉኝ ነበር። ብቻ የራሳቸው ጉዳይ ነው። የፈረንሳይ ህዝብ ወሬ ያበዛል። ስራ፣ ጀብዱ (Action) ስትለው በቁንጠኛ ሰዋሰው ስለ አርት ሊያወራልህ ይጀምራል። ተዋቸው እነሱን። እኔን ያስደሰተኝ ሌላ ነገር ነው።»

«ምንድነው?»

«ረብሻ ውስጥ ከገባሁ አመታት አለፉ። ናፍቆኛል—» በተጨበጠ ቀኝ እጁ ግራ መዳፉን እየወቀጠ «—ረብሻ ናፍቆኛል» አለ

እንግዲህ ኢክስ ውስጥ ኮሙኒስቶቹ የሚያዘወትሩት አንድ ካፌ አላቸው። ሮያሊስቶቹ አንድ ሌላ ካፌ ያዘወትራሉ (ሮያሊስቶቹ ፈረንሳይ ውስጥ ንጉስ ለማንገስ የሚፈልጉ ናቸው) ወንድ ለወንድ የሚዋደዱት አንድ ካፌ አላቸው። ፋሺስቶቹም የራሳቸው ካፌ አላቸው

ኢክስ እንደገባን ባህራም ፋሺስቶቹ ካፌ ወሰደኝ። ቢራ፣ ቡና እየጠጡ በየጠረጴዛው ያወራሉ። አብዛኛዎቹ ፂማቸውን በቁንጥ ያስተካከሉ ወጣቶች ናቸው። በጣም ያምራሉ

እኔና ባህራም መውጫው በር አጠገብ ያለችው ጠረጴዛ ጋ ቁጭ ብለን ቢራ ጠጥተን ሂሳቡን ከከፈልን በኋላ፣ ባህራም

«ምንም ቢመጣ ምንም፣ ከተቀመጥክበት እንዳትነሳ» አለኝ

«ምን ሊታረግ ነው?» ስለው



@BOOKALEM

«ታያለህ» አለኝ

ተነሳና ወደ ሽንት ቤት በኩል መራመድ ጀመረ። አንዱ ጎረምሳ ፋሺስት ከዚያው ሲመለስ ነበር ባህራምን የገጨው። ፋሺስቱ ሳያስብበት በልማድ "Pardon" ብሎት ሲያልፍ፣ ባህራም

«አንተ!» ብሎ ጮኸበት። ፋሺስቶቹ ወሬያቸውን አቆሙ። ካፌው በሙሉ በፀጥታ ባህራምን ማየት ጀመረ። የገጨው ፋሺስት ወደ ባህራም ዞሯል

ባህራም «ለምን ገጨኸኝ?» አለው

ፋሺስቱ «አንተ ነህ 'ንጂ የገጨኸኝ» አለው

«ውሸታም ፋሺስት! ውሻ ፋሺስት! ፈሪ ፋሺስት! ወንድ ከሆንክ ተከላከል። ልገርፍህ ነው» አለና ዘሎ ትግል ያዘው። የፋሺስቱ ጀርባ ወደኔ ስለነበረ፣ ባህራም ምን እንዳደረገው ለማየት አልቻልኩም። ብቻ ምንም ያህል ሳይታገሉ ፋሺስቱ ፍስስ ብሎ ወደ መሬት ወደቀ። ባህራም ከበላዩ እንደቆመ ዙሪያውን ተመለከተ። ከፋሺስቶቹ ማንም አልተነሳም

ባህራም ፋሺስቶቹን እያየ «ማንም ፋሺስት እንዲገጨኝ አልፈቅድለትም። ከንግዲህ ሌላ ፋሺስት የገጨኝ 'ንደሆነ፣ ቢሙን ነው 'ምላጭለት» አለና የወደቀውን ፋሺስት ተሻግሮ ወደኔ መጣ። አብረን ወጣን

(ፋሺስቶቹ እኔን ሌላ ጊዜ ቢያገኙኝ ይደበድቡኝ ይሆን? ብዬ ትንሽ ፈራሁ። ግን ደፍረው ጥቁር ተማሪ የሚደበድቡ አልመሰለኝም። ምክንያቱም እኛ የፈረንሳይ መንግስት እንግዶች ማለት ነን።)

ባህራም ኤክስ ውስጥ አራት ቀን ቆየ። ቀን ቀን ኮሙኒስቶቹን ሲመካከራቸው፣ እንዴት አድርገው መከላከል እንዳለባቸው፣ ፅሁፎቻቸውን እንዴት ቢያሰራጩ እንደሚሻል፣ እና ይህን የመሳሰለ ነገር ሲነግራቸው ይውላል። ማታ ማታ ፋሺስቶቹን በየጠባቡ መንገድ ሲደበድባቸው ያመሻል። በአምስተኛው ቀን ትምህርት ቤቱ ድረስ ሸኘሁት። ስለእምቧጓሮው ሲነግረኝ፣ ስለኳስ ጨዋታ የሚያወራልኝ መስሎ ተሰማኝ። በደስታ እየገነፈለ፣ ማድፈጡን፣ መዝለሉን፣ እጁን እንደ ሰይፍ አርጎ አንገት መምታቱን፣ እንደ



@BOOKALEM

ዳንስ አድርጎ ገለፀልኝ

«ማን ይህን ሁሉ ስሰራ አይቶኝ ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር! ያስተማረኝን ብልሀት በሙሉ ተጠቅሜበታለሁ» አለ

«ደህና ሁን» ብዬው ወደ ኤክስ ልመለስ ስል፣ ከኪሱ አንድ እቃ አውጥቶ አሳየኝ:: የፀጉር መቁረጫ መኪና «ቶንዶዝ»:: ምንድነው? አልኩት:: እየሳቀ «ፋሺስቶቹ ካፌ ሂድና እቺ ነገር ከሙኒስት መሆንዋን ትገነዘባለህ» ብሎኝ ተለያየን

ኤክስ እንደደረስኩ ፋሺስቶቹ ካፌ ገባሁ:: ብዙዎቹ እጃቸውን ወይም ጭንቅላታቸውን በፋሻ ጠምጥመዋል:: ግማሾቹ ፂማቸውን ላጭተዋል:: ፂማቸውን ያልላጩት ደሞ ጥቁር «ቤሬ» ቆብ አርገዋል:: ለካ ባህራም አንድ ፋሺስት በደበደበ ቁጥር ወይም ራሱን ወይም ፂሙን ይላጭለት ኖሯል

(እኔና ባህራም አንድ ግሩም የሆነ «ሀራኪሪ» የተባለ የጃፓን ፊልም አይተን ነበር:: እዚያ ፊልም አንዱ ጎበዝ እየዞረ የጠላቶቹን ፀጉር ይላጫል::)

ባህራም በሄደ በአራተኛው ቀን፣ አንዲት ኮሙኒስት ልጅ ካፌ ቁጭ ብዬ ሳለሁ መጣችና ወደ ኤክስ አንድ ነብሰ ገዳይ መጥቷል አለችኝ:: «ምን እንደሆነ — ማለቴ የቱ እንደሆነ — አናውቅም:: ግን መምጣቱን እናውቃለን:: ፋሺስቶቹ ናቸው ከማርሰይ ያስመጡት:: ባህራምን ሊደበድበው ወይም ሊገድለው ነው የመጣው::»

«ፋሺስት ነው?» አልኳት

«አይደለም:: የተገዛ ነብሰ ገዳይ ነው» አለችኝ

ያን ጊዜውኑ ሲልቪ ቤት ሄድኩ:: በኦቶቡስ እንዳልሄድ ምናልባት ፋሺስቶቹ ይከታተሉኛልና፤ ካንቺ ጋር ለሽርሽር የምንወጣ አስመስለን እንሂድ አልኳት:: በመኪናዋ ሄድን:: ለባህራም ነገርኩት:: ወደ ኤክስ ተመለስን

ሲልቪ ቤቷ ወስዳን እራት በላን:: ከዚያ ሶስታችንም ሄደን ፋሺስቶቹ ካፌ ገብተን ሁለት ሰአት ያህል አሳለፍን:: ይህን ሁሉ ጊዜ ባህራምና ሲልቪ ያወሩ፣ ይቀልዱ፣ ይስቁ ነበር:: እኔ ግን ሰውየው የቱ ምንም ያህል አላወራሁም:: ለባህራም ፈርቼለት ነበር::



@BOOKALEM

እንደሆን ብናውቅ እንኳ ለመከላከል እንሞክር ነበር። አሁን ግን ከማንኛውም አቅጣጫ ጦር ሊወረወርበት በሚችልበት ጭለማ ውስጥ፣ ባህሪም ብቻውን የሚራመድ መስሎ ተሰማኝ

አብሬያቸው ባለማውራቴ፣ የኔ ፍርሀት ቀስ እያለ ወደ ሲልቪ ተሳለፈባት

«ፈራሁ። በጣም ፈራሁ» አለች

ባህሪም «ምን ያስፈራሻል?» አላት። ግን ድምፁ እንደ ድሮ ልዝብ መሆኑ ቀርቶ፣ ትንሽ እሸሁም ሆኗል

«ማን እንደሆን ወይም የት እንደሆነ አናውቅም። አንድ ብቻውን መሆኑን 'ንኳ በእርግጥ አናውቅም።»

«እና?»

«አንድ ነገር ብትሆንስ? ብትሞትስ?» አለችው

«እኔ? ትቀልጂያለሽ? የኛ ቤተሰብ'ኮ እስኪጃጅ ካላረጀ አይሞትም። የኔ ወንድ አያት፣ ያባቴ አባት፣ በዘጠና ሰባት አመታቸው ብቻቸውን ሜካ መዲና ደርሰው ተመልሰዋል። ታድያ እንደተመለሱ የቤታችን ጣራ ዝናብ ማስገባት ሲጀምር ጊዜ፣ ሊያበጁት በመሰላል ወጡ። አበጅተውት ሲወርዱ ከመሰላል ወደቁና እግራቸው ወለም ብሏቸው ሁለት ሳምንት ሙሉ እንዲተኙ ሀኪም አዘዛቸው። ታድያ ሁለት ሳምንት እንዴት ይለፍ? ውሽማቸው ናፈቀቻቸው። እና ገና አንድ ሳምንት ሳይተኙ፣ ሌሊት ጠፍተው ውሽማቸው ቤት ሄዱ። መኝታ ቤቷ በመስኮት እገባለሁ ሲሉ ባልየው በጥይት ልባቸውን አፈረሰላቸው። ስንቀብራቸው የኔ አባት «አይ አባባ! አይ አባባ! እኛ ያረጀነው እያለን አንተ ወጣት ተቀጨህ!» ብሎ አለቀሰ።»

ስንስቅ ሲልቪ በጆሮዬ «እኔ ፍርሀት አቁነጠነጠኝ። ሽንቴ መጣ» ብላኝ ወደ ሽንት ቤት ሄደች

ባህሪምን «የጀምሺድን የሚመስል ታሪክ ከየት አመጣህ?» አልኩት

«ከጀምሺድ ነዋ!» አለኝ «ስማኝ። አንድ ነገር አርግልኝ። ኒኮልን ፈልግና ጀምሺድ ቤት ውሰድልኝ። ሽጉጥ አለው እሱ እዚያው ትደር። እና ነገ በሌሊት ተነስቶ ማርሰይ እንዲወስዳትና



@BOOKALEM

ለአንድ ሳምንት ያህል ተደብቀው እንዲቆዩ ንገረው::»

ቀፈፈኝ:: በባህሩም ትእዛዝ ኒኮልን ጀምሺድ ቤት ወስጄ ለጀምሺድ ላስረክበው ለአንድ ሳምንት ሙሉ! በጣም ቀፈፈኝ:: ግን ምን ማድረግ እችላለሁ?

«አንተም ይህን ስሞን ተጠንቀቅ:: ማታ ብቻህን አትውጣ» አለኝ:: ሲጋራ አቀጣጠለ:: እጁ ትንሽ ትንሽ ይንቀጠቀጣል:: ፍርሀት አሳደረብኝ

ሲልቪ ተመለሰች:: ደህና እደሩ ብያቸው ሄድኩ

ኒኮልን ቤቷ አገኘኋት:: ጀምሺድ ቤት ስንሄድ አጣነው:: ቤቱ ቁልፍ ነው:: ካፌ ዶርቢቴል ሄደን ጠየየቅን:: ተካ፣ ጀምሺድና ሉልሰገድ ኒስ ሄደዋል አሉን:: ኒኮልና እኔ የመጨረሻውን የማታ አቶቡስ ተሳፍረን ማርሰይ ወረድን:: አንድ ወሻቃ ቦታ ሆቴል አገኘን:: ባለ ሁለት አልጋ ክፍል ተከራየን:: ሁለታችንም ለባህሩም ሰግተናል:: እንቅልፋችን እንደማይመጣ ግልጽ ነው:: አንድ ቆሻሻ ብጤ ጭር ያለ ካፌ ገብተን ከልቫዶስ እየጠጣን፣ እያወራን፣ እየተያየን፣ ሳቃችን እየመጣ፣ እየተሳሳቅን፣ ድንገት ሳቃችንን አቋርጠን በፀጥታ እየተያየን፣ ስንተያይ ኒኮል በሚያስጉመጅ አኳኋን እየቀላች፣ እየቀላች፣ እየጠጣን እያወራን፣ ከአንድ ሰአት በላይ አሳለፍን፣ ሰከርን:: የተረፈንን ግማሽ ጠርሙስ ካልቫዶስ ይዘነው ሄድን

ሆቴላችን ስንደርስ፡ እንዳንተያይ መብራቱን አጥፍተን፣ ልብሳችንን አውልቀን፣ ወደየአልጋችን ገባን::

እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም:: ሰክሬ፡ ኒኮል እዚሁ ክፍል ውስጥ ተጋድማ፡ እንዴት እንቅልፍ ይውሰደኝ? አሰብ ጀመር:: ሉልሰገድ ቡና አይነት ቢራ እየጠጣ ስለሷ የነገረኝ ሁሉ አሁን ይታየኝ ጀመር:: በሮዝ ቀለም የተከበበች ወይን-ጠጅ ጨረቃ ነጭ ሞቃት ሰማይ መሀል - የኒኮል ጡት:: ወተት ጭኖቿ መሀል በወርቃማ ጭራሮ የተከበበ ነበልባል - የኒኮል ብልት:: ይሄ ሁሉ ከኔ አራት እርምጃ ብቻ ርቆ አልጋ ውስጥ ተጠቅሎ «ቅዱስ ብልግናዋን» ተከናንቦ ይጠብቀኛል:: አሁን ቀስ ብዬ ሄጄ አልጋዋ ውስጥ ብገባ እንደማታባርረኝ እርግጠኛ ነበርኩ:: (ውሀ እረንጓዴ አይኖቿ ብዙ ነገር ነግረውኝ ነበር) ግን መሄድ አልቻልኩም:: በጓደኝነት መካከል አላምንም:: ግን ባህሩም እዚያ በሞትና በህይወት



@BOOKALEM

እየተራመድኩ፣ እኔ የሱን ሴት ብነካበት፣ ከዚያ በኋላ ራሴን እንዴት ለማክበር እችላለሁ? ግን ያችን የመሰለች ሴት እንዴት ልልቀቃት፣ ይህን ሁሉ ጊዜ ስመኛት ቆይቼ፣ ባሬ እድል አጋጥሞኝ ሳገኛት እንዴት ልልቀቃት? ደሞስ ባህሪም ለኔ ምኔ ነው?

በጭለማው የምኞት ፍም እየጠበሰኝ ስገባበት

«ተኝተሀል?» አለችኝ

«የለም»

«እኔ ፈራሁ። ብቻዬን እዚህ ፈራሁ»

«ነይ ወዲህ»

በጭለማው መጥታ አልጋዬ ውስጥ ገባች። ሰስ ውስጥ ልብሷን አልፎ ሙቀቷ ነካኝ። በሀይል ተጠጋችኝና፣ ሰውነቷ ከላይ እስከ ታች እየተንቀጠቀጠ

«ፈራሁ። እኔ ፈራሁ» አለች

«አይዞሽ ማንም አይነካሽም።»

«ለራሴ አልፈራሁም'ኮ። አንተ እያለህ ምን ያስፈራኛል? እኔ የፈራሁት ለሱ ነው።»

«ለሱ ከፈራሽ ሞኝ ነሽ። ፋሺስቶቹን እንዴት እንደላጫቸው አታስታውሺም?»

«ቢሆንም ፈራሁ»

«አይዞሽ! ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም»

ገላዋ ልስልስ ያለ ነው። ከሴቶች ይበልጥ ሴትነት የሰፈረበት፣ የገብረ ሲጋ መቅደስ ያቀፍኩ መሰለኝ። ትንፋሿ አንገቴ ላይ የፍቅር ወት ነበልባል ያቀጣጥላል። ሁለታችንም ወጣት ነን፣ ሁለታችንም ሰክረናል፣ ሁለታችንም ምስጢራዊ ጭለማ ውስጥ ተደብቀናል፣ ሁለታችንም የምኞት ማእበል የሚያናውፀው ሙቀት ውስጥ ተዘ ቅለናል፣ የሁለታችንም ደም ፈልቷል። እጄን ከትከሻዋ ወረድ ባደርግና የማባብላት አስመስዬ ወገቧን ጥብቅ አድርጌ ባቅፈው እንደዚህ! — ደስ ማለቱ! . . . ቀስ አድርጌ በቸልታ እጄን ወደታች ሰደድ ባደርገውና ጳሴዋ ላይ ባስፍረውስ? . . . እንደዚህ — የሙታንቲዋ ጠርዝ ከእጄ ስር ታወቀኝ፣ ከገላዋ ሙቀት የባሰ የሙታንቲ



@BOOKALEM

ጠርዝ በምኞት ወጠረኝ:: እኔ ሳላውቀው እጇ ሙታንቲዋ ውስጥ እየገባ አፌ አፏን ጎረሰው:: የት እንደሆንኩና ማን እንደሆንኩ ረሳሁ:: በመርሳቴ ደመና ላይ የባህሪም ፈገግታ ብልጭ አለ

እጇን ከሙታንቲዋ እያወጣችና አፌን ከአፏ እያላቀቀችኝ፡ በሹክሹክታ

«ደግ አይደለም» አልኳት

«እምን ደግ አይደለም» አለችኝ እሷም በሹክሹክታ

«ግን በጣም በጣም እፈልግሻለሁ:: አንቺም ፈልገሸኛል፤ አይደለም?»

«እምን»

«ምን ይሻላል?»

«እኔ 'ንጃ»

«እኔ በበኩሌ ልተውሽ አልችልም»

ዝም

«ደሞ ልተውሽ አልፈልግም:: አንቺን መተው ራስን መካድ ነው::»

ዝም

«ምን ይሻል ይመስልሻል?»

«እኔ 'ንጃ»

«ባስገድድሽስ?»

«ማስገደድ አያስፈልግህም»

«እስከ ዛሬ ድረስ ያንቺን ያህል ያማረችኝ ሴት አጋጥሞኝ አያውቅም:: ደሞ እስከ ዛሬ ድረስ ሴት አግኝቼ ለሌላ ሰው ስል ትቼያት አላውቅም:: ዛሬ ግን — እንዴት ልበልሽ —»

«ይገባኛል:: ምንም ማድረግ አያስፈልግህም»

«አሁን ሁለታችንም የምናምንበት ነገር ብናደርግ በኋላ ይቆጨናል:: ግን እንድትለዪኝ አልፈልግም:: ምን ይሻላል?»

«እኔ 'ንጃ:: መብራቱን አብርተን የተረፈንን ካልቫዶስ እየጠ



@BOOKALEM

ማን ብናወራስ?»

በመብራቱ ስንጠጣ ስናወራ ምን ያህል እንደቆየን አላስታውስም:: እንዲያውም ከዚያ በኋላ ምን እንዳደረገን ወይም ምን እንደተባባልን የማስታውስ አይመስለኝም:: ብቻ፣ ከእንቅልፌ እመጣ በፊት እንዳየሁት ህልም ሆኖ ትዝ የሚለኝ አንድ ነገር አለ፣ ጠርሙሱ ውስጥ የቀረውን መጠጥ ከጨለጥነው በኋላ፣ ራሴን ደረቷ ላይ እያንተራስኩ

«ይሄ ጡት መያዣሽ ይቆረቁረኛል» አልኳት

«ቆይ ላውልቅልህ» ብላ አውልቃው እንደገና ራሴን ደረቷ ላይ አንተራሰችልኝ:: «ጡትሽ እንደ ሞቃት ሰማይ ነው፣ ሰማይ ላይ በዕጊረዳ ብርሀን የተከበበች ወይን ጠጅ ጨረቃ አለች» አልኳት

«ውሸታም! መቼ አየኸው?» አለችኝ

«ማየት የለብኝም»

«አሁን ዝም ብለህ ተኛ» አለችኝ

ከዚያ ወዲያ ምንም አላስታውስም

በነጋታው፣ ከሰአት በኋላ ወደ ስምንት ሰአት ላይ ስነቃ፣ ኒኮል ደረቴን ተንተርሳ ተኝታለች:: አፌ ውስጥ የፋንድያ ጣእም ተሰማኝ:: ኒኮልን ቀሰቀስኳት

«ደህና ነሽ?» አልኳት

«ደህና»

አፈርኩ

«ሳናውቅ የማንፈልገውን ነገር ሰራን 'ንዴ?» አልኳት

«የለም»

«ጎሽ!»

ኒኮልን ምሳ አብልቼ፣ አንድ ልብወለድ መፅሀፍ ገዝቼላትና ሆቴል ክፍላችን ውስጥ ትቼያት ወደ ኢክስ ሄድኩ:: ሲልቪ ቤት ስገባ፣ አልጋዋ ውስጥ ተጋድማ ሲጋራ እያጨሰች ሙዚቃ ትሰማ ለች:: የአይኖቿ ቆዳ እንደ መጥቆር ብሎ፣ የታችኛው ቆዳ አብጧል

«ምን ሆንሻል?» አልኳት

«ሊሊቱን አልተኛሁም»

«ለምን? ባህሪም የት ነው? ንገረን»

«ቆይ በደምብ ልንገርህ:: አንተ እንደ ሄድክ፣ ትንሽ ቆይተን እኔና ባህሪም ከካፌው ወጣን:: እየወረድን፣ ባህሪም ትከሻውን ገጥሞ እያለ ወደ ኋላ ይመለከታል:: አንዳንድ ጊዜ ከለከለኝ:: ጭለማው አስፈራኝ፣ የመንገድ መብራቶቹ በቂ ብርሀን አልሰጡኝም:: «አይዞሽ ይታየኛል:: ምንም ሊያረገን አይችልም» አለኝ:: «ማን እንደሆን አውቀሀል እንዴ?» አልኩት:: «አዎን:: አይዞሽ» «አንድ ብቻውን ነው?» «አዎን አይዞሽ:: በሁራሽ አትስጊ:: ብቻ እኔ የምልሽን ያለማመንታት አድርጊ::» «እሺ» «አይዞሽ::»

«እንግዲህ መንገዱ እዚያች ሰስት ትልልቅ ጥዶች ያሉባት ቦታ ሲደርስ ይጠመዘዝና፣ አንድ ሀምሳ ሜትር ሄዶ እንደገና ይጠመዘዛል? መጀመሪያውን መጠምዘዣ እንደዞርን «ሩጪ!» አለና በሳይኛው ከንዱ አንጠልጥሎ በሀይል አስሮጠኝ:: ሁለተኛውን መጠምዘዣ እንዳለፍን ቆምን:: ከመንገዱ ገለል አርጎ አቆመኝና፣ እሱ ከኪሱ ቆብ አውጥቶ ራሱ ላይ ደፍቶ፣ ኮቱን አውልቆ ለኔ ሰጥቶኝ፣ መንገዱ መሀል ላይ ቆመ:: ወደ መጣንበት መንገድ ይመለከታል:: እኔም እመለከት ጀመር:: ለብዙ አመታት እንደዚህ ቆመን የቆየን መሰለኝ:: ሰውየው ድንገት ከመጠምዘዣው ብቅ አለ:: ባህሪም ወደዚያው (ማለት ሰውየው ወዳለበት በኩል) ይራመድ ጀመር:: እያፏጨ! ሰውዬው እጁን ኪሱ እንደከተተ ወደ ባህሪም ይመጣል:: አጠገብ ሳጠገብ ሲደርሱ ባህሪም

"Bon soir!" አለው

"Bon soir" አለ ሰውየው

«ጉን ለጉን ደረሱ:: ሊተሻለፉ ሆኑ:: ባህሪም እንደሚደንስ ሰው በቂ ወደ ሰውዬው በኩል ዘለለና በእጁ ሆዱን ነካው መሰለኝ:: በኋላ፣ መብራት ስላልነበረ በቅጡ አልታየኝም:: ሆዱን ከነካው በኋላ እንዲት ሰከንድ እንኳ ግና ሳታልፍ ዘሎ የሰውየውን ማጅራት ወደቀ:: ባህሪም በሊላው እጁ መታው:: ሰውዬው ወደፊት ታጠፈ:: ባህሪም እየጉተተ ከመንገዱ ወደ ዳር ወሰደው:: ሁለቱንም ጨለማ ዋጣቸው::

«እዚያው እንደቆምኩ ቀረሁ:: ጭለማው ከቦኛል:: አሁን



@BOOKALEM

ያየሁት አንድ ሰው ሊጎዳው ሰው ሲጎዳው ነበር? በጭራሽ አይመስለኝም:: ሁለት ቅርፆች፣ ከልዩ ልዩ አቅጣጫ መጥተው ተገናኙ፣ አንዱ ወደቀ፣ ያልወደቀው የወደቀውን እየጎተተ ወደ ጭለማው አስገባው:: በቃ::

«አሁንም ለብዙ አመታት ብቻዬን እዚያ ጭለማ ውስጥ የቆምኩ መሰለኝ

«አትፍሪ አይዞሽ» አለ ከአጠገቤ:: ነጠርኩ:: «አይዞሽ እኔ ነኝ» አለኝ:: ባህራም ነው:: ለምን እንደሆን 'ንጃ፣ በሂደበት መንገድ ይመለሳል ብዬ ስጠብቅ ነበር:: እሱ ግን በጭለማው በኩል መጥቷል:: ኮቴውን ከኔ ወሰዶ ለበሰና ቆቡን አውልቆ ከሱ ከተተ:: በጭለማው ትንሽ ከተራመድን በኋላ ወደ ባቡር መንገድ ገባን:: እግሬ ላይ ብርድ ተሰማኝ:: ለካ ሳይታወቀኝ በፍርሀት ጫማዬ አምልጦኝ ኖሯል

«እዚህ (ሲልቪ ቤት) ከደረስን በኋላ «ገደልከው?» አልኩት

«የለም» አለኝ:: ግን እንደገደለው እርግጠኛ ነኝ:: በሬቤቢ ነው የገደለው:: እና ሲሊቲን ልተኛ አልቻልኩም::»

ሲልቪ ዝም አለች:: እኔም ዝም አልኩ

«ፓሪስን በፀደይ አይተሀት ታውቃለህ?» አለችኝ

«የለም»

«በጣም ውብ ናት:: ለአንድ ሳምንት ብንሄድ ምን ይመስልሀል?»

«መቼ?»

«ዛሬ»

«ዛሬ አልችልም:: ምእራፍ ማግኘሽ ላይ ነኝ:: ብትፈልጊ ከአንድ ሳምንት በኋላ እንሂድ:: ባኞሽ ሙቅ ውሀ አለው?»

ገላዬን ታጥቤ ከባኞው ልወጣ ስል የወንድ ድምፅ ከሲልቪ ጋ ሲነጋገር ሰማሁ:: ልብሴን ለባብሼ ወደ መኝታዋ ስገባ፣ ባህራም እልጋዋ ላይ ቁጭ ብሎ ሳንድዊች እየበላ ቀይ ወይን ይጠጣል:: ሰው የገደለ አይመስልም:: ግን ሰው የገደለ ሰው ምን እንደሚመስል አላውቅም:: ኒኮል የት እንዳለች ነገርኩት:: ሲልቪ ተራዋን ልትታጠ

ብ ባኛ ቤት ገባች

ባህራም «ይቅርታ አርግልኝ:: አንተ፣ ሲልቪ፣ ኒኮል ለአንድ ሁለት ሳምንት ከኢክስ መጥፋት አለባችሁ:: ኒኮልን ወደ ሌላ ቦታ እልካታለሁ:: አንተና ሲልቪ ተስማምታችሁ ወደ አንድ ቦታ ብትጠፉ ጥሩ ነው:: አየህ፣ ፋሺስቶቹ የበሰለ አስተሳሰብ የላቸውም:: ስለዚህ እኔን መጉዳት ሲያቅታቸው፣ በንጹት እናንተን ይጎዱዋችኋል:: ስለዚህ ንደ-ታቸው ትንሽ እስኪበርድላቸው ከኢክስ ራቁ:: እባካችሁን» አለኝ

በሹክሹክታ «ገደልከው?» አልኩት

ራሱን በመነቅነቅ «አዎን» አለኝ

«የመጀመሪያ ጊዜህ ነው ሰው ስትገድል?»

«ሶስተኛ ጊዜዬ ነው:: አንዱን በይሩት፣ ሌላውን ባግዳድ»

ይነግረኝ ይሆን? በማለት አየሁት:: ዝም አለ:: ዝም ሲል የኢራንን ሻህ ይመስላል:: እኔም ዝም አልኩት

«ፂምህን ብትላጭ ጥሩ ነው:: ለመጠንቀቅ ያህል» አለኝ

«እሺ» አልኩት



@BOOKALEM

## ክፍል ሶስት

# ጥሪ
# የሳጥናኤል ኮከብ

## አስር

## የሴሰኝነት ጥሪ
## ሲልቪ

እኔና ሲልቪ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ፓሪስ ተጓዝን። በኋ መሪነት ከፓሪስ ጋር ይበልጥ ተዋወቅኩ። በሲልቪ አስተማሪነት ከቅናት ጋር ይበልጥ ተዋወቅኩ። ራሴንም ይበልጥ አወቅኩ

ፓሪስ በገባን በሁለት ቀናችን፣ እንደ ልማዷ አንድ ደስ የሚላት ጎረምሳ አየችና እጣድፋ ወደ ሆቴላችን ወሰደችኝ። መብራቱን አጠፋች። እንደ ልማዷ በኔ ገላ ጎረምሳውን ተደሰተችበት፣ እቃሰተች፣ ነገሩ ሊያልቅ ሲል መኘች። ተኛን። ያን ጊዜ እኔም



@BOOKALEM

እኛም አላወቅነውም እንጂ፣ ከኔ ጋር እንዲህ ስትሆንና ስታደርግ የመጨረሻ ጊዜዋ ነበር

እኩሉ። ጭለማ ውስጥ ነኝ። ምን እንደቀሰቀሰኝ እንጃ። ከኔ ተንቀሳቀሰች። በእንቅልፍ ልቧ «"Non! Non! Non!" እያለች እየተጨነቀች ተፈራገጠች። በጣም የሚያስፈራ ህልም መሆን አለበት። እየቀሰቀስኳት

«አይዞሽ አይዞሽ፣ ከኔ ጋር ነሽ» አልኳት ራሷን እየደባበስኩ። በሀይል እየተነፈሰች ተጠጋችኝና

«አንድ ነገር አስደነገጠኝ። መብራቱን አብራልኝ» አለችኝ

አበራሁት። አይኔ ብርሀኑን ከለመደው በኋላ ታየችኝ። ጥቁር ረጃጅም ፀጉሯ ነጭ ትንፋሿና አንገቷ ላይ ተጠምጥሟል፣ ተለጣጥፏል። ግምባሯ ላይ ላቡ ያብለጨልጫል። ጠረግኩላት፣ ፀጉሯን ወደ ኋላዋ ሰበሰብኩላት

«ውሀ» አለችኝ። ራስጌ ካለው ጠርሙስ አጠጣሁዋት

«ደህና ነሽ?» ስላት፣ ሳቅ ብላ

«አጥፋው» አለችኝ። አጠፋሁት፣ አቀፍኳት

«ቅዠት ነበር። ኮሙኒስቶች የኢራንን ሻህ መንገድ ላይ አግኝተውት በጩቤ ሲገድሉት አየሁ። በኋላ ግን ባህራም ሆነ»

«አይዞሽ ነቅተሻል፣ አይዞሽ» እያልኩ እጇን ጀርባዋ ላይ ሳንሸራትት ትንሽ ከቆየሁ በኋላ

«"Tu es plutôt une mère Française qu' un sauvage Africain" አለችኝ («ፈረንሳዊት እናት ነህ 'ንጂ አፍሪካዊ አረመኔ አይደለህም'ኮ») ሁለታችንም በሳቅ መንፈርፈር ጀመርን። ታድያን ያን ያህል የሚያስቅ አልነበረም፣ ያን ጊዜ መሳቅ ስለፈለግን ነው 'ንጂ። እየተጠመጠመችብኝ፣ ደስታ ባፈነው ድምፅ

«መኖር 'ንዴት ጥሩ ነው!» አለችኝ

«ካንቺ ጋር ሲሆንማ!»

«የኔ ክስትሮ፣ ይልቅ ካንተ ጋር ሲሆን ነው 'ንጂ።»

እቅፍ አድርጌ ትንፋሿን ሳምኳት። በጭለማው ላዬ ላይ ወጣች፣



@BOOKALEM

እንደምትወደው ጀርባዋንና አንገቷን እያሻሸሁ

«ምን ይሰማሻል?» አልኳት

«እንደምትወደኝ ይሰማኛል»

«አውቀሻል»

«የተለየ ስጦታህ ምን 'ንደሆነ ልንገርህ?»

«ምንድነው?»

«የሰላም ተሰጥዎ ነው ያለህ:: ካንተ ጋር ስሆን ሰላም ይሰማኛል:: ካንተ ጋር ስሆን ፀፀትና ንስህ አያስፈልገኝም::»

«ፀፀትና ንስህ?»

በተለወጠ ድምፅ

«ቅድም ስለበደልኩህ — ገላህን ለጋራ ጥቅማችን ሳይሆን ለግል ደስታዬ ስላዋልኩት»

ፀፀት ሊጀምራት እንደሆነ ገባኝ፤ አሳዘነችኝ

«የኔ ቆንጆ፣ ቂል አትሁኚ:: አንቺ ገላሽን እንድደሰትበት ትሰጪኝ የለ?» አልኳት

«አዎን»

«ታድያ እኔ ገላዬን እንድትደሰቺበት ብሰጥሽ ምናለበት?»

«ከዚያ ይለያል»

«እስር ጊዜ ልዩ ይሁን:: በናንተ አገር ፍቅር ማለት ምንድነው? መስጠትና መቀበል አይደለም?»

«ነው»

«ታድያ ገላዬን ብሰጥሽና ተቀብለሽ ብትደሰቺበት ምን ፀፀት ያስፈልገዋል? እኛ አገር መስጠት ማለት መስጠት ነው:: ገላዬን ከሰጠሁሽ የራስሽ ሆነ ማለት ነው:: የራስሽ ከሆነ ደሞ የፈለግሽውን ልታረጊበት ትችያለሽ ማለት ነው»

«እንደሱ ሆኖ ነው 'ሚታይህ?»

«ነው 'ንጂ»

«እንዴት ጥሩ ነህ! እኔ ግን እንዴት መጥፎ ነኝ!»



@BOOKALEM

«እንዴት?»

«ውሸታም ነኝ!»

«ውሸታም?»

«አዎን:: ለምሳሌ፣ ያን ጊዜ ስትጠይቀኝ 'የሌላ ሰው ገላ እያቀፍሽ በሰውየው ገላ ከኔ ጋር ተኝተሽ ታውቂያለሽ ወይ?' አላልከኝም? እኔ ምን አልኩህ?»

«በጭራሽ አድርጌው አላውቅም አልሽኝ»

«አዎን:: ግን ውሸቴን ነበር:: ላንተ መዋሸቴ በጣም ይቆጨኛል:: ስለዚህ አሁን አንድ ውል እንግባ:: አንተ ላለፈው ውሸቴ ይቅርታ አድርግልኝ:: እኔ ደሞ ለወደፊቱ ሁልጊዜ እውነቱን እነግርሀለሁ::»

«ስሚኝ የኔ ቆንጆ:: ለኔ ምንም ነገር መንገር የለብሽም::»

«አውቃለሁ:: ለዚህ ነው ልነግርህ 'ምፈልገው:: ከዚያም በላይ፣ አንተ ልትረዳኝ ትችል ይሆናል:: እውነቱን ልንገርህ?»

«እሺ»

«አትጠላኝም?»

«በጭራሽ አልጠላሽም»

«እሺ:: ያኔ ታስታውሳለህ?»

«የኔ ሻህራዝድ የኔ ቆንጆ፣ እንዴት ልረሳው እችላለሁ?»

«ተመስገንን ፍለጋ የምመጣ ይመስልህ ነበር:: እኔ ግን አንተን ለማግኘት ነበር 'ምመጣው:: ሳይህ በጣም ደስ ትለኝ ነበር:: ካስትሮን ትመስለኝ ነበር:: ስንቀልድ ስንስቅ ጥርስህን አፍህን ሳየው፣ አንቀህ እንድትስመኝ እመኝ ነበር:: ታድያ አንተ እምቢ አልክ:: ስለዚህ ካንተ ስለይ፣ ተመስገን ጋ እሄድና አይኔን ጨፍኜ አንተን እያሰብኩ አቅፈው ነበር::»

«ያውቅ ነበር?»

«ምስኪን ተመስገን! እንዴት አርጎ ይወቅ?»

«እንጃ፣ ነግረሽው ሊያውቅ ይችላል ምናልባት?»

«እንዲህ አይነት ነገር እንዴት ሊገባው ይችላል?»



@BOOKALEM

«እሺ ቀጥል»

«ትጠላኛለህ»

«እንግዲህ ቂል አትሁኚ:: በኔ የመጣ ስለምንም አለመግባባት አትስጊ:: ንገሪኝ::»

«እንዴት አርጌ ልንገርህ?»

«እንደመጣልሽ»

«ከነገርኩህ በኋላ ምን እንደሚመስልህ ትነግረኝ እንደሆን»

«እሺ»

"Parole d'honneur?" («የክብሬታ ቃልህን ስጥተሃል?»)

"Parole d'honneur" («የክብሬታ ቃሌን ስጥቻለሁ»)

«እሺ:: እንዲህ ነው:: . . . አየህ፣ ካንተ ጋር ግብሬ ስጋ በጣም ደስ ይለኛል:: ደጋግሜ ነግሬሀለሁ:: ያንተን ግማሽ 'ንኳ ያህል እኔን ማስደሰት የቻለበት የለም:: ብቻ ምን ልበልህ፣ ታጠግበኛለህ:: ግን በሽታዬ ይመጣል:: ሲመጣ ደሞ መከላከያ የለኝም:: ገባህ?»

«ገና አልገባኝም»

«እንዳልኩህ፣ ታጠግበኛለህ:: ግን በሽታዬ ይመጣል:: በጣም ታምረኛለህ፣ በሀይል እመኝሀለሁ —»

«ታድያ አለሁልሽ አይደለም?»

«እንደሱ አይደለማ 'ምታምረኝ»

ልቤ መምታት እየጀመረ

«ታድያ 'ንዴት ነው?» አልኳት፣ ጉሮሮዬም መድረቅ ጀምሯል

«በሀይል ታምረኛለህ፣ ምኞቱ ያንገበግበኛል:: ግን ስትተኛኝ በገዛ ገላህ 'ንዳይሆን ያስፈልጋል:: የሌላ ወንድ ገላ ተውሰህ፣ በሱ ገላ አንተ 'ንድትተኛኝ 'ፈልጋለሁ:: እንደዚህ ያማርከኝ ጊዜ፣ ካንተ ተለይቼ መሄድ ይኖርብኛል::»

«ወዴት?» ጉሮሮዬ ጨርሶ ደርቋል

«አንተን ፍለጋ፣ ሌላ ወንድ ፍለጋ»



@BOOKALEM

«ታገኚዋለሽ?»

«ምን ይመስልሀል?» ጉሮሮዋ ውስጥ ወፍራም ተንከለኛ ሳቅ ተሰማኝ

ትናንት ማለት ይሄ ይሆን 'ንጄ? ታድያ ንጄቱና ብስጭቱ የታለ? እኔን 'ሚሰማኝ ጥልቅ የሆነ እሳት የሆነ የሚያቃጥል ትንዝር! እንደ ዛሬም እንንገብገበኝ እያውቅ! ተለይታኝ ስትሄድ፣ ወፍራም ዳሌዋን እያወዛወዘች፣ ውብ አይኖቿን ከፍት ከድን እየረገች፣ በፍትወት-ስጋ እስኪፈነዱ ብልታቸውን በሚያሳብጠው ፈገግታዋ የመረጠችውን እድለኛ ወንድ ስትጣራ ታየችኝ:: ሲጋዬ አላስታግስ አላስችል አለኝ፣ እላዬ ላይ እንደተጋደመች በጥድፊያ ገለበጥኳትና ጭኖቿን ፈልቅቄ ስገባ፣ በሙዚቃዊ ፈረንሳይኛዋ፣ በቅንዝር ድምፅዋ

"Ah, cheri, comme tu es sauvage! C'est delicieux" እያለች አቀፈችኝ:: (አንተዬ፣ እንዴት አውሬ ሆንሀል! ደስ ሲል!)

ዝም ጭጭ አልኩ፣ እውነትም አውሬ ሆኜ ነበር

አይ ሲልቪ! ለኔ እንዴት ደግ ነበረች! ስታባብለኝና ስታፅናናኝ እንደ ሀልም መስሎ ይታወቀኝ ነበር:: ጭንቅላቴንና ትከሻዬን እያሻሸች፣ በልዝብ ፈረንሳይኛዋ፣ በልስልስ ድምፅዋ እየደጋገመችልኝ «አይዞህ የኔ ቆንጆ፣ ከኔ ጋር ነህ የኔ ፍቅር፣ አንተን ነው 'ምወደው የኔ አበባ፣ አይዞህ ውደደኝ» ስትለኝ ይሰማኝ ነበር. . .

. . .በኋላ፣ እግሮቿ መሀል እንዳለሁ፣ ትንሽ ወደታች ገፋ አድርጋ ሆዷን እንተራሰችኝ:: እጇ ጭንቅላቴን ሲያሻሽኝና የተንተራስኩት ሆዷ ከትንፋሿ ጋር ከፍ ዝቅ ሲል፣ እሹሩሩ እንደምትለኝ የሚያጎናፅፍ፣ ሰፊ ጥልቅ የሆነ ሰላም እየተሰማኝ እንቅልፍ እያንጎላጀ ወሰደኝ

ስነቃ ሲልቪ በውብ አይኖቿ ታየኛለች፣ አልጋው ጎን ተምበርክካ፣ እጄን ከጉንጯ ጋር ታተሻሻለች:: መስኮቱ ተከፍቶ የፀደይ ብርሀንና ነፋስ ይገባል:: ውስጥ ውስጥ ውስጥ፣ ልቤ ልብ ውስጥ፣ ደስታው ሲመነጭ ተሰማኝ:: እንደተምበረከከች እጄን ከጉንጯ ጋር እያተሻሸች

«የመሄጃችን ሰአት ደርሷል ብዬ ነው የቀሰቀስኩህ:: ቁርስ



@BOOKALEM

ይምጣልሀ?» አለችኝ

«ይምጣልኝ:: ለምንድነው የተምበረከከሽው?»

«እኔ 'ንጃ:: ተኝተህ ሳይህ እንዴት ታምራለህ! ጎምህን ስትላጭ ለካ በጣም ቆንጆ ነህ!»

ተነስቼ ፊቴን ስታጠብ ሮጣውን አቀበለችኝ:: ቁርስ መጥቶልን ስንበላ ወተትና ቡናውን እሷ ቀዳችልኝ፡ ዳቦውን እሷ ቀባችልኝ:: ልብሴን ስለብስ አገዘችኝ:: አይኖቿ ሲያዩኝ፣ የለመድኩት ብርሀናቸው ውስጥ አይቼው የማላውቅ ልስልስ ያለ እስተያየት ሆነብኝ

ልንወጣ ስንል፣ ጉንጯን ይዤ ወደ ታች እያየሗት

«ዛሬ ምን ሆነሻል?» አልኳት

«ምን ሆኛለሁ?»

«ለኔ ያደረብሽ ፍቅር ያደገብሽ የሰፋብሽ ይመስላል:: ያለ ልማዳችን ትንከባከቢኛለሽ::»

«ዛሬ በጭራሽ እንዳትለየኝ አደራህን:: እሺ?»

«ምነው? ምን ሆነሻል?»

ቀና ብላ እያየች፣ እጆቿን ወገቤ ላይ እያሳረፈች

«ምንም አልሆንኩም:: በጣም ወድጄሀለሁ:: ካይኔ እንድትርቅ አልፈልግም::»

«ምነው? ምንድነው?»

«ምንም:: ወደድኩህ:: ዛሬ ገና ነው ሰው መሆንህ የገባኝ»

«ከዛሬ በፊትስ?»

«እስከዛሬ ሰው ሆነህ ታይተኸኝ አታውቅም:: ስለትምህርት ግድ የለህ፣ ስለገንዘብ ግድ የለህ፣ ጓደኛ የለህ፣ አትፈራ፣ አትበሳጭ — ብቻ ምን ልበልህ፣ ስለምንም ግድ የለህም:: «La vie, tu t'en fouts éperdument» («ስለ ኑሮ በጭራሽ ደንታ የለህም») ሁሉንም ሰው፣ ሁሉንም ነገር፣ ከላይ ሆነህ ወደ ታች ነው 'ምታየው:: ምንም ነገር ሊያሸንፍህ አይችልም፣ ማንም ሰው እጅ ሊያስነሳህ፣ ሊያለማምጥህ፣ ሊያምበረክክህ አይችልም:: ብቸኛ ከመሆንህ የተነሳ፣ የብረት ሰው ነህ – ማለት እስከዛሬ እንዲህ ሆነህ ነበር 'ምትታየኝ::»



@BOOKALEM

እንደምመስልሽ የብረት ሰው አይደለሁም፤ ተራ ደካማ ሰው ነኝ፤ ፈሪ ነኝ፤ ልላት ፈለግኩ። ግን ጊዜው የመናገር ጊዜ አልነበረም፤ የማዳመጥ ጊዜ ነበር። ንግግሯን እንድትቀጥል፤ ከሆነላትም የልቧን ተናግራ እንድትወጣላት፤ ለራሴም ምን እንደሚሰማት ለማወቅ እንድችል

«ዛሬስ እንዴት ሆኜ ታየሁሽ?» አልኳት

«ትላንት ሌሊት ስታቅፈኝ ሰው ሆንክ። ለመጀመርያ ጊዜ ሰው ሆንክ።»

«እንዴት?»

«ራስህን ረሳህ። እኔን አምነኸኝ፤ ከኔ ጋር በመሆንህ ራስህን መጠበቅ ስላላስፈለገህ፤ ራስህን ረሳኸው። ራስህን እጄ ውስጥ አስገባህ። ማለቴ ከበላዬ መሆን ትተህ፤ ወይ ታች መጥተህ ከኔ እኩል ሆንክ፤ ከዚያም አልፈህ የባሰውን ወርደህ እኔ ካንተ በላይ እንድሆን ፈቀድክልኝ — አመንከኝ። በናንተ አገር ቋንቋ እወድሻለሁ አልከኝ።»

«ባማርኛ አወራሁልሽ?» አልኳት፤ በጭራሽ አልታወቀኝም ነበር

«አዎን። ሳታውቅ ነው።»

«እወድሻለሁ ማለቴን እንዴት አወቅሽ?»

«በድምፅህ። እንደዚያ ወደኸኝ አታውቅም። በቋንቋህ ሲሆን ጊዜ፣ ሳታውቅ መሆኑ ሲታየኝ ጊዜ፣ በጣም ሰው ሆነህ አገኘሁህ። ለመጀመርያ ጊዜ፣ ፊዕመህ የኔ ሆንክ። እስካሁን የማንም ሆነህ ስለማታውቅ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የኔ ስለሆንክ፤ ሀሴት ተሰማኝ። በልቤ 'የኔ ነው! የኔ ነው! የራሴ ነው!' አልኩ። ዛሬ ሟት ደሞ—»

«ዛሬ ሟት ደሞ?»

«ተኝተህ ሳይህ እንዴት ታምራለህ! እንዴት ወጣት ነህ እንዴት ንፁህ ነህ! ያ ፊትህን የሚሸፍነው ጺምህ ተላጭቶ፤ እነዚያ ሁሉን ወደታች የሚያዩት አይኖችህ ተከድነው፤ ያ ሁሉን የሚንቅ አንገልህ ተኝቶ ሳይህ፤ ጀግናው ጦረኛ አኪሌስ የጦር ትጥቁን አውልቆ ያለ አንዳች መከላከያ ተኝቶ እንደማየት ነበር፤ በፍቅር አይን ለምታይህ ሲልቪ። እና ታድያ፤ ሳይህ፤ እርጅና እየራሳ እንደሚወስድህ፤ ሞት አድፍጦ አንድ ቀን ጉብ እንደሚልብህ አሉም



@BOOKALEM

ጠብቀኝ

«አንተ ደህና ሁሉ ሳትጠረጥር፣ ቀንጆ ራስህን ትራሱ ላይ አሳርፈህ፣ ንፁህ እንቅልፍህን ትለጥጣለህ:: በጭራሽ መከላከያ የሌለህ ሆነህ ታየኛለህ:: አሳዘንከኝ:: አዘንኩልህና እምባዬ መጣ::» ራሷን ደረቴ ላይ እንተራሰች:: ጭንቅላቷን እቅፍ አደረግኩት:: እንደዚህ ቆመን ረዥም ጊዜ ቆየን:: በኋላ፣ በቀስታ ቀና አድርጊ ሳያት፣ እምባዋ ይወርዳል:: እየተጠጋችኝ፣

«ዛሬ እንዳትለየኝ» አለችኝ

እቅፍ አደረግኳት:: ብዙ ነገር ልነግራት ፈለግኩ:: ግን የመናገር ጊዜ አልነበረም:: እንደተቃቀፍን እንቅልፍ እቀፈን . . .

. . . ቀኑን በብዙ ስትስቅና «ሻማንቴ» የሚለውን ፈረንሳይኛዋን ስትደጋግም ዋለች:: እኔ አንድ የሆነ ነገር በምመለከትበት ጊዜ እሷ ያላወቅኩባት መስሏት ስትመለከተኝ ብዙ ጊዜ ተሰማኝ:: እንደዚህ ስትመለከተኝ፣ አንድ ሁለት ጊዜ ድንገት ዘወር ብዬ አየኋት — ያዘነና የናፈቀ ገፅታ አየሁባት፣ በአይኗ እንደምትጠጣኝ ይመስል ነበር:: የማላውቀው እፍረት ተሰማኝ:: ይህን ያህል የሚወደድ ምን አለኝና ነው?

ማታ ከእራት በኋላ «ቡለቫር ሳን ሚሼል» ወሰድኳትና አንድ ሁካታ ያነሰበት ካፌ ገብተን ቢራ ካዘዘን በኋላ፣ እጇን ዘርግቼ ጉንጯን እየዳሰስኩ

«ዛሬ ምን ሆንሻል?» አልኳት

«እኔ 'ንጃ:: እዝኛለሁ:: እዝን ብያለሁ» አለችና፣ እጇን በሁለት እጇ ይዛ ሳመችው:: አሁንም እፍረት ተሰማኝ:: እጇን መሳሟ ሳይሆን አሳሳሟ

«አውራልኝ» አለችኝ

«ስለምን ሳውራልሽ?»

«ስላንተ:: ዛሬ ውስጤ አንድ ትልቅ ቀፎ ተከፍቷል፣ ባዶውን ነው:: ባንተ ልሞላው እፈልጋለሁ:: ከልጅነትህ ጀምሮ አውራልኝ:: ምንም ሳታስቀር በሙሉ ንገረኝ::»

ዒት ለነገራት ፈልጌ የነበረውን ነገርኳት:: ፍርሀቴን፣ ስጋቴን፣ ሞንታቴን ዘረገዘርኩላት:: ስጨርስ አንድ እጇን እያሻሸች

«ውይ የኔ ክርትሮ! ሰው ነህ ለካ!» አለችኝ:: በሌላው እጇ ፀጉሬን እያደባበሰች

«ምን መስዬሽ ኖሯል?» አልኳት

«የማትፈራ፣ የማትጨነቅ፣ የማትታመም፣ የማትሞት መስለህ ነበር 'ምትታየኝ:: አትሳቅብኝ! ሰው 'ንደመሆንህ፣ ሟች መሆንህን አውቅ ነበር:: ግን እውቀት ዋጋ የለውም:: ስሜት ነው ዋናው:: ስሜቴ ደሞ ስላንተ ሌላ ነገር ነበር የሚነግረኝ:: ተው አትሳቅ! እያው፣ እንዲህ አስበው 'ስቲ:: ጊ ደ ሞፓሳን የደረሰውን «ቤል-አሚ» የተባለውን ልብወለድ ታሪክ አንብበህ የለ? ቤል-አሚ እጅግ የተዋበ፣ ሸንትጥ የሆነ ጎረምሳ ነው:: ታስታውስ የለ፣ መዕሀፉ የሚያልቀው፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይሄ አይናማ ከበዝ በብዙ ሰው እየተደነቀ፣ ሀብታሟን ልጅ ሊያገባ ቄሱ ወዳሉበት ሲራመድ ነው:: ታድያ ቤል-አሚን ባስታወስከው ጊዜ፣ ሲያረጅ ወይ ሲታመም ወይ ሲሞት አስበኸው ታውቃለህ? ሁልጊዜ ወጣት እንደሆነ አይደለም የሚታይህ? . . . እንደሱ ነው እየሁ:: ባስብህ፣ ዘለአለም ወጣት፣ ዘለአለም ጤነኛ፣ ዘለአለም ኩሩ ሆነህ ነበር የምትታየኝ»

«ግባኝ»

«አሁን ግን ሰው ሆነህ ትታየኝ ጀመር:: ዒት እንደነገርኩህ፣ ማንም ሰው፣ ምንም ነገር ሊያሸንፍህ የማይችል ይመስለኝ ነበር:: የብረት ሰው ትመስለኝ ነበር:: አሁን ግን እንደ ቢራቢሮ ሆነህ ነው 'ምትታየኝ:: በጣም ቆንጆ ነህ፣ ኑሮ ፈገግታህ ተቁር ፊትህ ላይ ሲያበራ፣ አልማዝ መሳይ አይኖችህ በሳቅ ብልጭ ብልጭ ሲሉ፣ ወይም በምኞት ሲግሉ፣ በወጣትነት ፀሀይ ውስጥ የሚበር ውብ ቢራቢሮ ነህ:: እንደ ቢራቢሮ በቀላሉ 'ምትጠፋ ነህ:: ከዚህ ውጥተን መንገድ ስንሻገር መኪና ቢገጭህ ትሞታለህ፤ በብዙር ስንሄድ ከሌላ ባቡር ጋር ብንጋጭ ትሰባበራለህ፤ በኤሮፕላን ብትበር፣ እና ኤሮፕላኑ አንድ ነገር ቢሆን፣ እንደ ወረቀት ትቦጫጨቃለህ:: እንዲት ጥይት ብትመታህ ትሞታለህ:: . . .»

«አይዞሽ አይዞሽ—»

«ምን አይዞሽ ትለኛለህ? መሞትህ ነው ኮ፤ አይታይህም?»



@BOOKALEM

«ሲሳውም ይሞታል'ኮ:: አንቺም ሙሾር»

«ሲሳውን የት አውቀዋለሁ? ምን ነው? አንተ ግን አንተ ነህ:: ማንንም አትፈራም:: እንደ ሲራኖ ዶ ቤርዤራክ ነህ:: ወንድ ነህ:: የኔ ነህ:: እወድሀለሁ:: የኔን የራሴን ማርጀትና መሞት በሀሳቤ ልቀበለው እችላለሁ:: አንተ ታረጃለህ ትሞታለህ ቢሉኝ ግን አልቀበልም:: ይሄ እንፀባራቂ ፈገግታህ ሲጨልም፣ እነዚህ ብሩህ አይኖችህ ሲፈዙ ለማየት አልፈልግም:: አልቀበልም:: እምቢ! ኢንክስ ውስጥ ፀሀይ እየሞቁ በባዶ ብርጭቆ አያን ሞታቸውን ከሚመለከቱት ሽማግሌዎች እንዱ 'ንድትሆን አልፈቅድልህም:: አልፈቅድልህም! ይገባሀል? አልፈቅድልህም! ወጣት መአዛህን ወስደው የእርጅና ሽታ ሲለጥፉብህ እንዳትቀበል!»

«እሺ 'ሺ የኔ ቆንጆ፣ እሺ ይቅር፣ ረጋ በይ አይዞሽ:: አሁን ወጣት ነኝ፣ ካንቺ ጋር ነኝ»

«አሁን ብቻ ነዋ!»

«አሁን ብቻ አይደለም:: አይዞሽ አይዞሽ»

«ከዚህ ውሰደኝ»

«እሺ»

«ውሰደኝና ልብሴን አውልቀህ እቅፍ አርገኝ:: ከድሮ ይበልጥ እቀፈኝ:: ፍርሀት ይዞኛል፣ ሀዘን ተጫጭኖኛል:: መወደድ መታቀፍ እፈልጋለሁ::»

«እሺ የኔ ሲልቪ»

«እንሂዳ»

«እሺ»

«በል እንሂድ»

«እሺ የኔ ፍቅር፣ ይኸው መሄዳችን ነው::»

ሆቴላችን እንደደረስን፣ ቶሎ ልብሷን አውልቄ እቅፍ አረግኳት

«እወድሻለሁ የኔ ፍቅር፣ ከልቤ 'ወድሻለሁ» አልኳት

«ብላ አሳየኝ፣ በስጋህ አሳየኝ፣ በነብስህ አሳየኝ»

«ይኸው የኔ ፍቅር፣ ይኸው»



@BOOKALEM

በጭለማው፣ በሹክሹክታ

«እግልከቱ ሁሉ ሞተዋል:: እኛ ብቻ ነን የቀረነው:: አንተ ለኔ አምላኬ ነህ:: እኔስ አምላክህ ነኝ?»

«እምን አምላኬ ነሽ»

«ድገምልኝ»

«አምላኬ ነሽ:: አምላኬ ነሽ:: የኔ አምላክ ነሽ»

እፊ ውስጥ እየተነፈሰች «በላ መስዋእት አቅርብልኝ»

«እሺ:: ምን መስዋእት ትፈልጊያለሽ?»

«ሁልጊዜ ከላይ ሆነህ ወደታች ታዩኛለህ:: ዛሬ ታች ውረድና እኔ አዘቅዝቁ ልመልከትህ — ክብርህን ሰዋልኝ»

«እሺ:: ክብሬን ውሰጂው:: ላንቺ ክብሬን ብሰዋ ደስ ይለኛል»

በጭለማው በሹክሹክታ

«በላ»

«እዘዢኝ»

«እንዳታመነታ ልዛርግ»

«ዝግጁ ነኝ:: ንገሪኝ:: ምን ላርግሽ? ምን ልሁንልሽ?»

«ወደታች ውረድና ከእግሬ ጥፍር ጀምረህ እየሳምከኝ እየላሰከኝ ወደላይ ና::»

«እሺ የኔ' መቢት»

ከእግሯ ጥፍር ጀምሬ እስከ አፏ ሳምኳት ላስኳት:: በአፏ ተቀበለችኝና እየሳመችኝ፣ በጭለማው በሹክሹክታ

«ጥሩ ነበር፣ ግሩም ነበር:: ግን አይበቃም:: በጭራሽ አይበቃኝም» አለችኝ

«የፈለግሽውን ንገሪኝ:: አደርገዋለሁ:: አምላኬ ነሽ»

«እንዴት ነው ጭኖቼ መሀል ስመኸኝ የማታውቀው?»

«አድርጌው አላውቅማ»

«በጭራሽ አርገኸው አታውቅም?»



@BOOKALEM

«በቀረሽ»

በቀለማው፤ በሹክሹክታ

«በል ውረድና ቁናኛ መሀል ጎመኝ። ልክ እሬን እንደምትሰመኝ እርግዝ ጎመኝ፤ በከንፈርህ፣ በጥርስህ፣ በምላስህ ጎመኝ። እምላስክህ ነኝ። ካንተ 'ምፈልገው መሰጥኢት እሱ ነው።»

«እሺ»

ላረገው አልቀፈፈኝም። በቀረሽ አልተፈፈኝም። እንዲያውም በጣም ነው ደስ ያለኝ። ስስማት፣ በማክበርና በማምለክ ስስማት፣ እያቃሰተች ራሴን ስታጣሽ ቆይታ ቆይታ፤ በቁንጅናቱ ስብ ወደ ላይ ወሰደችኝና

«ትወደኛለህ። በእውነት ትወደኛለህ። እንዴት ጉሩም ነው! ትወደኛለህ። አንተ እኔን ትወደኛለህ!» እያለች ስታቃስት

«እያዞሽ እያዞሽ፤ ምንቸው ነኝ» እያልኩ አባበልኳት

«እንዴት እድለኛ ነኝ! እንደ ዛሬ ደስ ብሎኝ አያውቅም»

«ገዘተሽኝል»

«ገዘቼሀለሁ። እወድሀለሁ። አንተም ገዘተኸኛል። እንዴት ጥሩ ነው!»

«አሁን ተኚ። ደክሞሻል።»

«እሺ! አቅፈህ አስተኛኝ።»

ከትንሽ ሰዓታ በኋላ

«እንደዚህ ጥሩ ልጅ ሆነህ ጀርመኝ መውደድህ አያሳዝንም?»
አለችኝ

«የምን ጀርመኝ?»

«እኔ ራሴ»

«አ —! እንግዲህ እረፊ!»

«እውነቴን 'ኮ ነው። የመጣልኝ ጀርመኝ ነኝ»

«ምን 'ንደዚህ ያሰኘሻል? ዛሬ ምን ሆንሻል?»

«[illegible] ወደኸኛል። ስለዚህ ሴሰኛ መሆኔ [illegible]ሀለሁ? አንተም

@BOOKALEM

ይቀጡኛል:: ስለዚህ ላንተ ልነግርህ እፈልጋለሁ:: ምን አይነት ውሻ 'ንደሆንኩ እንድታውቅልኝ እፈልጋለሁ:: ንስሀ መግባት እፈልጋለሁ:: ከቻልክ ታድነኛለህ:: ማዳን ካልቻልክ ይቅርታህን ታለብሰኛለህ:: እሱንም ካልቻልክ ደሞ፣ እንደ ሸርሙጣ ትጠቀምብኛለህ»

እየሳቅኩ

«እሱንም ካልቻልኩስ?»

«ወደህም ባይሆን በግድህ ትችላለህ:: እኔ ከፈለግኩ እምቢ ሊለኝ የሚችል ወንድ አለ ይመስልሃል? ይሆን ንካ 'ስቲ . . . እምቢ ልትለኝ 'ምትችል ይመስልሃል?»

«አቤት ትእቢት! እሺ ቀጥዪ»

«ከልጅነቴ ልጀምር መሰለኝ:: በሽታው የጀመረኝ ያን ጊዜ ይመስለኛል:: እየህ፣ አባቴን በሀይል እወደው ነበር:: ሀብታም ነው፣ ስራ ካላስኘው አይሰራም፣ እኔ ከሱ ጋር ነው 'ምውለው፣ ስንስቅ ስንጫወት ነው 'ሚመሽው:: ታድያ አምስት አመት ሲሆነኝ፣ በኤሮፕላን አደጋ ሞተ:: እንግዲህ እኔ ያን ጊዜ እልገባኝም 'ንጂ፣ እናቴ አንድ ውሽማ ነበራት

አባቴ 'ንደሞተ፣ ይሄ ሰውዪ እኛ ቤት ይመላለስ ጀመር:: እናቴ በሌለችበት ያጫውተኛል፣ ይላፋኛል፣ ያቅቅፈኛል:: አንዳንዴ ሶፋ ላይ ተቀምጦ፣ ላዩ ላይ ያስቀምጠኝና ያሻሽኛል:: አባቴ በሀይል ይናፍቀኝ ስለነበረ፣ አይኔን እጨፍንና፣ በሀሳቤ «አባባ ነው አሉ አቅፎኝ ያለው» እላለሁ:: ሰውዪው ያሻሽኛል፣ እኔ አይኔን ጨፍኜ አባባን አስባለሁ:: እሱ እጁን ቂጤ ላይ፣ ጭኔ ላይ ያንሸራሽራል፣ ጉንጬንና አንገቴን ይስመኛል — እኔ በሀይል ደስ ይለኛል

«አሁን ሳስበው እንደሚመስለኝ፣ እናቴ 'ሲልቪ እንድትወድህ ካረግክ አገባሀለሁ' ብላዋለች:: ምክንያቱም፣ እሷ እየፈቀደችለት በወሰደኝ ቁጥር ሀሙስ ሀሙስ ለብቻው ሽርሽር ይወስደኝ ነበር:: ብቻችንን ነን:: መጋረጃውን ለአንድ ሰአት ያህል ቤቱ እንሄዳለን:: ሶፋ ላይ ወይም ድንክ ይዘጋና ቤቱን ግማሽ ጭለማ ያረገዋል:: ወይም ያጋድመኛል:: አልጋ ላይ ይጋደምና ላዩ ላይ ያስቀምጠኛል:: ወይም ያጋድመኛል:: ይሄ ሁሉ በፀጥታ ነው:: እኔ አይኔን ጨፍኜ 'ከአባባ ጋር ነኝ እላለሁ፣ እሱ ያሻሽኛል:: እያሻሸ እየሳመ ሙታንቲዬን ያወልቃል::



@BOOKALEM

እስታውሳለሁ፣ እጁ ላብ በላብ ይሆን ነበር:: ያሻሸኛል:: ጭኔን፣ ቂጤን፣ ብልቴን ቀስ እያረገ ይዳስሰኛል:: አንድ ሰአት ያህል እንዲህ ካረግን በኋላ፣ ወጥተን ሽርሽር እንሄዳለን:: የፈለግሁትን ይገዛልኛል::»

«በኋላስ?»

«አንድ ቀን እንዲህ እንደሆንን እማማ ደረሰችብን:: እማማ ከነሙየው ነጠቀችኝና አቅፋኝ አለቀሰች:: ሰሙየው ከዚያ በኋላ ቢታችን መጥቶ አያውቅም»

«ቀጥሎ 'ንግዲህ አደግሁ:: አስራ አምስት አመት ሆነኝ:: ከፖል ጋር ፍቅር ያዘኝ:: አንድ አመት ያህል ከተዋደድን በኋላ እንካስትሮን ለማገዝ ወደ ኩባ ሄደ:: ሁለት ወር ያህል አለቀስኩ:: ከዚያ አንድ ቀን አንዱ ልጅ ናይት ክለብ ወሰደኝ፣ አይኔን ጨፈንኩና፣ "Paul, Paul, mon amour!" («ፖል፣ የኔ ፍቅር») እያልኩ እያሰብኩ ከልጁ ጋር ጥብቅ ብዬ ደነስኩ:: እሱ በምኞት እብጦ በሀይል ይታከከኛል:: እየሳመኝ «እቤት እንሂድ?» አለኝ:: እሺ አልኩት:: ወሰደኝ:: ሲተኛኝ አይኔን ጨፍኜ ፖልን ነበር 'ማስበው:: በጣም ተደሰትኩ:: ግን ነገሩ ካለቀ በኋላ፣ አንድ አይነት ሀዘንና ፀፀት ልቤን ሞላው:: አለቀስኩ

«ከዚያ 'ንግዲህ አንድ ነገር በግልፅ ታየኝ:: ይኸውም፣ ወንድ በጣም እወዳለሁ:: ቢያንስ በሳምንት ሁለት ሌሊት ከወንድ ጋር ማደር አለብኝ:: ታድያ ወንዶቹ ይሰለቹኛል

«አይ ሲሰለቹ! እንደ ፖል አይደሉም፣ ውስጣታቸው እንደ እሳት የሚነድ፣ የህይወታቸው መሪ የሆነ ቋሚ እምነት የላቸውም:: በህይወታቸው የሚፈልጉት ምንድነው? ገንዘብና ሴት፣ ባዶ ናቸው፣ ይሰለቹኛል:: መጀመርያ ሳያቸው ግሩ ቢል ስልጣን:: በቃ:: ወንዳ ወንድ ነው:: ያምሩኛል:: አቋቋማቸው፣ አስተያየታቸው በጣም ጥሩ ነው:: ስለፖል ማሰብ እየዛቸዋለሁ:: የመጀመሪያ ጊዜው ከአንድ ስስት አራት ሳምንት እያስተባቸዋለሁ:: እነሱን 'ደስትባቸዋለሁ:: የለብኝም፣ ለኔ የሚሆን ምንም የላቸው:: በኋላ ይሰለቹኛል፣ ባዶ ናቸው:: ስለዚህ እያተፍኳቸው ገላቸውን እንደሆነ ቀምሼው ጠግቤዋለሁ:: ጊዜ እያለፈ እየተረሳኝ ሲሄድ ግን፣ ፖልን ሳይሆን ፖልን እስባለሁ:: ማንም ወንድ ሊሆን ይችላል:: ማርለን ሌላ ወንድ ማሰብ ጀመርኩ::



@BOOKALEM

ብፈንጆ ያለበት ፊልም አዶቼ 'ንደሆን፣ እነሱን እያቀፍኩ እሱን እስበዋለሁ። ብቻ ምን ልበልህ፣ ተበላሽሁ። ክፉኛ ተበላሽሁ

«ይህን ሁሉ ያባባሰው ምንድነው ብትል፣ ትምህርት በጣም መቅለሉ። ሳነብ በጣም ፈጣን ነኝ፣ ያነበብኩትን ደሞ አልረሳም። ብዙውን ጊዜ በማስታወሻ ደብተርም መፃፍ አያስፈልገኝ። ፈተና ሲሆን በፍፁም አልደናገጥም፣ ስለዚህ ሀሳብ በቀላሉ ይመጣልኛል፣ የሌሎቹን ተማሪዎች አንድ አራተኛ ያህል ብሰራ ፈተናውን ኮርቼ አልፋለሁ

«በስጋዬ ለመደሰት ብዙ ጊዜ አለኝ። በዚህ ላይ 'ንግዲህ ስጋዊ ፍትወት ከድርገኔ በላይ ተሰጥቶኛል፣ ወንዱ ራሱ ስልችቶኝ ካላስጠላኝ ወይም እሱን ካልደከመው ሊሊቱን ሙሉ ሳድርበት እችላለሁ። ወንድ ማግኘቱ እንዳይቸግረኝ ደሞ 'ንደምታየው ነው። ጠባብ ቀሚስ ወይም ሱሪ ለብሼ 'ወጣና፣ አይኔን ትንሽ ጣል ሳረግባቸው እየተንዘበዘቡ እንደ ውሻ ይከተሉኛል። መጥተው ይታከኩኛል፣ ምኞት ባሳበጠው ትኩስ ገላቸው ይተሻሹኛል። ሴት መሆን እንዴት ጥሩ ነው!. . .

«ስንት ቆንጆ ወንድ አለ — ጡንቸኛ፣ ጠንካራ፣ ወጣት፣ መልከ መልካም የሆነ ስንት ወንድ አለ! ታድያ ሁሉም የኔ ነው፣ ከፈለግኩ በአይኔ 'ጠራዋለሁ፣ ይመጣል። ግሩም ጡንቻ የተገማመደበትን ውብ ገላውን ለኔ ለግል መደሰቻዬ ያበረክትልኛል፣ እደሰትበታለሁ። ሲበቃኝ እሸኘዋለሁ። ባማረኝ ጊዜ 'ንደገና 'ጠራዋለሁ. . . ደስ ሲለኝ የወንዶች ጠረን! እኔ ከስራቸው ተመቻችቼ፣ በእጄ የገላቸውን ጠንካራ ጡንቻ ስዳስስ፣ እነሱ ከላዬ ሆነው እያዩኝ፣ እየወደዱኝ፣ እየሳሙኝ፣ እየላሱኝ፣ ያለ የሌለ ጡንቻቸውን አሳብጠው ለኔ ደስታ ከፍ ዝቅ ሲሉ፣ ድካሙና ስሜቱ ላብ በላብ ሲያረጋቸው፣ ያን ጊዜ የላባቸው መአዛ እቤት ደስ ማለቱ! ሴት መሆን ምንኛ ገንት ነው!»

ሲልቪ ይህን ሁሉ በጭለማው ስትነግረኝ፣ በልዝብ ፈረንሳይኛዋና በትንዝረኛ ድምፅዋ ስሰማው፣ ቃላቷ ምናቤ ውስጥ ግልፅ ያለ ትርኢት ይቀርፃሉ — ጥብቅ ያለ ሱሪ ለብሳ፣ ወፍራም ዳሌዋን እያወዛወዘች ስትራመድ፣ በሚያባብሉ አይኖቿ ቆንጆዎቹን ወንዶች ስትጠራቸው ትታየኛለች። ራቁቷን አልጋ ላይ ተጋድማ፣



@BOOKALEM

ወተት መሳይ ጭኖቿን ከፍት አርጋ፣ ልዩ ልዩ ወንድ ስታስገባ፣ እነሱ ሲደሰቱባትና ሲስሟት ይታየኛል። ኃይለኛ ቅናት እንቅ ያረገኛል — ማን አቤት ማስደሰቱ! እሷንም ሆነ ወንዶቹን እልጠ ላቿቸውም፣ ይልቅስ እኔም ከነሱ አንዱ መሆን አማረኝ፣ እንደነሱ ከላይዋ ሆኜ ጭኖቿ መሀል ገብቼ፣ እየሳምኳት እየላስኳት «ሲልቪ! ሲልቪ!» ልላት ፈለግኩ። በጭለማው እላይዋ ላይ ወጣሁ

«ምን ሆነህል የኔ ቢራቢሮ?» አለችኝ እግሯን እየከፈተችልኝ፣ እያቀፈችኝ፣ እጆቿን ገላዬ ላይ እያንሸራሸረች፣ አፌን በሰፊ አፏ እየሳመች

«ስንት ናቸው? ስንት ይሆናሉ?» አልኳት እየተንገበገብኩ፣ በጭለማው እርጥብ አፏን እየሳምኩ

«ምኖቹ?» አለችኝ

«ወንዶቹ። የተኙሽ ወንዶች ስንት ናቸው? ብዙ ናቸው?» ማሰብያዬ የለም፣ ተኝቷል፡ የምናገረው ቅዠት ነው፡ ግን ያለሁት ገነት ውስጥ ነው — የቅናት ገነት፣ በደስታ የሚያቃጥል የሚያንዘገዝግብ ገነት፡ ራስ የሚያዞር፣ ከብር የሚያስረሳ ገነት፡ እፍረት የማያውቅ ገነት። የጉርምስና ትኩሳታም ገነት

«ንገረኝ 'ንጂ። ብዙ ናቸው?» አልኳት

«ብዙ 'ንዲሆኑ ትፈልጋለህ?»

«እምን»

«በጣም ብዙ 'ንዲሆኑ ትፈልጋለህ?»

«እምን»

«ነግሬህ የለ? ሴሰኛ ነኝ፡ የተነሳብኝ ጊዜ ከወንዱ በላይ ሳትና ደስታ፣ ከወንዱ በታች ቅንዝር ነኝ። ስለዚህ ወንድ ሁሉ ይፈልገኛል። ቆንጆ ከሆን ደግሞ ያገኛኛል። . . . ብዙ ናቸው የተኙኝ ወንዶች። በጣም ብዙ ናቸው። ቁጥራቸውን በግምት 'ንኳ ላውቀው አልችልም። . . . ደስ አለህ? ደስ አለህ የኔ ቢራቢሮ?»

«እስኪቃጠል ደስ አለኝ. . . እንደዛሬ ጥመሽኝ አታውቂም።»

«መቅናት ደስ ይልሃል?»



@BOOKALEM

«አዎን! አዎን! አዎን!»

«እንግዲያው ስማኝ:: በቢታ ከኢጣሊያ እንደተመለስን አንተ ወደ ኢንስ ስትሄድ፣ እኔ ቤተቤን ለማየት ወደዚህ አልመጣሁም?»

«አዎን»

«ቢተቤን አንድ ቀን ብቻ ነው ያየሁዋቸው:: ሌሳውን ቀን ከወንዶች ጋር ነበር 'ማድረውና 'ምውለው:: በድሴት ቀንና ሌሊት ሙሉ፣ ያለማቋረጥ ወንድ እያቀያየርኩ በደስት ሰነብትኩ:: ለዚህ ነው ወደ ኢንስ ስመለስ አጥንና የነበረውና ልትተኛኝ ያልቻልከው:: አብዝቼ ነው:: አሰበው 'ሰቲ፣ ማታ አንድ ሶስት አራት ወንድ ሳቀያይር አመሽና፣ ሌሊት ካንዱ ጋር ስንታገል እናድራለን:: ከሰአት በኋላ አንድ ወይም ሁለት ማግኘት አለብኝ:: ማታ 'ንደገና ሶስት አራት . . . ይታይሀል?»

«አዎን ይታየኛል»

«ምን ይታይሀል?»

«በተራ ሲተኙሽ ሲልሱሽ ይታየኛል . . . ብዙ ብዙ ናቸው:: ታድያ'ኮ እነሱ ሁሉ እኔ ነኝ:: ቁጥራ በዛ 'ንጂ እኔው ነኝ:: ልዩ ልዩ ገላ 'የለበስኩ ነው 'ንጂ፣ እኔ ነኝ:: እኔ ነኝ፣ እኔ ነኝ . . . እኔ ነኝ!»

«አውቃለሁ የኔ ቆንጆ:: አንተ ነህ:: ሁሉም አንተ ነህ:: . . . የብቻህ ነኝ . . . አይዞህ እዚሁ ነኝ፣ ካንተ ጋር ነኝ፣ እትፈሀለሁ . . . አይዞህ ተኛ . . . እኔ 'ጠብቅሀለሁ . . . ተኛ የኔ ቆንጆ ቢራቢሮ . . . ተኛ»

ከአራት በኋላ «ቡለቫር ሳን ሚሼል» ሄደን እዚያው ወጣት የሰፈነበት ካፌ ገብተን፣ እዚያቸው ጠረጴዛ ጋ ተቀመጥን፤ ቢራ እየጠጣን ማውራት ጀመርን:: ዛሬ ግን ሲልቪ አሳዘነችም፤ የተለመደው ሳቋ አይኖቿን እየደጋገመ ያበራቸዋል፤ ከንፈሮቿን ያለማቋረጥ ይከፋፍታቸዋል:: አራት ላይ ሁለት ጠርሙስ ወይን ጠጥተን ነበር፤ አሁን ሁለት ጠርሙስ ቢራ ስንቀላቅልበት ጊዜ



@BOOKALEM

ጠሬያችን ሞቶ

«እቤት እንዴት ነው ያማርሽኝ!» አልኳት

«ሱሪ ስለለበስኩ ነው?»

«ማማሽ»

«ማማሽስ?»

«ከስሩ ሙታንቲ ስላላረግሽ ነው:: ለምን ሙታንቲ አልለበስሽም?»

«ለምን ይመስልሀል?» አይኖቿ ውስጥ ያ የሚያስከረኝ ቅንዝር ይታያል

«እኔ 'ንጃ:: ለምንድነው?»

«ማማሼ አንተ 'ንዳሁን እንድትመኘኝ ነው»

«ማማሹስ?»

«እይ! አይነገርም:: በብርሀን አይነገርም::» የአፏ አከፋፈት!

«ንገሪኝ:: ንገሪኝ:: ለምንድነው ሙታንቲ ሳትለብሺ የመጣሽው?»

«ልንገርህ?»

«ንገሪኝ!»

«ተው ይቆጭሀል!»

«ንገሪኝ!»

«ሱሪው ጠባብ ነው:: ያለሙታንቲ ስለብሰው ቂጤ የበለጠ አያምርም? የበለጠ አያስጐመጅም?»

«ያንገበግባል»

«እና ስራመድ ወንዶቹ እንዴት እንደሚያዩኝ አላየህም?»

ቅናቱ ጀመረኝ

«አላየሁም» አልኳት

«ያዩኝ ነበር:: ይታወቀኛል'ኮ:: ስራመድ ከኋላዬ ሆነው ሲያዩኝ፣ አይናቸው ከዳሌዬ ጋር ሲንከራተት ይታወቀኛል::»



@BOOKALEM

«እና ምን ይሰማሻል?»

«ደስ ይለኛል፣ ዛሬ በሀይል አላምርም?»

«ታምሪያለሽ:: ግን ከሊላ ጊዜ ይበልጥ 'ንደምታምሪ እንዴት አወቅሽ?»

«ይታወቀኛላ»

«እንዴት ይታወቅሻል?»

«ውስጤ ይሰማኛል:: እየሆነ ዛሬ ወንድ አምሮኛል:: በሀይል አምሮኛል:: ስለዚህ ፊቴ፣ ገላዬ፣ አረማመዴ ሁሉ ወንድ ሊስብ ይፈልጋል:: ስለዚህ በሀይል አምራለሁ::»

የትላንቱ ሌሊት አይነት ቅናት ውስጤ መንቀሳቀስ ጀመረ

«እንዴት ነው 'ምታየኝ አንተ!?»

«እንዴት ነው?»

«እማርከኝ መሰለኝ»

«በጣም አምረሽኛል»

«እኢም አምረኸኛል:: ግን ዛሬስ ልታጠግበኝ 'ምትችል አይመስ ለኝም:: ዛሬ የያዘኝ ምኞት እንደ እሳት ነው:: ለማጥፋት ብዙ ብዙ ውሀ ይፈልጋል:: አንተ ብቻህን ልታጠፋልኝ መቻልህን እንጃ»

የትላንቱ ሌሊት ቅናት እንቅ አደረገኝ፣ ሌላ ወንድ እንዲያምራት ተመኘሁ

«እና ምን ትፈልጊያለሽ? ንገሪኝ 'ስቲ»

«ትቆጣለህ!»

«ይልቅ ንገሪኝ»

«ተው!»

«ንገሪኝ:: ምን ያምርሻል?»

«ወንድ ያምረኛል:: ሶስት አራት ቆንጆ ቆንጆ ወንድ ባገኝ እፈቅዳለሁ::»



@BOOKALEM

«አንድ አይበቃሽም?»

«አይበቃኝም:: አልጠግብም:: ዛሬስ አንተ 'ንኳ ባትሆን አታጠግበኝም::»

«እና ምን ይሻላል?»

«አንተ ባትኖር መፍትሄ ነበረው»

«እኔ ሳልኖር እንዲህ አይነት ስሜት ሲመጣብሽ ምን ታረጊያለሽ?»

ጠረጴዛ ላይ ያለውን ጥቁር ቦርሳዋን መታ እያደረገች

«ማስታወሻ ደብተሬ ውስጥ የቴሌፎን ቁጥሮች አሉ።»

«የወንዶችሽ?»

ጭንቅላቷን በአዎንታ ነቀነቀች

«አሁንም ልትደውይላቸው ትችያለሽ'ኮ— ደነገጥኩ:: እንዲህ ማለት መቼ ፈለግኩና? በጭራሽ አልፈለግኩም:: ምን ነካኝ? እስቲ አሁን 'ንዲህ ይባላል? ምን አይነት ጉድ ውስጥ ነው የገባሁት!?

እጇን ቶሎ ሰዳ እጄን በሀይል ጨበጠች:: አይኖቿ ውብ ብርሀን ለበሱ፣ ቀያይ ከንፈሮቿን በምላሷ አረጠበች፡ ከውስጥ ውትት መሳይ ጥርሶቿ ይብለጨለጫሉ:: ማማሯ! ማስጎምጀቷ! ስሜት ባፈነው መፍራም ድምፅዋ

«ትፈቅድልኛለህ? ልደውልላቸው? አትጠላኝም? በኋላ 'ታባርረኛም? ልደውልላቸው? አንተን ነው 'ምወደው:: ግን በሽተኛ ነኝ:: መሄድ አለብኝ:: ግን 'ምትጠላኝ ከሆነ አልሄድም:: ልደውል? ልሂድ? ትፈቅዳለህ?»

አቅበጠበጣት:: አሳዘነችኝ:: ደሞ በሀይል አማረችኝ:: እንደዛሬ አምሮኝ አያውቅም:: ግን አሁን ላገኛት አልፈለግኩም:: — ከሆነልኝና ወደ ሌሎቹ ከሄደችልኝ፣ ከሌላ ጋር መሆኗን እያሰብኩ ማሰቃየት አማረኝ:: እሷ ወንዶች ያማሯትን ያህል እኔ መሰቃየት አማረኝ፣ መቅናት፣ መቃጠል አሰኘኝ:: ራሴንም ለማወቅ ተጠማሁ:: ማን ነኝ? ፍቅር ይገኛል? እና ፍቅር ምንድነው፣ ቅናትስ? የሌላቱስ ሙድና እንደዚት ያለ ነው

የማያፈቅሩዋት ሴት ጥብቅ ያለ ሱሪ ለብሳ ሌላ ወንድ ፍሬ?



@BOOKALEM

ስትሄድ ማየት፣ ሄዳ ስትመለስ፣ ቢያንስ ቢያንስ ሶስት ወንድ በየተራ ሲደሰትባት፣ ሲስማት፣ ሲልሳት፣ ሲያለፋት ከቆየ በኋላ፣ ከዚያ ተቀብለው ይህን ሁሉ እያወቁ ያችን የሚወዷትን ሴት ማቀፍ፣ መሳም፣ መላስ፣ በቅናት እየነደዱ ሴትዮዋን መተኛት — ይሄ ደሞ ከሁሉ የጠለቀ፣ ከሁሉ የላቀ፣ ከሁሉ የደመቀ ከሁሉ የጨለመ፣ የሚያቃጥል፣ የሚበርድ፣ የሚያስደስት፣ የሚያበሳጭ፣ የሚገድል፣ የሚያድን፣ ከስሜት በላይ የሆነ ስሜት ይሰጥ ይሆን?

«ልሂድ ትፈቅዳለህ?» አለችኝ

«በኋላ የት አገኝሻለሁ?» አልኳት:: ድምፁ የኔው አይመስልም

«ሆቴላችን»

«ከስንት ሰአት በኋላ?»

ሰአቷን አየች

«ከአምስት ሰአት በኋላ:: ልክ በሰባት» አለችኝ

«እሺ»

በጠረጴዛው ተንጠራርታ ግምባሬን ሳመችኝ

«አግባኝ:: እባክህን አግባኝ! ይቅር እሺ:: ይቅር:: "nous nous reverrons bientôt" («አሁን አሁን እንገናኛለን») ብላ እጄን ስማኝ ተነስታ ከካፌው ወጣች:: ስትሄድ ረዥርም አንገቷን እያወዛወዘችው፣ ወደኋላዋ የተለቀቀው ፀጉሯ ዥዋዥዌ ይጫወታል:: ከቀጭን ወገቧ ስር ወፍራም ዳሌዋ ይወዛወዛል፤ ስትራመድ ጠባቡ ሱሪዋ የቂጧን ውብ ቅርፅ ያሳያል --- ከውስጥ ሙታንቲ አልለበሰችም!!

ከጥቂት ደቂቃ በኋላ፣ ከካፌው ወጥቼ ሲኒማ ገባሁ

እንደ አጋጣሚ ኢንግማር በርግማን የተባለው ገናና የስዊድን ፊልም አዘጋጅ የፈጠረው «ሰባተኛው ማህተም» የተባለው እጅግ የተመሰገነ ፊልም ነበር . . . አንድ የጥንት ስዊድናዊ አርበኛ፣ ከኢየሩሳሌም የመስቀል ዘመቻ ሲመለስ፣ ልክ የክርስትያን ኤውሮፓን መሬት እንደረገጠ፣ ሞት የተራ ሰው መልክ ለብሶ ይመጣና

«ልወስድህ መጥቻለሁ» ይለዋል

አርበኛው «አሁን ካንተ ጋር መምጣት አይሆንልኝም:: ላደርጋቸው የሚገባኝ፣ ግን ገና ያልፈጸምኳቸው፣ አንድ ሁለት



@BOOKALEM

ትዳዮች አሉ» ይለዋል

ሞት «ልወስዳቸው ስመጣ ሰዎች ሁሉ ይህንኑ ነው 'ሚሉኝ» ይለዋል

አርበኛው «እኔ ግን እውነቴን ነው:: ላደርጋቸው የሚገባኝ ነገሮች አሉ:: . . . በቼስ ጨዋታ የሚችልህ የለም ይባላል» ይለዋል

«እውነት ነው»

አርበኛው «እኔ ግን የምችልህ ይመስለኛል:: ይዋጣልን 'ስቲ:: ምን ቸገረህ? በመጨረሻ ማሸነፍህ አይቀር» ይለዋል

«እሺ እንጫወት»

«እስከሸነፍ ድረስ ልኑር ፍቀድልኝና፣ እኔን ለማሸነፍ ምን ያህል ጊዜ 'ንደሚወስድብህ እናያለን»

«እሺ»

ጨዋታቸውን ይጀምራሉ

. . . እንደሱ ያለ አስደናቂ ፊልም አይቼ አላውቅም:: እጭለማው ውስጥ ሲልቪን አንድ አምስት ጊዜ ብቻ በድንገት እያስታወስኳት በሀይል ድንግጥ አልኩ:: ግን ያኤውኑ ፊልሙ ከሀሳቤ ያባርራታል:: ግሩም ፊልም ነበር:: ሲያልቅ ደገምኩት:: በጭራሽ አልጠገብኩትም:: ግን ሶስተኛ ላየው አልቻልኩም:: ሲኒማ ቤቱ ተዘጋ:: ወጥቼ ስለፊልሙ እያሰላሰልኩ ስራመድ ሰአቴን አየሁ:: ሰባት ከሩብ — ልቤ በሀይል መምታት ጀመረ:: ባለሁብት ቆምኩ:: ሲልቪ! . . . እንዴት እስካሁን የሷ ሀሳብ አላስጨነቀኝም? ይሄ ኢንግማር በርግማን እንዴት ያለ ፍፁም አርቲስት ቢሆን ነው?! እስካሁን ከሱ ጋር ነበርኩ:: ከሱ ጋር ስለሞትና ስለህይወት ሳስብ፣ ስጨነቅ ቆየሁ:: ከሲልቪ መንጭቆ ወስዶ ስለዋናው መሰረታዊ አጣዳፊ ጥያቄ፣ ሞት ስለሚባለው ጥያቄ አዋየኝ:: ሞት ምንድነው? ህይወትስ? . . . ግን ሲልቪን ያስረሳኝ ኢንግማር በርግማን ብቻውን እንዳልሆነ ገባኝ:: እኔም ራሴ ልረሳት ፈልጌ ኖሯል:: አልታወቀኝም 'ንጂ፣ ስለሷና ስለወንዶቿ ማሰብ ስላስፈራኝ፣ ሸሽቼ ኢንግማር በርግማንን የሙጥኝ ማለቴ ኖሯል:: በርግማን ከስንት ጨካኝ ስቃይ ከለለኝ! ስንት የላቀ ሀሳብ አሳተፈኝ!

አሁን ታድያ፣ በርግማን የሚባለው ግድብ ተነሳ፣ የሲልቪ ሀሳብ



@BOOKALEM

በሀይል ንርፎ መጥቶ አፈነኝ:: ተንገበገብኩ:: ሳያት ሳትፈራ ተንገበገብኩ:: አቶቡስ ለመጠበቅ ወይም የሜትሮ ባቡር በሆነ ሰአትም ይሰራ 'ንደሆነ ለመሞከር ትእግስት አጣሁ:: ታክሲ ተሳፈርኩ:: ሆቴላችን ገባሁ:: የክፍላችንን ቁልፍ ሆቴል ጠባቂው (concierge) ሰጠኝ:: ሲልቪ ገና አልመጣችም ማለት ነው:: ሰአቱን አየሁ:: ለስምንት ሩብ ጉዳይ:: እመጣለሁ ያለችው በሰባት ነበር:: ንዴቱ ውስጤ እየገነፈለ ወደ ክፍላችን ገባሁ

ንዴቴ ለመጠራቀም ጊዜ አላገኘም:: ያኔውኑ በሩ ተንኳኳ:: ሲልቪ በቀስታ እርምጃ ገባች:: በሩን ቆለፈችው:: ተወርውራ እግሬ ስር ተምበረከከች:: እቅፍ አርጋኝ ፊቷን እጭኖቼ መጋጠሚያ ሰፈር ደበቀች:: ማናችንም ቃል አልተናገርንም:: ትንሽ ጭንቅላቷን ከዳበስኩ በኋላ ቀስ አድርጌ አነሳኋትና አቀፍኳት:: ትንሽ ቆይቼ ለቀቅኳትና ልብሴን ማውለቅ ጀመርኩ:: እሷም ልብሷን ማውለቅ ጀመረች:: ሁሉን ነገር ስትሰራ በዝግታ ነው:: እንደመጠውለግ ብላለች፣ አይኖቿ ውስጥ የነበረው የፍትወት እሳት ተዳፍኗል

ሸሚዟን ስታወልቅ ነጭ አንገቷ ላይ አንድ ቀይ ነገር ታየኝ፣ ጠጋ አርጌ አየሁት፣ ተነክሳ ነው:: ሳላስበው፣ በድንገት ሳብ አድርጌ አፏ ላይ ሳምኳት:: ማልቀስ ጀመረች:: እየደባበስኩ

«አይዞሽ፣ አይዞሽ» አልኳት

«አፈርኩ፣ በሀይል አፈርኩ:: እንዴት ቆሻሻ ነኝ! እባክህ መብራቱን አጥፋው» አጠፋሁት:: ሱሪዋን በጭለማው አወለቅኩላት፡ አቀፍኳት:: ጠረኗ ሌላ ነው፣ ጎረምሳ ጎረምሳ ትሸታለች:: ራሴ ዞረብኝ፣ ሳብድ ይታወቀኝ ነበር፣ ግን እብደቱን ለመከላከል አልቻልኩም፣ አልሞከርኩምም

«የት ነበርሽ? የት ነበርሽ? ንገሪኝ! ሳልሞት ንገሪኝ! ሳልፈነዳ ንገሪኝ!» አልኳት

«እሺ፣ እሺ የኔ ቢራቢሮ፣ እሺ፣ እሺ»

«ንገሪኛ!» አልኳት፣ አፏን እየሳስኩ፣ ወደ ገላዋ እየተጠጋሁ እያቀፈች እየተቀበለችኝ

«ከነሱ ጋር ነበርኩ:: በሰባት ልመጣ ነበር፣ የመጨረሻው አልፎ



@BOOKALEM

ግብ ብሎ አልለቅ አለኝ»

«የመጨረሻው?»

«አዎን»

«ስንተኛው?»

«አራተኛው»

«እውነት? ከተለየሁሽ ጀምሮ አራት ወንድ ተኝቶሻል?»

«አዎን»

«አላምንሽም»

በውብ ፈረንሳይኛዋ፣ በደከመ የጭለማ ድምፅዋ፣ በሹክሹክታ

«ለምን አታምነኝም? አይታወቅህም? አያስታውቅም?» አለችኝ

«ኡ - ዉ! ንገሪኝ፣ ንገሪኝ!»

ነገረችኝ:: የሳሙዋትን፣ የላሱዋትን፣ የነከሱዋትን፣ ሁሉን አንድ በአንድ ነገረችኝ:: . . . የስሜቱ አዲስነት፣ ብዛት፣ ጥልቀትና ሀይል ካሰብኩት በላይ ሆነ:: መጨረሻ ላይ ከስሜት ብዛት ስጮህ በእጇ አፌን አፈነችኝ:: በብዙ ለስላሳ ቃላት «አይዞህ ያንተ ነኝ» እያለች አባበለችኝ:: ገና ከላይዋ ላይ ሳልወርድ እንቅልፍ ወሰደኝ

እንደ መሞት ነበር

እንደዚህ አድርጋ ሲልቪ የግል ገንዘቧ አደረገችኝ:: እንደ ልቧ ትገዛኝ ጀመር:: ሲያስኛት ትሄዳለች፣ ደሞ በቀን በቀን ያስኛታል:: በቅርቡ የፈነዳች አበባ መስላ ትሄዳለች፤ ጠውልጋ ደክማ ትመለሳለች፤ በዝግታ ልብሷን ታወልቅና፣ በተሳመ አፏ ትስመኛለች፣ የረጠበ ነበልባል ታቅፈኛለች፣ በታሽ በለሩ ገላዋ ትነግረኛለች፣ በዚያ ውስጥ ታስገባኛለች — ስላቀፏት ወንዶች ጥሩ ነው! ውብ ኮረዳ በልስልስ ፈረንሳይኛዋ «መኖር እንዴት ጥሩ ነው! መደሰት እንዴት ጥሩ ነው! መሆንና ቆንጆ ጎረምሳ እያቀያየሩ መግባት እንዴት ያለ ከዚያ ሁሉ መጥቶ ደሞ አንተ እቅፍ ውስጥ ልጮህ ስል አፌን ገነት ነው!» ትለኛለች:: መጨረሻ ላይ ያንተው ነኝ፣ የኔ ቢራቢሮ፣ ታፍናለች:: «አይዞህ የኔ ቆንጆ፣ አይዞህ አልቆጥራቸው፤ መጫወቻዬ አይዞህ፣ አይዞህ:: ሌሎቹን ከምንም በፈለግክ ጊዜ አትሄጂ በለኝ፣ ናቸው፣ አንተን ብቻ ነው 'ምወደው፤



@BOOKALEM

እርግፍ አርጌ 'ተዋቸዋለሁ፡ እሺ? እይዞህ የኔ ፍቅር፣ የኔ ማለት፣ አይዞህ ተኛልኝ፣ እኔ 'ጠብቅሀለሁ፡ አይዞህ፡ እዚሁ ነኝ ተኛ፣ ተኛ...»

ኑሮዋችን እንደዚህ ቀጠለ:: አውቀን ይሁን ሳናውቅ 'ንጂ፣ አንድ ፕሮግራም ብጤ መከተል ጀመርን:: ከአል.ጋ ለምሳ እንነሳለን:: ከዚያ ፓሪስን በእግርና በአቶቡስ እንዞራለን:: አንዳንዴ ሉቭርን ወይም ሌላ ሚዩዚየም እንጎበኛለን:: እራት ከበላን በኋላ እንለያያለን:: እኔ ሲኒማ 'ገባለሁ:: ስንት ግሩም ፊልም አየሁ! እሷ ወደ ወንዶቿ ትሄዳለች

ስባት ወይ ስምንት ሰአት ሲሆን ሆቴላችን እንገናኛለን:: ድክም ጥውልግ ባለው ውብ ገላዋ ታቅፈኛለች፣ ወባ እንደያዘው እስክንቀጠቀጥ ታስቀናኛለች፣ እስክሶህ ታስደስተኛለች፡ ማአበሉ ሲያልፍልኝ ታባብለኝና ታስተኛኛለች:: ለምሳ ከአል.ጋ እንነሳለን

እንዲህ ስንል ብዙ ቀናት አለፉ

አንድ ማታ ከእራት በኋላ ካፌ ቁጭ ብለን ስናወራ

«ከበሽታዬ አዳንከኝ'ኮ» አለችኝ

«እንዴት?»

«በአንዱ ወንድ ገላ ሊላውን ወንድ ማቀፍ ተውኩ::»

«እንዴት አርገሽ ተውሽ?»

«እኔ 'ንጃ:: አንተ እየፈቀድክልኝ እስኪወጣልኝ ጠገብኩ መሰለኝ:: ብቻ ድኛለሁ:: አድነኸኛል»

«እኔ ያዳንኩሽ አይመስለኝም:: ራስሽ ነሽ የዳንሽው»

«አንተ ባትኖር አልድንም ነበር»

«ጥሩ:: አንቺ ዳንሽ:: እኔ ደሞ ታመምኩ»

«ምነው?» አለችኝ በስጋት ድምፅ

«እያወቅሽው:: ሌሊት ሌሊት እንዴት ነው 'ምሆነው?»

«ታድያ ሰው ሆንክ ማለት ነው 'ንጂ፣ እሱ ምን በሽታ ነው?»



@BOOKALEM

«ከሱ የባሰ ምን በሽታ ትፈልጊያለሽ? ካንቺ ጋር ፍቅር ይዞኛል። ለብቻዬ ላረግሽ መሞከር ይገባኛል፣ ግን ሌሎች ወንዶች ሲተኙሽና ከነሱ ተቀብዬ ስተኛሽ በሀይል ደስ ይለኛል። ይሄ በሽታ አይደለም?»

«እሺ። ይሄ በሽታ ያልከው እንዴት ነው 'ሚያረግህ?»

«እርግጠኛ አይደለሁም?»

«ቢሆንም ንገረኝ። ምን ቸገረህ?»

«እሺ። እንዲህ ይመስለኛል። አየሽ፣ እወድሻለሁ። ከልቤ እወድሻለሁ። ያላንቺ አንድ ቀንም መኖር 'ምችል አይመስለኝም። አንቺን ሌላ ሰው ቢወስድብኝ፣ ላንድ ሰአት ብቻ 'ንኳ ቢሆን አልች ልም፣ አንቺን ቢቀሙኝ እንደ ሞት ከፉና አስፈሪ ሆኖ ይታየኛል። እና እንደማይቀሙኝ እርግጠኛ ለመሆን አልችልም 'ይወስዱብኝ ይሆን?' እያሉ ማሰብ ብቻ አንድ ራሱን የቻለ ገሀነብ ነው»

«ግን ሲወስዱኝ ደስ ይልሀል?»

«ቆይ'ኮ። እምነት ቢኖረኝ ጥሩ ነበር። ግን ላምንሽ አልችልም። ማንንም ማመን አልችልም። ፍጥረቴ ነው። ቆንጆ ነሽ፣ አፍሽ ይስቃል፣ አይኖችሽ ይጣራሉ፣ ዳሌሽ ምኞት ይቀሰቅሳል — ማንም ወንድ ቢያገኝሽ አይምርሽም፣ አንቺ በበኩልሽ ግብረ ስጋ ትወጂያለሽ። ቆንጆ ወንዶች ትወጂያለሽ፣ እነሱ ደሞ ከፋታቸው በየቦታው ይብቅላሉ። ስለዚህ፣ በሆነ ሰአት እኔን ትተሽ ከሌላ ወንድ ጋር ልትተኚ ትችያለሽ። ይሄ ደሞ ለኔ ሆዴን በቀዝቃዛ ጩቤ እንደ መውጋት ነው፣ በሀይል ያስፈራኛል። አይታይሽም?»

«ቀጥል»

«አንቺንም ማመን አልችል፣ ወንዶቹም ይምሩልኛል ብዬ ማሰብ አልችል። ልከለክልሽ ደሞ አልችልም፣ ነፃ ሰው ነሽ። ልከለክልሽ ብችልም፣ ወንዶቹ እንዳይተኙሽ ለመጠበቅ እችል 'ንደሆነ ነው 'ንጂ፣ አንቺ እንዳትመኚያቸው ለመከልከል በጭራሽ አልችልም። ውስጡን ከተመኘሻቸው ደሞ፣ እነሱ አይወቁት 'ንጂ አንቺን ቀምተውኛል ማለት ነው። ስለዚህ አንቺን የመነጠቅ ፍርሀቱ ውስጡን ከማግኘት ጋር የተሳሰረ ነው፣ ሊለይ አይችልም። እኔ ካገኘሁሽ ሌላም ሊያገኝሽ ይችላል። ስለዚህ ሁልጊዜ እንደፈራሁ፣



@BOOKALEM

እንደተንቀጠቀጥኩ ነው:: ሁልጊዜ!»

«እሁ»

«ምንም መውጫ የለኝ:: እዚህ ፍርሀት ውስጥ መኖር ለብዙ ጊዜ አይቻልም. . . . ትንሽ ቆይቶ ያሳብዳል:: እኔም አበድኩ::»

«አበድክ? እንዴት?»

«ማበድ ማለት እንዴት ነው? የሆነውን ነገር እንዳልሆነ አድርጎ ማየት ወይም መቁጠር፣ ይኸው ነው ማበድ ማለት፣ አይደለም? አሁን አንዱ ተነስቶ ናፖሊዮን ነኝ ቢል አበደ እንላለን:: ምክንያቱም፣ የሆነውን (እሱን ራሱን) እንደ ሌላ ሰው (እንደ ናፖሊዮን) አርጎ ስለሚያይ ብቻ ነው»

«እሺ አንተ 'ንዴት አበድክ?»

«ቆይ:: ሰው የሚያብደው ለምንድነው? ምን እየነካው ነው? በዙሪያው የሚታየው እውነት (réalité) በጣም ከመጨከኑ ከማስፈራቱ ወይም ከማስቀየሙ የተነሳ፣ ይሄ ሰው ይህን እውነት ሊቀበለው አይችልም፣ ይክደዋል 'ይሄ እውነት አይደለም፣ እውነት ሊሆን አይችልም' ይላል:: ይሄ እውነት ካልሆነ፣ እንግዲያው እውነተኛው እውነት ሌላ ነው:: እዚህ ላይ ለሱ የሚስማማውን 'እውነት ይመርጣል:: . . . . ገብቶሻል::»

«ገብቶኛል:: አሁን ወዳንተ 'ንምጣ»

«ይኸው መጣን:: ለአንድ ደቂቃም ቢሆን ስላንቺ ነገር እርግጠኛ ልሆን አልቻልኩም:: ይሄ መጠራጠር ከመጠን በላይ ስለሚያሰቃየኝ፣ ልቀበለው አልቻልኩም:: ስለዚህ ካድኩት::»

«እንዴት?»

«እኔ 'ዚህ አንቺን ይገፍ ሌሎቹ ሊነጥቁኝ አልነበረም! መከላከያ በፍፁም አላገኘሁም? ስለዚህ በውስጤ በድብቅ (ከሌሎቹ ደብቄ) እንዲህ አልኩ 'እነሱም ሰዎች እኔም ሰው:: ስለዚህ ወስደው ቢደሰቱባት ምናለበት? ያው 'ንደኔው ናቸው:: እኔና እነሱ ያው ነን:: እኔ እነሱ ነኝ፣ እነሱ እኔ ናቸው. ' አልኩ:: እዮሽ፣ እንዲህ ከሆነ መሰጋትም የለብኝ፣ መፍራትም አያስፈልገኝ:: በዚህ አኳኋን፣ እውነተኛውን እውነት ከጀ፣ በሱ ቦታ የሚመቸኝን እውነት ተካሁ



@BOOKALEM

ስለእኩ ስትነግሪኝ ለምን ልቤ እንደሚጠፋ ልንገርሽ»

«ለምንድነው?»

«ከነገርሽኝ ነገሩን አወቅኩት ማለት ነው:: ካወቅኩት ደሞ አያስፈራኝም:: ጭለማ ሲሆን፣ ምን ይመጣብኝ ይሆን? በማለት እፈራለሁ 'ንጂ፣ በብርሀን ካየሁት ማንም ሰው ቢሆን አያስፈራኝም:: ማለቴ፣ ሳላውቀው አንድ ሰው ይተኛሽ ይሆን? ብዬ 'ፈራለሁ 'ንጂ፣ እያወቅኩ ከሆነ፣ አስር ሰው ቢተኛሽም አልፈራም:: እያወቅኩት ከተደረገ፣ ድርጊቱ የኔ ሆነ ማለት ነው:: የኔ ከሆነ ሊጎዳኝ አይችልም. . . . እንዴት እንደተኙሽ ስትነግሪኝ፣ እኔ እነሱን ሆኜ ተኛሁሽ፣ ተወስዶብኝ የነበረውን ገላሽን፣ ቃላትሽ መለሱልኝ ማለት ነው:: . . . ስለዚህ ነው የተኙሽ ወንዶች ቁጥር 'ንደመብዛቱ መጠን የኔ ደስታ 'ሚበዛው::»

«አልገባኝም»

«አየሽ፣ ማንም አልተኛሽም ማለት ያስፈራኛል:: ጭለማ ውስጥ ነኝ ማለት ነው:: . . . አንድ ሰው ተኝቶኛል ብትይ፣ ትንሽ ይሻለኛል:: ግን አሁንም አንድ ሰው ደብቀሽኝ ሊሆን ይችላል:: አራት ወንድ ተኛኝ ብትይ የበለጠ ይሻላል:: ምክንያቱም የደበቅሽኝ ነገር የለም ማለት ነው:: ስለዚህ መፍራት አያስፈልገኝም፣ ምክንያቱም የተወሰደብኝ ሁሉ ተመልሶልኝ አቅፌዋለሁ ማለት ነው::»

«ገባኝ:: አንድ ጥያቄ::»

«ምን?»

«እኔም እነሱም ያው ነን ካልክ፣ ምን 'ንዳረጉኝ ባታውቅስ ምን ልዩነት ያመጣል?»

«ይህን አትጠይቂኝ:: ላስረዳሽ አልችልም:: እኔም ራሴ አይገባኝም:: ምናልባት እኔም እነሱም ያው ለመሆን የምንችለው፣ እነሱ ያረጉትን ካወቅኩ ብቻ ይሆናል::»

ዝም ዝም ሆነ:: ታችኛ ከንፈሯን እየነከሰች ስታስብ ቆየች

«ልንገርህ?» አለች

«ምን?»

«እኔ በበኩሌ ሌላ ሆኖ ነው 'ሚታየኝ»



@BOOKALEM

«እንዴት ሆኖ ነው 'ሚታይሽ?»

«በጭራሽ በሽታ አልያዘህም:: እንደሌላ ወንድ ነህ»

«ሌሎች ወንዶች 'ከሌላ ጋር ተኝተሽ ነይልኝ' ይሉሻል?»

«አይሉኝም»

«እኔም 'ሚሉሽ አልመሰለኝም»

«ስማኝ 'ንግዲህ:: ከርከሩን ተውና አድምጠኝ:: በግብረ ስጋ በኩል ስለሴቶች ታውቃለህ 'ንጂ፣ በጥቅሉ ስለ ሴቶች ምን ታውቃለህ? እነሱ ካልነገሩህ ስለነሱ ለማወቅ አትችልም:: እነሱ ደሞ የውስጡን አይነግሩህም:: ለምሳሌ፣ አንተ እኔን ከሌሎች እየተቀበልክ እንደምትደሰትብኝ ለሰው ትነግራለህ ይመስልሃል? ለማንም አትናገርም:: ሌሎችም ወንዶች ውስጣዊውን ምስጢር አይነግሩህም:: ስለዚህ ሴት ካልሆንክ ወንዶችን በዚህ በኩል ልታውቃቸው አትችልም:: እኔ ልንገርህ

«ብዙ ጋብቻዎች መቀዝቀዝ ሲጀምሩ፣ ሴትዮዋ ተስፋ ትቆርጥና ውሽማ ትይዛለች:: ባልየው ሲያውቅ ምን እንደሚያደርግ ታውቃለህ? ለጊዜው ይናደዳል፣ ይደበድባታል፣ እንፋታ ይላል:: በኋላ ግን ታርቀው ይቅርታ ያደርግላትና፣ በጣም ሊወዳት ይጀምራል:: ቀዝቅዞ የነበረው ጋብቻ ይሞቃል፣ ይታደሳል:: ለምን? ሴትዮዋ ሌላ ወንድ ጋ ስለሄደች ነው

«መንገድ ዳር ውጣና ጎረምሶቹን ሴት ሲያድኑ እያቸው:: ሴትዮዋ በጣም ጨዋ ከመሰለቻቸው፣ ምንም ቆንጆ ብትሆን አይከተሏትም:: ትንሽ በመጠኑ ስድ ብጤ ከሆነች ግን — አስተያየቷ፣ አረማመዷ፣ ወይም አለባበሷ በቀ ልቅነት ካሳየ — ጎረምሶቹ ይሻሚታል:: በቀላሉ ሊያገኙዋት ስለሚችሉ ብቻ 'ንዳይመስልህ:: ዋናው ምክንያት ሌላ ነው:: ባለጌ ከመሰለች፣ እንግዲያው ብዙ ወንድ አውቃለች ማለት ነው:: ለዚህ ነው 'ሚሻሚት

«አዎ፣ የሰው ልጅ ፍጥረቱ 'ንደዚህ ነው:: አንድ የለመድከው ሰው ሊለይህ የሆነ 'ንደሆነ ልትወደው ትጀምራለህ:: ለህይወትህ የሚያስፈራ በሽታ የያዘህ የመሰለህ 'ንደሆነ፣ በፊት ከምንም የማትቆጥራትን ህይወትህን በሀይል ልትወዳት ትጀምራለህ



@BOOKALEM

«ሀኪም ጨጨው እንዳትበላ ያዘዘህ ’ንደሆን፣ ጨው ምንኛ ግሩም ቅመም ’ንደሆን ትገነዘባለህ. . . ሴትህ ወደሌላ የሄደችብህ ’ንደሆን፣ እንዴት ቆንጆ ’ንደሆነች እንደ አዲስ ሊታይህ ይጀምራል

«በራሴ የሚያጋጥመኝን ለምን አልነግርህም? በዚህ ሰሞን ከማያቸው ወንዶች ሁለቱ እንዴት እንደሚሆኑ ላሜውትህ:: ሁለቱም ያው ናቸው:: ስለዚህ ስለአንዱ ልንገርህ:: ማርሴል ይባላል:: በጣም ቆንጆ ነው:: ብዙ ሴት ያወቀ ወጣት ነው:: ማታ ከእራት በኋላ ካንተ ’ንደተለየሁ፣ በቀጥታ ወደሱ የሄድኩ ’ንደሆነ፣ ንፁህ ነኝ፣ የማንም ላብ አልነካኝም፣ ጠረኔ የራሴ ነው:: ልብሴን አስወልቆ ያቅፈኛል፣ በደምብ ያስደስተኛል:: አንዳንዴ ታድያ፣ ካንተ ’ንደተለየሁ በቀጥታ ወደሱ አልሄድም:: በፊት ሌላጋ ’ደርሳለሁ:: እና እሱጋ ስሄድ የሌላ ወንድ ላብ ነክቶኛል፣ ጠረኔ የብቻዬ ሳይሆን ከጎረምሳ ጠረን ጋር ተቀላቅሏል:: አሁንም ልብሴን ያስወልቀኝና ያቅፈኛል፡ ግን እንደነብር ይሆናል፣ ይጨፈልቀኛል፣ ይነክሰኛል:: ስለሌላ ወንድ አንነጋገርም፡ ግን ሌላጋ ’ንደነበርኩ በማወቁ የበለጠ እንደሚጣፍጠው ግልፅ ነው:: ይታይሀል?»

«በሚገባ! እና እኔ ’ንዲህ ’ምሆንበት ምክንያቱ ምን ይመስልሻል?»

«ቀላል ነው:: አንደኛ፣ ሌላ ወንድ ከተኛኝ ቆንጆ ነኝ ማለት ነው:: ብዙዎች ከተኙኝ እጅግ በጣም ቆንጆ ነኝ:: ስለዚህ የበለጠ ትፈልገኛለህ:: ሁለተኛ፣ ሌላው ተኝቶኝ አንተ ቀጥለህ ከተኛኸኝ፣ ከሱ ቀምተህ ወሰድከኝ ማለት ነው:: እኔ በሀይል ቆንጆ ሆኜ ከሌሎቹ ሁሉ ቀምተህ ከወሰድከኝ፣ ከሌሎቹ ሁሉ የበለጠ ወንድ ነህ:: በጣም ደስ ይልሀል:: በጣም ደስ በወንድነት ከሁሉ በላይ ሆንክ፣ ስለዚህ ደስ ይልሀል:: ወንዶች ሁላችሁም እንደሱ ናችሁ:: ግን. . .» አየችኝ

«ግን ምን?» አልኳት

«አብዛኞዎቹ ወንዶች ውጪውን ጎበዝ ቢመስሉም ውስጡን ፈሪ ናቸው:: የውስጥ ስሜታቸውን አይተው መቀበል ይፈራሉ:: ስለዚህ ከራሳቸው ይደብቁታል:: ሁሉም ወንድ – አብዛኛው ወንድ ልበል – የራሱን ሴት ሌሎች ሲቀምሱበትና እሱ ነጥቋቸው መልሶ የራሱ ሲያረጋት፣ የበለጠ ወንድነት ይሰማዋል:: በሀይል ደስ ይለዋል:: ግን ይህን እንደ ጉድ አርጎ ስለሚቆጥረውና ስለሚያፍርበት፣ እያየውም



@BOOKALEM

አውቆ አይኑን ይጨፍናል:: ስለዚህ ያስመስላል፣ ያስመስላል፣ ያስመስላል:: አቤት ስንት ማስመሰል አለ!

«እዚህ ላይ ነው አንተን ከልቤ 'ማደንቅህ:: እቺን ያህል አትፈራም:: ወደነብስህ ውስጥ አትከራህ ትመለከታለህ:: እዚያ ውስጥ ምንም ቀፋፊ ነገር ብታይ አይንህን አትጨፍንም:: ስለዚህ ያለማስመሰል ትኖራለህ — ውስጣዊውን ኑሮ ማለቴ ነው:: እንግዲህ ወደ ውስጥህ ተመለከትክ፣ ውስጥህ እኔን ሌሎች ቢተኙኝ ከነሱ ቀምተህ ስትተኛኝ ደስ እንደሚለው ነገረህ:: ስለዚህ እኔን 'ሂጂ ወንዶችሽ ጋ' አልከኝ:: ሄድኩ:: ተመለስኩ:: ተደሰትክብኝ:: ወንድ ነህ:: አንተ እውነተኛ ወንድ የሆንከውን ያህል እኔ እውነተኛ ሴት ሆኜ 'ንደሆን እጅግ ኩራት ይሰማኛል::»

«አንቺ 'ንደምትይኝ ከሆንኩ፣ አንቺም 'ንደኔ አይነት ነሽ:: ልክ 'ንደኔ አይነት! አብዛኛዎቹ ሴቶች፣ ፍቅር ከያዘኝ ወንድ ጋር ብቻ ነው ግብረ ስጋ ደስ 'ሚለኝ ይላሉ:: ይህም ማስመሰል፣ ማስመሰል፣ ማስመሰል ነው:: አንቺ ግን ለራስሽ አትዋሺም:: 'ቆንጆ ወጣት ሆኖ ቆንጆ ወንድ እያቀያየሩ መደሰት እንዴት ያለ ገነት ነው!' ትያለሽ:: 'እኔኮ አልችልም፣ ቆንጆ ወንድ ሳይ እያስችለኝም፣ ቁንጅናውን መንካት መዳሰስ አለብኝ፣ በወጣትነቱ መደሰት አለብኝ' ትያለሽ

«አንድ ቀን አንድ ነገር አልሽኝ:: እስከመቼም አልረሳውም::»

«ምን አልኩህ?»

«ሰክረን ሳይሆን ሞቅ ብሎን ነበር:: እና ስለስነ ጽሑፍ ስናወራ ቆይተን ወደ ግብረ ስጋ ወሬ ተሸጋገርንና፣ እንዲህ አልሽ — 'ሴት መሆንን የመሰለ ነገር የለም:: አምላክ ከመሆን ይበልጣል:: ያንን ሽንቅጥ ጎልማሳ ታየዋለህ? መልከ ቀና ነው:: ጤነኛ ነው:: ኩሩ ነው:: የትኛው አምላክ ነው ይህን ጎልማሳ ለራሱ ለማድረግ የሚችል? እኔ ግን በአይኔ ልጠራው 'ችላለሁ:: በደስታ ይታዘዘኛል:: የግል የውስጥ ፍሬውን ለኔ ይሰጠኛል — ከፈለግኩ:: ምክንያቱም ሴት ነኛ! ቆንጆ ሴት ነኝ፡ ቆንጆ ወጣት ሴት እስከሆንኩ ድረስ ከአማልክት በላይ ነኝ፡ የጣማሹ አለም ጣኦት ነኝ::

«'ወንዶቹን እያቸው:: አለባበሳቸው፣ አረማመዳቸው፣



@BOOKALEM

አስተያየታቸው ግሩም አይደለም? — ይሄ ሁሉ የተደረገው ለኔ ነው:: ለኔ ለራሴ! ለሚቀጥሉት አስር አስራ 'ምስት አመታት፣ የአለም ንግስት ነኝ:: ሁሉ የኔ ነው:: ሁሉ ስልህ፣ የአለም ባንክና የኒው ዮርክ ፎቆች፣ የፓሪስ ሻንዜሊዜ ጎዳና ማለቴ አይደለም:: እሱ 'ሱ ምን ዋጋ 'ለው? ምን ሊያረግልኝ ይችላል? ሁሉ የኔ ነው ስልህ፣ ዋጋ ያለው ሁሉ የኔ ነው ማለቴ ነው:: የጎረምሶቹ ኩሩ አረማመድ፣ የጋለ አስተያየት የኔ ነው:: የተገማመደ፣ የተወጣጠረ ጡንቻቸውና ከሻኔል ሽቶ ይበልጥ የሚሰርፀው መአዛዊ ጠረናቸው የኔ ነው:: ወጣትነት የገተረው ወንድነታቸው ለኔ ነው:: ይገባሀል 'ምልህ? የኔ ናቸው:: እያንዳንዱ ጎረምሳ አንድ ራሱን የቻለ የተለየ አለም ነው:: አዲስ ወንድ ልብሱን አውልቆ በጡንቸኛ ፀጉራም እጁ ባቀፈኝ ቁጥር፣ አንድ አዲስ አለም ውስጥ ነኝ:: ታውቃለህ፣ እስካሁን ስንትና ስንት ወንድ አቅፎኛል:: ታድያ ላይ ላዩን 'ንደሆነ ነው 'ንጂ፣ አንዱም እንደሌላው አያቅፈኝም:: እያንዳንዱ ከሌሎቹ ልዩ የሆነ ግለኛ ወንድ ነው:: እኔም በበኩሌ አንዱንም 'ንኳ እንደሌላው አድርጌ አቅፌ አላውቅም:: ከልዩ ልዩ ወንድ ጋር ልዩ ልዩ ሴት ነኝ:: ካንዱ ጋር አይናፋር ነኝ፣ ከሌላው ጋር አይናውጣ ነኝ፣ ካንዱ ጋር የተቀጣሁ ጨዋ ነኝ፣ ከሌላው ጋር ስድ ባለጌ ነኝ፣ ከሌላው ጋር ሳቂታ ነኝ፣ ከሌላው ጋር ትራጂክ ነኝ:: ብቻ ምን ልበልህ፣ ብዙ ሴቶች ነኝ:: ብዙ ቆንጆ ሴቶች ነኝ:: ታድያ ይሄ ሁሉ እኔ ራሴ ነኝ:: እና ግሩም ድንቅ ነው:: መኖር የማይደገም ትልቅ ተአምር ነው:: ወጣት ሴት ሆኖ ልዩ ልዩ ወጣት ወንድን ማቀፍ ደሞ የተአምር ተአምር ነው::»

ወጣት ሆነን አንኖርም ግን!?' አልሽና

«'ለምን ዘለአለም
'የት?' አልኩሽ:: ድንገት ቦርሳሽን እያነሳሽ፣ 'እንሂድ' አልሽኝ:: ሄድንና እጅግ በጣም 'ሆቴላችን እንሂድ:: አምሮኛል' አልሽኝ:: ተደሰትን::»

«ይህን ሁሉ ታስታውሳለህ?»

«ኧረ ስንት ሌላ ነገር አስታውሳለሁ:: ስላንቺ ምንም ነገር ልረሳ 'ምችል አይመስለኝም. . . ልጅ ሳለሁ አባቴ ከቤታችን ጓሮ አትክልት ይተክሉ ነበር:: ለኔ ትንሽዬ 'ርስት' ሰጡኝና በቆሎ ዘራሁ ባት:: በቀን አስር ጊዜ እየተመላለስኩ በቆሎዎቼ በቅለው 'ንደሆነ



@BOOKALEM

አይ ነበር:: ከስስት ቀን በኋላ አንዷ ብቅ አለች:: አቤት እንዴት ነው ደስ ያለኝ! አረንጓዴ ነበረች፣ ህይወት ነበረች:: እየሮጥኩ ሄጄ እናቴን ጉትቼ አመጣኋትና በቆሎዬን አሳየኋት:: አባቴ ከእርሻ ሲመጡ ጉትቼ ወስጄ በቆሎዬን አሳየኋቸው:: 'ርስቴ' ላይ አብረው የተዘሩት ሌሎች በቆሎዎችም በቀሉ:: ግን እኔ ያችን የመጀመሪያዋን ነበር 'ምወደው:: በየቀኑ 'የሄድኩ አያታለሁ:: እያደገች ስትሄድ በየቀኑ ትንሽ ልዩነት አገኝባታለሁ፣ ማለት ሁልጊዜ አዲስ ነበረች፣ ግን ሁልጊዜ ያችው በቆሎዬ ነበረች:: እስካሁን አልረሳኋትም:: እስከሞትም አልረሳትም. . . «የኔ ሲልቪ፣ አንቺም ለኔ እንደዚያች በቆሎዬ ነሽ፣ የጎልማሳነቴ ልዩ ፍቅር ነሽ:: በየቀኑ የበለጠ እያወቅኩሽ ስሄድ፣ በየቀኑ የበለጠ እየወደድኩሽ እሄዳለሁ::»

እጁን የያዘ እጄን እያሻሻች

«እኔም እወድሀለሁ:: እንዳንተ ያለ ወንድ አጋጥሞኝ አያውቅም::»

«አሁን ሰአትሽ አልደረሰም?» አልኳት

ሰአቷን እያየች

«ደርሷል» አለች:: «ይድረስ:: Je m'en fouts! ዛሬ ካንተ ጋር ነው 'ማመሸው:: ደሞ ከንግዲህ ሌሎቹን አልፈልጋቸውም:: ይህን ሰሞን ካንተ መለየት አልፈልግም::»

«አዳዲስ አለሞችን ማየት ይቀርብሻላ»

«ያንተ አለም ከሀያ አዳዲስ አለም ይበልጥ ያስደስተኛል'ኮ:: አታውቅም?»

«አውቃለሁ 'ንጂ» አልኳት እየሳቅኩ

«አቤት ትእቢት! ትንሽ መግደርደርም የለ?» አለችኝ በጉልህ ሰማያዊ አይኖቿ እያየችኝ፣ በስሬ ውብ አፏ እየሳቀችብኝ፣ እየወደደችኝ

ድንገት ሳቁን እየተወች «አንድ ነገር ልነግርህ እፈልግ ነበር» አለችኝ

«ንገሪኝ»

«እንዳትቆጣ:: ወንድ ሆነህ አትስማኝ፣ ደራሲ ሆነህ አዳምጠኝ



@BOOKALEM

ንጂ።»

«እሺ»

“Parole d'honneur?”

“Parole d'honneur!”

«አንተን እወድሃለሁ። ከልቤ አፈቅርሃለሁ። ግን ፖልን ልረሳው አልችልም። የመጀመሪያዬ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን፣ ሳልጠግበው ስለሄደብኝ ጭምር ይመስለኛል። ይገባሃል?»

«ይገባኛል»

«እና አንዳንድ ጊዜ ይናፍቀኛል። ይመስለኛል፣ በውስጤ የልጃገረድነቴ ጊዜያት ከሱ ጋር ተዋህዷል። እና ያ ጊዜያት ሲናፍቀኝ፣ ፖል ይናፍቀኛል። ከልቤ ላወጣው ልረሳው እሞክራለሁ። ግን የምችል አይመስለኝም። የምልህ ይገባሃል?»

«ይመስለኛል»

«ስለዚህ ፖልን የሚመስል ሰው ሁሉ ደስ ይለኛል፣ ይስበኛል። . . . እና ስለባህራም ልነግርህ እፈልጋለሁ።»

ይናገራል ብላ ዝም አለች። መናገሩ እየከበዳት ሄዷል። ዝም ብዬ ሳያት ቀጠለች

«አንተ ነህ ባህራምን እንድወደው ያረግከኝ። ስለሱ ብዙ ብዙ አወራህልኝ። አራት ወር ሙሉ አወራህልኝ። ከወሬህ እንዳየሁት፣ እንደማውቅህ አንተ ማንንም በጣም በጣም ታከብረዋለህ። ግን እንዴት ያለ ሰው ቢሆን ነው? አታከብርም። ስለዚህ፣ ይሄ ባህራም እንዴት ያለ ሰው ቢሆን ነው? አልኩ። አንዲት ሴት እንዲህ ካለች ደሞ መመለሻ የላትም። ይህን ያባሰው ምንድነው? ከወሬህ እንደተገነዘብኩት ባህራም እንደ ፖል ያለ ሰው ነው። እንደሌላው ሰው ከተራ ጭቃ ተጠፍጥፎ አልተሰራም። ጀግናዎቹ ከሚሰሩበት ከልዩ ጭቃ ተቀርፆ፣ በልዩ ንፁህ እሳት ውስጥ ነው የተጠበሰው። ባህራምን እንደዚህ አድርገህ ነው ያሳየኸኝ

«አንተ ያንን ያህል እያከበርከው፣ ከፖል ጋር ያንን ያህል እየተመሳሰለ፣ እንዴት ደስ ላይለኝ ይችላል? እኔ ደሞ እንደምታውቀኝ ነኝ። እንዴት ላልመኘው እችላለሁ?»

«ፍቅር ይዞሻል?»



@BOOKALEM

ራሷን በሀይል እየነቀነቀች፣ ከኋላዋ ጥቁር ሀር ፀጉሯ እየተወዛወዘ፣ የደሲት ሳይሆን የመስቃየትና የመደናገር ፈገግታ ውብ እፏን እየሸመቀቀው

«እኔ'ንጃ! እኔ'ንጃ! እኔ'ንጃ!» አለችና ራሷን ጠረጴዛው ላይ ደፋች

ራኽም ወጣታ

እጄን ሰድጄ ራሷ ላይ አሳረፍኩት። ቀና ብላ አየችኝ። እምባዋ ይወርዳል

«ስስት ፍቅር አንድ ላይ ሊይዝ ይችላል?» አለችኝ

«ሴትዮዋ ተራ ከሆንች አይችልም» አልኳት

ጠረጴዛው ላይ የነበረ እጄን ወስዳ ከጎንጯ ጋር እያተሻሸች፣ በእምባዋ እጄን እያረጠበች፣ በተጨነቀ ድምፅ

«ብዙ ጎዳሁህ፣ የኔ ቢራቢሮ?» አለችኝ

«ግድ የለሽም» አልኳት

«አለኝ 'ንጂ። ላንተ ብዙ ግድ አለኝ። ለዚህ 'ኮ ነው 'ምነግርህ።»

«አውቃለሁ»

«ለኔ እንዴት ጥሩ ነህ! አሁን ምን ይሻለኛል?»

«ቆንጆ ነሽ። ተወዳጅ ነሽ። ለምን አትወጂውም?»

በመሀረቧ እምባዋን እየጠረገች

«አንተስ? አትቀየምም?»

«ሌሎች ጋ ትሄጂ የለ? ስለዚህ ለኔ ያው ነው»

«ውይ! እንዴት ደግ ነህ!?»

«ለምን?»

«ውሸትክን ነዋ» ተናፈጠች «እኔ 'ንድደሰት ብለህ ትሰቃያለህ።»

«የምን ስቃይ?»

መሀረቧን አጥፋ እየመለሰችልኝ



@BOOKALEM

«እንግዲህ አትቀኚ:: ይበቃሀል:: አውቅሀለሁ:: አውቅሀለሁ'ኮ:: ከምትገምተው በላይ አውቅሀለሁ:: ፊትህ ላይና አይኖችህ ውስጥ ስንትና ስንት ነገር ይታዩኛል መሰለህ::»

«ምን ይታይሻል?»

«ስለባህራም ስነግርህ በብዙ ነው ያዘንከው::»

«ላንቺ ነዋ ያዘንኩልሽ::»

«እሱም ታይቶኛል:: ግን ለራስህም በሀይል በመሰቃየት ላይ ነህ:: እና በጣም አዝናለሁ:: እንዲህ በመሆኔ በጣም አዝናለሁ::»

«በማዘን የትም አይደረስም::»

«አውቃለሁ የኔ ቆንጆ:: ግን ማዘን አይቀርም::»

ዝም ዝም ሆነ

«በኔ ብቻ ሳይሆን በባህራምም ጭምር ነው ያዘንከው:: ልክ ነኝ?»

ዝም አልኳት

«እንግዲህ ልንገርህ:: እውነቱን ብታውቅ ይሻላል:: ልንገርህ?»

«እሺ::»

«ያን እለት ማታ ያ ሰውዬ ባህራምን ሲገድለው አልመጣም? እና አንተ ኒኮልን ይዘህ ማርሰይ አልሄድክም? — ከኒኮል ጋር ምንም አልሰራችሁም? እውነት ተናገር::»

«ምንም አልሰራንም:: ይልቅ ቀጥዪ::»

«እና ሰውየውን ሲገድለው አላየሁም? እሱን ነግሬሀለሁ:: እና ከዚያ ወደ ቤት ሄድን:: ባህራም ልክ ምንም እንዳልሰራ በእርጋታ ሶፋ ላይ ተቀመጠ:: እኔ መጠጥ ስጠሁትና ሶፋው ላይ አልጋ ብጤ አነጣፍኩለት:: እንጥሬ ስጨርስ 'እንግዲህ እዚህ ውስጥ ይተኛል:: ከጆግና ጋር ነው'ኮ ነብስ ገድሏል፤ ግን እዚህ ውስጥ ይተኛል' ብዬ አሰብኩ:: ዘወር ብዬ ያለሁት:: ከነብሰ ገዳይ ጋር ነው ያለሁት' ብዬ አሰብኩ:: ዝም ሲል የኢራንን ሻህ አየሁት:: አንተ 'ንደ ነገርከኝ ነው:: ጆግና ስለሆነ አንድ ቀን የኢራንን ይመስላል:: 'ማን ማን ያውቃል? ጆግና ስለሆነ አንድ ቀን የኢራንን ሻህ ይገድለው ይሆናል'ኮ!' ብዬ አሰብኩ



@BOOKALEM

«እና በሀይል ተመኘሁት፡፡ ፍትወት ያንን ያህል አንቆ ይዞኝ አያውቅም፡፡ ራሴን 'ተይ እንደሱ አታርጊ! ተይ!' እያልኩ ከተቀመጠበት ሄድኩና እግሩ አጠገብ ተምበርክኬ ወደላይ አየሁት፡፡ እንደ ቄስ እጁን ራሴ ላይ አሳረፈና

«ምን ሆነሻል?» አለኝ

ቀ--ስ ብዬ ተነሳሁና አፉ ላይ ሳምኩት

አሁንም «ምን ሆነሻል?» አለኝ፡፡ ግን ገብቶታል

«ፈልጌሀለሁ» አልኩት

«እኔ አልፈልግሽም» አለ

«አውቃለሁ ትፈልገኛለህ፡፡ ትፈልገኝ የለ?»

«አዎን፡፡ ካየሁሽ ጀምሮ እንደፈለግኩሽ ነው፡፡»

«ይኸዋ፡፡ አለሁልህ!»

«አይሆንም!»

«ለምን አይሆንም?»

«ምክንያቱን መቼ አጣሽው» አንተን ማለቱ ነው

«እሱ 'ንደሆነ ግድ የለውም» አልኩት

«እኔ ግድ አለኝ!»

«ለምን?»

«ጓደኛዬ ነው፡፡ እፈልግሻለሁ፡፡ ግን እሺ አልልሽም፡፡ ስለዚህ እርሺው!»

«አልረሳውም፡፡ ልረሳው አልችልም፡፡ ልረሳው አልፈልግም፡፡ ሌሊት እመጣለሁ!» አልኩትና ሄጄ አልጋዬ ውስጥ ገባሁ፡፡ ልተወው ቆረጥኩ፡፡ ምናልባት አንድ ሰአት ያህል ቆየሁ፡፡ ከዚያ በላይ ግን ልቆይ አልቻልኩም፡፡ እንደዚህ አሳስችል ያለኝ እሱ ስለሆነ ብቻ ነበር፣ ወይስ ሰው ሲገድል ስላየሁት ነበር? አላውቅም፡፡ የሆነ ሆኖ፣ እሱ 'ዚያ ተጋድሞ እኔ 'ዚህ ሆኜ ልታገስ አልቻልኩም

ራቁቴን ወጣሁ፡፡ ሽቶ ተቀባሁ፡፡ ከመኝታዬ ወጣሁ፡፡ የንግዱ



@BOOKALEM

ቤቱን መብራት አበራሁ:: እንቅልፍ አልወሰደውም ነበር:: ሄድኩና ከበላዩ ቆምኩ:: ወደላይ አየኝ:: ሲያየኝ ብዙ ጊዜ ቆየ:: እጁን ሰደደ:: ጭኔን ይዞ ወደታች ጎተተኝ

ካሸነፈኩት በኋላ ወደ አልጋዬ ሄድን::»

ዝም አለች:: ያችን ሌሊት እንደምታስታውስ ያስታውቃል:: እንዴት ያለች ሌሊት ነበረች ይሆን? ብጠይቃት እንደማትነግረኝ እርግጠኛ ነበርኩ:: ስለሌሎቹ ወንዶች በሰፊው ትንገረኝ 'ንጂ፣ ስለነሱ ጥቃቅኑን ሲጋዊ ተግባር ሳይቀር ትዘርዝርልኝ 'ንጂ፣ ስለፖልና ስለ ባህሩም አትነግረኝም:: እኔም ስለነሱ መጠየቅ ልክ አልመሰለኝም:: ዝም አልኩ:: ቀጠለች

«ስለሌሊቱ ልንገርህ 'ንዴ?» አለችኝ

«ልትነግሪኝ ትፈልጊያለሽ?»

«አልፈልግም:: ከፈለግክ ግን እነግርሀለሁ::»

ይህን ያለችኝ «ሳትፈልጊ ብትነግሪኝ ደስ አይለኝም» እንደምላት አውቃ ነው 'ንጂ፣ ንገሪኝ ብላትም እንደማትነግረኝ አውቃለሁ

«ሳትፈልጊ ብትነግሪኝ ደስ አይለኝም» አልኳት

ዝም አለች:: እኔም ዝም አልኩ

«እንግዲያው ከአልጋ ውጪ የሆነውን ልንገርህ::»

«እሺ::»

«ባህሩም ጧት ተነስቶ ገላውን ታጥቦ ቁርስ ከበላን በኋላ

«አንድ ነገር ላስረዳሽ እፈልጋለሁ:: ፍቀጂልኝ» አለኝ

«ምንድነው?» አልኩት

«በጣም ቆንጆ ሴትዮ ነሽ:: ማንንም ወንድ ማዘዝ ትችያለሽ:: ባንቺ መገዛት በጣም እፈልግ ነበር:: ግን ትላንት ሌሊት የመጨረሻችን ሌሊት መሆኑን እወቂ» አለኝ

«ለምን?» ብለው

«እያወቅሽ አትጠይቂኝ:: የሱን ስም እዚህ ባላነሳ ፈቃዴ ነው:: ትላንትም ነግሬሽ ነበር:: ትላንት ልታሸንፊኝ ቻልሽ:: ከንግዲህ



@BOOKALEM

ወዲያ ግን በጭራሽ እንዳትጠጊኝ:: አደራሽን:: ስለሊሊቱ በጣም አመሰግንሻለሁ:: ግን በጣም በጣም ይቆጨኛል!» አለኝ

«እኔ ነኝ ሊቆጨኝ 'ሚገባው:: ግን ፊዕሞ አልቆጭም» አልኩት

«አውቃለሁ:: የተለያየን አይነት ሰዎች ነን:: አየሽ፣ እኔ በሰው ልጆች ብዙ እምነት አለኝ:: ለምሳሌ፣ እሱ ኒኮልን ቢፈልጋትም ለኔ ብሎ እንደሚተዋት እርግጠኛ ነኝ:: ስለዚህ፣ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ታውቂ የለ?»

«አላውቅም ኸረ:: ምን ማድረግ አለብህ?»

«የበደልኩትን ጓደኛዬን ሄጄ ይቅርታ መለመን አለብኝ»

«ምን?»

«ሄጄ ይቅርታ 'ለምነዋለሁ:: ትላንት ማታ የሰራሁትን እነግረዋለሁ»

«ይቅርታ ባያረግልህስ?»

«ያረግልኛል»

«ባያረግልህስ?»

«እሱ 'ንግዲህ የራሱ ፋንታ ነው»

«ጓደኝነታችሁ አበቃ ማለት አይደለም?»

«ጓደኝነታችን በውሸት ተደግፎ ከሚቀጥል ቢያበቃ ይሻላል::»

«ይህን ስትነግረው እሱ ይጎዳ የለም?»

«ጠንካራ ነው:: ምንም ነገር ሊጎዳው አይችልም:: ወንድ ነው» አለኝ:: አየህ፣ እኔ ብቻ አይደለሁም የብረት ሰው ሆነህ 'ምትታየኝ»

«ቀጥይ» አልኳት

«'እና የኔንስ ነገር 'ንዴት ታረጋለህ? ብትነግረው ይተወኛል:: እኔ ደሞ እወደዋለሁ:: ታድያ፣ ተደስተህብኝ ስታበቃ፣ ለጓደኝነትህ ንፅህና ስትል የኔን ፍቅር ታፈርስብኛለህ?' አልኩት::»

«'ያምነኛል' አለኝ 'አንቺ አማርሽኝና በጉልበት ተኛሁሽ ብል፣ ማንም ወንድ ያምነኛል'



@BOOKALEM

ሊሄድ ሲል «'አንድ ነገር ልለምንህ 'ባክህን' አልኩት»

«ምን?»

«እኔ ራሴ እንድነግረው ፍቀድልኝ»

«እኔ ብነግረው ይሻልሻል» አለኝ

«ግድ የለህም» አልኩት

«እሺ» አለኝ

«ግን እውነቷን ነው 'ምነግረው» አልኩት

«ለምን?» አለኝ

«ጓደኝነት ብቻ ነው በእውነት ውስጥ መኖር ያለበት? ፍቅርስ እውነት አይወድለትም?» አልኩት

ሳቅ አለ። «ይቅርታ 'ርጊልኝ። እንዲህ አይነት ፍቅር አልመሰለኝም ነበር። እንግዲያው አንቺ ብትነግሪው ይሻላል» አለኝ

«እና እንዲህ ሲለኝ የባሰውን ወደድኩት። ምን ይሻለኛል?» አለችና፣ እንደገና ራሷን ጠረጴዛው ላይ ደፋች

ዝም አልኳት። እንደዚህ ሆነን ረዥም ጊዜ ቆየን። እንደተደፋች ዩ መጥቶ ከኋላዋ ቆመና ይገላምጠኝ ጀመር። ባለ ፀጉራም እጅ ገርምሳ ነው። ምናልባት ሊደበድበኝ የሞከረ 'ንደሆን ለመከላከል ከሴ ቢራ የሞላ ብርጭቆዬን ጨበጥኩ። በልቤ «እባክዎ ፈረንሳይ!» አልኩ

ሲልቪ ቀና አለች። አሁንም እምባዋ ይወርዳል። መሀረቧን ጠኋት። እምባዋን ስትጠርግ በዩ እሷ ሊታየው ወደምትችልበት ታ (ወደኔ አጠገብ) ራመድ አለና፣ እኔን በሚቆጣ፣ ግን እሷን ማባብል ድምፅ

"Mademoiselle a besoin de quelque chose?" አለ («ማድሟዜል ምታስፈልጋቸው ነገር አለ?»)

ወደሱ ተመለከተች። የተጨበጠ ፀጉራም እጁ ታያት። ገባት።

"Merci, monsieur, je suis avec un ami" («እግዜር ይስጥልኝ ሴዬ፤ ከጓደኛዬ ጋር ነኝ») አለችና፣ በብሩህ ፈገግታ እጄን ለቶ ... «በጣም ውድ የሆነ ጓደኛ» አለች። («በጣም ውድ የሆነ ...ን እየያዘች "un très cher ami"



@BOOKALEM

ኋደኛ»)

ቦዬ በለዘበ ድምፅ "Pardon, monsieur" አለኝና ሄደ:: አንዳንዶቹ ፈረንሳዮች ግሩም የሆነ ጠባይና አስተዳደግ አላቸው

ሲልቪ ፈገግታዋ እየጠፋ

«ምን ይሻለኛ ይመስልሀል?» አለችኝ

«በሱ በኩል ተስፋ የለሽም:: ተይው» አልኳት

«ከዚህ ውሰደኝና ውድድ አርገኝ 'ስቲ:: ትችላለህ?»

«ለምን አልችልም?»

«ይህን ሁሉ ከነገርኩህ በኋላ?»

«አሁንም እወድሻለሁ::»

«አውቃለሁ:: እኔም እወድሀለሁ::»

ከፍለን ስንወጣ የቦዬ ፈገግታ ሸኘን — ፍቅራችንን ወዶልናል



@BOOKALEM

# አስራ አንድ

# የሞት ጥሪ
# እማንዳ

ወደ ኢክስ ልንመለስ ሶስት ቀን ሲቀረን ሲልቪ ቤቶቿን ለመሰናበት ሄደች:: ጊዜው ንፁህ ብርሀንና ለስላሳ ሙቀት በዝግተኛው ነፋስ የሚንሳፈፉበት ውብ የፀደይ ቀን ነበር:: የፓሪስ ሴቶች ወደ ሰፊው ስመ ጥሩ ጎዳና ወደ ሻንዜሊዜ እንደሚንሸራሸሩ ታወቀኝ:: በሜትሮ ወደዚያው ሄድኩ

ሱቆቹ የፀደይ ሞድ ልብሶቻቸውን መስኮቶቻቸው ላይ ዘርግተዋል፣ ካፌዎቹ ጠረጴዛ ወንበሮቻቸውን ወደ መንገዱ አውጥተው ከአብዛኛዎቹ ጠረጴዛዎች በላይ በልዩ ልዩ ቀለማት ያጌጡ ሰፋፊ ጃንጥላዎችን ዘርግተዋል:: ሰዉ ይንጋጋል፣ ትራፊኩ ይፈሳል:: አንዱ ካፌ ውጪ[1] ሰዉ የሚተላለፍበት ቦታ አንዲት ትንሽ ጠረጴዛ አጠገብ ተቀመጥኩ

በፀደይ ቀን ሻንዜሊዜ ጎዳናው ዳር ቁጭ ብሎ ቢራ እየጠጡ አላፊ አግዳሚውን ፈረንሳዊት እና የስንትና ስንት ሌላ አገር ሴት መቃኘት:: ከዚህ የበለጠ ምን ደስታ ይገኛል? ሴቶቹ የፀደዩን ብርሀንና ነፋስ ለመቀበል የፈነዱ አበባዎች ይመስላሉ:: የወፍ ቋንቋ መሳይ ፈረንሳይኛቸውን በልዝብ ድምፃቸው እንደዘፈን እየተቀባበሉ፣ የተነጠፈውን ድንጋይ በረዥም ተረከዛቸው ኳ! ኳ! እያረጉ፣ ውብ ባሊያቸውን እያወዛወዙ ወደላይና ወደታች ይተላለፋሉ:: አይኔ አብሯቸው ይመላለሳል

ቀስ እያለ አይኔ ሰከረ:: ውበት በዛበት:: የአንዷን ኩሩ አረማመድ ሳይደንቅ ትንሽ እንደ ተራመደችልኝ፣ ህዝቡ መሀል ገብታ ትጠፋለች:: የሌላዋ ግሩም ቅርፅ አይኔን ይስባል፣ ከዳሌዋና ከወገቧ



@BOOKALEM

ከተረሳ፣ የቱን እንደምመርጥ ግን ሳይወሰን ህዝቡ ይመጣታል:: ይቀ ... ይመለሰኛል:: የምትቀጥለዋ ወጣት ነች የእንጂ ወገርና እንግት ልቤን ... በጸሌዋ እንግስታሌ ላይ ቀብቶ ያለ ቤሪ ሰብሳ ስታልና እያሌ ... ህዝብ ይመጣታል:: ሌላ ወብት ሌላ ይተነሳል:: እሷንም የሚንጋጋው ህዝብ ይለዩል:: እንደዚህ ሰል እያሌ በሲ ሌት ላይ ተጭኖ ሲሄድ እያሌን ይለዩል:: በኩል ሲመጣ ነው ወደ ሳሱ ሲሄዱ ሌትዋል።

የቢራቱን ሃሳብ ከፍሎ ወደ ሌትቀቀዋ ከጋላ ሲያዩዋት ምንም የእንጂ ወገር እያሌን ማረከው:: ሌትቀቀዋ ከጋላ ሲያዩዋት ምን እትል:: ኸረ ቸንዚሊዜ በላየሁዋት ነው እንጂ፣ ሌላ ቦታ ባያት እትል:: እጠር ያለች ወጣት ናት:: ቀይ ቦርሳ እንዳ በጣም ደስ ትላለች:: እጠር ያለች ወጣት ናት:: ቀይ ቦርሳ እንጨ ቤዋለች:: ገላዋን እቀፍ አርጎ የሚሸፍን፣ ነጭ ባለ ሸንሽን የሀገ ቀሚስ ለብሳለች:: ወገቧን ስራ ቀይ ቀበቶ እትሮጋታል:: ቀይ ባለረዥም ተረከዝ ጫማ የረገጠችው እግሮቿ ወፈር ብለው ተለማቸው ወደ በሩ የሚያያላ ነው:: ወፍራም ጸሊዋ ከትከሻ ልብ ስር ሲወዛወዝ ያስታውቃል፤ ምጥቀት ይቀሰቅሳል:: ግን ዋናው ውበቷ ወገሬ ነው:: ይሄ ንፁህ ነጭ ወገሬ ወይኗላዋ ትከሻዋ ድረስ ተለቀ ወሀዬ ውስጥ ይብለጨለጫል:: የሬጋ የጨለረቃ ብርሀን የሚመስል ንፁህ ወገር ከዚህ በፊት የት ነው ያየሁት? የት? መቼ? የት?

ሌትቀቀዋ ወደ ቀኝ በኩል ተጠምዛ ከቸንዚሊዜ ወጥታ እንድ ሌላ መንገድ ይዛ ወደላይ በኩል መራመድ ጀመረች:: ለምን ተከተልኳት? አላውቅም

መንገዱ ዳር ብዙ መኪናዎች ቆመው ነበር፤ እሷ እንድ ፖርሽ ጃጉዋር ስፖርት መኪና ውስጥ ገባች:: እሌፌያት ወደ ላይ በሎ መንገዱን ሰቀቀል፤

"Hi there!" አለችኝ:: ባለሁበት ቆምኩ:: የአማንዳ ድምፅ ጆሮዬን ማመን አልቻልኩም:: ግን ወገሩም የሷ ነው:: እውነ እስታወስኩ:: ወይሷ ቦርኩ:: ከመኪናዋ ወጥታ እየሮጠች መጣችና ተጠመጠመችብኝ:: ሽቶዋ በጣም ደስ ይላል::

«አማንዳ ነሽ እውነት?»

«አዎን»

«ታዲያ ያ ሁሉ ሙሚ የት ሄደ?»

«ሸጥኩት» አለችና ትንሽ ከኔ ራቅ ብላ እንድ ሁለት ሁ እየተሽከረከረች «ምን ይመስልሀል?» አለችኝ



@BOOKALEM

«ተአምር ነው:: በአይኔ ባላይሽ ኖሮ አላምንም ነበር»

"Thank you"

«እውነቴን ነው:: አሁን'ኮ ማን እንደሆንሽ ሳላውቅ ከኋላሽ በኩል ሳይሽ የማናት ቆንጆ ፈረንሳይ? እያልኩ ስከተልሽ ነበር»

«እንዲት ሴት ምን መስማት 'ንደምትወድ ብጥር አርገህ ታውቃለህ መቸስ::»

«እውነቴን ነው እሬ!»

«ደስ ካልኩህ አብረኸኝ ምሳ ብላ 'ስቲ»

«ጥሩ»

ወደ ቆንጆ ጥቁር መኪናዋ ገባን:: አማንዳ ድሮ ቁምቡርስ ነበረች፣ አሁን ግን ቢራቢሮ ሆናለች:: ትርፍ አገጯ ጠፍቷል፡ አንገቷ ዙርያ ተጠፍጥፎ የነበረው ሥጋ ረግፏል:: ፊቷ ሙሉ ነው፡ ግን ደስ ይላል:: ከንፈሮቿ ሮዝ ብጤ ቀለም ተቀብተው፣ ሰማያዊ አይኖቿ በጥንቃቄ ተኩለው፡ ቀይ ጉትቻዋ ከነጭ ፀጉሯ አጠገብ ሲታይ በረዶ አጠገብ የተንጠለጠለ እንጆሪ ይመስላል:: ከአስቀያሚዎቹ ሴቶች ማህበር ወጥታ፣ ቆንጆዎቹ ማህበር ገብታለች:: ድምፅዋ ሳይቀር ተለውጧል:: ድሮ አልቃሻ ብጤ ነበር፡ አሁን ግን ልስልስ ያለ ቆንጆ ድምፅ ነው

«ንገሪኝ 'ስቲ:: ምን እንደዚህ ለወጠሽ?» አልኳት

«አንድ ሰካራም» አለችኝ

«ምን?»

«ሉን ተሰናብቼ ወደ አገሬ ስሄድ፡ አሮፕላኑ ውስጥ አንድ ሰውዬ አጠገብ ተቀመጥኩ:: ሰውየው ሰክሮ ነበር:: ሉ ትዝ እያለኝ ለብቻዬ ሳለቅስ

«'ምን ያስለቅስሻል? የወደድሽው ሰውዬ እምቢ አለሽ? ደግ አረገ! በዚህ አድሜሽ ምን እንዲህ አወፈረሽ?' አለኝና ያኔውኑ ረሳኝ፣ እንቅልፍ ወሰደው

ለመጀመርያ «እኔ ግን ቃላቱን እስከ መቼም አልረሳቸውም:: ይኸውም፣ ጅል ሆኜ ነው 'ንጂ፣ ጊዜ አንድ እውነት ተገለፀልኝ:: ቁንጅና እውርጂ መዞር የለብኝም:: ቁንነቴን ውፍረቴን እንደ ቁንነት ተሸክሜ



@BOOKALEM

ሊቀበለው እችላለሁ:: ሊቀበለው ቆረጥኩ:: ሳን ፍራንሲስኮ ገጂ፣ ሙያቸው ከብዶት መቀነስ ከሆነ ሰዎች ጋር አራት ወር ሙሉ ሰራሁ:: ውጤቱን አንተም አመሰገንከልኝ» አለች:: ሳቋ ውስጥ መማትንትና የህይወት ድል አድራጊነት ይጨፍራል!

ባለ አራት ኮከብ (ማለት ከሁሉ ይበልጥ ምቾት ያለበት) ሆቴሏ ወሰደችኝ:: ከፍያ ሆነ በቴሌፎን ሁለት ምሳ አዘዘች:: አሁንም አስደነቀችኝ:: ኢትዮ ሳውቃት ፈረንሳይኛውን በአስቀያሚ የአሜሪካን ቅላጼ ነበር የምታዜመው፤ አሁን ግን የፓሪስ ፈረንሳይኛ ሲሆን ምንም አልቀረው:: እያየችኝ ስትስቅ

«እንደዚህ የሚያስደስት ለውጥ አይቼ አላውቅም»

"Thank you, you're really sweet" አለችኝ

ከምሳ በኋላ «ፓሪስ ምን ትሰራለህ?» አለችኝ:: ነገርኳት::

«አንቺስ?» አልኳት::

«ከኒው ዮርክ የዛሬ ሳምንት መጣሁ:: ይሄ ጃጉዋር ከእንግላንድ እስኪመጣልኝ ነበር 'ምጠብቀው:: ነገ ወይም ተነገ ወድያ ወደ ኢትዮ መሄዴ ነው:: . . . ሉን ማግኘት አለብኝ:: ደህና ነው? አሁንስ የሚፈልገኝ ይመስልሀል? ለጊዜው ሴት አልያዘ 'ንደሆን ጥርጥር የለውም:: ይዞ 'ንደሆነ፣ ነጥቄ መውሰድ ይኖርብኛል::»

«ምን?»

«ነጥቄ 'ወስደዋለሁ:: ምነው ገረመህ? የድሮዋ አማንዳ መሰልሁህለሁ 'ንዴ? ተለውጫለሁ'ኮ:: ተዘጋጅቼ ነው የመጣሁት:: ቢያንስ አርባ የሳይኮሎጂ መፅሀፍ አንብቤያለሁ:: ደሞ ሉን አውቀዋለሁ:: ግብረ ስጋ በጣም ይወዳል:: ለሱም ተዘጋጅቻለሁ::»

«እንዴት?»

«ለሌላ ሰው ቢሆን ይህን አልነግረውም:: አንተ ግን ትወደኛለህ:: ወፍራም ሳለሁም ትወደኝ ነበር:: ለኔ ግድ ነበረህ:: የተጎዳሁ ሰው ሆኜ ሰላየኸኝ ደሞ በጣም ደስ ብሎሀል:: ይሄ ለኔ ትልቅ ስጦታ ነው:: በጣም ተወዳጅ ነህ:: እና ለምን እንደሆነ ሳላውቅ በጣም አምንሀለሁ:: ለምንድነው 'ማምንህ?»

«ምክንያት የለውም፣ ምክንያት አያስፈልገውም::»

@BOOKALEM

«እውነትክን ነው:: ብለህ ነህ:: እውነቱን ነው፣ ብለህ ነህ:: አገሬ ሆኜ ብዙ ሳስብህ ነበር:: ኢክስ ሆኘንም እወድህ ነበር፣ ግን ያኔ ስሜቱን ለመናገር እፈራ ነበር:: ድፍረት መስሉ ይታየኝ ነበር:: አሁን ግን ሳልፈራ ስሜቴን ልናገር እችላለሁ:: ተለውጫለሁ:: ጤነኛ ሆኛለሁ:: ስለዚህ ልንገርህ:: በጣም ነው 'ምወድህ:: ግምህን ስትሳጭ በጣም ታምራለህ:: ቆንጆ ስለሆንክና ስለምወድህ ልስምህ እፈልጋለሁ:: ትፈቅድልኛለህ?» አለችና ፊት ለፊቴ ከተቀመጠችበት ሶፋ ተነስታ በዝግታ እፈ ላይ ስማኝ ተመልሳ ቁጭ አለች:: አይኖቼኝ ሳቀች

ግራ ስለገባኝ «አሁን እታረሳሺኝ:: ለግብረ ስጋ ተዘጋጅቻለሁ ስትዪ ምን ማለትሽ ነው?» አልኳት

«ቀላል ነው:: ሳላስበው ከአንድ የሰላሳ ሰባት አመት ህንድ ጋር ገጠምኩ:: ፒ-ኤች-ዲ ያለው ሊቅ ነው:: ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ጎብኚ መምህር ነው:: እሱ ስለ ግብረ ስጋ ያስተማረኝን ብነግርህ ልታምነኝ አትችልም:: ልነግርህም አልችልም:: ቃላቱን አላውቀውም:: ግን ስራውን በሀይል እችልበታለሁ:: ፕሮፌሰሩ ገና ገና ቀሽም ነሽ ይለኛል:: እውነቱን ነው፣ ከህንዶቹ ጋር ስተያይ ቀሽም ነኝ:: ግን ሱን ሄጄ አንድ ሌሊት ከኔ ጋር ሳሳድረው እብድ እንደሚሆንልኝ እርግጠኛ ነኝ::»

«ከዚያስ?»

«ከዚያ 'ንጃ:: ሉ ከፈለገ አሜሪካ 'ንሄዳለን:: ካልፈለገም ኢክስ እንቀራለን:: ወይ ፓሪስ እንመጣለን:: ካንድ ሶስት አመት በኋላ፣ ሀሳቤን ያልለወጥኩ 'ንደሆን፣ እንጋባለን::»

«እምቢ አላገባሽም፣ ያለሽ 'ንደሆንስ?»

«እሱንም አስቤበታለሁ:: ተዘጋጅቻለሁ::»

አየሁዋት:: ትችላለች:: የፈለገችውን ለማግኘት ትችላለች

በሶስተኛው ቀን አማንዳ፣ ሲልቪ፣ እኔ በአማንዳ ጃጉዋር ወደ ግርስይ አመራን:: ኢክስ ስንደርስ እርብ ማታ ነበር:: ሉልሰገድ ከጆምቪድ ጋር ሞንቴ ካርሎ ሄዷል:: እንግዲህ አማንዳ እስከ ሰኞ ሟት መታገስ ይኖርባታል::



@BOOKALEM

እኔ ፓሪስ ሄጄ ቅናት ውስጥ ስንፈላሰስ ኢክስ ውስጥ ምን ምን ተደረገ? ከባህራም፣ ከተካና ከኒኮል የሰማሁትን ሳገጣጥመው እንደ ‹ሚከተለው ሆነ፡-

አንድ ማክሰኞ ከሰአት በኋላ (ኒኮል ከፋሺስቶቹ ተደብቃ ሰንብታ ከተመለሰች በኋላ) ባህራም የሚሰራበት ትምህርት ቤት ዲሬክተር ቢሮው አስገባውና፣ «ከስራዎ ላሰናብትዎ ነው» አለው። ባህራም «ምነው?» ቢለው «በስራዎ በጣም ተደስቼ ነበር፤ ግን የጋርደን ከተማ የፖሊስ ሹም እንዳሰናብትዎ አዘዘኝ» አለው

«እዚህ ውስጥ የፖሊስ ሹም ምን አገባው?» አለ ባህራም

«አዩ፣ እርስዎ የውጭ አገር ዜጋ እንደመሆንዎ መጠን፣ እዚህ አገር ስራ ለመያዝ ልዩ ፈቃድ ያስፈልግዎታል። እስካሁን ያለ ፈቃድ ወረቀት ስለሰሩ እርስዎም እኔም ልንቀጣ እንችል ነበር። ግን የፖሊስ ሹሙ ጓደኛዬ ነው።»

«የስራ ፈቃድ እንደሌለኝ እንዴት አወቀ?» አለ ባህራም

«ሰው ነግሮት። ይመስለኛል፣ ኢክስ ውስጥ ጠላቶች አሉዎት።»

ባህራም ገባው። ፋሺስቶቹ መሆን አለባቸው

«እሺ ደመወዜን ይስጡኝ» አለ። የሁለት ወር ከሶስት ሳምንት ደመወዝ አለው። ዲሬክተሩ ገንዘቡን ከቢሮው ጠረጴዛ ኪስ አውጥቶ አቀበለው። ባህራም ገንዘቡን ቆጠረ። የተዋዋሉት ገንዘብ ሲሶ ነው።

«ሌላውስ?» አለ ባህራም

ዲሬክተሩ ከጠረጴዛው ኋላ እንደተቀመጠ፣ ትዝብት ባለ ክፉ ድምፅ

«የምን ሌላ?» አለው

«ይሄ ሙሉ ደመወዜ አይደለም። አንድ ሶስተኛው ነው።»

«ማን ነው ያለው? ደመወዝህን ሰጥቼሃለሁ። ከፈለግክ ውሰደው፣ ካልፈለግክ ተወው። ድሮ አልጄርያ ሳለሁ አረቦቹን ከዚህ ባነሰ ደመወዝ ነበር የምናሰራችሁ»

ባህራም ረጋ ባለ ድምፅ «አረቦቹን ቅኝ ግዛት ስላደረጋችኋቸው በካልቾ ብለው ካገራቸው አስወጧችሁ። የሆነ ሆኖ፣ እኔ አረብ አይደለሁም። የኢራን ሰው ነኝ። የኢራን ሰው ሰውን አይነካም፤ ግን



@BOOKALEM

ማንም ሰው የኢራንን ሰው አይበድልም:: ስለዚህ—» አሉና፣ ድንገት በጠረጴዛው ተንጠራርቶ ሰውዬውን አነቀው:: ሰውየው ራሱን ለማስጣል አልሞከረም:: ባህራም ሲያፈጥበት፣ በደነገጠ ድምፅ

«አይነቁኝ:: እስም በሽታ አለብኝ» አለው

ባህራም ለቀቀው:: ሰውዬው ከጠረጴዛው ኪስ ሌላ ገንዘብ አውጥቶ ባህራም ፊት ቆጠረው:: ባህራም ገንዘቡን አንስቶ ኪሱ ከተተ:: ሰውየውን አየው:: ወምበሩ ላይ ተቀምጦ ወደ ላይ ይመለከተዋል:: ባህራም አፉ ውስጥ ብዙ ምራቅ ሰበሰበ:: ሰውዬው ፊት ላይ ተፋው:: ሰውዬው መሀረብ ሊያወጣ እጁን ወደ ኪሱ ሲከት ባህራም ትቶት ወጣ

ከዚያ እየጨሰ ወደ ኢክስ የሚወስደውን አቶቡስ ተሳፈረ

ያን ቀን ተካን ባያገኘው ጥሩ ነበር

ተካ በበኩሉ ከአንድ ወር በላይ ሲበሳጭ ሰንብቷል:: ጀርመንዋ ልጅ እየባሰባት ሄደ:: በፊት 'ንኳ ከዚያ ካገሯ ልጅ ጋር 'ምትወጣው አልፎ አልፎ ነበር:: አሁን ግን ቢያንስ በሳምንት አራት ማታ ከሱ ጋር ነች:: ተካ 'ንግዲህ ቢበዛ በሳምንት ሁለት ማታ ቢያገኛት ነው:: ለዚያውም ሁለቱም ማታ የንትርክ ማታ ነው:: ሁልጊዜ ስለጀርመኑ ይጨቃጨቃሉ

«ከሱ ጋር ምን ትሰሪያለሽ?»

«በራሴ ህይወት ምን አገባህ?»

«አብራችሁ ትተኛላችሁ?»

«ምን አገባህ?»

በጥፊ እየመታት «ንገሪኝ! ይተኛሻል?» ይላታል

በንዴት «እዎን ይተኛኛል! በል ምን ትሆን!?» ትለዋለች

እንደገና እንድ ሁለት ጥፊ ያቀምሳትና፣ በግድ ታግሎ ይተኛታል

አንድ ማታ ግን፣ ዝግ ባለ ድምፅ

«ልሰናበትህ ነው የመጣሁት» አለችው

ልቡ እየፈራ «ምነው? የት ልትሄጂ ነው?» አላት



@BOOKALEM

«የትም አልሄድም:: እስቲ ዛሬ 'ንኳ ሳንሞላ 'ንደር:: የመጨረሻችን ሌሊት ነው:: ሄርማን ሲያገባኝ ቆርጧል:: እሺም እሺ ብየዋለሁ::»

በሰላም አደሩ:: ከዚያ በኋላ አነጋግሬው አላውቅም

ጀርመንዋ ያስለመደችው ሲቀርበት ጊዜ ያንዣብበው ጀመር:: በቶሎ ሴት ማግኘት እንዳለበት ገባው:: ቢመለከት፣ ኒኮል አለች:: መልኳ አጅግም ነው፣ ወንድ በብዙ ልትስብ አትችልም:: ለዚያ አይደል ባህራምን በገንዘቧ 'ምትኖረው? ግን አሁን ባህራም አብዛኛውን ጊዜ ከኢኒክስ ውጪ ነው:: ስለዚህ ሌላ ወንድ መፈለጓ አይቀርም:: እንድያውም ይህን ጊዜ እሱ (ተተካ) ሴት ያስፈለገውን ያህል እሷም ወንድ መፈለጓ አይቀርም:: ሌላ ሴት እስኪያገኝ ማቆያ ትሆነዋለች:: እሷም በበኩሏ ባህራም እስኪመጣላት ማቆያ ይሆናታል:: የጋራ ጥቅም!

ማክሰኞ ከምሳ በኋላ ቤቷ ሄደ.

ቡና አፈላችለትና «ዛሬስ ምን ሰማህና ልትጎበኘኝ መጣህ?» አለችው

«አንድ ነገር አስቤ ነው» አላት

«ምን?»

«እኔንና አንቺን የሚጠቅም ሀሳብ ነው»

«ንገረኝ»

«ደስ ትይኛለሽ:: ስለዚህ ባህራም በሌለበት ጊዜ እዚህ ብመጣ ጥሩ ይመስለኛል»

«መጥተህስ?»

«እናወራለን፣ እንጫወታለን» እያለ እጁን እጇ ላይ አስቀመጠ

እጇን እያሸሸች «ለኔ 'ሚሆን ጨዋታ ያለህ አይመስለኝም» አለችው

«አለኝ»

«የለህም»

«ከባህራም በምን እንሳለሁ?»

@BOOKALEM

«በሁሉም ነገር»

«ምን ነሽ:: ይልቅ አንድ አቃጣሪ አረብ እየከፈለኝሽው ከሚተኛሽ፣ እኔ ያለ ገንዘብ ብተኛሽ አይሻልሽም?» አላት

ፊቷ በቁጣ እሳት መሰለ፣ ግን ድምፅዋ አልተለወጠም

«ወንድ ከሆንክ ሂድና ባህሪምን አቃጣሪ አረብ ነህ በለው:: እኔ ወንድ ስላልሆንኩ የሚገባህን ቅጣት ልሰጥህ አልችልም:: ግን ቆሻሻ ነህ:: እንጎልህም ቆሻሻ ነው፣ ሰውነትህም ቆሻሻ ነው:: እግርህ ይገማል፣ እፍህ ከራስ እስኩል ይቆንሳል:: አሁን ቤቴ ሳይገማ ተነስና ሂድልኝ» አለችው

ተነሳ:: ቁጭ እንዳለች ሳታስበው በጥፊ መታት:: ከወምበሯ ተከንበለች:: ከወለሉ ላይ በፀጉሯ ጎትቶ አነሳትና እንገቷን ሳማት:: ስትፍጨረጨር እጇን ጠምዞ ወደ አልጋዋ ወሰዳት:: አልጋው ላይ ጣላትና አንድ ጡቷን ጭብጦ እርጎ ያዘ:: መፍጨርጨሯን ተወች:: በአፏ ብቻ

«ተወኝ! ብትተወኝ ይሻልሃል!» እያለች ትርከራለች

እጁን ሰደደና ሙታንቲዋን ሊያወልቅ ሲል እንደገና መፍጨርጨር ጀመረች:: ጡቷን የባሰውን በሀይል ጨበጠው:: ፀጥ አለች:: ሙታንቲዋን አወለቀው:: እምባዋ ይወርድ ጀመር:: ቁጣዋ ወደ ልመና ተለወጠ

«እባክህ ተወኝ:: ምን አረግኩህ?»

ልመናዋን ከምንም አልቆጠረውም:: ጡቷን ጨብጦ 'ንደያዘ

የሱሪውን ቀበቶ ፈታ

እሁንም እምባዋ እየወረደ «እባክህን ተወኝ:: እርጉዝ ነኝ::

የሁለት ወር ነብሰ ጡር ነኝ» አለችው

የሱሪውን ቁልፍ ይፈታ የነበረው እጁ ባለበት ደረቀ:: ጡቷን

ይዞ የነበረው እጁ ለቀቃት:: ሱሪውን መልሶ ቆለፈ:: ትቷት ወጣ

እልጋዋ ላይ ተደፍታ ስታለቅስ ባህሪም ደረሰ:: ኪጋርደን

እየበሸቀ መምጣቱ ነበር:: በጥፊ ተመትቶ የቀላውን ፊቷን አየ::

እያለቀሰች የሆነውን ሁሉ ነገረችው

ተናዶ ተነስቶ ፍለጋ ወጣ:: ኒኮል ተከተለችው:: ምናልባት



@BOOKALEM

አደገኛ ነገር እንዳይሰራ ፈርታለች፡፡ እሱ በረንዳው ሲራመድ እሷ አልደረሰበት ብላ ከኋላው ክፍት ሰኡሱነ ስትል፤ ኢክሰን አቋርጠው ሲቴ አጠገብ ሲደርሱ — ባህራም ተካን አየው፡፡ ጠራው፡፡ ተካ ቆመ፡፡ አንድ ትልቅ ዛፍ ስር ነበር፡፡ ባህራም ደረሰና ቃል ሳይናገር በጥፊ መታው፡፡ ተካ በቡጢ ሰነዘረበት፡፡ ባህራም ገምበስ ብሎ አመለጠና፣ በፍጥነት የተካን እጅ ይዞ ጠምዞ በሀይል ወረወረው፡፡ ከዛፉ ጋር አጋጨው፡፡ ከዚያ በኋላ ተካ ሊከላከል አልቻለም፤ እንደሉ የርቢታል፤ ባህራም እጅ ውስጥ እንደ ህፃን ሆነ፡፡ ባህራም ጭንቅላቱን ይዞ ፊቱን ከዛፉ ጋር ደጋግሞ ደጋግሞ አጋጨው፡፡ የተካ ፊት በደም ተበከለ፡፡ ኒኮል ደርሳ ባታስጥለው ኖሮ ምናልባት ይገድለው ነበር

ተካ አልሞተም፡፡ ብቻ ሳየው ግራ እጁ በፋሻ ተጠምጥሞ፤ ደረቱ ላይ ታጥፎ፤ ከአንገቱ በፋሻ ተንጠልጥሏል፡፡ ፊቱን ሰል እንጂ የላይኛ የፊት ጥርሱ ወልቋል

ከሁለት ሳምንት በኋላ ወርቅ ጥርስ አስተከለ

ባህራምን «እውነት ኒኮል አርግዛለች?» አልኩት

«አዎን» አለኝ «እንግዲህ ታስርከኚ ማለት ነው፡፡»

ዝም አልኩ፡፡ ምን ልበል?

«ያ ሁሉ የሬቮሉሽን ወሬ ከንቱ ቀረ፡፡ ኒኮል ካረገዘች ሁለት ወር አለፈ፡፡ ታስርከኚ፡፡»

«ለምን አላስወረዳችሁትም?»

«እንዴት አርገን ልጃችንን እንገድላለን?» አለኝ

ለዚህ መልስ አልነበረኝም፡፡ ዝም አልኩ፡፡ ማን ያውቃል? ምናልባት የተረገዘው ልጅ የባህራም . . .

* * *

አማንዳ ወሬውን ስትሰማ አብሬያት ነበርኩ፡፡ ሆቴል ክፍሏ ውስጥ ቁጭ ብለን ስናወራ በሩ ተንኳኳ

"Come in... I mean, Entrez!" አለች እየሳቀች

ተካ እጁን እንደጠመጠመ ገባ፡፡ አየነው



@BOOKALEM

«ሰምተሀል?» አለኝ በአማርኛ:: ሸራፋው ክፍት ከደን ይላል

«ምን?» አልኩት

«ሞንቴ ካርሎ ሆቴል ውስጥ ጆምቪድና ያገራችን ልጅ ሞተው ተገኙ::»

"What is it? What is it?" አለች እማንዳ

«እርግጠኛ ነህ?» አልኩት

"What is it?"

«እርግጠኛ ነኝ:: ፖሊሶቹ ‹እንደሚሉት› ጆምቪድ መጀመርያ የኛን ልጅ በሽጉጥ ግምባሩን ብሎ ገደለውና —»

"What is it?"

«— ቀጥሎ የራሱን እንጎል ብትንትን አደረገ:: አሁን ሬሳዎቻቸው ወደየአገራቸው ሊላኩ ነው::»

እማንዳ ተነሳችና (እኔ ለካ ሳይታወቀኝ ተነስቻለሁ) ትከሻዬን እየነቀነቀች፣ በእንግሊዝኛ

«እባክህን ንገረኝ:: ምንድነው?» አለችኝ

«አዝናለሁ» አልኳት

«ሉ ነው?» አለች:: በሀይል ፈርታለች «ንገረኝ፣ ሉ ነው?» በጭንቅላቴ አዎን አልኳት

«ምን ሆነ? ምን ሆነ? ንገረኝ» አለችኝ

«ሊታገኚው ባትሞክሪ ይሻላል:: ወደ ፓሪስ ተመለሺ::»

«ለምን? ለምን? ምን ሆኗል?»

«ሊታገኚው አትችይም»

በሀይል እየነቀነቀችኝ፣ በጠንካራ ድምፅ

«ንገረኝ!» አለችኝ

«ከንግዲህ ማንም ሊያገኘው አይችልም» አልኳት

በሹክሹክታ መሳይ ድምፅ፣ «ሞቷል?» አለችኝ

ዝም አልኳት:: ወደ ተካ ዞረችና፣ በተዘረጋ እጇ በሩን



@BOOKALEM

እያመለከተች

«Get out!" ብላ ጮኸችበት

ባማርኛ «ቂንጥራም!» ብሏት ወጣ:: በሩን ዘጋ::

ረጋ ባለ ሁኔታ ቦርሳዋን ከሶፋው ላይ አነሳች፣ ወደ በሩ መራመድ ጀመረች:: ዘልዬ ቀደምኳትና በሩጋ ቆምኩ::

«አሳልፊኝ» አለችኝ:: አታለቅስም:: ያዘነችም አትመስልም:: አይኖቿ ፍዝዝ ብለው፣ በህልም ውስጥ ያለች ትመስላለች

«የት ትሂጂ?» አልኳት

«ሂጂ ሉን እየዋለሁ»

ሁለት እጄን ትከሻዋ ላይ ጫንኩና

«እንድ ታዪው አይፈልግም:: እንደድሮው ሲስቅ ሲጫወት እንድ ታስታውሺው ነው 'ሚፈልገው» አልኳት

«ሲስቅ ሲጫወት! ሲስቅ ሲጫወት!» አለችና ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች:: ትከሻዋ ላይ ባሉት እጆቼ ወደኔ ሳብ አደረግኳት:: ራሷን ደረቴ ላይ አንተራሰችና ለቅሶዋን ቀጠለች

አልቅሳ ስትጨርስ ሀኪም ጠራሁላት:: የሚያስተኛ መርፌ ወጋትና ሄደ

«አጠገብሽ ብሆን እወድ ነበር» አልኳት

ክፍሉ ውስጥ አንድ ትንሽ አልጋ አስነጠፈችልኝ:: ተኛች:: ሲመሽ ወጣ ብዬ እራት በልቼ ተመለስኩ:: ተኝታለች:: ልብወለድ መፅሀፍ ሳነብ አምሽቼ ተኛሁ::

ጧት ተነሳች:: ገላዋን ታጠበች:: ረዥም ስስ ሀምራዊ የሌሊት ልብሷ ላይ ከፎጣ የተሰራ ወይን ጠጅ የቤት ካፖርት ደርባለች:: ብርሀን መሳይ ፀጉሯ በሚያስደስት አኳኋን ተሞነጫጭሯል:: አብረን ቁርስ በላን:: ሉልሰገድን እንዳናነሳ ፈርተን ስለሆሊውድ ማውራት ጀመርን

ቁርስ በልተን ስናበቃ፣ እኔ ሶፋው ላይ ቁጭ እንዳልኩ ተነሳችና ከፊቴ ቆመች:: በዝግታ የፎጣ ካፖርቷን መቀነት ፈታች:: ካፖርቱን አውልቃ ለቀቀችው:: ምንጣፉ ላይ እግሮቿ ዙርያ ተጠ ቀለለ:: ሀምራዊ ስስ የሌሊት ልብሷ ድምቡሺ ገላዋን እንደ ደመና



@BOOKALEM

ከሆታል 'ንጂ አልሸፈነውም:: ጡት መያዣና ሙታንቲ አላደረገችም:: አቤት ወርቃማ ጭገሯ ማማሩ! እጇን ዘርግታ ፊቴን ከተቀመጥኩበት ወደፊት ጎንበስ በማለት ምንጣፉ ላይ በዓይኔ ፊቴን ለስላሳ ሆዷ ላይ አሳረፍኩ፤ እጆቼን ወፍራም ዳሌዋ ዙርያ ጠመጠምኩ:: ራሴን እቅፍ አደረገችኝ:: እንደዚህ ሆነን ረዥም ጊዜ ቆየን:: ምን እንደፈለገች ስላልገባኝ፣ ምንም ባላደርግ ይሻላል በማለት ባለሁበት ረጋሁ:: በኋላ፣ ከተምበረከክሁበት አስነሳችኝ:: ወደ አልጋዋ ወሰደችኝ:: መኖሩን ሰምቼው የማላውቅ አዲስ የማብሬ ስጋ አገር አሳየችኝ

ይሄ ሁሉ ሲሆን፣ ያ ትርጉሙ የማይታወቅ ፈገግታ ፊቷ ላይ ብቅ ጥፍት ይል ነበር:: ምሳ ከበላን በኋላ ሻንጣዋን መኪናዋ ኋላ ወምበር ላይ አስቀመጥኩት:: አብሬያት ከኢክስ ወጣሁ:: ወደ አቪኞን የሚወስደውን መንገድ እንደያዘች መኪናዋን አቆመች:: አየችኝ:: ሰማያዊ አይኖቿ እምባ አቀረሩ:: አንገቴን ሰባ እፌ ላይ ሳመችኝ:: መሀረቤን እያቀበልኳት

«አሁን የት ነው 'ምትሄጂው?» አልኳት

«እኔ 'ንጃ:: ብቻ ከ'ንግዲህ ኢክስን ማየት አልፈልግም» አለች እንባዋን እየጠረገች

ከአጭር ዝምታ በኋላ «አንድ ነገር ልጠይቅሽ እፈልግ ነበር» አልኳት:: ማን እመነታሁ::

«ገብቶኛል» አለችኝ «ሟት ለምን እንደዚያ እንደሆንኩ ልትጠይቀኝ ነው 'ምትፈልገው?»

«አዎን»

ሳቅ እያለች «አንተስ ለምን እሺ አልከኝ?» አለችኝ

«እኔማ ሻንዜሊዜ ካየሁሽና ሌላ ሴት እየመሰልሽኝ ከተዋወቅን ጀምሮ እምረሽኝ ነበር::»

«እንደሱ ቢሆን ኖሮ ፓሪስ የተገናኘን ጊዜ በጣም ደመች አልነበረም? ይልቅ እውነቱን ንገረኝ::»

«እኔ ለራሴ በጣም ደስ እንዳለኝ አውቃለሁ'ንጂ፣ ምንም አልገባኝም:: አንቺ ንገሪኝ 'ስቲ»



@BOOKALEM

ያ ምስጢራዊ ፈገግታ ፊቷ ላይ ብቅ አለ

«እውነቱን ለመናገር የሚበቃ ቃላት የለኝም» አለችኝ «ግን እንዲህ ልበልህ:: ሞት መጥቶ በግድ ካልወሰደኝ በስተቀር፣ እውስጤ ገብቶ ስፍራ እንዲይዝ አልፈቅድለትም:: መቸም ቢሆን፡ ጥልቅ ሀዘን ውስጥም ብሆን፡ ህይወት ሞትን ድል እንዲነሳው እፈልጋለሁ:: ሳት ሳይታወቅህ፣ እውስጤ ገብተህ ሞትን እንዳባርረው አግዘኸኛል:: ምነው በመገረም ታየኛለህ? ተለውጫለሁ አላልኩህም ʼንዴ?»

«አሁንማ ገባኝ:: ውስጥሽ ከፀጉርሽ ይበልጥ ውብ ሆኗል»

አይኖቿ እንደገና እምባ ሞሉ:: እንደገና በአንገቴ ስባ በረዥሙ ሳመችኝ

«ተጠንቀቀሽ ʼንጂ፣ እሺ?» አልኳት

ሳቅ አለች «አትስጋ:: አገርህ ከመሄድህ በፊት ፓሪስ ብቅ ብለህ ታየኝ የለ?»

«እመጣለሁ:: እስከዚያ አድራሻሽን ላኪልኝ::»

«ትፅፍልኛለህ?»

«በሳምንት በሳምንት::»

«ጥሩ ልጅ ነህ:: በጣም ጥሩ ልጅ ነህ::»

«ላንቺ ብዬ አይደለም:: ለራሴ ብዬ ነው:: እንዳንቺ ያለች ብርቱ ውብ ሴት ካየሁ አያስችለኝም::»

እንደገና በአንገቴ ስባ አፌ ላይ በሀይል ሳመችኝ:: ከመኪናዋ ወረድኩ:: ሞተሩን ቀሰቀሰች:: ጭልጥ አለች:: እስክትመለዘዝ በአይኔ ተከተልኳት:: ጥልቅ ሀዘን ተሰማኝ:: የሄደችበትን መንገድ ሳይ የቆየሁበት አይኔ ብዥ አለብኝ:: አይኔን በሀይል ጨፈንኩ:: እምባው ጉንጬ ላይ መውረድ ጀመረ:: እጄን ኪሴ ከተትኩ:: መሀረቤ የለም:: አማንዳ ይዛው ሄዳለች

ፊቴን ወደ ከተማው መለስኩ:: ኤክስ ራቅ ብላ ትታየኛለች:: ከበላይዋ ንፁህ ሰማይ ተዘርግቷል:: የአማንዳን አይኖች ይመስላል

@BOOKALEM

# አስራ ሁለት

# የቀይ ኮከብ ጥሪ

## ባህራም

ባህራም እየተለወጠ ሄደ፡፡ እነ ማአ-ትዜ-ቱንግ የደረሱዋቸውን መፃህፍት ማንበብ ተው፡፡ ስለኮሙኒዝም ማውራት ተው፡፡ ከካርል መጣላት ተው፡፡ እኔንም ይሸሸኝ ጀመር፡፡ እንደቀስተ ደመና ውብ የነበረውን የሬቮሉሽን ተስፋውን በብዙ የእሳት ቃላት ይነግረኝ ስለነበረ፤ አሁን ቀስተ ደመናው ተሰባብሮ ወድቆ ከበሰበሰ በኋላ፡ እንደገና ሊያነጋግረኝ አልፈቀደም፡፡ ኒኮልም ፊት ነሳችኝ፡፡ የባህራምን ክንፍ እንደሰበረችው ስላወቅኩ ፊት ነሳችኝ

የኤክስን ሰማይ የሉልሰገድና የጀምሺድ መቀሰፍ አላስደነገጠውም፡ የአማንዳ ጉብዝና አላስደነቀውም፡ የኒኮል ማርገዝ አላናደደውም፡ የባህራም መታሰር አላሳዘነውም፡፡ የኤክስ ሰማይ ለዚህ ሁሉ ደንታ የለውም

የኤክስ ሰማይ አብዛኛውን ጊዜ እንደ አማንዳ አይን ብሩህ ሰማያዊ ነው፡ አንዳንድ ጊዜ እንደ ኒኮል አይን ውሀ አረንጓዴ ይሆናል፡ ወደ ማታ ጊዜ እንደ ሲልቪ ጉንጭ ይቀላል

የኤክስ ሰማይ ደመና አይለብስም፡ ሁልጊዜ ራቁቱን ነው፡ ሁልጊዜ ውብ ነው፡ ሁልጊዜ ሰማያዊ ነው፡፡ ሌሊት የአልማዝ ከዋክብትና የሰላም ፀጥታ ለብሶ ያድራል

የኤክስ የፀደይ ፀሀይ እየበረታች ሄደች፡፡ ንፁህ ብርሀኗ ቀስ እያለ ወደ ብጫ ሀሩር ተለወጠ፡ ለስላሳውን የፀደይ ንፋስ በጋ መጥቶ ኤክስ አደከመው፡ የሚወብቅ የአየር ባህር አደረገው፡፡



@BOOKALEM

ውስጥ እንደ ስራ ድካም ተንሳፈፈ:: እሮጊቶቹና ሽማግሌዎቹ ጥላ ውስጥ ቁጭ ብለው በዝግታ እያለከለኩ፣ የሞትን ምህረት የሚጠብቁ ይመስሉ ጀመር

አንዳንድ ጊዜ ባህራምንና ኒኮልን ምግብ ቤቱ ሲገቡ ወይም ሲወጡ አያቸዋለሁ:: ባህራም ከስቷል፤ አይስቅም፤ በፍጥነት አይራመድም:: ሽበቱም የበዛ መሰለኝ:: ኒኮል ግን ወፈር ብላ፤ እርግዝናዋ በጣም አምሮባታል፤ በዝግታ ስትራመድ ታስጎመጃለች

ቀስ በቀስ፣ ምግብ ቤት መምጣቱን ተወ

ተካ «የኒኮልን ማርገዝ ለመሸሸግ ያሉት ነው» አለኝ:: ሌላ ነገርም ነገረኝ — ባህራም ማታ ማታ ኒኮልን ቤቷ ትቷት ያወጣና ሲኒማ ይገባል፤ ከሲኒማ ወጥቶ ካፌ «ሰንትራ» ይሄዳል፤ እዚያው ያድራል፤ ሲነጋ ወደ ኒኮል ቤት ይኳትናል፤ ተኝቶ ይውላል

አንድ ማታ ወደ ስድስት ሰአት ላይ ከሲኒማ ወጥቼ ወደ ቤቴ በኩል ስራመድ፣ ከኋላዬ አንድ ፈጣን እርምጃ ሲከተለኝ ተሰማኝ:: እንዳልሰማሁ መንገዴን ቀጠልኩ:: ደረሰብኝ:: ባህራም:: ወደ ካፌ «ሰንትራ» ሄደን ቢራ ካዘዝን በኋላ

«ቁጭ ብለን ካወራን ብዙ ጊዜ ሆነን» አለኝ:: አይኖቹ እንደ መድከም ብሏቸዋል፤ ፊቱ ላይ የአምስት አመት ያህል እድሜ ተጨምሯል

«አንተ አትገኝም» አልኩት

«በገዛ ራሴ ጥፋት በታሰርኩ፣ አንተ ጋ መጥቼ ባለቅስብህ ተገቢ መስሎ አልተሰማኝም»

«ጥሩ እድል አጋጥሞህ ቢሆን ኖሮ ግን መጥተህ ታጫውተኝ ነበር፤ ደስታህን ታካፍለኝ ነበር»

«አዎን:: ይኸውልህ፦ ልክ ከፓሪስ እንደተመለስክ እንድንነጋገርበት አቅጄ ነበር:: ግን ገና ሳትመለስ ጣጣ ውስጥ ገባሁ:: ስትመጣ ታድያ፣ መንፈሴ ተሸንፎ ስለነበረ ያቀድኩትን ችላ አልኩት:: አሁን ፈቃደኛ ከሆንክ ብንነጋገርበት ጥሩ ይመስለኛል»

«ጥሩ»

መጀመር አስቸገረው:: ሲጋራ አቀጣጠለ::

«ስለሲልቪ ጉዳይ ነው:: ነግራሀለች?»



@BOOKALEM

«እምን፡፡»

«ምን አለችህ?»

የነገረችኝን ባጭሩ አጫወትኩት፡፡ ዝም ብሎ ሰማኝ፡፡ ስጨርስ

«ውሸቷን ነው» አለኝ

«እንዴት?»

«እኔ ነኝ የለመንኳት፡፡ እሷ እምቢ ብላኝ ነበር፡፡ በብዙ ተለማመጥኳት፡፡ 'አሁን አሁን ከሞት ጋር ስታገል ነበር፤ ውስጤ በፍርሀት ተሞልቷል፤ ብቻዬን ነኝ፤ የሰው ሙቀት ያስፈልገኛል፤ በጣም ያስፈልገኛል' አልኳት፡፡ እሺ አለችኝ፡፡ ግን እሺ ያለችኝ ብዙ ከተለማመጥኳት በኋላ ነው»

«ማንኛችሁን ለመን?»

«እኔን»

«ለምን?»

«ውሸት አልነግርህማ»

«እሷስ ለምን ውሸት ትነግረኛለች?»

«እንዳንጣላ ብላ»

ዝም አልኩ፡፡ ንዴቱ ውስጤ ሲጠራቀም ይሰማኛል

«ከፈለግክም አገጣጥመን» አለኝ፡፡ ቁጣዬን ለመግታት ስል መዋሸት ጀመርኩ

«ግድ የለም ይቅር፡፡ አሁን ስላንተ ንገረኝ» አልኩት፡፡ ድምፁ እንደተለወጠ ተሰማኝ

«ይቅርታ አርገህልኛል ማለት ነው?» አለኝ

«እንርሳው» አልኩት

«እፍረት ይሰማኛል፡፡ አይንህ ውስጥ ንቀት ይታየኛል»

«ንቀት አይደለም» አልኩት

«ታድያ ምንድነው?»

«ስሜቴን ልግለፅልህ?»



@BOOKALEM

«እምን»

እኔ ሳላውቀው የተጨበጠ ቀኝ እጄ በፍጥነት ሄዶ አገጩን መታው። ከነወምበሩ ወደኋላ ተገለበጠ። እጆቼን እንደ ጨበጥኩ ከበላዩ ቆምኩ። የተገለበጠው ወምበር አጠገብ እንደተጋደመ ወደ ላይ ያየኛል። ማንኛችንም አልተንቀሳቀስንም። ወደ ላይ እያየኝ ቀስ ብሎ መሀረቡን ከኪሱ አወጣ። መሀረቡ ውስጥ ተፋ። ደም። ቀና ብሎ ቀይ ፈገግታ ሰጠኝ። እጁን ዘረጋልኝ። ጨበጥኩት፤ ወደ ላይ ሳብኩት። በየቦታችን ተመልሰን ተቀመጥን

ካፌው ውስጥ ሌሎች ሰዎች እንዳሉና እንደሚያዩን ገና አሁን ታወቀኝ። አፈርኩ። ግምባሬን አላበኝ። መሀረቤን አውጥቼ ጠረግኩት። ባህሩም እንደገና መሀረቡ ውስጥ ተፋ። ሳቅ እያለ

«እንደሱ 'ንኳ ይሻላል» አለኝ

አንድ ነገር አስታወስኩ። ባህሩም ቢፈልግ ነብሴ እስኪወጣ ሊደበድበኝ ይችል ነበር! እንደገና አላበኝ። በመሀረቤ ጠረግኩት

ከዚህ በኋላ ከባህሩም ጋር እንደ ድሮው ማውራት ጀመርን። ኒኮል ማርገዟን ስታውቅ መበሳጨት የደረሰበትን አጫወተኝ። ብስጭቷ እየባሰበት ሄደ። ጀመረች። ባህሩም ከስራ ሲወጣ ሊልሰገድና ጀምሺድ ከሞቱ በኋላ፤ ብስጭቱ ወደ እምባ ተለወጠ። ባህሩም ያባብላት፤ በሲጋ ይገናኙትና ማታ ማታ ታለቅሳለች። ያስተኛታል

እሷ ስትተኛ እሱ ሲጋራ አቀጣጥሎ በጨለማው ስለ እሷ አመጣጥ ያስባል። ከንቱ! ያ ሁሉ ዝግጅት ከንቱ ቀረ። ያ ሁሉ የዘር በከንቱ አለፈ። ማን — ያ ኢራን ሳለ የ«ፍሬ» አስቀው የበለ ስለእምባጓሮ ያስተማረው ውድ ጓደኛው — ማን በሱ ቦታ ቢሆን እዚያ አሁን ምን ባደረገ ነበር? ለመሆኑ! ማን የት ይሆን? እንግሊዝ አገር ይሆን?

«ይገርምሀል» አለ ባህሩም ሲነግረኝ «አንድ አስር ቀን ያህል በተርታ፤ ማታ ማታ ስለማኑ ብዙ ብዙ አሰብኩ። እና አንድ ቀን ከሱ ደብዳቤ መጣልኝ። አይገርምህም? አድራሻዬን እንዴት እንዳገኘ 'ንጃ።»

«ደብዳቤው ምን ይላል?» አልኩት።



@BOOKALEM

ከኪሱ ሁለት በአረብ ፊደላት የተፃፉ ደብዳቤዎች አውጥቶ አንዱን ተረጎመልኝ

«ብዙ ብዙ የምነግርህ አለኝ። ግን በደብዳቤ አይሆንም። ስንገናኝ ነው። እዚህ ለንደን ውስጥ ሶስት ሚሊዮን ፓውንድና አንድ ዘመናዊ ማተሚያ ቤት አለን። ገንዘቡ ከቻይና፣ ከሶቭየት ህብረትና ከሌሎች ወዳጆች የተሰጠን ነው። ብዙ ሌላ እርዳታም ተሰጥቶናል። አስራ አምስት ሺ ክላሽንኮቭ ጭምር! እንግዲህ ጊዜው ደረሰ። ፎቶግራፍህን ላክልኝና ፓስፖርት ይዤልህ እመጣለሁ። እኔና አንተ አገራችን እንገባለን። እዚያ ብዙ ብዙ ስራ ይጠብቀናል። ዝግጁ ነህ? እንዲያው ነው የምጠይቅህ እንጂ ዝግጁ እንደሆንክ እርግጠኛ ነኝ። ይህን ሁለት አመት የት የት ነበርኩ መሰለህ? ፔኪንግ፣ ሞስኮ፣ ፕራግ፣ ቡዳፔስት — ብቻ ስንገናኝ እነግርሀለሁ። ቶሎ ፎቶህን ላክልኝ»

ባህሩም ደብዳቤውን አጥፎ ኪሱ ከተተ። ረዥም ዝምታ

ሰዎቹ ካፌው ውስጥ ያወራሉ። እንዷ ኮረዳ ከሽንት ቤት ወጥታ ሁለት ጎረምሶች መካከል ተቀመጠች።

«ፎቶህን ላከለት?»

«የለም»

«ምነው?»

«ከሱ ጋር ልሄድ አልችልማ»

«ለደብዳቤው መልስ ፃፍክለት?»

«እምን። ‘ካንተ ጋር ልመጣ አልችልም። ሀሳቤን ለውጫለሁ’ አልኩት»

«መቼ ነበር ይሄ የሆነው?»

«ከአስራ አምስት ቀን በፊት። ዛሬ ሌላ ደብዳቤ ደረሰኝ። ‘ሀሳቤን ለውጫለሁ ብትለኝ አላምንህም። ይልቅ ምን እንደሆንክ ንገረኝ’ ይላል።»

«ትነግረዋለህ?» አልኩት

«እኔ ‘ንጃ»

ዝም ብለን ብዙ ጊዜ ቆየን



@BOOKALEM

«ደብዳቤው ከደረሰህ በኋላ ነው እዚህ 'ሰንትራ' ማደር የጀመርከው?»

«አዎን። ኒኮል ጋር ማደር አልቻልኩም። ለቅሶዋ ሲያሳብደኝ ነው።»

አሁንማ «ስትዘጋጅበት፣ ስትጓጓለት የነበረው ስሌት ሲመጣልህ እኔ ከለከልኩህ፣ ገደልኩህ፣ እኔ አንተን ገደልኩህ!» እያለች ነው 'ምታለቅሰው። አልቻልኩትም። ባንድ በኩል ቁጭት፣ ባንድ በኩል የሷ ለቅሶ። በዛብኝ።»

ካንድ አመት ተኩል በፊት፣ በክረምት፣ ቤቱ ማሞቂያ ስላልነበረውና የክረምቱ ብርድ ስለበረታበት፣ ካፌ «ሰንትራ» ያድር ነበር። አሁን ደሞ የኒኮል እምባ እያባረረው ካፌ «ሰንትራ» ያድራል። ሲጋራ እያጨሰ ሲተክዝ ያድራል። ስለ ኢራን ሲያሰላስል ያድራል። ከንቱ ሀሳብ ሲያወጣ ከንቱ ሀሳብ ሲያወርድ ከንቱ ሌሊቶችን ያነጋል

* * *

ያን ሰሞን የሲልቪ መፅሀፍ ለሶስተኛ ጊዜ እምቢ አለ። ለሶስተኛ ጊዜ አባረረችኝ። እኔም መፃፍ አቃተኝ። እንዴትስ ላያቅተኝ ይችላል? ሲልቪ በጉልህ ሰማያዊ አይኖቿ ብርሀን ካላየችኝ፣ በውብ ሰፊ አፏ ሙቀት ካልሳመችኝ፣ በለስላሳ ገላዋ ካላቀፈችኝ እንዴት ልሰራ እችላለሁ? መስራቱን ተውኩት

ዩኒቨርሲቲው አጠገብ ያለው መናፈሻ ውስጥ የኤክስ አዛውንት በበጋው አቧራ ውስጥ "boule" ሲጫወቱ፣ በኮሚክ የደቡብ ፈረንሳይኛቸው እየፎከሩ አንዷን የብረት ኳስ በሌላ እያነጣጠሩ ወርውረው እየገጩ፣ እየተሳደቡ ወይም እየተሳሳቁ ሲንጫጩ አያለሁ

ከዚያ ወደ ኩር ሚራቦ ሄጄ Monoprix የተባለው ትልቅ ሱቅ ፊት ለፊት ከአንዱ ሽማግሌ ወይም ከአንዷ አሮጊት አጠገብ አግድም ወምበር ላይ እቀመጥና፣ የኤክስ ሚስቶችና እናቶች ከመንገዱ ወደ ሱቁ እየገቡ፣ ከውስጥ "Monoprix" የሚል የታተመባቸው የሞሉ ቡኒ የወረቀት ከረጢቶች ይዘው ወደ መንገዱ ሲጎርፉ አያለሁ። አስተያየታቸውም ሆነ አለባበሳቸው ወይም አረማመዳቸው የጎረምሳ አይን አይስብም። ድሮ የጎረምሳ አይን ስበው፣ ፍቅረኛ ይዘው፣ አግብተው፣ ወልደው በቅቷቸዋል። አሁን



@BOOKALEM

ወይም እርጅተዋል፣ ወይም ወፍረዋል፣ ወይም ተዝረክርከዋል

ኮረዳዎቹ ጡታቸውን አሹለው፣ ጸሊያቸውን አሳብጠው፣ አይናቸውን ተኩለው፣ ፀጉራቸውን ተሰርተው፣ ሽቶ አርከፍክፈው፣ እጅጌ የሌለው የበጋ ልብስ እየለበሱ፣ የብብታቸውን የተለያየ ከለር ፀጉር እያሳዩ፣ በጎረምሳ ታጅበው እየሳቁ እያወሩ፣ በኩር ማራቦ ይመላለሳሉ:: ወይም ካፌዎቹ በር አጠገብ መንገዱ ላይ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ግማሽ ጭናቸውን እያሳዩ፣ ልዩ ልዩ ቀዝቃዛ እየጠጡ ያወራሉ

አሮጊቶቹና ሽማግሌዎቹ እግድም ወምበር ላይ ፈዘው ቁጭ ብለው ፀሀይ ይሞቃሉ:: እኔም ቁጭ ብዬ ስለሲልቪ፣ ስለባህራም፣ ስለኒኮል፣ ስለሉልሰገድ፣ ስለአማንዳ እያሰብኩ አላፊ አግዳሚውን እመለከታለሁ

ሲልቪ መቼ መጥታ ወደ እቅፏ ትጠራኝ ይሆን? ጊዜው አላልፍልህ ይለኛል:: ወደ ዘጠኝ ሰአት ላይ ሲኒማ 'ገባለሁ:: ከሲኒማ ወጥቼ እንዱ ካፌ 'ሄድና አንድ ቢራ 'ጠጣለሁ

አንድ ቀን ወደ አስራ ሁለት ሰአት ላይ ነበር:: ሰማዩ ቀልቶ፣ ፀሀይዋ እንደ ቀይ ብርቱካን ከምእራባዊው አድማስ በላይ ተንጠልጥላለች፣ ግን ገና አትጠልቅም፣ እስከ ሁለት ሰአት ተንጠልጥላ እኩስን ታሰውባታለች

እየሩ የሚለሰልሰበት ጊዜ፣ ብቸኝነት የሚፈለግበት ሰአት ነው፣ የትዝታ የትካዜ ሰአት

«ካፌ ኒኮል» ሄድኩና፣ በረንዳው ላይ ፊቴን ወደ ፀሀይዋ አድርጌ ቁጭ ብዬ ቡና አይነቱን ቢራ አዘዝኩ:: አሮጊቷ ቢራውን እያቀረቡልኝ

"Ça fait longtemps qu'on vous a pas vu, monsieur" አሉኝ:: (ብዙ ጊዜ ሆነን ካየንዎት)

"Oui, madame." አልኳቸው

«ጓደኛዎትስ ደህና ናቸው?»

«ደህና ነው:: አገሩ ገብቷል»



@BOOKALEM

«ትምህርታቸውን ጨረሱ?»

«አዎን»

"Il etait très gentil, votre ami" («በጣም ጥሩ ሰው ነበሩ ጓደኛዎት»)

"Oui, madame"

አሮጊቷ ሄዱ፡፡ ብቻዬን ቀረሁ፡፡ ከቀይዋ ፀሀይ ጋር፣ ከቡናማው መንግስተ ሰማያት ማለት ቢራ ጋር፡፡ ከሉልሰገድ ትዝታ ጋር. . . የሚበቅልበት ማለት ነው. . . ሊት በየዛፉ ስር፣ በየግድግዳው ጥግ የሚበቅልበት ማለት ነው. . . እየሀ፣ የኒኮል ጡት እንደ ነጭ ውብ ሰማይ ነው፡፡ ሰማዩ መሀል ላይ በሮዝ ቀለም የተከበበች ወይን ጠጅ ጨረቃ አለች. . . እኔ 'ምልህ፣ በሮዝ ቀለም የተከበበች ወይን ጠጅ ጨረቃ አለች. . . ትባርክሀለች ከኒኮል ጋር አልጋ ላይ የወጣህ ጊዜ፣ በቅዱስ ብልግናዋ ትባርክሀለች . . . አይ አንተ ባላገር! መባዳት ቁላን እምስ ውስጥ መክተት ይመስልሀል፡፡ ስንት ሳይንስና ስንት አርት እንዳለው ባወቅክ! ኒኮልን በቀመስክ! . . .

ፀሀይዋን ከለለች፡ ከሉልሰገድ ነጠለች፡፡ ቀና ብዬ አየሁት፡፡ ባህራም፡፡ አጠገቡ አንድ ቀጭን ባለመነፅር ሰውዬ ቆሟል፡፡ ቁመቱ ከባህራም ትንሽ ይበልጣል፡፡ ያገሩ ልጅ ይመስላል

ብድግ አልኩ፡፡ ሰውዬው ፈገግ አለ፡፡ ፈገግታው ደስ ይላል፡፡ የልጅ ፈገግታ ይመስላል፡፡ እጁን እየዘረጋ፣ በጣም ወፍራም በሆነ ድምፅ በእንግሊዝኛ

«ከለንደን መምጣቴ ነው» አለኝ

ጨበጥኩት፡፡ አጨባበጡ ልዩ ሆኖ ተሰማኝ፡፡ እጁ አይመችም፡፡ በኋላ ሳየው መሀል ጣቱ ወደ አንድ በኩል ተጣሟል አይታጠፍም፡፡ ሌሎቹ ጣቶቹ ረገርገምም ቀጫጭን ቆንጆ ናቸው

«እንኳን ደህና መጣህ!» አልኩት፡፡ ቁጭ አልን፡፡

ባህራም ግን አልተቀመጠም፡፡ እኔን «ይሄ ማን ነው፡፡ የፈለግከውን ልትነግረው ትችላለህ» አለኝና ወደ ካፌው ውስጥ ገባ

የማኑ ግምባር በጣም ጠባብ ነው፣ ወደኋላ የተበጠረው ፀጉሩ ከቅንድቦቹ ጋር ሊገናኝ ምንም ያህል አይቀረው

ሳቅ አለ፡፡ የላይኛ የፊት ጥርሱ ሁለቱ የራሱ አለመሆኑን



@BOOKALEM

አስተዋልኩ፣ ሰው ሰራሽ የአጥንት ጥርስ ነው:: ጥያቄው እመለሰበትና መሀል ጥቱን በግራ እጁ እያሻሸ

«ጥርሶችህ የት ሄዱ?» አልኩት:: የልጅ ሳቁን እየሳቀ፣ ስባራ

«አገሬ ትቻቸው መጣሁ:: እስር ቤት ውስጥ» አለኝ:: ወፍራም ድምፁ ውስጥ መመረር አይሰማም:: ሲስቅ ከመነሰሩ ኋላ አይኖቹ ጥቅጥ ይላሉ

«እህ!» አልኩት:: ምን ማለቴ 'ንደሆነ 'ንጃ

«አሁን ጥርሶቼን ፍሊጋ አገሬ መመለስ አለብኝ:: ባህራም ቢያፋልጉኝ ቶሎ አገኛቸው ነበር:: እሱ ግን አላግዘህም አለኝ»

«የጥርስ አዳኝ መሆን አልፈልግም አለ?»

«እህስ! ያውም የኔን የጓደኛውን ጥርሶች! አይገርምህም?»

«በጣም 'ንጃ!» ይሄ ምን አይነት ንግግር ነው? የሚል ሀሳብ ጨረፈኝ

«ካንተ ጋር ብተዋወቅና በሰፈው ባወራ ደስ ይለኝ ነበር:: ግን እቸኩላለሁ:: ጥርሶቼ ናፍቀውኛል» አለ:: ይስቃል

«ይገባኛል» አልኩት እየሳቅኩ

«ባህራም እንደሚያስፈልገኝስ ይገባሀል?»

«አዎን»

ሳቁ ከፊቱ ጠፋ:: ጉንጮቹ ወደ ውስጥ የጎደጎዱ ናቸው:: በብዙ የሚመገብ አይመስልም:: ቆንጆ ጣቶቹን እየሁዋቸው፣ ንፁህ ናቸው፣ የሲጋራ ልማድ አልተለጠፈባቸውም

አሮጊቷ ሲመጡ ማኑ ቀዝቃዛ ውተት አዘዘ:: አንዲት ኮረዳ ባጠገባችን ስታልፍ ሽቶዋ እንድ ጊዜ አወደን:: ነጭ ሸሚዝና ሰማያዊ ቁምጣ የለበሰው ቅርፅዋ አይን ይማርካል፣ የሚወዛወዝ ዳሌዋ ያስጎመጃል:: ማኑ አይኑን ጣል አረገባት፣ ያኔውኑ ረሳት፣ ወደ ካፌው ውስጥ እስክትገባ በአይኑ አልተከተላትም:: ስምሣብም፣ ለሲጋራም፣ ለመጠጥም፣ ለሴትም ጊዜ ያለው አይመስልም:: ጊዜውን በሙሉ ለሬቮሉሽኑ መድቧል? ስራውም፣ ጨዋታውም፣ እረፍቱም



@BOOKALEM

ያው ሬቮሉሽን ይሆን?

እንዲህ አይነቶቹ ታጥቀው ሲነሱ፣ በሁለት አመት ውስጥ ሞስኮ፣ ፒኪንግ፣ ቡዳፔስት ወዘተርፈ እየዞሩ ሶስት ሚልዮን ፓውንድና አስራ አምስት ሺ መትረየስ የሚያከማቹ ጎልማሶች ታጥቀው ሲነሱ፣ እስር ቤት ውስጥ ማታቸው ተሰብሮ ጥርሳቸው የተሸረፈ ሰዎች ታጥቀው ሲነሱ፣ ለሲትም ለመጠጥም ጊዜ የሌላቸው ጎረምሶች ታጥቀው ሲነሱ፣ የኢራን ሻህ ለምን ያህል ጊዜ ዙፋኑ ላይ ሊቆይ ይችል ይሆን?

ማን እንዲህ አለኝ

«ባህራም እዚህ አገር ውስጥ ደምበኛ ስራ ለመያዝ የሚያበቃ ትምህርት ወይም የሙያ ችሎታ የለውም:: ግፋ ቢል አንድ ፋብሪካ ውስጥ ይቀጠራል:: ሲሰራ ውሎ ማታ ሲጠጣ ያመሻል:: እኔ ወደምሄድበት አብሮኝ ለመምጣት አለመቻሉ እየቆጨው ይሄዳል:: ከሁለት አመት በኋላ ዋና ሰካራም ይወጣዋል፣ ራሱን አይጠቅም፣ ማንንም አይጠቅም:: ልጅቱም — ኒኮል ነው ስሟ? — እሷም ሲበላሽ እያየች ትንቀዋለች:: እበላሸሁት ብላ ፀፀት ውስጥ መኖር ትጀምራለች:: ትንሽ ቆይታ ፍታኝ ትለዋለች:: ኑሮው በሙሉ ፈሩን ሳተ ማለት ነው

«ከኔ ጋር የመጣ 'ንደሆነ ግን —»

«ይህን ሁሉ አውቃለሁ'ኮ» አልኩት

«እንግዲያው አግዘኝ! እሱንም አግዘው:: በዚያውም በሀያ ሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ታግዛለህ»

«ላግዝህ መቻሌን እንዴት ታውቃለህ?» አልኩት

«ማወቁንማ አላውቅም:: ምናልባት ብትችል ብዬ ነው 'ንጂ:: እየህ፣ ባህራም ያስፈልገናል:: በጣም ያስፈልገናል:: ለሱም የኛ አይነት ኑሮ ያስፈልገዋል»

«ላግዝህ 'ምችል አይመስለኝም:: ግን አንድ እኔ 'ማውቀው ነገር አለ:: ምናልባት ሊረዳህ ይችል ይሆናል»

«ንገረኝ»

«ግን እኔ ማወቄን ባህራም እንዳያውቅ»



@BOOKALEM

«ግድ የለህም»

ስለኒኮል፣ ስለሉልሰገድና ስለጆምቪድ የማውቀውን እጫወትኩት:: ጭንቅላቱን አሰር ጊዜ ወደ ላይ ወደ ታች እየነቀነቀ በፀጥታ አዳመጠኝ:: ነገሬው ስጨርስ፤

«ገባኝ:: እንኳን አንተን አገኘሁህ!» አለኝና ተነሳ:: እኔም ተነሳሁ:: ባህሩም ከካፌው ውስጥ መጣ:: ማኑ እየጨበጠኝ (የተጣመመች ጣቱ እየቆረቆረችኝ)

«ሊታማዘኝ ባለመቻልህ አዝናለሁ:: ደህና ሁን» አለኝ

ከባህሩም ጋር ጎን ለጎን እየተራመዱ ከኔ ራቁ:: ማኑ ትንሽ ትንሽ ያነክሳል:: ከበላያቸው ሰማዩ ደም ለብሷል

ቅድም ወደ ካፌው የገባችው ባለቁምጣ ልጅ ወጣች:: ስትራመድ የውብ ቂጧን ክፍ ዝቅ በአይኔ ተከተልኩ:: አይቼው የማላውቀው የኒኮል ቂጥ ትዝ አለኝ:: . . . አየህ፣ የኒኮል ቂጥ እንደያው ለመቀመጫ የተፈጠረ ቂጥ አይደለም፡ የውበት ክምር ነው:: አንዳንዴ አልጋው ላይ በሆዷ አስተኛትና ያንን ቂጧን እየዋለሁ፣ እየዋለሁ፣ እየዋለሁ! አይቼ አልጠግበውም:: እያየሁት በእጇ እንዲህ፣ እንዲህ፣ እያደረግኩ እዳብሰዋለሁ:: ጎምበስ ብዬ እንደ ቤተ ክርስትያን እስመዋለሁ:: . . . አይተህልኛል የኒኮልን አይኖች? አረንጓዴ የውበት ሀይቆች፣ የሀዘን ሀይቆች:: አቤት አይኖቿ ውስጥ ያለው ሀዘን ሲያምር!. . .

የኒኮል ውበት ለባህሩምም እንዲህ ጎልቶ ይታየው ይሆን? እንግዲህ ከኒኮልና ከማኑ ማን ያሸንፍ ይሆን?

ለመሆኑ የዚህ የማኑ አለም ውስጡ እንዴት ያለ ይሆን? የመጠጥ ሙቀትና የኮረዳ ትኩሳት የሌለበት አለም አይቀዘቅዝም? ወይስ ቀዩ የሬቮሉሽን ኮከብ፣ ዘለአለማዊው የሳጥናኤል ኮከብ ንፁህ ሙቀትና ውብ ትኩሳት ይሰጠው ይሆን? እነካስትሮ፣ እነሆ-ቺ-ሚን እነማኦ በወጣትነታቸው እንደማኑ ነበሩ? ወይስ እንደ ባህሩም ነበሩ?

ግን እንደ ባህሩም ቢሆኑ ኖሮ እንደ ኒኮል ያለች ውብ ኮረዳ ግማሽ መንገድ ላይ አታስቀራቸውም ነበር? ወይስ ገርማዊው



@BOOKALEM

የሳጥናኤል ኮከብ በተይ ብርሀኑ ከፉት ሲጠራህ፣ ከለበላላ የቤት ልጅ ጭን ሙቀት ወጥተህም ቢሆን ጥሪውን ማክበርህ አይቀርም ይሆን? እስቲ 'ናያለን

ቀዩ ሰማይ እየጠቆረ ሄደ:: ከፊው ውስጥ መብራት በራ:: ሌላ ቢራ አዘዝኩ:: ስለኒኮል ማሰብ ጀመርኩ:: በጭለማው እሌጋ ውስጥ ተቃቅፈን፣ እጄን ሙታንቲዋ ጠርዝ ላይ ሳሳርፍ ትገዝ አለኝ:: የፍትወት ትኩሳት ጀመረኝ:: ያን ሰሞን እርግዝናዋ አሩፍቷት፣ ከመቸም የበለጠ ታምራለች:: በቢጋው ሙቀት በዝግታ ስትራመድ የግብረ ስጋ 'መቤት ትመስላለች:: ባየኋት ቁጥር ፍትወት ያቁነጠንጠኛል:: ለመሆኑ፣ ማኑን ስለነሉልሰገድ ያጫወትኩት ለምን ኖሯል? ባህራም ሄዶ የሚወደውን ሬቮሉሽን እንዲቆሰቁስ ነበር? ወይስ ባህራም ሄዶልኝ እኔ ኒኮልን እንድቆሰቁስ ነበር? ወይስ ሁለቱም ነበር?

ማታ አምስት ተኩል ላይ ከሲኒማ ስወጣ፣ ሲልቪን በሩ ላይ አገኘሁዋት:: ሳያት ከመጠን በላይ ደስ አለኝ:: ፈራሁ:: እቺን ልጅ እንዴት አድርጌ ልለያት እችላለሁ? ፈገግታዋ ልቤን አሞቀው:: የተዘረጋ ቀኝ እጇን በግራ እጄ ተቀብዬ እያሻሸሁ

«እንዴት ታምሪያለሽ!» አልኳት

«ዛሬ ከኔ ጋር ማደር ትፈልጋለህ?»

«በጣም! ታድያ ግን እንቅልፍ አልፈልግም»

«ካልክስ እኔም አልፈልግም»

መኪናዋ ጋራዥ ገብታ ስለነበረ፣ ወደ ቤቷ ስንራመድ፣ ትከሻዋን እያቀፍኩ

«እንዴት አገኘሽኝ?» አልኳት

«ቢቴ ሄጄ አጣሁህ:: ስለዚህ ሲኒማ ቤት ሳይሆን

እየሳቀች «ቢቴ ሄጄ ... የኢጣልያ ፊልም የሚታይበት መሆን አለበት አይቀርም አልኩ:: የኢጣልያ ፊልም የሚታይበት መሆን አለበት

አልኩ::»

"Á la Sherlock Holmes, quoi!" አልኳት (በሸርሎክ ሆምዝ ዘዴ



@BOOKALEM

ነዋ)

እየተራመድን፣ ዳሌዋ በአንዱ እርምጃ እየተጠጋኝ በሌላው እየራቀኝ፡ እየራቀኝ — እየተጠጋኝ — እየራቀኝ፣ የጫማዋ ኳ-ኳ እየተሰማኝ

«ደስ ይለኛል» አለችኝ «እየሄድን እጅህን ራሴ ላይ ስታሳርፈው በሀይል ደስ ይለኛል:: እጅህ ከክፉ የሚከልለኝ ይመስለኛል፡ የሚባርከኝ ይመስለኛል:: ካንተ ጋር ባልሆንኩ ጊዜ ሳስብህ፣ መጀመሪያ ትዝ 'ሚለኝ እጅህ ራሴ ላይ ሲያርፍ ነው»

እየተራመድን እጇን ሳምኩት

«አሁን የሳምከው የተራ ሰው እጅ እንዳይመስልህ» አለችኝ፣ «የደራሲ እጅ ነው»

«የውብ ደራሲ እጅ ነዋ ያውም!» አልኳት

«እውነቴን'ኮ ነው:: ዛሬ ከኤዲስዮን ግራሴ (Editions Grasset) ደብዳቤ ደረሰኝ:: አስራ ሶስቱ አንተ የመረጥካቸው አጫጭር ልቦለዶቼ Treize de Sylvie ተብለው ሊታተሙ ነው::»

«ውሸትሽን ነው!»

«መፅሀፉ ለሚመጣው ፀደይ ይወጣል»

«ማርሰይ እንሂድ?» አልኳት

«ለምን?»

«ይህን ግሩም ቀን ማክበር አለብን:: ይገባሻል? እንግዲህ'ኮ ስምሽ ከነፍራንስዋዝ ሳጋን፣ ከነኮሌት ጋር ሊጠራ ነው:: ቀስ ብሎ ከነፍሎቤር፣ ከነፕሩስት፣ ከነማልሮ ጋር ይጠራል»

«ይመስልሀል?»

«እርግጠኛ ነኝ»

«እንዴት ጥሩ ነው!»

«ብቻ 'ንዳልኩሽ ነው:: የመሰለሽን ሁሉ ሳትፈሪ ፃፊ»

«አልፈራም» «አልፈራም:: በጭራሽ አልፈራም»

«እንደሱ ነው! አሁን ማርሰይ 'ንሂድ?»



@BOOKALEM

«የለም:: ቤት 'ንሂድና በሩን ቆልፈን፣ ራቁታችንን ወጥተን፣ እንዳንድ ቀኑ እንሰሳዎች 'ንሁን:: በሀይል ናፍቀሽኛል»

«እኔም በሀይል ናፍቀሽኛል»

"Parole d'honneur?"

"Parole d'honneur! እጅሽን አምጪ 'ስቲ:: አይታወቅሽም?»

«ይታወቀኛል:: ለኔ ነው 'ንዲህ 'ሚዘለው?»

«ላንቺ አይደለም:: ለእንትንሽ ነው»

ሳቀች፣ ቅንዝረኛ የጉሮሮ ሳቋን ሳቀች

ከኢከስ ወጣ 'ንዳልን

«ባህራም ሰውየውን የገደለው እዚችጋ ነበር» አለች:: ትንሽ ሄድ ካልን በኋላ «እኔ እዚችጋ ነበርኩ»

«ከዚያ ቤትሽ ወሰድሽው»

እየተጠጋችኝ «አዎን» አለች

«ከዚያስ?»

«ከዚያማ የሆነውን ነግሬህ የለ?»

«የነገርሽኝ በሙሉ እውነት ነበር?»

«አዎን»

«ባህራም ግን እኔ ነኝ በብዙ ተለማምጬ እሺ ያሰኘኋት 'ንጂ እሷስ እምቢ ብላኝ ነበር» አለኝ

«ውሸቱን ነው»

«ለምን ይዋሻል?» አልኳት

«እንዲያማላን ፈርቶ::»

«አንቺ አለመዋሸትሽን በምን አውቃለሁ?»

«እኔ ለምን 'ዋሻለሁ? ታውቀኝ የለ? ስንትና ስንት ጉድ አውጥቼ ነግሬህ፣ እዚች ላይ ውሸት እነግርሀለሁ? ይመስልሀል?»

«ከዚያ በኋላ ተገናኝታችሁ ታውቃላችሁ?»



@BOOKALEM

«የለም»

«ምነው? እምቢ አልሽው ወይስ እምቢ አለሽ?»

«ሁለታችንም ተውነው»

«ለምን?»

«እሱ ሳንተ ሲል ይመስለኛል»

«አንቺስ?»

«እኔም ሳንተ ስል ይመስለኛል:: ግን እርግጠኛ 'ይደለሁም::»

«እንዴት?»

«ተለውጫለሁ መሰለኝ:: ለምሳሌ ከፓሪስ ከተመለስን ካንተ ሌላ ማንም ወንድ አልሄድኩም:: በፊት ግን ካንተ ሌላ በሳምንት ቢያንስ አንድ ወንድ ካልቀመስኩ አይሆንልኝም ነበር:: ፓሪስ ሆነን ሌሎቹ ጋ እየላክከኝ የራስህ የብቻህ አደረግከኝ መሰለኝ»

«ሌሎቹ ጋ እየላክኩሽ የብቻዬ አደረግኩሽ?»

«አትሳቅ:: እኔ የምሬን ነው:: በፊት፣ ሌላ ወንድ እያሰብኩ እንዳትቀናህ ስለፈቀድክልኝ፣ እንደ ልቤ አደረግኩትና ጠገብኩት:: ሙሉ አሁን ማንንም ሳትቀና ሌላ ሰው ማሰብ የለብኝም:: ደኛለሁ:: ሙሉ ነፃነት ስለሰጠኸኝ ነገሩን ጠገብኩትና ወጣልኝ:: አሁንም 'ንደሱ እርገህል መሰለኝ::»

«እንዴት ማለት?»

«ፓሪስ ሆነን እንደ ልቤ ወንድ እንዳሳድድ ፈቀድክልኝ:: ወንድ እያቀያየርኩ እስኪደክመኝ ተደስቼ ስመለስ፣ በሙሉ ልብህ ተቀበልከኝ:: ስትቀበለኝ ጊዜ ወንድ መለዋወጡ ክልክል መሆኑ ቀረ:: በዚህ ሰለቸኝ፣ ጠገብኩት:: ተውኩት ይመስለኛል::»

«እርግጠኛ ነሽ?»

«እርግጠኛ ለመሆንማ ጊዜ ያስፈልገኛል:: ግን 'ሚገርም ነገር ነው:: ሙሉ ነፃነት ስለሰጠኸኝ ታሰርኩ:: አይታይህም?»

«መታሰርሽን ግን አላወቅነውም» አልኳት ለመቀለድ እየሞከርኩ

«እኔ አውቄዋለሁ:: ለምሳሌ፣ ከዚህ በፊት መፅሐፌ 'ምቢ ሳለኝ፣ እንተን አባርሬ ምን ነበር 'ማረገው መሰለህ?»



@BOOKALEM

«ከመዕህሩሽ ጋር 'ምትታገዪ ነበር 'ሚመስለኝ»

«ተሳስተሀል። በየቀኑ ከምሳ በኋላ ማርሰይ 'ወርድና፣ ከስእት በኋላውን፣ ማታውን፣ አንድ አራት አምስት ወንድ ተኝቶኝ፣ ወደ እኩለ ሌሊት ላይ ድከም ብሎኝ ወደ ኤክስ 'መለሳለሁ። በቀን በቀኑ ይህን አረጋለሁ። አንድ ቀን ልሄድ ስዘጋጅ ፃፊ ፃፊ ይለኛል። መፃፍ እጀምራለሁ። ወንዶቹ በቁኝ ማለት ነው። በፊት 'ንዲህ ነበር 'ማረገው»

«አሁንስ?»

«አሁንም ሳደርገው ተነሳሁ። ማርሰይ ወረድኩ። ግን ምንም ሳላረግ ተመለስኩ»

«ወንዶችሽ 'ምቢ አሉሽ?»

በጉሮሮዋ ውስጥ ቅንዝረኛ ሳቋን እየሳቀች

«ትቀልዳለህ?» አለችኝ «ተለውጬ ነው 'ንጂ። ወንድ መሄድ ሱስ መሆኑ ቀረ»

«ሱስ መሆኑ ቀረ 'ንጂ መደረጉ ግን አልቀረም፣ እ?»

«መደረጉማ ለምን ይቀራል? የስሜት ደስታ አይደለም'ንዴ?»

ይህን ጊዜ ቤቷ ልንደርስ አንድ መቶ ሜትር ያህል ቀርቶናል። ታሻሸው የነበረውን እጄን ለቀቀችና

«ማን ይቅደም?» ብላ ትታኝ ሮጠች። እንዳልቀድማት ብዙ ጫማዬን በሀይል እያስጮህኩ ተከተልኳት። እሷ 'የምኖርበት' እኔ 'የሳቅኩ ቤቷ ጋ ስንደርስ፣ በሩን ቀድማኝ በእጇ ነካችው

«ቀደምኩህ!» አለችና በሩን ተደግፋ ቁና ቁና ስትተነፍስ፣ ጉንጮቿን በእጆቼ ይዤ ግምባሯን ሳምኩት

«እንደዚህ ለዋውጠኸኝ፣ በኋላ ያላንተ 'ንዴት ልሆን ነው!» አለችኝ። በሀይል አሳዘነችኝ። ሆዴ ሽምቅቅ አለ። ወደኔ አስጠግቼ ራሷን እየደባበስኩ

«ውይ የኔ ቆንጆ! እንድተውሽ አትፈልጊም 'ንዴ?» አልኳት

«አልፈልግም — አልፈልግም — አልፈልግም!» እያለች በጣም



@BOOKALEM

ተጠጋችኝ፣ ራሷን እንገቴ ውስጥ ሸሸገች:: እምባዋ እንገቴን ነካኝ

«እኔም ልተውሽ አልፈልግም፣ ዮኒ ቆንጆ፣ አልተውሽም:: እስከመቼም አልተውሽም:: ምንም ቢመጣ አልተውሽም» አልኳት

«እፈራለሁ:: ካንተ መለየቱን ሳስበው 'ፈራለሁ:: አንተ አገርህ ትሄድና፣ ከዚያ በኋላ አንገናኝም:: እስከመቼም አላይህም:: በቃ ለዘለአለም?! ውይ! እቀፈኝ! እቀፈኝ!. . . መኖር እንዴት አስቸጋሪ ነው!»

«አይዞሽ እንለያይም፣ ዮኒ ሲልቪ»

«እንለያይም?»

«እንለያይም:: አይዞሽ አታስቢ:: አሁን እንግባ»

አልጋ ውስጥ ሳዬ ላይ አደረግኳትና፣ ጀርባዋንና አንገቷን ቁንጥላቷን እየደባበስኩ ብዙ ጊዜ ከቆየን በኋላ:

«አሁን ተለያይተን በወድያኛው ህይወት 'ምንገናኝ 'ንኳ ቢሆን፣ ምናልባት እችለው ነበር» አለችኝ «ግን መለያየቱ ለዘለአለም ሲሆን፣ አንድ ጊዜ አይህና ከዚያ በኋላ ለዘለአለም ለዘለአለም እስከመቼም የማንተያይ ስንሆን፣ በጣም ያስፈራኛል!» ብላ ተጠመጠመችብኝ

«አይዞሽ እንለያይም»

«እንለያይም?»

በሩ ተንኳኳ:: ድንግጥ አለች

«አይዞሽ አይዞሽ»

በሩ እንደገና ተንኳኳ

«ማነው በይ» አልኳት

«ማነው?» አለች ጮክ ብላ

«ባህራም!»

ድንጋጤዋ ወደ ብሽቀት ተለወጠ:: እየተነጫነጨች ተነስታ የሌሊት ካፖርቷን ራቁት ገላዋ ላይ ጣል አርጋ፣ መቀነቱን እየታጠቀች ሄዳ በሩን ከፈተች

ባህራም «ይቅርታ በዚህ ሰአት ስላስቸገርኩ» እያለ ገባ:: ጥቁር



@BOOKALEM

ሙሉ ሱፍ ልብስ፣ ውሀ ሰማያዊ ሸሚዝ፣ ደማቅ ሰማያዊ ክራቫት፡፡ ፂሙን ተላጭቶ፣ ፀጉሩን ወደ ኋላ አበጥሯል፡፡ ከጎንና ከጎን የበቀለው ሽበት፣ የእርጅና ምልክት መሆኑ ቀርቶ ልዩ ጌጥ መስሏል፡፡ የድል አድራጊነት ፈገግታ የሚጨፍርበት ፊቱ ወጣትነት ተላብሷል

መጥቶ እተጋደምኩበት አልጋ አጠገብ ወምበር ላይ ሲቀመጥ

«እንዲህ ዘንጠህ የት ልትሄድ ነው?» አልኩት

ሲልቪ መጥታ ከጎኔ አልጋው ውስጥ ገባች

«አገሬ መግባቴ ነው» አለ

«ምን?»

«ልሰናበታችሁ ነው የመጣሁት»

«መሄድህ ነው በቃ?» አለችው ሲልቪ

«አዎን»

«ቆይ ዊስኪ ላምጣልህ» ብላ፣ ከአልጋው ወጥታ ወደ ወጥ ቤት ሄደች፡፡ ቶሎ ከኪሱ አንድ ወረቀት አውጥቶ፣ ወምበር ላይ እተሰቀለው ኮቴ ኪስ ውስጥ ከተተና፣ በሹክሹክታ

«ለብቻህ አንብበህ ቅደደው» አለኝ

«ላንተም ላምጣልህ?» አለች ከወጥ ቤቱ

«ለኔም ላንቺም አምጪ» አልኳት

ይዛ መጣች፡፡ አልጋ ውስጥ ገባች፡፡ ዊስኪውን አነሳሁና ባህራምን

«መልካም ጉዞ!» አልኩት

ፉት አልን

«ከመሄዴ በፊት ጥቂት ልነግርህ 'ሚገባኝ ነገር አለ» አለኝ፡፡ ሲልቪ ትታን ልትሄድ ስትል «ካንቺ 'ሚደበቅ ያለበት አይደለም» አላት

«እሺ» አልኩት

«ብዙ ልነግርህ በፈቀድኩ፡፡ ግን አብዛኛው የኢራን ከመኒስት ፓርቲው ፓርቲ ምስጢር ነው፡፡ አንተን አምንሀለሁ፡፡ ግን



@BOOKALEM

እንድነግርህ አይፈቅድልኝም»

«ይገባኛል:: ምንም መናገር የለብህም»

«አውቃለሁ:: ሁለት ነገር ብቻ በጠቅላላ ባጭሩ ልንገርህ»

«እሺ»

«ሁለት አመት ሙሉ በይሩት ነበርኩ:: ግን ዩኒቨርሲቲው ውስጥ የህክምና ትምህርት አልተማርኩም:: ሌላ ስራ ነበረኝ:: በቅርብ ምስራቅ ውስጥ ያሉትን የኢራን ኮሙኒስቶች ሳደራጅ ነበር:: በሌላ በኩል ደሞ ከሻህ ሰላዮችና ከሲ.አይ.ኤ ጋር ረዥም ጦርነት ስናካሂድ ነበር:: ሲ.አይ.ኤ ሊገድለኝ ሲሆን ጊዜ፣ ቱዴህ (የኢራን ኮሙኒስት ፓርቲ) እንድሸሽ አዘዘኝ:: ወደ ኢክስ መጣሁ:: እውነተኛ ስሜን ልነግርህ አልችልም፡ ግን ባህራም አይደለም:: ባህራም አፍሻር በይሩት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ህክምና ይማር ነበር:: በሱ ስም የውሸት ፓስፖርት አውጥቼ ነው::»

«ቤቶችህ ይህን ያውቃሉ?»

«ታላቅ ወንድሜ ያውቃል:: ስም በቀየርኩ ቁጥር አዲስ ስሜን በደብዳቤ 'ነግረዋለሁ፣ ከቤት ገንዘብ ሲመጣልኝ እሱ በአዲሱ ስሜ እየላከው ነው:: እዚህ ላይ አንድ ነገር አለኝ 'ምነግርህ»

«ምን?»

«ደጋግመህ መልክህ የኢራንን ሻህ ይመስላል ብለኸኛል:: እውነትክን ነው:: ሻህ የስጋ ዘመዴ ነው»

አጭር ዝምታ

«ላሳየኸኝ ጓደኝነትና ለዋልክልኝ ውለታ ላመሰግንህ አልችልም:: ስለዚህ ሳላመሰግንህ መሄዴ ነው» አለኝና ተነሳ:: በቁሙ ዊስኪውን ጨለጠ፣ ብርጭቆውን ኮሞዲኖ ላይ አኖረው:: ልሸኘው ካልጋ ልነሳ ስል

«አትነሳ:: ማኑ 'ዚህ ውጭ ይጠብቀኛል:: አብረኸኝ ብትመጣ ያለቅስብኛል:: እሱ ሁልጊዜ 'ንደተጠነቀቀ ነው:: ወዴት በኩል 'ንደምንሄድ አንተ'ንኳ እንድታውቅ አይፈልግም» ይስቃል:: ማኑን ስለሚወደው ይስቅበታል:: ከማኑ ጋር ለመሆን በመቻሉ እጅግ ደስ ብሎታል:: ወጣትነቱን እንደገና አግኝቷል::



@BOOKALEM

እጁን ዘረጋው። ጨበጠኝ። በኋላ በኩል ተንጠራርቶ ሲልቪን ሳማት። ሊሄድ ወደ በሩ በኩል ከዞረ በኋላ

«ለመሆኑ» አልኩት

ዞረ። ፊቱ ላይ ፈገግታ የለም። የኢራንን ሻህ ይመስላል። አፍንጫው ትልቅ ነው

«ለመጀመሪያ ጊዜ ሳገኝህ ስድስት አሜሪካኖች ይዘውህ ሊደበድቡህ መጀመራቸው ነበር» አልኩት

“A bas les Yankees!” አለኝ እየሳቀ

“A bas!” አልኩት

ሰአቱን አየ። ቸኩሏል

«ሊደበድቡህ ይዘውህ ሳለ፣ ማኑ ያስተማረህን የመከላከል ዘዴ ለምን አልተጠቀምክበትም?» አልኩት

«ተማሪዎች ይሁኑ ወይ የሲ.አይ.ኤ ሰዎች ይሁኑ እርግጠኛ አልነበርኩም። ምናልባት እኔን ፍለጋ የመጡ የሲ.አይ.ኤ ሰዎች ቢሆኑስ? ያን አይነት ያምባጓሮ ዘዴ ማወቄን ካወቁ ባህሪዬ አለመሆኔን ይጠረጥራሉ። ለዚህ ነው። በሉ ደህና ሁኑ። ማኑ ይጠብቀኛል»

«ደህና ሁን!» አልነው ሁለታችንም

“Vive l'Etoile Rouge!” አለኝ (ቀዩ ኮከብ ለዘላለም ይኑር!) (“Et vive l'amitie!” (ጓደኝነትም ለዘላለም ይኑር)

“Vive!” አልኩት

በፈጣን እርምጃው በሩጋ ደረሰ። መለስ አለ። አሁንም የድል አድራጊነት ፈገግታ ወጣት ፊቱ ላይ እየተጫወተ

«ሳልነግራችሁ ረስቼ» አለን «ያን ጊዜ ሊገድለኝ ተገዝቶ የመጣውን ሰውዬ ማን እንዳስመጣው ታውቃላችሁ? ማንም ቢያስመጣው የኔ ሞት በፋሺስቶቹ ላይ መሳከኑ አይቀርም ነበር። ይልቁንም አስመጪው ቀስ ብሎ ከመንግስቶቹ ተማሪዎች መካከል ይሆን ወሬ የነዛ ’ንደሆን። ገባችሁ? በውነቱ ማን ነበር ገዳዩን ገዝቶ ያስመጣው አንድ የሻህ ሰላይ ነበር። ማን ይመስላችኋል?»

«ማን?» አልነው ሁለታችንም



@BOOKALEM

ደስ የሚል ወጣት ሳቁን ሳቀ

«ጀምሺድ ጓደኞችን የሻህ ሰላይ ነበር. . .

«እንዲህ ተቃቅፋችሁ ደስ ስትሉ! እንግዲህ ባሰብኳችሁ ቁጥር፣ እንዲህ ሆናችሁ ነው 'ምትታዩኝ:: እንዴት ቆንጆ ነው! መቼም እንደማትለያዩ ተስፋ አለኝ:: አቤት እናንተ 'ምትወልዱት ልጅ! ይታየኛል:: እንደ ካስትሮ ያለ ጀግና ነው 'ሚሆነው»

እጁን አወዛወዘልን:: ወደኛ እያየ በሩን ከፈተ:: ወጣ:: በሩን ዘጋ:: ከህይወታችን ወጣ:: ሁለታችንም እንወደው ነበር:: ግን ሲለየን በጣም አላዘንም:: ብቻውን እንዳልሆነ እናውቃለን፣ ውጪ ጨለማው ውስጥ ጓደኛው እንደሚጠብቀው እናውቃለን:: ሁለቱንም ሀያ ሚሊዮን ህዝብ እንደሚጠብቃቸው እናውቃለን:: ይሂዱ:: መንገዳቸውን የሳጥናኤል ኮከብ ያብራላቸው!!

እኔና ሲልቪ ባህራም የወጣበትን በር በሀዘን ስንመለከት ብዙ ጊዜ ቆየን:: ካጠገቤ ብድግ አለች:: ከበላዩ ቆማ የሌሊት ካፖርቷን አውልቃ ጣለችው:: ራቁቷን ቆመች:: እግሯን፣ ጉልበቷን፣ ጭኗን መሳም ጀመርኩ

«ቆይ» አለችና፣ ከእልጋው ወርዳ፣ ሀር በጉሯንና ውብ ወጣት ዳሌዋን እያወዛወዘች ወደ በሩ ሄዳ ቆለፈችው:: ወደኔ ስትራመድ የተገተሩት ወጣት ጡቶቿ ይንቀጠቀጣሉ:: እንስላውን ወደዚያ ገፋሁት:: መጥታ ላዬ ላይ ወጣች:: አበባ መሳይ ጡቷን አጎረሰችኝ:: እጄን ወፍራም ዳሌዋ ላይ አኖርኩት:: ሌሊቱ ተጀመረ

ሟት ተነስቼ ቁርስ ከበላሁ በኋላ ከሲልቪ ቤት ወጥቼ ወደ ቤቴ አመራሁ:: ትላንት ማታ ባህራም ኪሴ ውስጥ ያስቀመጠውን ወረቀት መንገድ ላይ አነበብኩት:: ኒኮል የፃፈችለት ደብዳቤ ነው

«ውድ ባህራም

«እንዴት ልጀምር? አስቸጋሪ ነው:: እወድሃለሁ! ከልቤ
'ወድሃለሁ:: አሁን የምነግርህ ነገር የማልወድህ ሊያስመስለኝ
ይችላል:: ግን እወድሃለሁ፣ ከልቤ አፈቅርሃለሁ ከአ ጋር መኖር
«የልፈቅሉሽንህ መኖር አትችልም::



@BOOKAlem

አትችልም። ስለዚህ እኔን ትተኸኝ መሄድ አለብህ

«እኔ ሬቮሉሽን በጭራሽ ሊገባኝ የማይችል ብዙ ብዙ ነገር አለ። ለምሳሌ ደም ማፍሰስ። ብዙ ተከራክረንበታል፤ ታስታውሰዋለህ። ደጋግመህ «አይገባሽም! ሬቮሉሽን በጭራሽ አይገባሽም» ብለኸኛል። እውነትክን ነው። አይገባኝም። ግን በደምብ የገባኝ አንድ ነገር አለ። አንተ ያለ ሬቮሉሽንህ መኖር አትችልም። ስለዚህ መለየት አለብን።

«እዚህ ቀጥሎ የምነግርህ ሊገባህ አይችልም። ስለዚህ እንዲገባህ ለማድረግ አትሞክር። ዝም ብለህ እመነው። ይኸው — የማፈቅረው አንተን ነው። የተረገዘው ልጅ ግን ያንተ አይደለም። የሉልሰገድ ነው። ልነግርህ ሞክሬ ነበር። ብዙ ጊዜ ሞከርኩ፤ አቃተኝ። አሁንም ቢሆን መንሰራሙ ጓደኛህ ባያግዘኝ ኖሮ አልችልም ነበር

«አዝናለሁ። ስላደረስኩብህ ሁሉ ችግር በጣም አዝናለሁ። ብትችል በልብህ ይቅር በለኝ። ባትችል ጥላኝ። ብቻ ሂድና ሬቮሉሽንህ ውስጥ ኑር። ደስታ ሊሰጥህ የሚችል እሱ ብቻ ነው።

«በሄድክበት ይቅናህ። ደህና ሁን።

ያንተ ኒኮል።

P.S ልታገኘኝ አትሞክር። አታገኘኝም። ልሰናበትህ ባለመቻሌ አዝናለሁ። ግን ፊትህ ላይ ቂም ማየት እፈራለሁ። ደህና ሁን።»

ይህን ደብዳቤ ሶስት ጊዜ ደጋግሜ አነበብኩት። ኒኮል ለምን ፃፈችው ይህን? ቀዳደድኩት። ቁርጥራጮቹን በተንኳቸው። ሲቴ ሄጄ ገላዬን ታጥቤ፣ ልብሴን ቀይሬ ወደ ኒኮል ቤት ሄድኩ

አልጋዋ ላይ ተጋድማ ሲጋራ እያጨሰች ሙዚቃ ትሰማለች

ታቹን ነጭ ክሮሽ እንደ ሽማኔ ጥለት የከበበው ቡና አይነት ቀሚስ ለብሳለች። ስገባ ፈገግ እያለች

«እንኳን መጣህ! ጭር ብሎኝ ነበር» አለችኝ

«ደህና ነሽ?»

«ደህና ነኝ። በጣም ደህና ነኝ። ግን ሌላ ሰው ማየት አልፈልግም። እባክህን በሩን ቆልፈው»

ቆልፈው ስመጣ፣ የተጋደመችበት አልጋ ላይ እንድቀመጥ



@BOOKALEM

በእጇ አመለከተችኝ። ጥፍሮቿ ሀምራዊ ተቀብተው ያብለጨልጫሉ። ተቀምጣለች፤ እያሁዋት። በጣም የተለወጠች መሰለኝ። ከንፈሮቿ ‘ንጂ ጥፍሮቿ ሀምራዊ መሳይ ቀለም ተቀብተዋል፤ ቅንድቦቿን ወደ ሰማያዊ የሚመስል ጥቁር ቀለም አይምቋቸዋል፤ ከግምባሯ ንጣት ጋር ሲታዩ በጣም ያምራሉ። የአይኖቿ ቆዳ ልክ የአይኖቿን የሚመስል ውሀ አረንጓዴ። ኩል ተቀብቶ፤ አይኖቿ ውስጥ ተነክሮ የወጣ ይመስላል። ከመጠን በላይ አምሮባታል። ከተንቃቂት ግብዣዊት ጋር ያለሁ መሰለኝ። ፀጉሯ እንደ ድሮው አመዳም አይደለም፤ ንፁህ በሩማ ቀለም ተነክሯል

«ምን ነካሽ?» አልኳት

«ምነው?»

«እንደዚህ ‘ምታምሪ አይመስለኝም ነበር»

"Merci"

«እውነት ግን ምንድነው?» አልኳት

«እንደዚህ ነኝ። ሳዝን ሰው እንዲያውቅብኝ አልፈልግም። አሁን ያዘንኩ እመስላለሁ?»

«በጭራሽ»

«ለዚህ ነው አይኔንም የተኳልኩት፤ ፀጉሬንም የተነከርኩት»

«አዘንሻል?»

«እንደ ዛሬም አዝኜ አላውቅ። ሲሄድ ደህና ዋል አለህ?»

«አዎን»

«የፃፍኩለትን አሳየህ?»

«አዎን። ለምን ፃፍሽው?»

«እንዴት እንደፃፍኩት ልንገርህ?»

«ንገሪኝ»

«ከትላንት ወዲያ ማታ፤ እንደዚህ ተጋድሜ ሙዚቃ ስሰማ፤ አንድ ሰው መጣ። መልኩ ሰው ይመስላል ‘ንጂ፤ እንደኔና ‘ንዳንት ሆዋሳቱ ውስጥ ደም እንደሚፈስ ልምልልህ አልችልም። ምናልባት ረቂቅም ቀጭን ነው፤ መንፅር ከነሀስ የተሰራ ሰው ሊሆንም ይችላል።

@BOOKALEM

ያረጋል። ግምባር የለውም፣ ከአይኑ ቀጥሎ አፍንጫ ይመጣል። ድምፁ ወፍራም ከመሆኑ የተነሳ ከሆዱ ነገሺ, ከጉሮሮው የሚወጣ አይመስልም።

«ጠልተሽዋል እ?»

«መጥላት አይደለም። ፈራሁት። ቀፈፈኝ። እየሁ፣ ገባና በወፍራም ድምፁ

«ኒኮል ማለት እርስዎ ነዎት?» አለኝ

«ነኝ» አልኩት

«ጥሩ። እኔ ከኢራን ኮሙኒስት ፓርቲ ተልኬ የመጣሁ ነኝ»

«ታድያ እኔ ከኢራን ኮሙኒስት ፓርቲ ምን አለኝ?»

«እርስዎ አይናገሩ። ጊዜ የለኝም» አለኝ። ድምፁ በጭራሽ አይለዋወጥም። ምንም ነገር ሲናገር በዚያው በወፍራም ድምፁ ነው

«የኢራን ኮሙኒስት ፓርቲ ባህራምን ይፈልገዋል። በጣም ይፈልገዋል። እኔን ፓርቲው ልኮኛል። ከትእዛዝ ጋር። ወይም ባህራምን ይዘኸው ና፣ ወይም ገድለኸው ተመለስ ተብያለሁ»

«ልትገድለው? ለምን?» አልኩት

«ቀላል ምክንያት። የኛን ምስጢር ያውቃል። ምስጢራችንን በሙሉ ያውቃል። ስለዚህ፣ ወይም ከኔ ጋር ይመጣል፣ ወይም ይሞታል። ሌላ ምርጫ የለም። ግን አንድ ነገር አለ» አለኝ

«ምን?»

«ባህራም አልመጣም የሚለው በእርስዎ ምክንያት ነው። እርስዎ ባይኖሩ ይመጣል። ስለዚህ እርስዎ እንዳይኖሩ ማድረግ።»

ሆዴ እየፈራ፣ «እንዴት?» አልኩት

«መግደል» አለኝና፣ ከኪሱ አንድ የታጠፈ ጩቤ አወጣ። ጫን ሲለው ጩቤው እንደ ብልጭታ ከፍት አለ

«ሻህን ልግደለው!' አለኝና፣ ያንን የኢራን ሻህ ስእል አመለከተኝ። ባህራም ነው እዚያ የለጠፈው። ልተኛ ስልና ልነሳ ስል፣ ሻህ እንዲታየኝ እፈልጋለሁ፣ ብሎ ሰቀለው።»

ግድግዳው ላይ የኢራን ሻህ የጦር ጠቅላይ አዛዥ የማእረግ



@BOOKALEM

ልብሱን ለብሶ ቆሞ በከለር የተነሳው ትልቅ ፎቶ አለ

«ለምሳሌ ሻህ እርስዎ ነዎት:: ጉሮሮውን ይመልከቱ» አለና ጩቤዋን ወረወረ-ች:: የሻህ ጉሮሮ ላይ ሰካት አለች:: ሰውየው ወደ ስእሉ ሄዶ ጩቤውን ነቀለና አጥፎ ኪሱ ከተተ

«መንገድ ላይ እርስዎ ሲራመዱ ወይም ሲሮጡ እኔ በፈጣን መኪና እየሄድኩ ጩቤ ብወረውር፣ ጉሮሮዎትን አልስተውም:: ገባዎት?» አለኝ:: በድምፁ ሊያስፈራራኝ በጭራሽ አልሞከረም:: ልክ የጂኦሜትሪ ፕሮብሌም እንደሚያስረዳኝ ያህል ነበር

«ገባኝ» አልኩት:: እንደዚያን ጊዜ ፈርቼ አላውቅም

«ለባህራም ይንገሩት»

«ምን ብዬ?»

«ያረገዝኩት ካንተ አይደለም፣ ይበሉት»

«ታድያ ከማን ነው ልበለው?»

«እንደፈለጉ:: ለምሳሌ ከጀምሺድ ወይም ከሱልሰገድ ነው ቢሉት ይችላሉ:: እነሱን ሊጠይቃቸው አይችልም»

«እሺ» አልኩና ደብዳቤውን ፃፍኩ:: አጣጥፎ ኪሱ ሲከተው «ባህራም ይህንን ካነበበ በኋላም ከርስዎ ጋር መሄድ ባይፈቅድስ?» አልኩት

«እምቢ አይልም»

«ቢልስ?»

«እገድለዋለሁ:: ደህና እደሩ' አለኝና ወጣ:: እንደሱ ያለ ከስውነት የራቀ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም»

ኒኮል ዝም አለች:: ዝም ብዬ አየኋት:: በጣም ታምራለች:: ውሀ አረንጓዴ ኩኋና ሀምራዊ የከንፈር ቀለሟ የፈርአን ዘመን ገብፃዊት አስመስሏታል:: ሳቅ አለች

«ምነው ትኩር ብለህ ታየኛለህ?»

«አማርሽኝ» አልኳት:: ውስጡን ደነገጥኩ:: እንደዚህ ለማለት አላሰብኩም ነበር:: ውሀ አረንጓዴ ቀዳ ሽፍን ግልጥ በሚያደርጋቸው ውሀ አረንጓዴ አይኖቿ አየችኝ:: ሀምራዊ ከናፍሯ በፈገግታ ተላቀቁ:: እጇን ጉልበቷ ላይ አሳረፍኩ፣ አልከለከለችኝም



@BOOKALEM

«ጫማዬን ሳወልቅ ነው» አልኳት

ኮቴንም አውልቄ አጠገቧ ተጋደምኩና እጇን እንተራሰኳት

«ደራሲ መሆን እንደምፈልግ ታውቂ የለ?» አልኳት

«አውቃለሁ:: ልትጠይቀኝ 'ምትፈልገው ጉዳይ እንዳለም አውቃለሁ»

«ታውቂያለሽ?»

«አዎን:: ለምሳሌ፣ ልጄ ምን ይሆናል? አይደለም አንዱ ጥያቄህ?»

«ካልፈለግሽ አትመልሺ»

«ብነግርህ ግድ የለኝም:: መሀን ለሆኑ ሰዎች አራስ ልጆችን የሚሰጥ ድርጅት አለ:: ወልጄ ልጄን ለድርጅቱ አስረክባለሁ::»

«ለምን አላስወረድሽውም?»

«ለምን 'ገድለዋለሁ? ቢኖር አይሻለውም? እኔኮ በህይወት አምናለሁ:: አንተስ፣ አታምንም?»

«አምናለሁ:: በህይወትም በውበትም አምናለሁ» አልኩና ጉንጯን ሳምኳት:: ራሴን በለስላሳው ወደዚያ እየገፋች

«ቆይ» አለችኝ

«ምነው?»

«ሌላ ነገር እያሰቡ ሲስሙኝ አይመቸኝም:: መጀመሪያ ጥያቄህን ሁሉ ልመልስልህ»

«እሺ»

«የሚቀጥለው ጥያቄህ፣ ልጁ የማን ነው? ነው:: እርግጠኛ 'ይደለሁም:: የጀምሺድ፣ ወይም የባህሩም ሊሆን ይችላል:: ግን የሉልሰገድ አይመስለኝም:: የመጨረሻ ጥያቄ፣ ባህሩምን እወደዋለሁ ወይ? አዎን 'ወደዋለሁ:: ከልቤ 'ወደዋለሁ፣ አፈቅረዋለሁ:: እንግዲ ያው ለምን ጀምሺድንና ሉልሰገድን ጠቀለልኳቸው? አላውቅም:: ግን አይቆጨኝም:: የተጋደሉት በኔ ምክንያት ይመስለኛል:: አሳዘኑኝ:: በመጣትነታቸው በመቀጨታቸው አዘንኩላቸው:: ግን እዚህ ውስጥ እኔ ጥፋተኛ ነኝ ብዬ አንድ ጊዜ 'ንኳ አምኜ አላውቅም:: ገና ለገና



@BOOKALEM

ሁለቱ ተኝተውኛል ተብሎ፣ ከዚህ በኋላ፣ እኔን ነፃነትና ምርጫ እንዳላት ሴት ሳይሆን፣ እንደ ንብረት ቆጥረው ተጣሉብኝ:: ስለዚህ የራሳቸው ጉዳይ ነው»

አየኋት:: ስለምንም ግድ የሌላት፣ በጣም ጠንካራ፣ በጣም ቆንጆ ሴት ናት:: በሀይል ደስ አለችኝ::

"Tu t'en fouts, eh?" አልኳት («ደንታ የለሽም፣ እ?»)

"Epérdument?" («በጭራሽ») አለችና፣ እንደተጋደምኩ ብድግ ብላ፣ በክርኗ ትራሱ ላይ ተደግፋ ወደታች አየችኝ:: ጎምበስ ብላ አይኖቼን ተራ በተራ ሳመቻቸው:: ፈገግ እያለች

«ስላንተም ቢሆን ደንታ የለኝም:: ስለኔ ምንም ብታስብ የራስህ ጉዳይ ነው:: ብቻ ደስ ትለኛለህ:: በሀይል ደስ ትለኛለህ:: እንዴት ቆንጆ ነህ!» አለችና ጎምበስ ብላ ሀምራዊ አፏን አፌ ላይ ደቀነች:: አቀፍኳት:: ውብ ብልግና ተጀመረ

«. . . ያቺ ልጅ መንግስተ ሰማያትን አጣጥፋ ጠቅላ በጭኖቿ ውስጥ ደብቃ ነው 'ምትዞረው ልልህ እችላለሁ . . . እኔ 'ምለው፣ እንደ ኒኮል ያለች ሴት እየተኙ ሁለት አመት ኖረው ቢሞቱ ምናለበት? ቢሰነብቱ ትርፉ ማርጀት አይደለም? እርጅና መጥቶ፣ አጥንቶቼን አኮራምቶ፣ ጅማቶቼን ሸምቅቆ፣ ቆዳዬን አጨማዶ፣ አይኔን አጨናብሶ፣ ጠረኔን ሰርቆ በቁሜ በኤክስ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ሽታ ከሚገንዘኝ፣ ኒኮልዬ ጭኖች መሀል ገብቼ ሙቀቱ ውስጥ ቀልጬ፣ ርጥበቱ ውስጥ ሟሙቼ ጥፍት ብል እመርጣለሁ:: የሰው ልጅ መጨረሻውን መምረጥ ቢችል፣ መጨረሻዬ ኒኮል ውስጥ ቢሆንልኝ እመርጣለሁ. . .»



@BOOKALEM

## አሻሪ ታሪክ መገፀገሃሪያት

ውድ አንባብያኔ

ዛሬ መፅሀፋችን ስጠግቢያ°ማይሆን ዝናር፡ ቃኖሪቀልረ፣ ለሉውጥ ያበዛሉ። ደሄ ኢውነታዊ ሰቦሉይ አንድ ኮሪደሻ የዓሌው ነው። ታድያ፣ ህጋዊ ሰማችን ያው ነውሽንጂ፣ ውሰማችን ግን አኒ ሌላ ኢሱ ሌላ። ሰው ለመሆኔ መለኪ፣ ሰሜቱ፣ ኢምነቴ፣ የወደፊት

እቅዴ፣ ሁሉም በሂደት ሲለዋወጥ እንዴት እደምንሰፍችሁ! እንዳንዴማ ሳሊታወቀኝ ተካታትዬ ሰዎች አየሆንኩ የማኖር ይመስለኛል

ለምሳሌ —የምትገኝ እጋቶሪ እንደማው። በተዓለበት ዘመን ምትን ካጋቶሬያችን አካል አፈሪውና እመካው ነበር — እንም በሚም አፈታወቀብኝም ነበር'ንጂ ዛሬ ግን የዚያን ደሃል ገማኝን'ጓኋ አሉሬ ሪውጋሙ ምናለባት የገቡ አመካው ደምናል'ንጂ — ወረውም፣ ሬሳውም፣ ምእም አስቀያሚ ጥምብ ለመሆኑ። በዚህ ከቀጠለኩ ካቀቴት አመት በኋላ አሄን ታሀል'ንኳን አልፈራውም! (ያ ጊዜ ደርሶ እንና መሰሎቼ ስንገናኝ "ገታ ሞት ቀወደ ሀሉ!"

"ሀሎ ሉያ! የጌታ ሞት ሰም የተገለኘ"



@BOOKALEM

ይሁን!!። እንገናኛለን በቀድሞው የፌሬ ሱሳሞታ ምትክ፣ ታያላችሁ! እስክዚያው ለአሁን ወደ ትካሻ ሳታችን እንመለስ)

የ ወጣት ሲፅፈው፣ በሠዶወቴ ዘለን ይታተማል የሚል ተስፋ አልነበረውም። ምናልባት አንዳንድ ጊዜ ለራሱ «በልጅ ልጆቼ ዘመን ይታተም ይሆናል — ያን ጊዜ፣ ግብዝነትን እንደ ገርማ ሞገስ ለብሶ ‹ባለህበት ሂድ!› ስሉት የሚያመካለው ገህነቻን ምናልባት አርምጃውን ይቀይር ይሆናል፣ ብሎ ያስብ ይሆናል ... ምናልባት ... ይሆን ይሆናል ...

አላህ ታድያ እንደምስለመሰን፣ እኛ በከንቱ እየተጠነቀቅን ያቀድነውን፣ እሱ በማይለቅ ቸርነቱ አሻሽሎ እስበለጦ ይፈፅምለን ዘንድ መለኪያም ፈቃዱ ሆነ! እኛ ትካሻ ሳታችን (እና ሊሎቹ ፀሀፊዎቻችን) ‹እንደ ወረደ› እንዲታተሙ— ለን ኪቀደ፣ ስለዚህም ቀና ገፀባህሪያችንን ገህራምን ሲምቀመስለው ያገራችን ወያኔ — ባኋላ ኢሕአዴግ) ድል ሲቀዳጀልን፣ በትረ ስልጣን እስጠበጠልን፣ የሳንሱርን ልጓም አውልቆ

@BOOKALEM

ለኢዮጲ እስከመደመሰን፣ እቺን፡ ዝክር፡ እንፅፍ-
ናትሁ ዘንድ ክህሎት እስታጠቀኝ፤ ሀደሉ
ይሀሉ ምስጋኔ፣ ስላም የተመሰገነ ይሁንለን አሜን!

እርፉ አስተዋይ ናጎሰ ነገስት… ህይወቴና የሌትዮ-
ጲያ አርምጄ። ብሎው የፋንታን እኔደ እርእስ በመከተለ
። ህይወቴና የትኩሳት አርምጄ። በማለት እቀጥላለሁ

•መጀመርያ ትኩሳታችንን ናርናት

—ነፀገህሬያቱ እና
እኔ(እየናርኳትም እየዛገብኳትም)

•ቀጥሎ በሬቦሰድ መሬክ ዓናኚት

•ቀጥሎ መስፍን አለማየሁ፣ ደምሴ ፅጌ እና የሺ-
ጥላ ኮከብ። ብሌገና። የሚገለውን ልብሷን አውለቀው፣
የተከበረውን የዶሴኝታ ጨርቅ ሊብስ አለብሰዋት
(በኝተሬ ቷንቷ ደም። የግብዝነት ማቅ ለበሳ፣ የዶሴኝታ
ዝ ደርግም) አደባባይ ወግኛ

•ቀጥሎ እነሆ፣ ራቁቷን እንደተፈጠረች፣ እንደ
ወረደ። የሚሌ መፈክር እንገን ብቻ!

ለዚህ ሌዩ ሰዩ አጋጣሚ ደጋግሚ ሳነሳት፣ ለናፍቆት



@BOOKALEM

ወደ ኤክስ-አን-ፕሮቫንስ እየተመላለስኩ እንደ መጎብኘት ነበር... እና በመፅሀፉ ውስጥ ያለነው ሰዎች በያንዳንዷ ጉብኝት ያው እኛው ነን:: እኔ አዛውንቱ ጉብኚያችን ግን በኑሮ ሂደት እየተለዋወጥኩ ስለሆነ፣ እነሱም ማንነታቸው ይለዋወጥብኛል:: ለነሱ ባለኝ የፍቅርና የናፍቆት ቅኝም ተከተለ ሳቅርብላቸው

ገነራም ምንም የማይበገረው ቆራጥ ጀግና ነው:: አራት ነጥብ

ለራሴ ከሁሉም አብልጬ የምወደውና የማከብረው የማደንቀው ግን ኢማንዳ ዱቤን ነው —እና ፅናትዋን! ገህራም ቢጋተርና ድል ቢያደርግ ጠላቶቹን ነው:: ኢማንዳ ግን የድል አክሊሉ የምትደፋው ከሁሉ የከፋውን ሁሳት፣ ወዳጅ መስሎ በስውር የሚጎዳትን ተቀናቃኝ፣ ወረዳ የሰው መሳቂያ ያደረጋትን የገዛ ድክመትዋን፣ ድል ነስታ፣ ሸንቅጥ ሸጋ ኩሩ ለመሆን ስለበቃች ነው:: በመጨረሻ የደረሰባት ቅራኔ እንኳ ሊበግራት አልቻለም — ከብረት የጠነከረች ሰንሳሳ እንስት!!

ፉልሳገር እንደሆነ እንቁ ነው መልአክ ነው:: 'ሉ' ገያጋጥማትና "ርካሽ አይደለሽም፣ ሰው ነሽ" ብሎ በስንትና ስንት ትእግስትና ዘዴ ገያጎምናት ነበር፣ እንደ



@BOOKALEM

ተደበላለቁ ሲኦሉ ኢርቀን ተገሩ ነበር። መሆኑሽ ሰጋ
ሉብም መግኘት፣ ሪሚሪ ታሪቅት . .

መሆኑሽ ከመሆን ጋር ደገም ሉሌሰገድ በገሀኝ፤
“ወገኔ! እናቴ መነቴ ትወሌድ!” የሚገሉሉት ነው፣
ሌቲኮሌ ናትወት (እና የሌስን ከብር ከመጠበቅ) የተፋ ከመው

እነዚህ ወዲጆቹ በሌሴ፣ በበሚ፤ ገኜቲ የማስታወሱ-
ቸው ናቸው። የSherlock Holmesን እርእ፤ በመከተል
በማንቅሉ ጎስለ ግን ከሁሉ በላይ የማደንቀው የኩሌሰገድን
ሀማወቸኝ፦ የገህሬያን ያገር ሌጆ ሂምቪ ደን ነው። ሰውን
ከእንሰሳ የሚለየው ራሱን መግደል መቻሉ ነው፣ ደሊኤል
በተሰባበረች ሪሪንጊሊኛው፣ ጀማንነት ማለት አሌ ሆቸን
ወሪም ሰዎችን መግደል አይደለም። እኔ ጀገና የምሆነው
ራሴን የገደልኩ እለት ነው

የኔር እኅማው ደኒ ሲሆን፣ ናቅሪ በመሉ ሉቋማር
ነው (ገሀሪያም ከእሊን ያከው ናቅር፣ እና ኩሌሰገድ
ሌቲኮሌ ገና ያለው ናትወት ምሪዶ የሆነውን ያሀል) ደሀን
የምናውቅበት ሰንታቸን እንሆን ደሆን ጀሌሎች ሰዎች
የሚታዩቸው እጣቋጅ፣ እስሶቹ፣ ምሌቃቃው የገክፀጋ
ዞር የሚያስመስለው ጭምብል ብቻ ነው

ተካ እንደሆነ ያው በሾቂ ተካ ነው፣ እድሜ ለገሀሪያም



@BOOKALEM

በወርቅ ጥርሱ ፈገግ ማለት ሳያበዛ አለቀበርኝ'ንጂ

ወደ ሲልቪ ስንመጣ የ"ሌቱ ቶም አይነጋልኝ"ዋ ና ገፀባህሪ ክንፈ ይመጣ ብኛል። ምክንያቱም"ሌቱ ቶም አይነጋልኝ"ን ያነበቡ ሰዎች ትንሽ ጊዜ ካለፈ በኋላ በትውስታቸው ከሁሉም ጉልቶ የሚታያቸው ገፀባህሪ ክንፈ ነው — "ትኩሳት"ን ያነበቡ ደግሞ "ሲልቪ የማውቃት ሰው ትመስለኛለች፣ በቅርብ ሳውቃት የምፈልጋት ልጅ ናት" ይሉኛል

ለማሳረገያም እነሆ። የጀመርናና የመጨረሻ ገፀባህሪያ-ችን "ትኩሳት"ን ሊፅፍልን ሲፈልግ ምን ያህል ጥረትና ትጋትን እንደነበረው ስናጤን የባህሪም አይነት ቃል ዛሳቂ ፍቅር ካለው — ደፃፍነው ግን፣ እሱ ራሱ ለባህሪም እንደነገረው፣ ሳገርና ለህዝብ ብሎ እንኳን እድሜውን ሙሉ ሊሰዋ ቀርቶ፣ ያንድ ሰአቱን እንቅልፍ አይከፍልን-ችውም። ምክንያቱም እሱ ውስጥ ያደረው ልዝብ የተረቶ ዛር ነው እንጂ፣ ባጎዮናኤል ኮከብ ብርሀን የሚራመደው ቆራጡ የባህሪም ወጣቢ አይደለም።

ውድ አንባብያን ሆይ

ይህን በነፃነት ተኑሩ፣ በነፃነት ተፅሮ፣ በነፃነት

@BOOKALEM

የታተመውን ልቦለድ እየተዝናናችሁ፣ ኢሌሮ ኢሌሮም
እያሳቃችሁ እንዲነበባችሁት በመተማመን፣ እጆቼን
(ሁላችሁንም!) በሁለቱ እየዘረጋሁ
"ሁሉ በሰላም! ኑሩ በሰላም!"

ስብሐት ለአብ



@BOOKALEM